ተግሣጽና ምክር

እውነትን ከሐሰት ለይቶ ማወቅ ለሚፈልግ ሰው
ተጻፈ

ከዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዘብሔረ ዓድዋ

በወራሽ ልጆቻቸው ፈቃድ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.
ለአራተኛ ጊዜ ታተመ

ተግሣጽና ምክር

እውነትን ከሐሰት ለይቶ ማወቅ ለሚፈልግ ሰው
ተጻፈ።

ከዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዘብሔረ ዓድዋ።
በወራሽ ልጆቻቸው ፈቃድ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.
ለአራተኛ ጊዜ ታተመ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

የኢየሱስ እውነተኛ መልክ ሥዕል።

ይህ ሥዕል የተሣለው ጢባርዮስ ንጉሠ ነገሥት በከበረ ድንጋይ ላይ «ኤሜራልድ» ካስቀረጸው ምስል ላይ ነው። ይህም ቅርጽ የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ሀብት ሆኖ ከቈየ በኋላ እ.ኤ.አ. ፲፬፻፶፫ ዓ.ም. በቱርኮች እጅ ወድቆ ስለ ነበረ ዳግማዊ ባዝዜድ የተባለው ሡልጣን በክርስቲያን ጦርነት ጊዜ ሮዲ ላይ ወንድሙ ተማርኮ ታስሮ ስለ ነበረ እርሱን ለማስለቀቅ ለፓፓ ኢኖቼንሶ ስምንተኛው ይህ ቅርጽ፣ የክርስቶስ ጎን ከተወጋበት ቅዱስ ጦር ጋር አብሮ የተሰጠ ነው። በኢኮኖግራፍ ለተነሣው ለዚህ እጅግ ማራኪነት ላለው ሥዕል በአይሁድ አገር ተጠባባቂ ገዥ የነበረው ፒሌንቱሎ ለዚሁ ለጢባርዮስ ንጉሠ ነገሥት በጻፈው የታወቀው ታሪካዊ መልእክቱ <u>የሰጠው ጽሑፋዊ አገላለጽ</u> ዐይነተኛ ምስክር ነው።

ይህ ቃል ከሥዕሉ ግርጌ ተጽፎ የሚገኘው የጣልያንኛው ትርጉም

From the Library of
FESSEHA ATL. WOLDE YOHANNES

በእርሱ ምክንያት ለአንተ ኃጢአት እንዳይሆንብህ፤

ወንድምህን ገሥጸው እንጂ በልብህ አትጥላው::

ዘሌ 19:17

ልቤ መልም ነገር አውጥቶ ቢያገሣ
ለወንድም ምክር ነው እንዲድን ከአበሳ
ሐሰት የለያያት መንጋይቱ ከኒሣ
ጽሑፍ ብትመረምር ሕግን ተመርኩዛ
አንዲት ትሆናለች በወንጌል ታድሳ
የኢትዮጵያ ወጣት ተነሣ ተነሣ
ፀሓይ ወጥቶልሃል የይሁዳ አንበሳ::
ሕዝ. 34÷22-36፤ ዮሐ. 10÷1-16::

ለሰው ሕይወት ታሪክ ሐሳቡ በሙሉ
የተረዳውን ነገር የመሰለውን ቅሉ
ጽሑፍ ጽፎ ቢተው ይበልጣል ከሁሉ
ይብዛም ይነስም ስጦታው ዕድሉ
ቁም ነገርን መተው በዓለም እስካሉ
ለሰው ልጅ ይገባል ሊቃውንት ይላሉ::
1ቆሮ. 12÷1-11::

በአጭሩ ዕድሜያችን ቶሎ በሚያልፈው
ማስታዋሻ መተው ለሰው ጌጡ ነው
ከሐውልት ይበልጣል ሕይወት ከሌለው
ሲመክር ይኖራል ላስተዋለው ሰው
ዘመንፈስ ቅዱስ ነው ከጥንት ያቈየው::
1ተሰ. 5÷11፤ ዕብ. 3÷13::

እውነተኛ ብርሃን



ማኅተም ከተገኘ ዘመን ከሰጠን
በጽሑፍ ለመግለጽ ሐሳባችንን
የሚበጅ እንጻፍ ለሀገራችን
አእምሮው እንዲሰፋ ደጉ ሕዝባችን::

ይህን መጽሐፍ ያለ ጸሓፊው ፈቃድ ማንም ሰው ገልብጦ ሊያትመውና ሊያሳትመው ሕግ አይፈቅድለትም::

It is forbidden by the law to all to translate and print this book without the permission of the author.

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ÷ የእግዚአብሔርም ፍቅር÷ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን:: አሜን :: 2ቆሮ. 13÷13::



ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ::
ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዘብሔረ ዓድዋ

ግርማዊ ሐዋርያ ሕዝባቸውን ሲመሩ
ብለው ተናግረዋል በአእምሮ ጠንክሩ
እውነትን ከሐሰት በዕውቀት መርምሩ
ሁልጊዜ ነቅታችሁ በሃይማኖት ኑሩ
እውነትን ተከተሉ በሰማይ እንድትከብሩ
የድል አክሊል ዋጋው ታላቅ ነው መከሩ::

አንባቢዎች ሆይ!

ይህ የነገርኋችሁ ቃል እውነት ነው፤ እውነተኛውን መንገድ ክርስቶስን ብቻ ብትከተሉም እውነት ራሱ ከሐሰት ባርነት ነጻ ያወጣችኋል፤ ዮሐ. 8÷30-32፤ 14÷6::

ማውጫ

አርእስት **ገጽ**

ልዩ ማስታወሻ 1
የአቶ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዐጭር የሕይወት ታሪክ 2
መግቢያ 10
ልዩ መግለጫና መቅድም 12
ምዕራፍ 1 የእምነት ዐዋጅና ትርጓሜ 15
ምዕራፍ 2 ማይ ንዝፀምኡ ምኽሪ ንዚሰምዑ 19
ምዕራፍ 3 ልዩ ደብዳቤ 23
ምዕራፍ 4 ቅዱስ መጽሐፍ 27
ምዕራፍ 5 ምርጥ ቃላት 29
ምዕራፍ 6 ተግሣጽና ምክር 32
ምዕራፍ 7 ስለ አማላጅነት 39
ምዕራፍ 8 ስለ ፍጡር ጭከናና የአምላክ ርኅራኄ 45
ምዕራፍ 9 እውነትና ሐሰት 50
ምዕራፍ 10 ሕያዋንና ምዉታን አይተዋወቁም 58
ምዕራፍ 11 ስለ ቃል ኪዳን 67
ምዕራፍ 12 የማይመስል ምሳሌ 74
ምዕራፍ 13 ንስሓ ሐዘን ልቅሶ 80
ምዕራፍ 14 ስለ መምረጥ 84
ምዕራፍ 15 እውነተኛ የሚያድን ተስፋ 87
ምዕራፍ 16 መጠርጠርና መመርመር 93
ምዕራፍ 17 ስለ ማሥርና መፍታት 99

ምዕራፍ 18 ስለ መድኃኒትነቱ..107
ምዕራፍ 19 የአዳም መድኃኒት ከመጽሐፈ ብሊት....................112
ምዕራፍ 20 ስለ ጥምቀትና ቍርባን..115
ምዕራፍ 21 ስለ ተዝካርና ዝክር...120
ምዕራፍ 22 ስለ በዓላት 128
ምዕራፍ 23 ሞትና ሐዘን 134
ምዕራፍ 24 ስለ ምጽዋት ጸሎትና ጾም 140
ምዕራፍ 25 የሐሰት ወሬ አትቀበል...150
ምዕራፍ 26 ስለሚያሰክር መጠጥ 158
ምዕራፍ 27 ስለ መብልና ፈቃድ 167
ምዕራፍ 28 ስለ ልማድ 171
ምዕራፍ 29 ስለ ስግደት...177
ምዕራፍ 30 አድራጊ ማድረጊያ ተደራጊ..................................188
ምዕራፍ 31 ጠቅላላው ማስረጃ..191
ምዕራፍ 32 መንፈሳዊ ምክር ለመንፈሳውያን........................199
የሃይማኖታችን መሠረትና ጸሎት...208

ልዩ ማስታወሻ

«ተግሣጽና ምክር» የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ ከተጻፈ ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ ብዙዎችን አነጋግሯል፤ ከመንፈሳዊ እንቅልፍም ቀስቅሷል። በመጽሐፉ መነሻነትም ብዙዎች የወንጌልን እውነት ተረድተዋል፤ በታሪክ መልክ ብቻ ያውቁት የነበረውን የክርስቶስን አዳኝነትም በትክክል አምነውበት ድኅነተ ነፍስን በእምነት ለመቀበል ችለዋል።

መጽሐፉ በተደጋጋሚ ታትሞ የተሠራጨ መሆኑ ይታወቃል፤ የመጨረሻው እትም ታትሞ ከወጣ ግን ከሦስት ዐሠርት ዓመታት በላይ ተቈጥሯል። ስለዚህ በዚያን ዘመን በነበሩ ሰዎች እጅ ካልሆነ በቀር በተለይ በዚህ ዘመን ትውልድ እጅ አይገኝም። ጸሓፊው በመጽሐፋቸው ያነሡአቸው ዋና ዋና ችግሮች የብዙዎችን ኅሊና ቀስቅሶ በግለሰቦች ደረጃ የተወሰነ ለውጥን እንዳመጣ ባይካድም የሚፈለገው አጠቃላይ ለውጥ ግን ገና አልመጣም።

ዛሬ ያለው ትውልድ በአስተሳሰቡና በአመለካከቱ÷ በትምህርቱና በዕውቀት ደረጃው በዚያን ጊዜ ከነበረው ትውልድ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ አንጻር ብዙ ለውጦች እንዳሉ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ጸሓፊው ያነሡአቸው መሠረታውያን ችግሮች አሁንም ድረስ እንዳሉ አሉ። ስለዚህ ዛሬ ያለው ትውልድ ይህን ተገንዝቦ÷ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ የያዘውን ሃይማኖት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እንዲመረምርና እውነተኛውን ነገር ከሐሰተኛው እንዲለይ መርዳት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ተግሣጽና ምክር እንደገና እንዲታተም አስፈልጓል።

መጽሐፉ እንደገና እንዲታተም ሲታሰብ የጸሐፊው አስተሳሰብና አመለካከት÷ ያስተላለፉትም መልእክት በሙሉ እንደተጠበቀ ሆኖ÷ አንዳንድ ነገሮች ግን ተሻሽለው ቀርበዋል። ይህም የሆነው የዘመኑ ትውልድ መጽሐፉን ያለምንም ችግር በቀላሉ አንብቦ እንዲረዳው ለማስቻል ነው። ጸሓፊው አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው መሆኑን በመግለጽ÷ አንባቢው ያለውን የቋንቋ አቀራረብ ችግር አቃንቶ እንዲያነብና መልእክቱን እንዲረዳ «ማስጠንቀቂያ» በሚለው ርእስ ሥር አሳስበው ነበር። በዚህ እትም ላይ ግን ይህን ችግር ከሞላ ጎደል ለማስተካከል ተሞክሯል። ከዚህም በተጨማሪ በግዕዝና በትግሪኛ ቋንቋዎች ተጽፈው ሳይተረጐሙ እንዳሉ የተቀመጡትን ለመተርጐም ጥረት ተደርጓል። በተለይም የግዕዝ ቅኔያት (መወድስ) እንደአመቺነቱ በግጥም መልክና በስድ ንባብም ተተርጕመዋል።

የአቶ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ
አጭር የሕይወት ታሪክ፡፡

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ከአባታቸው ከነጋድራስ አብርሃ ወልዱ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለላ ተክሉ በዓድዋ ከተማ እንደ ኢትዮጵያውያን አቈጣጠር በ1905 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ አባታቸው ነጋድራስ አብርሃ በከተማው ከነበሩት ታዋቂ ነጋዴዎች መካከል አንዱ ነበሩ፡፡ ልጃቸው የቤተ ክህነትን ትምህርት በዘመኑ ገናና ወደ ነበረው የዓድዋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አስገብተው ከፊደል መቍጠር ዳዊትና ወንጌል ንባብ ቀጥሎም ለዲቁና የሚያበቃቸውን የቃልና የዜማ ትምህርት እንዲማሩ አደረጉ፡፡ ይሁንና ገና የ0ሥራ ሦስት ዓመት ወጣት እያሉ አባታቸው በድንገተኛ የወባ ሕመም ስለ ሞቱ፥ ትምህርታቸውን አቋርጠው ሕፃናት የሆኑ ታናናሽ ወንድም እህቶቻቸውን ለማሳደግና እናታቸውን ለመርዳት በሥራ መሰማራት ግድ ሆነባቸው፡፡

ንግዱም ከዓድዋ ከተማ ወደ አሥመራ፥ ጐንደር፥ ደሴ፥ መቀሌ እያሉ በበቅሎ ጭነት ማንኛውንም ቀላል ሸቀጣ ሸቀጥ ማዘዋወርና መቸርቸር ነበር፡፡ ስለዚህ ዘመን ትዝታ ሲያነሡ «. . . የመረብ ወንዝ ጐርፍ ሲሞላ የበቅሎ ጅራት የሙጥኝ ይዘን ነበር የምንሻገረው፥ . . . የደባርቅ ቆፈን ምኑ ቅጡ! ጥዋት ከወንዙ ንጹሕ መስተዋት መስሎ የተጋገረውን በረዶ በድንጋይ ሰብረን ውሃ ይቀዳል . . .» ይሉ ነበር፡፡

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ እውነትን ለማወቅና መጻሕፍትን ለመመርመር የነበራቸው ምኞትና ጥማት በአባታቸው ሞት ቢሰናከልም እንኳን ንቁ አእምሮ፥ ቅንና ብሩህ ልቦናን ስለ ታደሉ፥ አዘውትረው ለማንበብና ለመመራመር፥ ከሊቃውንትና ከካህናት መነጋገርና መከራከር ይወዱ ነበር፡፡ ክርክራቸውም ለዘብ ባለ ቀልድና ጨዋታ የተዋዛ እንጂ እንዲሁ ደረቅ የእልህ ክርክር አልነበረም፡፡ ካገር አገር እየዞሩ ሲነግዱም ከትግሪኛና ከግዕዙ ሌላ የጎንደሩንና የወሎውን አማርኛ፥ ዐረብኛና፥ ጣልያንኛም አጥርተው ለማወቅና ለመነጋገር መልካም የሕይወት ትምህርት ቤት ሆነላቸው፡፡

ንግዱ በሚገባ ደርቶ በዓድዋ ከተማ ከታናሽ ወንድማቸው ጋር በመተባበር በጊዜው ድንቅ የተባለ ዘመናዊ ቤት አሠሩ፡፡ የንግድ ሱቅም ከፈቱ፡፡ ሕፃናት የነበሩ ወንድም እህቶቻቸውንም አሳድገው፥ ለዐቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን አድርሰው ዳሩ፡፡ እርሳቸውም የአለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ የልጅ ልጅ የነበሩትን ወ/ሮ ሐረጉን አገቡ፡፡

ቀቁ   ይህ ሁሉ ሲሆን ዓድዋ በደጃች ገብረ ሥላሴ ልጅ በደጃች ተክለ ሃይማኖት ትተዳደር ነበር:: ታላቁ የዓድዋ ሊቅ አለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩም ትምህርት ቤት ከፍተው ወንጌልን ስላስተማሩ÷ ጸረ ማርያም ተብለው ከተከታዮቻቸው ጋር ብዙ እስራት÷ ንብረት መወረስ÷ ግርፋት÷ በርበሬ መታጠን ሌላም ብዙ ስቃይ ያዩበት ዘመን ነበር:: (ስለ እኚህ መጽሐፍ ቅዱስን ከግእዝ÷ ከዕብራ ይስጥና ከስዊድንኛ ቋንቋዎች አመሳክረው ወደ ትግሪኛ ቋንቋ ስለ ተረጐሙት ሊቅ÷ ሌላ ራሱን የቻለ መሉ ጽሑፍ ለወደፊት ማቅረብ ይቻላል::) አቶ ዘመንፈስ ቅዱስም ሁሉን ረጋ ብለው መመርመር እንጂ ሌላ ጠላው ወደደው ብለው በሰው ስለማይመሩ÷ ለመማርና ለመመራመር ወደ አለቃ ተወልደ መድኅን ተጠጉ:: በዚህም ምክንያት የአባታቸው የነጋድራስ አብርሃ ንብረት በሙሉ ተወርሷል::

አለቃ ተወልደ መድኅን የወጣቱን የዘመንፈስ ቅዱስን አስተዋይ አእምሮ÷ ብሩህና ንቁ ልቦና ተመልክተው «ዛሬ ገና የመንፈስ ልጄን አገኘሁ» በማለት÷ ከሁሉ ይበልጥ በማቅረብ የመጻሕፍትን ምስጢር ያስተምሯቸው ጀመር:: በጊዜው «ጸረ ማርያም» ማለት በትግራይ አነጋገር ለፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ የዘለፋ መጠሪያ ነበር:: ይኸውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማርያም ታድናለች÷ ትማልዳለች ብላ ስለምታስተምርና÷ እነርሱ ደግሞ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው ነው በማለት ስለማይቀበሉት «ጸረ ማርያም» (የማርያም ጠላት) የሚል ስም አተረፉ::

አለቃ ተወልደ መድኅን ሸምግለው ስለነበር አልጋ ላይ ጋደም ብለው÷ አቶ ዘመንፈስ ቅዱስም አጠገባቸው ወንበር ላይ ተቀምጠው «ተግሣጽና ምክር» ከተባለው መጽሐፋቸው አንድ አንድ ምንባቦችን እየመረጡ÷ በተለይ ግጥሞችን እያነበቡላቸው ሳለ አዳምጥ ነበርና የግጥም ድምፀ ቃና ለመጀመሪያ ጊዜ በአእምሮዬ የተቀረጸበት በመሆኑ ፈጽሞ አልረሳውም:: ታዲያ መጽሐፉ ገና ታትሞ ያልወጣ ስለ ነበር÷ ሁለቱም አንድ አንድ ነጥቦችን ይዘው እየተጨዋወቱና እየተመካከሩ÷ እየተከራከሩና እየተወያዩ ሲያመሹ ያኔ እኔ የአራት ወይም የአምስት ዓመት ልጅ ነበርሁ፤ ይኸን ሁሉ ከመሬት አጎዛ ላይ ተቀምጬ እሰማና እመለከት ነበር::

ዓመት አልቆየም መጽሐፉም ታትሞ ወጣ:: ጠዋት ቁርስ ስንበላ የሆነ ሰው ውጭ ሲጣራ ሰማን፤ አባቴን ጣቢያ እንደሚፈለጉ ነግሮ ይዟቸው ሄደ:: አባቴም ታሠሩ:: በጨርቅ የተቋጠረ ምሳ ተሸክሜ እስር ቤት ሳመላልስ ትዝ ይለኛል:: በዋስ ተፈትተው ቤት

ቢመለሱም እንኳ፥ የታተመው «ተግሣጽና ምክር» መጽሐፍ በጠቅላላ ተይዞ የትም እንዳይሸጥ ጥብቅ ትእዛዝ ተላለፈ። በአባቴም ላይ «ቤተ ክርስቲያንን ተሳድቧል» የሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ፍርድ ቤት ቀረቡ። ጉዳዩ ይግባኝ እየተባለ ከዓድዋ ወደ መቀሌ፥ ከዚያም አዲስ አበባ ከጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ድረስ ደረሰ።

ተግሣጽና ምክር በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት መካከል ባሉት ልዩነቶች ቢያተኩርም እንኳን በጣሙን የሚዘልፈው መሠረተ ሃይማኖቱን ሳይሆን ልማድ ይዘው፥ ሃይማኖትን ተመርኩዘው በቤተ ክርስቲያኑ የነበሩትን ጉልህ ጥፋቶችን ነው። ከእነዚህም ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፥ የፍልሰታ፥ የሁዳዴ፥ የረቡዕና ዐርብ አጽዋማትን፥ የቅዱሳንን ስም እየጠሩ የበዓላትን ቀን በማክበር የሥራ ቀናትን መቀነስ፥ ሰው ሲሞት የሣልስት፥ የዐሥራ ሁለት፥ የአርባዓ፥ የሙት ዓመት ተዝካር ወዘተ . . . እያሉ የሟቹ ቀሪ ቤተሰቦች የሚተዳደሩበትንና ልጆቹ የሚያድጉበትን ንብረት ማባከን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከቶ ያልተጠቀሱትንና ፍጹም ሊታመኑ የማይችሉትን ገድልና ድርሳናትን መስበክንና ማስተማርን በጥብቅ ይነቅፋል። ታዲያ ጥቅማቸው የተነካ ብዙ የቤተ ክህነት ሰዎች ስለ ተናደዱ አባቴን እስከ ጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ድረስ አደረሷቸው። የታተመው መጽሐፋቸውም ታስሮ እንዳይሸጥ ተከለከለ።

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ከጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ቀርበው ምንም ጠበቃ ይሁን ነገረ ፈጅ ሳይፈልጉ በአንድ እጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው፥ በሌላው ጥቅሶችን እያወጡ በመጠቈም፥ ከመላው የቤተ ክህነት መሪዎች ጋር ፊት ለፊት፥ ዐይን ለዐይን ተፋጥጠዋል። በኋላም ከጃንሆይ ችሎት ፊት ቀርበው ንጉሡ «በሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሶ ይኸው ይከራከራችኋል፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሳችሁ ነው መልስ መስጠትና መርታት...» ቢሏቸው፥ አጥጋቢ ጥቅስ አቅርበው ሊከራከሩና ሊረቱአቸው አልቻሉም። በዚህ ጊዜ ጃንሆይ «እንግዲያውስ በቂ መልስ ከሌላችሁ የተያዘው መጽሐፍ ነጻ እንዲለቀቅ አዝዘናል። መልስ አለን የምትሉ ከሆነ መጽሐፍ ጽፋችሁ ዓጸፋውን መልስ ስጡት፤ እስካሁን ለተጉላላው እናንተ በግዳችሁ ትከፍሉታላችሁ።» ብለው ፈረዱላቸው።

ፍርዱን የሰማ ከጥግ የቆመ አንድ ባሕታዊ በንዴት ተንደርድሮ ከአጠገቡ የነበረውን የክብር ዘበኛ በጥፊ ጆሮ ግንዱን ማጎኑ ይነገራል። አቶ ዘመንፈስን ያገኘ መስሎት ይሁን ወይም ንጉሡን እንጃ፥ በወታደሮች ተይዞ ከችሎት ወጣ። አባቴ ሙግቱን ረትተው ቤት ሲመለሱ በታላቅ ደስታ ነበር የተቀበልናቸው።

ጃንሆይ «ለተጉላላኸው እኔ ልክፈልህ እንጂ ካህናቱስ አይከፍሉህም::» ብለው የሸለሟቸው አንድ ሺህ ብር፥ ከሊቀ መኳሱ እጅ አምስት መቶ ሆና እንደተቀበሉ ይናገራሉ:: በዕለቱ በዓድዋው ቤታችን ትልቅ ፈንጠዝያና ድግስ ሆነ::

ተግሣጽና ምክር በይፋ ይሸጥ ጀመር:: ብዙዎች በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባህላዊ ሰንሰለት ታስረው የነበሩ ሰዎች የሕሊና ነጻነት በማግኘታቸው፥ ከሩቅ እሳቸውን በደብዳቤና በማጠያየቅ እየፈለጉ ይተዋወቁ፥ ያመሰግኑ፥ ይመርቁ፥ ልዩ ልዩ ስጦታዎችና ማስታወሻዎችንም ይልኩላቸው እንደ ነበር አስታውሳለሁ:: ከውጭም ከኢየሩሳሌም፥ ከሱዳንና ከኬንያ ጭምር የሚመጡላቸው ደብዳቤዎችና ብዙ ስጦታዎችም ነበሩ::

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ በመጻፍ ብቻ ቢሰማሩ ኖሮ እኛ ልጆቻቸው በረኃብ እናልቅ ነበር:: ግን ትጉሕና ታታሪ ነጋዴ ስለ ነበሩ ቀን ቀን በንግድ፥ ማታ ማታ ደግሞ መጻሕፍትን ሲያነብቡ፥ ሲመራመሩና ሲጽፉ ያነጉት ነበር:: በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች ድካማቸውን እየተመለከቱ «አለቃ መቼ ይሆን የሚያርፉት?» ሲሏቸው የዘወትር መልሳቸው «ዕረፍት በመቃብር» የሚል ነበር::

ተግሣጽና ምክር ተሸጦ ስላለቀ በድጋሚ ሁለተኛ እትም አሳትመው አወጡ:: በሁለተኛው እትምም ተጨማሪ ሐሳቦችንና ግጥሞችን ጽፈዋል:: ከጻፏቸውም ግጥሞች መካከል: -

«ተግሣጽና ምክር መልካም ገሰገሱ
መልክና ታምርን በገድል እየጣሱ
ሾላ መነጠሩ ተራራ አፈረሱ
በስንት መከራ ካቡን ቤት ደረሱ
እውነት ስለያዙ የትም ተከሰሱ፥
ዳኛው ቅዱስ መጽሐፍ ሲበይን ለእነርሱ
በጽሑፍ መልስ ስጡ ልማድ አትላሱ
ብሎ ነገራቸው ተፈሪ ቅዱሱ፥
መልስማ ለመስጠት የትኛውን ሊጠቅሱ
ማጉረምረም ብቻ ነው ወጋቸው እነርሱ፤
ተግሣጽና ምክር ምንኛ በረቱ
12 ዓመት ታስረው ቢንገላቱ
ተስፋ ባለመቁረጥ ጨክነው ሞገቱ
ግን የማታ ማታ አቶ እውነት ረቱ::»

የሚል የደረሰባቸውን ግፍ የሚገልጽ ይገኝበታል:: እንደ ገናም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ጠላት፥ ጸረ ማርያም የሚሉ ትችቶች ስለ

ተሰነዘሩባቸው እርሳቸው ግን ቤተ ክርስቲያንን የሚወዱና እንድትታደስ የሚመኙ እንጂ ጠላትዋ እንዳልሆኑ ሲጽፉ፡ -

«ወዳጆቼ ሆይ! ዓለም መካሪውን እንደሚጠላ ሁላችሁም በክርስቶስ ላይ የደረሰውን ሁሉ አይታችኋል። እኔም ደግሞ በትንሹ ዐቅሜ አገሬን ይልቁንም አሮጌዋ ቤተ ክርስቲያናችን ከዕንቅልፍዋ ነቅታ፥ የወንጌል ቀንዲልዋን አብርታ የቤትዋን ጕድፍ ጠርጋና ተሰናድታ፥ ጥበብ በተባለው እንዶድና ሥልጣኔ በተባለው ሳሙና፥ ልማድ ያሳደፈውን ልብስዋን አጥርታ፥ ንጽሕት ሆና እንድታምርና እንድታጌጥ ብዬ ሕፃናዊ በሆነው፥ በትምህርት ባልበሰለው አዕምሮዬ ጥቂት ኃይለ ቃላትን ጨመር አድርጌ ስለ ዘለፍኋት፥ ባለማወቋ ክፉ ስም ሰጥታ እንደምንታዝንብኝና እንደምትጠላኝ አልስተውም። «እኔ ግን እናትህ ባረጀች ጊዜ አትናቃት . . . ክፉውን በበጎ አሸንፋት እንጂ አትቃወሙት . . . ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚረግሟችሁ መርቁ፥ ስለሚያሳድዷችሁና ስለሚጠሏችሁ ጸልዩ። . . .» የሚለውን ቃል ተምሬአለሁና ከቶ አልቀየማትም። . . . በጎውን ነገር ብቻ እመኝላታለሁ እንጂ እርሷ ብትጠላኝም . . . «አባት እናቱን ያልተወ የኔ ተማሪ ሊሆን ብቁ አይደለም . . .» የሚለውን ባታውቅ ነውና እኔስ ምንም አልጠላትም። . . . እኔ በማን ጡት ባደግሁ ነው እርሷን የምጠላ? እርግጥ ነው፥ ንጹሕና ነጭ የሆነውን የጤፍ እንጀራ (ወንጌልን) ባገኘሁ ጊዜ የተፍረቀረቀውን የዘንጋዳ ቂጣዋን (ገድለ ተአምርዋን) አምዘግዝጌ በመጣሌ ብትቀየመኝም ይቅርታዋን ከመለመን በቀር ሌላ የማደርግላት ነገር እንደሌለኝ ኅሊናዬና አምላኬም ያውቃሉ። . . .» በማለት የደረሰባቸውን ዘርዝረው ለመግለጽ ችለዋል።

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ሃይማኖትን ተመርኩዞ፥ ባህል ተቈራኝቶ ኅብረተሰብን የሚጎዳውን ሁሉ እንዲቀር የሚጥሩ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ተመሥርታና ታድሳ እንድትጸና የታገሉ ቢሆንም፥ እንኳን እንዲሁ ለመታደስ ብቻ ተብሎ ባህል ይሁን ልማድ ይለወጥ፥ ዐዲስ ዐዲሱን እንያዝ የሚሉ ሰው አልነበሩም። ይልቁንም ሁሉን ነገር በመመርመር፥ መልካም መልካሙንም በመከተል፥ መጥፎ መጥፎውንም በማራቅ የሚያምኑ፥ የሁለቱንም ልዩነት ወንጌል እንዳለው «በፍሬው ታውቁታላችሁ» የሚሉ ነበሩ። በዚህም አያይዘው «ኢትዮጵያ የፈረንጁን ጎረምሳ ከነንፍጡ ዐቅፋ ሳመችው . . .» እያሉ ዘመናዊ

የሆነ ሁሉ ጠቃሚ አይደለም፥ መምረጥና መለየት ደግሞ የተጠቃሚው ፈንታ ነው ይላሉ።

በአሥመራ ከተማ ወደ ሃያ ዓመት ገደማ ሲቀመጡ፥ በሃይማኖት ጉዳይ ከአሥመራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ካህናት ጥቂት፥ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ከፕሮቴስታንትም ጭምር በየጊዜው ከቤታችን ጠርተው እያመጡ፥ «ሁላችንም የክርስቶስ አካል ከሆንን እንዴት ተለያይተን እንኖራለን?» እያሉ ሊተባበሩ የሚችሉበትን መንገድ ያነጋግሩ ያወያዩ ነበር። ሊቃውንቱም ተሰብስበው፥ ከአንድ ማዕድ እየቈረሱ የሚለያዩበትን ነጥቦች በመተው በሚቀራረቡበት ነጥቦች ላይ በማትኮር ሲወያዩ ያመሻሉ።

ተግሣጽና ምክር በታተመ በግምት ሰባት ዓመት ያህል ቆይቶ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወገን በሆኑት በመልአክ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ዘዲማ ጊዮርጊስ ጉጃም ተጽፎ፥ «ኲኲሐ ሃይማኖት» (የሃይማኖት ዐለት) በሚል ርእስ የተዘጋጀ የመልስ መጽሐፍ ታትሞ ወጣ። ከመጽሐፉም መግቢያ ላይ «. . .ነፋስ ነፈሰ፥ ዝናብ ዘነበ፥ ጕርፉም ጐረፈ፥ ቤተ ክርስቲያንዋንም ሊያፈርሳት ቃጣ። ቤተ ክርስቲያንዋ ግን በጽኑ መሠረት፥ በኲኲሐ ሃይማኖት የቆመች ስለሆነች ሊያናውጻት አልቻለም. . .» ይላል። ታድያ ዘመንፈስ ቅዱስ የብዕር እንጂ የመጠሪያ ስማቸው «ጕርፉ» ስለ ሆነ፥ አባቴ ከጓደኞቻቸውና በቅርብ ከሚያውቋቸው ሊቃውንት ጋር ስለዚህ ሲያነሡ «ጕርፉ እንዳይወስዳችሁ . . .» እያሉ ይቃለዱና ይጫወቱ ነበር።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በመጽሐፋቸው ብዙውን ያተኮሩት በተግሣጽና ምክር ደራሲ ላይ ግላዊ ዘለፋና ማቃለል (PERSONAL INSULT) ስለ ነበር፥ ቅር ለማሰኘትና ለማስቀየም የሚበቁ ብዙ ክፍሎች ነበሩት። አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ግን ኲኲሐ ሃይማኖት ታትሞ በመውጣቱ የተሰማቸው ደስታ ወሰን አልነበረውም። ጸሓፊው ከእርሳቸው ጋር ሳይተዋወቁ መጽሐፋቸውን ብቻ በማንበብ የጽሑፍ መልስ አትመው በማቅረባቸው፥ አባቴ የአድናቆት እንጂ የሐዘን ይሁን የቅሬታ ስሜት አልነበራቸውም።

በየጊዜው አዲስ አበባ ሲመላለሱ ከተዋወቋቸው የሥነ ጽሑፍ ጓደኞቻቸው መካከል አቶ ዓለማየሁ ሞገስ የተባሉ ጕጃሜ በዩኒቨርሲቲ የአማርኛ የቅኔ መምህር ነበሩ።)፥ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ለግል ሥራ ወደ አሥመራ የመምጣታቸውን ወሬ ሰምተው ለአባቴ ነገሯቸው። አባቴም ይህንን ሲሰሙ ያረፉበትን

ቦታ አጠያይቀው በማግኘት «ጒርፉ እባላለሁ፥ መጽሐፍዎን አንብቤ የተደሰትኩ አድናቂዎ ነኝ. . .» ብለው ተዋወቀው ለምሳ ቤት ይዘዋቸው መጡ። ምሳ ተበልቶ፥ ማዕድ ተነሥቶ፥ ብዙ ከተጨዋወቱ በኋላ አባቴ፥ «. . . ተግሣጽና ምክርን የጻፍኩ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ማለት እኮ እኔ ነኝ . . .» ሲሏቸው፥ መልአከ ብርሃን በጣም ተደናግጠው «እኔማ ማንም ዘመናዊ ጎረምሳ መሰለኝ እንጂ እንዲህ የመሰለ ሊቅ፥ ጨዋ ባለትዳር ሰው መሆንዎን መች ዐውቄ . . .» በማለት ይቅርታ ለመጠየቅ ከተቀመጡበት ተነሡ። አባቴም ልብሳቸውን ይዘው፥ « . . . የለም ይቀመጡ፤ ምንም ይቅር የሚባል የተቀየምኩበት ከቶ የለኝም . . . » ብለው በማስቀመጥ፥ በመጽሐፉ በጣሙን ያተኮሩት በዋና ዋና መንፈሳዊ ክርክሩና ይዘቱ እንጂ በስድቦቹና በዘለፋው እንዳልሆነ ገልጸው ጨዋታቸው ቀጠለ። ከዚህ በኋላ ሁለቱም ወዳጆች ሆነው በተደጋጋሚ እየተገናኙ ብዙ ተጠያይቀዋል። በሁለቱም መካከል ምንም ቂምም ሆነ ቅሬታ አልነበረም።

አሥመራ በሚገኘው ቤታችን ለመጠየቅ የሚመጡ፥ አባቴም አዲስ አበባ ሲሄዱ ፈልገው የሚጠይቋቸው ብዙ ደራስያንና የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ወዳጆች ነበሯቸው። ከእነዚህም ከብዙ በጥቂቱ ከላይ የተጠቀሱት አቶ ዓለማየሁ ሞገስ፥ መምህር ይኄይስ ወርቄ፥ አቶ አቤ ጉበኛ፥ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ (ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊን የጻፉት)፥ አዝማች ክንፉ ኪዳኔ (የወርቅ ሠሪና ጥንታውያን የአክሱም ነገሥታትና የአሠሯቸው ገንዘቦች የሚለውን መጽሐፍ የጻፉ)፥ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን መዝገበ ቃላትና መጽሐፈ ስዋስው አዘጋጅተው በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ያሳተሙት አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ፥ አቶ አማረ ማሞ እና ለጊዜው የዘነጋኋቸው ብዙዎች ስለ ማኅተምም ሆነ ስለ መጻሕፍት ምርምር፥ ስለ ሥነ ጽሑፍ አስተያየታቸውን ለመጠየቅ የሚመጡ ነበሩ። ሁሌ አባቴ በሐሳብና በምክር የሚያውቁትን ያህል ሁሉን ሳይቆጠቡ ስለሚለግሷቸውም በምሳ በእራትም ጊዜ ቤታችን እንግዳ ምንም አይለየውም ነበር።

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ከባለቤታቸው ዐሥር ልጆች ወልደው፥ ዘጠኙን ትተው አልፈዋል። በንግድና በሥነ ጽሑፍ ሥራ፥ ልጆችንም አስተምረው፥ ቀጥተው በማሳደግ ደከመኝ ሳይሉ በታታሪነት በኖሩት ኑሮ በድንገተኛ የዐናት በሽታ (TONSIL) አሥመራ ከተማ በሚገኘው እቴጌ መነን ሆስፒታል ለዐሥር ቀን ያህል ተኝተው ሕመሙ ስለጸናባቸው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ። «ዕረፍት በመቃብር . . .» እያሉ ሲመኙት እንደ ነበሩም ፈጣሪ «ይብቃህ፥ ልጄ ና ወደ ዕረፍቴ ግባ።» ብሎ እንደ ጠራቸው

ይመስላል። መቃብራቸውም በአሥመራ ከተማ ቤት መኻእ በተባለው ቦታ ነው። «የሰው ዕድሜ መርዘምና ማጠር፥ እንደ ቢላ መርዘምና ማጠር ነው፤ ቁም ነገሩ ግን ከርዝመቱ ወይም ከእጥረቱ ሳይሆን ከስለቱ ነው» እያሉ ሁሌ ሲናገሩት የነበረ ንግግር ነው። እግዚአብሔርን በክርስቶስ ስለሰጣቸው ዕረፍት እናመሰግነዋለን።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

መግቢያ

አንተ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ የሐሳቤን መግለጫ የምታነብ፥ በተለይም ወጣቱ ኢትዮጵያዊው ወንድሜ ክርስቶስን በማመንና በእውነተኛው ጥምቀትም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለህ ሁለተኛ ከመንፈስ የተወለድህና ከቅዱስ መጽሐፍም ጋር የተዋወቅህ ትሆናለህ በማለት፥ ወንድሜ እያልኩኝ ደፍሬ መጻፌ ይህንኑ ትልቅ እምነትህንና ስጦታህን አምኜ ነው እንጂ፥ በመጻሕፍት ለሚያላግጡ ከሐዲዎች፥ ደንቆሮዎች፥ ተጠራጣሪዎች አኅርው (እሪያዎች) ለሆኑ ሰዎች እንዳልጻፍኩት አስቀድሜ ልገልጽልህ እወዳለሁ፤ ምሳ. 23፥9፤ ማቴ. 7፥6፤ 2ጢሞ. 3፥1-9፤ ሕዝ. 36፥25-27።

ወንድሜ ሆይ! እንደዚህ ብዬ ስነግርህ ለጊዜው ትነቅፈኝ ይሆናል፤ በመንፈሳዊ ሐሳብ ልብህን ዳኛ አድርገህ በዚህ የተጻፈውን ቃላት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየ ምዕራፉና ቁጥሩ አውጥተህ እየለየህ ብሉያትንና ሐዲሳትን ብቻ ብታነብ ግን፥ እኔ ከልቤ አውጥቼ ከሕሊናዬ አንቅቼ እንዳልጻፍኩት ትረዳዋለህ። ስለዚህ ገንዘብ ብታገኝ የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ገዝተህ አስተውለህ እያመሳከርህ አንብብ። (አማርኛ በመሆኑ ምስጢሩ በቶሎ እንዲገባህ ብዬ ነው፤) ገንዘብ ብታጣ ግን ይህን ከዚህ ውስጥ ተጠቅሶ ያለውን መጻሕፍት ሁሉ፥ በየቤተ ክርስቲያኑ በዕቃ ቤት ውስጥ ዝም በል፥ አትናገር ተብሎ የኋሊት ተቆልፎ ታገኘዋለህ፤ ቋንቋው ግዕዝ ሁኖ የማትረዳው ቢሆን፥ አእምሮ ያለው ተርጓሚ፥ የተማረ ካህንና ሰዋስው (መዝገበ ቃላት) ይዘህ ማንበብና መመርመር፥ ማስተዋልም ያስፈልግሃል እንጂ ጀምረህ ሳትጨርሰው አስቀድመህ ብትነቅፍ፥ ፍሬ ሳታገኝበት መቅረትህን ዕወቀው። መንቀፍ ወይም ማቀፍ የሚገባውም ከባሕረ መጻሕፍት ውስጥ ገብቶ ዋኝቶ ነው እንጂ በውጭ ሁኖ አይደለም። ብትነቅፍ ወይም ስሕተቴን ብታርምልኝ እርሱን በሚያህል ጽሑፍ ካልሆነ በወሬና በአድማ መንቀፍ አይበቃም (አይገባም)። ይልቁንም ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን (የቤተ ክርስቲያን ብርሃን) የተሰኘው አባታችን ቅዱስ ጳውሎስ «ኵሎ አመክሩ ወዘሠናይ አጽንዑ፤. . . ከመ ትፍትኑ ወታመክሩ ዘይኄይስ ግብረ» «ሁሉን መርምሩ መልካሙን ያዙ፤ . . . የተሻለውን ሥራ ፈጽሞ ትፈትኑ ዘንድ» 1ተሰ. 5፥21-22፤ ፊልጵ. 1፥10 እያለ ይመክርሃልና፥ ይህንኑ የአባትህን ምክርና ኑዛዜ (ትምህርት) አጽንተህ ይዘህ ሁሉን መመርመር ያስፈልግሃል። አስቀድመህ ግን ራስህን በራስህ መርምረኸው ስታበቃ፥ ወደ ሕይወት በሚያስገባው በጠባቡ መንገድ ወይም ወደ ሞት

በሚወስደው በሰፊው ጎዳና ላይ እየሄድህ እንደሆነ ልብህን በልብህ ታዘበው፤ ሰቆ.ኤር. 3÷39-41፤ ማቴ. 7÷1-14፤ 2ቆሮ. 13÷5::

ነገር ግን በሰው ያለው መንፈስ አስተዋይ የሚያደርግ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው፤ ኢዮ. 32÷8፤ መዝ. 49÷20፤ 1ቆሮ. 2÷10-15::

ማስጠንቀቂያ

1ኛ. የተወደድህ አንባቢ ሆይ ይህችን አነስተኛ የሐሳቤ መግለጫ የምትሆን መጽሐፍ ስጽፍ÷ በመጀመሪያ የሚበቃ ትምህርት አልተማርሁም፤ ዳግመኛም የጻፍኩት በልዩ ጊዜና ቦታ ሳይሆን የዕለት ምግብ ከማገኝበት የንግድ (የሱቅ) ሥራዬ ላይ ሆኜ በተደራቢነት ስለሆነና እኔም ለአማርኛው ባዕድ (ትግሬ) በመሆኔ÷ ብዙ የአነጋገር ጉድለትና ጸያፍ እንደምታገኝበት እተማመናለሁና የጎደለውን ሞልተህ÷ የጠመመውን አቅንተህ÷ የደፈረሰውን ቃላት አጣርተህ ታነብልኝ ዘንድ በማክበር አሳስብሃለሁ፤ ሮሜ 15÷1-7፤ 1ቆሮ. 10÷24፤ 2ቆሮ. 5÷10-13::

2ኛ. ይህችን መጽሐፍ አስቀድሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሮ ላልተገነዘባቸውና ይልቁንም በግእዝ ጠባይ አንደበቱ ላልታሸ ሰው ምስጢሩ ከበድ ሳይለው አይቀርም፤ ሆኖም ደረቅ ቂጣ የዐዋቂዎች እንጂ የሕፃናት ምግብ (ወተት) እንዳልሆነ ለአንባቢዎች ደግሜ አስጠነቅቃለሁ፤ ዕብ. 5÷10-14፡

መንፈስ ቅዱስ ብርሃኑን ይግለጽልህ!
ደራሲው

ልዩ መግለጫና መቅድም

«የተኛህ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል፤» ኤፌ. 5÷14፤ ሮሜ 13÷11-14።

«አሮጌው ሥራ ፈጽሞ ሄደ፤ እነሆ ሁሉ ታደሰ።» 2ቆሮ. 5÷17

እናንተ የአገሬ ልጆች÷ በውሃ ጥማት የተጠቃችሁ ስለምን አልኮል (አዋልድ) ትጠጣላችሁ? ለሚጎዳችሁና ለማያረካችሁ ለምን ገንዘብ ትሰበስባለችሁ? ስለማይጠቅማችሁ ልምከራችሁ፤ ይህችን ትንሽ መጽሐፈ ተግሣጽ ገዝታችሁ÷ ወደ ቅዱስ መጽሐፍና ወደ ኢየሱስ የሕይወት ምንጭ መግቢያና መድረሻ (መሪ) እንድትሆናችሁ÷ እውነቱን ከሐሰት እየለያችሁ ወተት ወተትዋን (ጥቅስ ጥቅሷን) በዚች ቋጫ (ጽዋ) ብትጠጧት (ብታነቧት) ከጥማት ረክታችሁ÷ በኢየሱስ ስም ስርየት አግኝታችሁ÷ አማላጃችሁም እርሱ ብቻ መሆኑን ካመናችሁ ከርሱ ጋር በሰማይ ለዘለዓለም ትነግሣላችሁ፤ ምሳ. 8÷10-36፤ ኢሳ. 55÷1-3፤ ዮሐ. 4÷5-14፤ ኤፌ. 2÷4-7።

እናንተ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ያመናችሁ÷ በእርሱ የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ÷ ይህችን ትንሽ መጽሐፍ ጻፍሁላችሁ፤ 1ዮሐ. 5÷10-13።

እኔ ግን በእውነት ከሰው ሁሉ ይልቅ ደንቆሮ ነኝ፤ ጥበብ አልተማርሁም የቅዱሳንም ዕውቀት የለብኝም፤ ምሳ. 30÷1-3፤ 1ቆሮ. 3÷18።

እኔ የማላስተውለውን ነገር ተናገርሁ፤ ይህንንም አለማወቁ ግሩም ነው፤ ኢዮ.42÷3።

እኔ በዕድሜ ታናሽ÷ የ36 ዓመት ልጅ ነኝ፤ ስለዚህ ሠጋሁ፤ ዕውቀቴንም እገልጥላችሁ ዘንድ ፈራሁ፤ ነገራችሁን ጠበቅሁ÷ እንዲሁም ተመለከትኋችሁ÷ ነገር ገን ልማድና ስንፍናን የሚገሥጽ አንድ ሰው አላኘሁም። ነገር (ቃል) ተሞልቻለሁ÷ እናገራለሁ÷ ጥቂትም እተነፍሳለሁ÷ ከንፈሬንም ገልጬ እመልሳለሁ።

ነገር ግን በቁልምጫ መናገር አላውቅም፤ አለዚያስ ፈጣሪዬ ከሕይወቴ ፈጥኖ ይቈርጠኛል፤ ኢዮ. 32÷21-22።

ሰውን (ዓለምን) ደስ የሚያሰኘውን መናገር ከፈለግሁ ግን የክርስቶስ ባርያ ባልሆንኩኝ ነበር ገላ.1÷10።

በክርስቶስ ወንጌል ግን አላፍርም፤ የእግዚአሔርን ኃይል ለሚያምን ሁሉ መድኃኒት ነውና፤ ሮሜ 1÷16፤ 1ቆሮ. 1÷18::

የሀገሬ ካህናት ሰው የወንጌልን እውነት መርምሮ እንዳያገኛትና እያታለሉ የሚኖሩበት ሥጋዊ ጉዳይም እንዳይቀርባቸው ሲሉ÷ ይህንኑ ተግሣጽና ምክር የተባለውን ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወለደውን መጽሐፌን በኢትዮጵያ እንዳይሸጥ አስከለከሉ÷ አሳሰሩ፤ በእሳትም አቃጠሉ÷ ሲያነቡት ከተገኙ ሰዎችም ጥቂቶችን አሰሩ:: የክርስቲያን ሃይማኖት መሠረቱ ግን «ነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት» «በሁሉ ዘንድ ባለች÷ የሐዋርያት ጉባኤ በምትሆን በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን» ሲሆን ÷ ታዲያ አሳሪዎቹ ናቸው ወይስ ታሳሪዎቹ ነን የሐዋርያት ተከታዮች ነን የምንል? እንጃ! ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነብኝ፤ ዛሬም ቢሆን ጸሐፍትና ፈሪሳውያን የጨለማው ሥልጣናቸው በወንጌል ብርሃን ገና አልተገፈፈም መሰለኝ፤ ይገርማል! እኔ ግን ሃይማኖቶችን ሁሉ ስመረምር የመሐመድ ብቻ ካልሆነ በቀር በእሥራትና ግርፋት÷ በኃይልና በሰይፍ የቆመ ሃይማኖት በታሪክ ዓይን ከቶ አላየሁም፤ ወይ ዕውቀት ማነስ! «አጋዧን ያየች ፌጪታ መጅዋን ሸሸገች» እንደሚባለው ዕውቀትስ ቢኖራቸው አሽከሮቹን (አገልጋዮቹን) ከነመጻሕፍቶቻቸው ቀርቶ የምስጋናውን ጌታም ባልሰቀሉትም ነበር፤ 1ቆሮ. 2÷8::

ወንድሞቼ አንባቢዎች ሆይ! እውነትን ግን እንኳን ከምድር በላይ አስረዋት ይቅርና÷ ከምድር በታች ቢቀብሯትም በድንጋይ መዝጊያ ተዘግቶ÷ በብርቱ ጥንካሬ ተሠርቶ በትጉሃን ዘበኞች በሚጠበቅ ጥልቅ ሕንጻ ውስጥም ቢዘግዋት÷ አእላፍ ሐሰተኞችም ቀብረው ሊይዟት ስላልቻሉ÷ በሦስተኛው ቀኗ ተነሥታ ሁሉንም ከንቱ አድርጋ እስከ ዛሬ ድረስ በእውነተኝነትዋ እየፎከረች÷ ዐዋቂዎች ነን የሚሉ ሰዎችን ስታሳፍራቸው ትኖራለች፤ ማቴ. 27÷57-66፤ 1ቆሮ. 1÷18-22::

ለነገሩ እውነታቸውን ሳይሆን አይቀርም፤ ይህ መጽሐፍ በልማዳቸው ምስጢረ ካህናት የሚባለውን ስውር ጥቅማቸውን ሁሉ ግልጥልጥ አድርጎ÷ በየሆዱ የነበረውን የብዙ አዋቂ ሰው በሽታ (እበጥ) ፍርጥርጥ አድርጎና ገላልጦ÷ በጥቶና (ቀድዶና) ዋናው የኀጢአት ሐኪም ክርስቶስ ብቻ ለሰው ሁሉ በግድ እንደሚያስፈልገው ስላስረዳ÷ በእነርሱ ዘንድ የሚገኘውን ግብዝ የማታለያ መድኃኒት ገዢ እንደማያገኙለትና ሥጋዊ መብታቸውንም እንደሚያስቀርባቸው ስለተረዱት÷ በሥጋዊ ዳኝነት

ቆሞ ለተመለከተው፥ «ጅብ ከሚበላኝ ጅብ በልቼ ልቀደስ» ነውና፥ እኔ የነገው የፍርድ ቀን የሚያመጣውን አላውቅም እንጂ ለዛሬውስ «ሊታሰር ይገባዋል» ባይ ወሮ በላ በድምፅ ብልጫ ቢበዛም የእግዚአብሔር ቃል በመታሰሩ የሚያለቅሱ የተመረጡ ጥቂቶች አይታጡምና እንባቸው ምን ያመጣ ይሆን? በማለት የገዛ ሕሊናዬ ትክክለኛ ነጻነትና ፍርድ አጥቶ፥ በሐዘን እተጨነቀ ተቸግሮ ሲያስቸግረኝ፥ ተወኝ ያለው አይቀርም አይዞህ የእግዚአብሔር ቃል ከቶ አይታሰርም እያልሁ፥ ደካማውን ሕሊናዬን በቅዱሳት መጻሕፍትና በሕያው ተስፋ እስከዚያው ድረስ አጽናናዋለሁ፤ 2ጢሞ. 2፥9፤3፥16።

አዬ! መሪዎቻችን ራሳቸውን ብቻ ሲያሰማሩ ኀፍረትን አያውቁትምና፥ የነቢያትና የሐዋርያትን መጻሕፍት ሲያሳስሩት ምንም አላፈሩም፤ ኤር. 8፥9-12።

አቤቱ አምላኬ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትምና በምሕረትህ ይቅር በላቸው፤ የሐዋ. ሥራ 7፥51-60።

እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የጥበብና የፍቅር፥ የኃይልና የድፍረት እንጂ የፍርሀትና የኀፍረት መንፈስ አልሰጠንምና ምስጋና ይገባዋል፤ 2ጢሞ. 1፥6-10።

ነገርህን (ቃልህን) ባገኘኋት ጊዜ በላኋት፤ ለልቤ ደስታና ሐሴትም ሆነችልኝ ኤር.15፥16፤ ሕዝ.3፥1-3፤ ራእ. 10፥8-11።

ወንድሞቼ ሆይ! ከሰው ስሕተት ከብረትም ዝገት አይታጣምና በተሳሳትሁት ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናችኋለሁ፤ መዝ. 19፥12።

ትንሹ አገልጋያችሁ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ
ዘብሔረ ዓድዋ

ምዕራፍ አንድ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ:: በአንድ አምላክ ፫ አካላት÷ በ፫ አካላትም ፩ አምላክ መኖሩን አምነን እንናገራለን::

የእምነት ዐዋጅና ትርጓሜ

«ወከልአሰ መሠረተ አልቦ ዘይክል ሣርሮ ዘእንበለ ዘተሣረረ ወመሠረቱሂ ኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ::» «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና÷ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::» 1ቆሮ.3÷11::

አንተ ግን እኔ ልልክህ ነውና ተነሥተህ ወገብህን ታጠቅ÷ በፊታቸውም እንዳላሳፍርህ ብላቴና ነኝ ብለህ አትፈር፤ እነሆ እኔ ይህንን ሕዝብ ባንተ ፊት እንደ ዕንጨት ነገሬንም በአፍህ እንደ እሳት አደርገዋለሁና፤ ትበላውማለች:: እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋራ ነኝና÷ በዚህ ሕዝብ የጸና የናስ ቅጥር አድርጌ አቆምሃለሁ፤ ይዋጉሃል ከቶም አያሸንፉህም፤ ከክፉ ሰዎች እጅና ከኀያላንም ቡጢ እቤዠሃለሁና በእነርሱ ፊት አትፍራ፤ ኤር. 1÷7-10፤ 15÷10-21:: እነሆ ዛሬ በአሕዛብና በነገሥታት ላይ እንድታፈርስና እንድትሠራ÷ እንድትገለብጥና እንድታጠፋ÷ እንድትተክልና እንድትነቅል÷ እንድታነሣና እንድትጥል ብዬ አቆምሁህ፤ ኤር. 1÷4-19፤ ሉቃ. 2÷34::

እነርሱ ግን እሾህና ሳማ ይሆኑብሃልና አትፍራ፤ አትደንግጥም:: ግንባርህን በግምባራቸው ፊት ከአልማዝና ከቡላድ ደንጊያ ይልቅ አጸናዋለሁ ሕዝ.2÷1-10፤3÷1-11:: ዝናም ከሰማይ ወርዶ ምድርን እንደሚያርስና ለዘሪ ፍሬ እንደሚሰጥ÷ ከአፌ የምትወጣው ቃሌም እንዲሁ የላክኋትን ትፈጽማለች፤ የምሻውን ሁሉ ታደርጋለች እንጂ በከንቱ ወደ እኔ አትመለስም:: በእውነቱ ቃሌ እንደ እሳት ወይም ደንጊያውን እንደሚሰብር መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር ኢሳ.55÷8-11፤ ኤር.23÷29፤ ሕዝ.36÷22-29:: ስለዚህ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ «ርጉመ ለይኩን ኵሉ ዘይትአመን በፍጡር÷ ኢትእመኑ በመላእክት÷ ወኢበዕጓለ እመሕያው እለ ኢይክሉ አድኅኖ፤ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እምተአምኖ በዕጓለ እመሕያው፤ ይኄይስ ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እምስተሰፍዎ በመላእክት ወከንቱ ተአምኖ በሰብእ::» «በፍጡር የሚታመን ሁሉ የተረገመ ይሁን! በመላእክት አትታመኑ÷ ማዳን

በማይችሉ በሰው ልጆችም አትታመኑ፥ በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል፤ በመላእክት ተስፋ ከማድረግም በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል፤ በሰውም መታመን ከንቱ ነው።» እያልህ ደጋግመህ ንገራቸው፤ መዝ. 118፥8-9፤ 146፥3-7፤ 17፥5-8፤ ሕዝ. 3፥1-21፤ ማቴ. 18፥15-17፤ ሉቃ. 9፥23-27፤ የሐዋ. ሥራ 26፥14-18።

«ዘይሰምዕ ይስማዕ፤ ወዘየዐቢ ይዕበይ» «የሚሰማ ይስማ፤ የማይሰማ አይስማ» ሕዝ. 3፥27፤ ራእ. 22፥10-12።

ሃይማኖት ማለት አምነህ የምትሄድበት መንገድና ሄደህም በእርግጥ የምትገባበት አገር ወይም ሕያው መኖሪያ ማለት ነው። ወይም ገና ያልታየውን መንግሥት ስማያት በዐይነ ልቡና አይቶ፥ በእደ ሕሊና በተስፋ ጨብጦ መያዝ፥ ወይም ከሁሉ በፊት አምላክህን፥ ቀጥሎም ሰውን ሁሉ እንደ ነፍስህ መውደድና ማፍቀር ማለት ነው፤ ማቴ. 5፥9፤ 42-48፤ 22፥37-40፤ ሮሜ 8፥24-25፤ 2ቆሮ. 4፥18፤ ዕብ. 11፥1።

ሃይማኖት ለሚባል ሁሉ ዋናው ፍሬ ነገሩና ምንጩ የመንገዱ ትርጓሜ ፍቅር እንደሆነ አንዳንድ አዝማሪዎች እንኳ ሳይቀሩ በሚከተለው ድርሰት ገልጸውታል።

> ውዳሴ ማርያም ቃል ትምህርት
> መዝገበ-ቅዳሴ ሰዓታት
> ድጓ ዝማሬ መዋሥዕት
> ትንሽ ፍሬ አጣሁበት፤
> የጋላን ሃይማኖት ይዣለሁ
> ወንድሜን እወዳለሁ።

የፍቅር አባት መምህራችን ክርስቶስ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁ በዚህ ይታወቃልና፥ እኔ በሄድኩበት መንገድ ተከተሉኝ ብሎአልና፤ ዮሐ. 13፥34-36።

ይህ መንገድና ይህ አገር (በር) ግን ቅዱሳት መጻሕፍት (ብሉይና ሐዲስ) እንደሚነግሩን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው። እርሱ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ «አነ ውእቱ ፍኖትኒ፥ ወጽድቅ፥ ወሕይወት፤ ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ።» ዮሐ. 14፥6፤ ዕብ. 7፥25። «አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘበአማን፤ ዘቦአ እንተ ኀቤየ ይድኀን፤ ወይረክብ ምርአየ።» ዮሐ. 10፥9።

«አማን አማን እብለክሙ ዘይሰምዕ ቃልየ ወዘየአምን በዘፈነወኒ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም፤ ወኢየሐውር ውስተ ደይን፤

አላ ዐደወ እሞት ውስተ ሕይወት፤» ዮሐ. 5÷24 «ወይቤላ ኢየሱስ አነ ውእቱ ትንሣኤ ወሕይወት፤ ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ ወኵሉ ዘሕያው ወየአምን ብየ ኢይመውት ለዓለም፡፡» ዮሐ. 11÷25፡፡ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ ሞትን ለዘለዓለም አያይም፡፡» ዮሐ. 8÷51፡፡ «ደጁ እኔ ነኝ፤ ማንም በኔ የሚገባ ይድናል፤ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ፤ ቸር ጠባቂ ራሱን ስለ በጎች ይለውጣል፤ እኔ ሕይወት ከነትርፉ እንዲሆንላችሁ ብዬ መጣሁ፡፡» ዮሐ. 10÷7-15፡፡ «እኔ የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ማንም ከእጄ ሊነጥቃቸው አይችልም፡፡ እኔና አብ አንድ ነንና፡፡» ዮሐ. 10÷28-30፡፡ «አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም÷ ዘተለወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት÷ አላ ይረክብ ብርሃነ ሕይወት፡፡» ዮሐ.8÷12፡፡ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደእኔ የሚመጣ አይራብም፤ የሚያምንብኝም ለዘለዓለም አይጠማም፡፡» ዮሐ. 6÷35 «በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው» ዮሐ. 3÷36፡፡ ሥጋዬን የበላ÷ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፡፡» ዮሐ. 6÷54 «በኔ የሚያምን የሕይወት ውሃ ፈሳሽ ከሆዱ ትፈሳለች፡፡» ዮሐ. 7÷38 «አማን አማን እብለክሙ ዘየአምን ብየ ቦ ሕይወተ ዘለዓለም፡፡» ዮሐ. 6÷47፡፡ በእኔ የሚያምንብኝ ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሁኜ ወደ ዓለም መጣሁ፡፡» ዮሐ. 12÷46፡፡ «በኔ እመኑ እኔ ሕያው ነኝና፤ እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ፡፡» ዮሐ. 14÷11-19፡፡ «እኔ ለጽድቅ እመሰክር ዘንድ ወደ ዓም መጣሁ፡፡» ዮሐ. 18÷37፡፡ «ኢየሱስም በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡» ዮሐ. 20÷19፡፡ «ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፡፡» ዮሐ. 14÷27፤ 20÷19፡፡ «ወደ እኔ ኑ÷» ማቴ. 11÷28፤ «ከእኔም ተማሩ» ማቴ. 11÷30፤ «በእኔም ጽኑ» ዮሐ. 15÷4፤ «አነ ውእቱ ጒንደ ወይን ዘጽድቅ÷ ወአንትሙሂ አዕጹቂሁ÷ ወእመቦ ዘኢነበረ ብየ ይገድፍዎ አፍኣ ከመ ዐጽቅ ይቡስ÷ ወያውዕይዎ በእሳት÷ ወበእንተዝ ንበሩ በፍቅረ ዚአየ፡፡» «እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፤ . . . በኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፤ ያቃጥሉአቸውማል፤ . . . በፍቅሬ ኑሩ፡፡» ዮሐ. 15፡1-10፡፡ እያለ አስተካክሎ ነግሮናል፡፡ ጽድቅ ሲል በዕብራይስጥ ቃል ቅኑ÷ ቀጥ ያለ÷ የማያሳስት እውነተኛ መንገድ ማለት ነው፡፡ ይህን መንገድ ፈልሞልን (ቀይሶልን) የምንገባበት÷ አገርም ለማሰናዳት የሄደልን ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ዮሐ. 14÷1-4፤ ዕብ. 4÷14-16፡፡

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ፤ እመጽእ ካዕበ ወእነሥአክሙ

ጎቤየ ከመ ተሃልዉ አንትሙኒ ኀበ ሀሎኩ አነ።» ዮሐ. 3÷13፤14÷3። ቦታ ላዘጋጅላችሁ ሄጃለሁ፤ ተመልሼ መጥቼ ወደ ቤቴ መንግሥተ ሰማያት ላስገባችሁ÷ ከኔ ጋር እንድትኖሩልኝም÷ ከአባቴ ጋር ላስታርቃችሁ÷ ላማልዳችሁ ነውና ትእዛዜንና ሕጌን እየፈጸማችሁና ትምጻእ መንግሥትከ ብላችሁ ጸሎት እያዘወተራችሁ በተስፋ ነቅታችሁ እስክመጣ ድረስ ጠብቁኝ ብሎ አዞናል። ስለዚህ እርሱን ብቻ አማላጃችን መሆኑን አምነን ሌሎችን የማይጠቅሙ የፍጡራን አማላጆችን ትተን÷ <u>«እነሆ ለሁሉ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እሰጠው ዘንድ ፈጥኜ እመጣለሁ፤ ዋጋዬም ከኔ ጋር ነው።»</u> ራእ. 22÷12 ስላለን÷ ጌታ ሆይ! ኢየሱስ ና እያልን የእርሱን ትእዛዝ ብቻ እየፈጸምን÷ በኃጢአታችን እያዘንን እርሱን መጠበቅ ይገባናል። አሁን ግን የአማላጅነቱን ነገር ሽማግሌው ሐዋርያው ዮሐንስ የነገረንን እውነተኛ ምክር እንስማ። «ልጆቼ ሆይ! ኃጢአትን እንዳትሠሩ÷ ከእናንተ ማንም ኃጢአት ቢሠራ ግን ከአብ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ አማላጅ አለን።» ይለናል እንጂ እኔ ወይም እናቴ አለንላችሁ አይልም፤ 1ዮሐ. 2÷1-2፤ ዮሐ. 19÷25-27።

እውነተኞች ክርስቲያኖች ማለትም ዐሥሩን ቃላተ ኦሪትና ስድስቱን ቃላተ ወንጌልን አጥንቶ÷ ፈጣሪውን ብቻ በሃይማኖት እጅ ይዞ÷ በሠሩት ኃጢአት እያዘኑ÷ ዘወትር ወደርሱ እየጮሁ ምሕረትን ከመሐሪው እየለመኑ በጸሎት ተግቶና ነቅቶ መኖር ነው። የማይሰሙ ምውታንን አስምሩኝ ከማለት የሚሰማውን ሕያው ማረኝ ማለት ይበልጣል፤ መዝ. 51÷1-4፤ ማቴ. 24÷42-51፤ ዕብ. 7÷8-28።

«ሥቃያቸውንና ጩኸታቸውን ሰማሁ፤ ላድናቸውም ወረድሁ።» ዘፀ. 3÷4-8። «ወደ እኔም የጮኸ እንደሆነ÷ መሐሪ ነኝና እኔ እሰማዋለሁ» ዘፀ. 22÷27 «ለአንቺ የሰበሰብሻቸው ሁሉ ዓውሎ ነፋስ ይወስዳቸዋልና በጮህሽ ጊዜ ሊያድኑሽ አይችሉም።» ኢሳ. 57÷13። «የዚያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ትጮሃለህ፤ እርሱም እነሆኝ አቤት ይልሃል።» ኢሳ. 58÷9 «እንግዲህ ሃይማኖት ማለት ከመስማት ነው፤ መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።» ሮሜ 10÷16።

ምዕራፍ 2

ማይ ንዝፀምኡ ምኽሪ ንዚሰምዑ

ኣቱም ኢትዮጵያውያን ኣሕዋተይ፤ እቲ ብዘይ ፍልጠት ኣምላኽ እተማላለስኩሙሉን ፍቓድ ኣህዛብ ዝገበርኩምሉን ዝሓለፈ ዘበን ይእኽልኩም፤ 1ጴጥ. 4÷1-3:: ካብ ደጊምሲ ተንስኡ ንቕሑ በርትዑ ሰባኡት ኩኑ ኣብ እምነት ክርስቶስ ጥራይ ፅንዑ፤ 1ቆሮ. 16÷13:: በይዛኻትኩም መርምርዎ'ሞ ንኹሉ ተዓዘቡዎ ነቲ ፀፅቡቐ'ውን ኣፅኒዕኹም ሓዙዎ፤ ካብቲ ከክፋኡን ሐሕማቐን ህደሙ ናብቲ ቅኑዕን ፅቡቐን ሰናይን ልገቡ፤ 1 ተሰ. 5÷15-24::

ከመይከ ናብቲ ኣረጊት ልማድን ዘይጠቅም ኣረጊት ፅድቅን ፍረ ዜብሉ'ሞ ብዙሕ ዝዓይነቱ ጋሻ ሃይማኖትን አትኽዱ? ንብርሃነ-ኣምሮኹም ብመብራህቲ ነብያትን ሓዋርያትን እናተ መራሕኹም <u>ናብቲ ንምድሓን እትዓብዩሉ ሕዋስ ዜብሉ ፅሩይ ፀባ ወንጌል መፂእኹም ግዳ ብዘይ ዋጋ ዘይትእንገዱሞ ሓቂ ዘይትፈርዱ?</u> ክሳዕ መኣዝከ ኢኹም ብኽልተ እግር - ልቢ እትኽዱ? ንምድሓንኩም ዚኸውን ነገር ንምግባር ሎሚ እናፈራሕኹም ስርሑ ሕጊ እናሓሎኹም ብሓጢኣትኩም ድማ እናሓዘንኩም አንቀጥቅጡ'ሞ አምበድብዱ፤ ንፈጣሪኹም አይተሕዝንዎ ሑሩ ብዚብሃል ሰይፊ ኽይትሕረዱ፤ ስንቅኹም ቋፅሩ ብጥምየት ከይትነዱ፤ ሰብዶ ይምለስ እዩ እንድሕር መቓብር ወሪዱ፤ አነ ነገርኩኹም ፅባሕ አብ ናይ ዘለዓለም ሓዊ ከይትእጐዱ፤ እምበኣርሲ ምኽሪ ጴጥሮስ ሓዋርያ ሰሚዕኹም በይዛኻትኩም ተማዓዓዱ ገነት ክትኣትውዋ በቲ ፍቁር ወዱ ሓቅን ፍቕርን ሓዙ ሓሶት ኣይትውደዱ::

፩. እቲ ብፍልጠት ክብሩን ደግነቱን ዝፀውዓና አምላኻዊ ሓይሉ ንህይወትን ንፍርሓት እግዚአብሄርን ዚኸውን ኩሉ ካብ ዚህበና፤

፪. ብኣኡ እታ ኽብርትን ዓባይን ተስፋ ዝረኸብና ኣብ ዓለም ብፍትወት ስጋ ካብ ዘሎ ጥፍኣት ወፂእኹም ተማቐልቲ አምላኻዊ ባህርይ ምእንቲ ኽትኮኑ፤

፫. ብትግሃት ዘበለ ተጋደሉ ኣብ እምነትኩም ደግነት ወስኹ ኣብቲ ደግነትውን ፍልጠት፤

፬. ኣብታ ፍልጠት ከአ ምግታእ ርእስኻ አብቲ ምግታእ ርእስኻ ድማ ዓቕሊ ኣብቲ ዓቕልእ'ውን ፍርሓት እግዚአብሔር፤

፯. ኣብ ፍርሓት እግዚአብሔር ድማ ምፍቃር ኣሕዋት ኣብቲ ምፍቃር ኣሕዋት'ውን ፍቕሪ ንዅሉ ሰብ።

፰. እዚ ነገራት'ዚ እንተልዩኩም እናማዕበለ'ውን እንተኸደ ንምፍላጥ ጐይታና ኢየሱስ ክርስቶስ ሃካያትን ዘየፍርዩን ክትኰኑ ኣይሓድገኩምን እዩ።

፱. እቲ እዙ ነገርዚ ዜብሉስ ካብቲ ናይ ቀደም ሓጢኣቱ ምፅራዩ ዝረስዒ ዕዉር ነቲ ኣብ ቀረባ ዘሎ ጥራይ ዚርኢ እዩ።

፲. (ዚመስል) ስለዚ ኣንቱም ኣሕዋትና ንምፅዋዕኹምን ምሕራይኩምን ክተፅንዑዎ ኣዚኻትኩም ተጋደሉ። እዚ እንተገበርካትኩምሲ ከቶ ኣይክተንደልህፁታን ኢኹም።

፲፩. ከማኡውን ናብቲ ናይ ጐይታናን መድሓኒናን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ መንግስቲ ምእታው ብምልኣት ኪወሃበኩም እዩ። 2ጴጥ. 1፥3-11።

እምበኣርከስ ንዅሉ ኽፍኣትን ጕርሕን ግብዝናን ቅንእን ኵሉ ሓሜትን ኣርሕቑዎ። እግዚኣብሔር ሕያዋይ ምዃኑ ጥዒምኩምዎ እንተ ኾይንኩምሲ ብእኡ ንምድሓን ምእንቲ ኽትዓብዩ ከምቶም ሕዚ እተወልዱ ሕፃናት ነቲ ሕዋስ (ውጥንቅጥ) ዜብሉ መንፈሳዊ ፀባ (ወንጌል) በሃጕም'ሞ ናብቲ ብሰብ ንዑቕ ብኣምላኽ ግና ሕሩይን ክቡርን ዝኾነ ህያው እምኒ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ናባኡ ቕረቡ። ንሱ ድማ ነቲ ሓቅን ሓሶትን ፈሊኹም ንኽትፈልጡ ንዓይኒ - ልቦናኻትኩም ብመንፈስ ቅዱስ ገይሩ ከብርሆ እዩ። ብእኡ ዚኣምን ድማ ከቶ ኣይኪሓፍርን እዩ። ንዕኡ ንበይኑ ካብ ሕዚ ንዘለዓለመ ዓለም ስብሓት ይኹኖ ኣሜን። መዝ. 34፥8፤ 1ጴጥ. 2፥1-10፤ ኤፌ. 1፥17-18።

ትርጓሜ

ውሃ ለተጠሙ ምክር ለሚሰሙ

እናንት ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼ፤ ያ አምላክን ባለማወቅ የተመላለሳችሁበትና የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ፤ 1ጴጥ. 4÷1-3:: ከእንግዲህስ ተነሡ፤ ንቁ፤ በርቱ፤ ጐልማሶች ሁኑ፤ ክርስቶስን ብቻ በማመን ጽኑ፤ 1ቆሮ. 16÷13:: ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ፤ 1ተሰ. 3÷15-24::

እንዴትስ ወደ አሮጌ ልማድና ወደማይጠቅም አሮጌ ጽድቅ÷ ፍሬ ወደሌለውና ወደ ልዩ ልዩ እንግዳ ሃይማኖት ትሄዳላችሁ? ይልቁንስ ለአእምሮአችሁ ብርሃን በነቢያትና በሐዋርያት መብራት ብትመሩ ለመዳን ወደምታድጉበት ጭማሪ (ድብልቅ) ወደሌለው ንጹሕ የወንጌል ወተት መጥታችሁ ያለዋጋ ለምን አትስተናገዱም? እውነትንስ ለምን አትፈርዱም? በሁለት እግረ ልቡና (ሐሳብ) የምትሄዱትስ እስከ መቼ ድረስ ነው? (የምትራመዱ) ለድኅነታችሁ የሚሆን ነገር ለማድረግ ዛሬ እየፈራችሁ ሥሩ፤ ሕግን እየጠበቃችሁ በኀጢአታችሁ ደግሞ እያዘናችሁ ተንቀጥቀጡ፤ ራዱም:: ፈጣሪያችሁን አታሳዝኑት፤ «ሑሩ» በሚባለው ሰይፍ እንዳትታረዱ፤ ስንቃችሁን ቋጥሩ በረኃብ እንዳትነዱ፤ ሰዎች ይመለሳሉ ወይ ወደ መቃብር ከወረዱ? እኔ ነገርኋችሁ በዘላለም እሳት እንዳትማገዱ፤ እንግዲያውስ የሐዋርያው ጴጥሮስን ምክር ሰምታችሁ እባካችሁ ተሰናዱ፤ ወደ ገነት እንድትገቡ በፍቁር ወልዱ፤ እውነትና ፍቅርን ያዙ ውሸትን አትውደዱ:: ፫. የመለኮቱ ኀይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራን ለሕይወት እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለሰጠን፤

፬. በእርሱ የከበረችውንና ታላቋን ተስፋ ያገኘን በዓለም በሥጋ ምኞት ካለው ጥፋት ወጥታችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ፤

፭. በትጋት ተጋደሉ፤ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም ዕውቀትን፤

፮. በዕውቀትም ራስን መግዛት፤ ራስንም በመግዛት መጽናትን፤ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፤

፯. እግዚአብሔርን በመምሰል፥ የወንድማማች መዋደድ (መተሳሰብ)፤ በወንድማማች መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ፤

፰. ይህ ነገር ካላችሁ፥ እያደገም ቢሄድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማወቅ ሰነፎችና የሚያፍሩ እንድትሆኑ አይተዋችሁም፤

፱. ይህ ነገር የሌለው ከቀድሞው ኀጢአቱ መንጻቱን የረሳ ዕውር፥ በቅርቡ ያለውን ብቻ የሚያይ ነው የሚመስል፤

፲. ስለዚህ እናንተ ወንድሞቻችን መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ:: እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም::

፲፩. እንዲሁም ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና፤ 2ጴጥ. 1÷3-11::

እንግዲህ ክፋትን ሁሉ፥ ተንኮልን ሁሉ፥ ግብዝነትንም ሁሉ ቅንኣትንም፥ ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፥ ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ያልተቀላቀለ መንፈሳዊ ወተት (ወንጌል) ተመኙ:: በሰው ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደሆነ ሕያው ድንጋይ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ወደ እርሱ ቅረቡ:: እርሱም እውነቱንና ውሸቱን ለይታችሁ እንድታውቁ ዐይነ ልቡናችሁን በመንፈስ ቅዱስ ያበራዋል:: በእርሱ የሚያምን ከቶ አያፍርም፤ ለእርሱ ብቻ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ምስጋና ይሁን፤ አሜን፤ መዝ. 34÷8፤ 1ጴጥ. 2÷1-10፤ ኤፌ. 1÷17-18::

<u>ምዕራፍ 3</u>

<u>ልዩ ደብዳቤ</u>
<u>ለማከብርህ ወንድሜ አቶ ማመን ብቻ</u>

እጅጉን ለጤናህ እንደምን አለህ? እኔ ግን ኪዳኑን የማይከዳ፥ በጭንቅ የሚረዳ ያባቶቹ የአብርሃምና የይሥሐቅ፥ የያዕቆብና የዮሴፍ አምላክ፥ ሕዝበ እስራኤልን ከምስር (ከግብጽ) ባርነት አውጥቶ ባሕረ ኤርትራን በእደ-ሙሴ አሻግሮ፥ በእደ ኢያሱም ምድረ-ርስት ከነዓንን ያወረሰ እውነተኛው አምላክ ይክበር ይመስገን በጣም ደኅና ነኝ::

ውድ ወንድሜ ሆይ በዓለም ተገናኝተን ቃል ለቃል እስክንጫወት ድረስ ይህችን <u>ተግሣጽና ምክር</u> የተባለችውን ትንሽ ደብዳቤ እጽፍልህ ዘንድ ሕሊናዬ አነሣሣኝ::

ወዳጄ ሆይ በዚህ ዓለም ከሁሉ በፊት እምነትን (ፈሪሃ እግዚአብሔርን) የሚመስላትና የሚስተካከላት ነገር (ጥበብ) እንደሌለ ሁላችንም ማወቅ ይገባናል፤ ኢዮ. 28፥12-38:: ሰውም የተፈጠረው የእምነት ባለቤትና አገልጋይ እንዲሆን ነው፤ እምነት የሌለው ሰው ግን ከእንስሳት ጾታ (ወገን) ካልሆነ በሰብእነት ጾታ ገብቶ ሊቈጠር ከቶ አይችልም፤ መዝ. 49፥20:: በእምነትም በዓለም ላይ ካለው የፈተና ወጥመድ አምልጦ፥ በሞት ጊዜም የተስፋና የደስታ ዕረፍት ሊገኝ ይችላል::

ስለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን የሚታመነው ሰማይና ምድርን የፈጠረው ፩ አምላከ ብቻ ካልሆነ በቀር ሌላ ከቶ የሚታመን የለም፤ ማር. 12፥28-33::

ወዳጄ ሆይ! እኛ የክርስቶስ ወገን ክርስቶሳውያን የምንባለው ግን ለደኅንነታችን ከሰማይ ወርዶ የተሰቀለውን ወልደ-አምላክ ኢየሱስን ብቻ አምነን (ይዘን) በትእዛዛቱ ካልተመላለስን፥ እንኳን ከሚመጣው ዐዲሱ የደስታ ዘላለማዊ ዓለም ልንገባ ይቅርና በዚህ በኃላፊው ዓለምም ቢሆን ሐዘንና ሥቃይ ካልሆነ፥ አንድ ቀን እንኳን ደስታና ዕረፍት ልንቀምስ ከቶ አንችልም፤ ዮሐ. 3፥36፤ ሮሜ 2፥3-11::

አሁን ግን እምነት ከሰው ጋርና ለሰው ተፈጥራለችና ሰው አስቀድሞ እውነተኛይቱን አምላካዊት እምነት በሕሊናው መርምሮ ተረድቶ አምኖ መያዝ ይገባዋል:: እምነት ግን የሁሉ ሰውና የጅምላ ጉዳይ አይደለችም፤ 2ተሰ. 3፥1-5:: የግል ግብር ስለሆነች አማኙ

ሁኔታዋ ምን እንደሆነ፥ ቁመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋና ጥልቀትዋ (ኤፌ. 3፥14-19) መርምሮ ክቡር ዋጋዋም መንግሥተ ሰማይ መሆኑን አስተውሎ ሊያምን ይገባዋል:: ሳይመረምሩና ሳይረዱ አማኝና ማኅበረተኛ መሆን ግን ጉም ዘገንና ነፋስ ጨበጥ መምሰል ይባላል:: እህል ተቋጥሮ ቢቀመጥ አይጠቅምም፤ ተበጥሮና ተፈጭቶ፥ ተነፍቶና ተቦክቶ ተጋግሮ ቢበላ ግን ሕይወትነቱ ይታወቃል:: እንደዚሁ እምነትም መኖሯ ብቻ አይበቃም፤ ህላዌዋን የሚያስታውቅ የሚንቀሳቀስ ሕይወት ያለው፥ የሚታይና የሚበላ ፍሬ ወይም ሕያው ምግባር ሊኖርባትና ሊገኝባት ይገባል:: ሰው የተፈጠረው፥ ከወዴት እንደመጣና ወዴትም እንደሚሔድ፥ ማን እንደፈጠረው፥ ምን ሊሠራም እንደተፈጠረ ሊያስብና መርምሮ ፈጣሪውን ዐውቆና አምኖ ለማገልገል ነው፤ ኢዮ. 10፥8-13፤ ሚክ. 6፥8::

የተወደድህ ወንድሜ ምእመን ሆይ! የዘመኑ ልጆች ዕድላችን ሁኖ እግዚአብሔር አንድ ሆኖ ሳለ የክርስቲያን ሃይማኖት ግን ማሠርና መፍታት በሚለው አርእስት በ13ኛው ምዕራፍ እንደተመለከተው ቁጥሩና ባህሉ፥ ስሙም ከ20 እስከ 30 ዓይነት ይሆናል:: ሌሎችም የፈጠራ ሃይማኖቶች ደግሞ ክሕደት፥ ጥንቈላ፥ ፊሎሶፊ፥ አስትሮኖሚ ማተማቲክ ሳይንስ ፖሊቲክ ናቸው፤ መጨረሻቸው ወይም ዋኖቻቸው እነ ራስ አቶሚክ እነ ዐፄ ሃይድሮጅን የሚባሉ ዓለምን ሊያሳልፉ የሚችሉ፥ የሰው ልጆችን ከጭንቅና ጥርጣሬ እያደረሱ የሚያስቸግሩ በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ ያልተመሠረቱ በተጥባበ ሰብእ (በሰው ጥበብ) ለጊዜው የቆሙ ብዙ ሃይማኖቶች በዓለም ሞልተዋል::

ስለዚህ በዐይነ-ልቦናህ ወንፊት፥ በእዝነ-ልቦናህም ወንጠፍት (ማጥሪያ) ሰካበትና ሁሉንም አምላክ በሰጠህ ብርሃነ አእምሮ ነፋፍተህና አጣርተህ፥ በቅዱስ መጽሐፍ ሚክሮስኮፕ ነጽረህ (አይተህ)፥ እውነቱን ከሐሰት ለይተህ እመን እንጂ ዐዋቂዎች ነን እያሉ ሰዎች የፈለሰፉትን ወይም የፈጠሩትን ፍሬ የማይገኝበትን የማይታይና የማይጨበጥ ረቂቅ ወሬ ሁሉ ሳትመረምር ማመን ብቻ አትሁን:: በሰው ውስጥ ያለው መንፈስ እግዚአብሔር የመከረውን ሳይቀር ጠልቆ ይመረምራልና መርምር፤ 1ቆሮ. 2፥4-13::

ሌላው ሁሉ ይቅርና ከሰማይ የወረደችው የወንጌል ፀሓያዊት እምነትም ብትሆን፥ የላይ ብልትዋንና የውስጥ አንጀትዋን አንብበህ መርምረህ ከመጻሕፍተ ሐሰት እውነተኛነትዋን ሳትረዳት በልማድ ብታምናት ከቶ አትረባህም::

የተጻፈውን ሁሉ ማንበብና መመርመር ይገባል፤ እውነተኛ ውንና መልካሙን ቃላት ግን አምኖ የፍሬውን ፍጻሜ አይቶ አጥብቆ መያዝ ነው፤ 2ቆሮ. 13÷5፤ ኤፌ. 5÷10::

ውድ ወንድሜ ሆይ! ክፉ ከሚመስል ሁሉ ሽሽ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ መንፈሳችን÷ ነፍሳችን÷ ሥጋችን ሁለንተናችንም ያለ ነውር ተጠብቆ ይገኝ ዘንድ እየተመኘ ሁ÷ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ለመገናኘት ያብቃን እልሃለሁ:: ሰላመ እግዚአብሔር ፍጥረቶቹን ይጠብቀን፤ አሜን፤ 1ተሰ. 5÷15-28፤ 2ጴጥ. 3÷14::

ወዳጄ ሆይ! በሰነፎች ስሕተት ተወስደህ ከጽኑይቱ የወንጌል እምነትህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ:: የእግዚአብሔር ተስፋ አይዘገይምና ነቅተህ ትጠብቀው ዘንድ አደራዬን እጥልብሃለሁ:: ጳውሎስና ጴጥሮስ «በኋለኛው ዘመን በፈቃዳቸው የሚሄዱ መንፈስ የሌላቸው ሥጋውያን የምጽአቱ ተስፋ የለም ብለው የሚክዱ የሰይጣናትን ትምህርት የሚከተሉ ፌዘኞች አላጋጮች ይነሣሉ::» ብለው የነገሩን የማይታበል ቃላቸው በእርግጥ ለዛሬው ዘመናችን የተናገሩት መሆኑን የተረዳኸው ሁን፤ 1ጢሞ. 4÷1-7፤ 2ጢሞ. 2÷1-9፤ 2ጴጥ. 3÷1-18:: አንተ ግን ምእመን ሆይ! ከዚህ ሁሉ ሽሽ፤ የያዝከውን አክሊል ማንም እንዳይወስድብህ ነቅተህ ተጠንቅቀህ ጠብቅ፤ እውነትን ፈልገህና መርምረህ አግኝተህና አጥብቀህ ያዛት፤ ነገ የሚሆነውን አታውቅምና መንፈሳዊውን ነገር ለነገ አትበል፤ ሥጋን የሚገድሉትን አትፍራ፤ እየዋሹ መቶ ዓመት ከመኖር አንድ ቀን እውነትን ተናግሮ መሞትና መንግሥተ ሰማያት መግባትን ምረጥ፤ ፍርሀትንና ድፍረትን ጊዜያቸውንና ቦታቸውን ለይተህ እወቅ እንጂ ሕሊናህን በሁለት ነገሮች አታፈራርቀው÷ ከየዋሆች ጋራ እንደ ርግብ የዋህ÷ ከተንኰለኞች ጋራ እንደ እባብ ተንኰለኛ ሁን፤ ትዕግሥትን ጓደኛህና ገንዘብህ አድርጋት፤ ፍሬ ለማይገኝበት ለባልቴቶች ተረትና ክርክር አፍህን አትክፈት በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተገለጸውን ቃላትና ሕሊናህም ከማይደርሰው ትርጓሜና ምርምር አትግባ አትቅረብም::

አባታችን ቅዱስ ያሬድ «ሥላሴ ይትነከር ወኢይትነገር» እንደሚለን ዕፁብ ድንቅ መንክር ወመድምም ብለህ አምነህ አመስግን እንጂ÷ የሦስትነትን ምስጢር ፈልጌና መርምሬ አገኘዋለሁ ብለህ አትድከም፤ ዘዳ. 29÷29፤ መክ. 12÷12-14::

ውድ ወንድሜ ሆይ! ምን እበላለሁ እያልህ አትጨነቅ፤ አስቀድመህ የእግዚአብሔርን መንግሥቱንና ጽድቁን ፈልገህ ብትይዝ ሁሉንም በገዛ እጁ ይጨምርልሃል:: ማናቸውም ዓለማዊ ነገሮችና የሥጋ ፍትወቶች አክሊልህን እንዳይዘርፉህ በጸሎትና

<u>በንጽሕና ነቅተህ ጠብቅ፡፡ እውነትና ትሕትናን፥ ትዕግሥትና ርኅራኄን የሕይወት ዘውድ አድርገህ ያዛቸው፡፡</u> ክፉ ላደረጉብህ ይቅርታን እየሰጠህ በጎ መልስላቸው እንጂ፥ በማንም ላይ ቂም አትያዝ፤ የሴት ባሕርይ ደካማና ሰነፍ መሆኑን አውቀህ ለሚስትህ ራራላትና ተንከባክበህ ያዛት፤ 1ጴጥ. 3፥7፡፡

ደንቆሮን ተቆጥቶ እንዳይጠላህ አትምከረው እግዚአብሔርን የሚፈራ ጠቢብን ለመምከሩ አትታክት፤ ከሰው ሁሉ ጋር በፍቅርና በጥበብ ኑር፤ ሰውን ሀብታምና ትልቅም ቢሆን ስለ እውነት ስትል አትፍራው፥ አትፈረውም፡፡ የኀጥአን ሕይወትና ኑሮ እንደ ሊባኖስ ዛፍ ሰፍቶና ረዝሞ ብታየው በቅጽበት ዐይን ኀላፊ፥ ረጋፊና ጠፊ ነውና ናቀው እንጂ አትቅናበት፤ ወዳጄ፥ ወንድሜ፥ ሚስቴ፥ ልጄ ብለህ ሰውን አምነህ ምስጢርህን አታውጣ፡፡ ስለምን ብትለኝ የዘመኑ ሰው ልቡ እንደ እስስት በየጊዜው ተለዋዋጭ ሁኗልና ነው፡፡ በመከራ ጊዜ ዘምር፤ በደስታም ጊዜ ፍራ፤ የስካር ጓደኛና የመጠጥ አመለኛ እንዳትሆን አደራህን፤ ድሆችና ሐዘንተኞችን በተቻለህ ሁሉ እርዳ አጽናና፤ ለቁጣ ስፍራ ስጠው እንጂ በጥቃቅኑ ነገር አትቆጣ፤ በዕድሜና በሀብት እኩያህ ካልሆነ ሰው ጋር ጓደኝነትን አትጀምር፤ ከመፋቀር በፊት የሰውን ዓመልና ጠባይ መዝን፤ ገንዘብህን አክብረህ ያዘው እንጂ በማይገባ ቦታ አታውለው፤ የሐሳብህን መግለጫ ትንሽ መጽሐፍ ጽፈህ አሳትም፤ ባለ ጸጋ ለመሆን አትድከም፤ ከስስት ተጠንቀቅ፤ ለመናገር ታገሥ ለመስማትም ቸኩል፤ ከመጠጥ ጥሩውን ከወሬ አተላውን ምረጥ፤ ያነበብከውን የሰማኸውን ነገር ሁሉ በሕሊናህ መርምረህ ሳታስተውለው አትመነው፤ ሌትና ቀን ሕገ እግዚአብሔርን ብታስብ አካሄድና ኑሮህ የተከናወነ ይሆንልሃል መዝ.1፥1-3፡፡ ምርምር በተባለችው በቅዱስ መጽሐፍ ከተማ ተጻፈ፤ ከወንድምህ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዓድዋ 1941 ዓ.ም ዘኢትዮጵያ ደኅና ሁን አሜን፡፡

ምዕራፍ 4

ቅዱስ መጽሐፍ

ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የሰው መጽሐፍ አይደለም። እርሱ በመለኮታዊ ጥበቡ በቅዱሳን ሰዎች አድሮ በመንፈሱ እየመራ አስጽፎና ለዘለዓለም ጠብቆ እያስፋፋው ይኖራል፤ 2ጴጥ. 1÷21፤ 2ጢሞ. 3÷16-17። ይህ መልእክት ለዘለዓለማዊ ሕይወትና መድኃኒተ ሰብእ እንዲሆን ብሎ ለፍጥረቱ ሁሉ ከሃሊ ኵሉነቱን (ሁሉን ቻይነቱን) እንዲገልጽለትና ወደ እውነተኛው አምልኮ እንዲመጣ የላከው መልእክት ነው፤ ሮሜ 1÷19÷8፤ 1ጢሞ. 2÷4፤ ቲቶ 2÷11-15።

አጎስቲኖስ እንደሚለው «እነዚህ መልእክቶች እኛ ወደምንመኛት ቅድስት አገር እርምጃችንን በተስፋ እንድንቀጥል ከርስዋ ወደኛ ተልከው የመጡ ናቸው። ከነዚህ መልእክቶች የመድኃኒትን ትእዛዝ በእምነት ጽዋዕ እየቀዳን የሕይወታችንን አካሄድና ግዕዝ (ሁኔታ) በእነርሱ አቅንተን ከሄድን አንቅዕተ ማየ ሕይወት (የሕይወት ውሃ ምንጮች) ስለሆኑ ከእነርሱ የሚጠጣ ለዘለዓለም አይጠማም። እርሱ ከሰማይ የወረደ መና ስለሆነ ሲሳየ መላእክት ነው። ከርሱ የሚበሉ ሞትን ለዘለዓለም አይቀምሱም። የዔድን ገነት ማለት እርሱ ነው። ፍሬውና ቅጠሉ ቢበሉት ክፉ ለተባለው ሁሉ ፈውስና መድኃኒት ነው። እርሱ ለክርስቲያናዊ ነፍስ ከሚያገኘው ፀርና ፈተና የሚያጸናው መንፈሳዊ ምግብ ነው። እርሱ ጥርጥርን ከሚያመጣው ጥፋት የሚያድን ፈውስ ነው። እርሱ ኃጢአትን የሚያርቅ እውነተኛ መሥዋዕት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ ነገሩን በማሳጠር ለማያውቁ አብዳን (ሞኞች) የጥበብ መምህር÷ ለተሳሳቱ ጊጉያንም (በደለኞችም) ወደ ቅን መንገድ መላሽ ነው። በቅን መንገድ ለሚሄዱ ያጠነክራል። ልበ በሽተኞችን ከሥቃይ ያሳርፋል። ጽድቅን ለሚራቡ ያጠግባቸዋል። ከጠላትም ይጠብቃቸዋል በችግር ጊዜ ያጽናናቸዋል።» እያለ በእውነት መስክሮለታል።

ቅዱስ አጎስቲኖስ «በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሕሊናዬ የማይደርስበት ጥልቅ ምስጢር ስለሆነ ከማውቀው ይልቅ የማላውቀው ይበዛል።» ይላል። እኔም ደግሞ ከማውቃቸው ሁለት ሦስት ቃላት አስከትዬ እጽፋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ በመከራ ጊዜ የማይከዳ እውነተኛ ጓደኛ ነው። እርሱ ከሁሉ ይልቅ አብልጦ የሚወደድ ወዳጅ ነው። እርሱ

የማያሳስት ሐሰት የሌለበት እውነተኛና የቀና የሕይወት መንገድ ነው። እርሱ ከወርቅና ምዝምዝ ወርቅ ይልቅ የበለጠ ክቡር ነው።

እርሱ ሌባ ቈፍሮ የማይሰርቀው ጻጼና ቈንቈኜም (ብልና ነቀዝ) የማይበላው ሕያው መዝገብ ነው። እርሱ በእውነት የነፍሳት እረኛ ነው። እርሱ በእውነትና በኃጢአት የተቀጠቀጠውንና የተደቈሰውን መንፈስ የሚጠግን ዋና ሐኪም ነው። እርሱ ለመሸከም የሚመች ቀላሉና ልዝቡ የሕይወት ቀምበር ነው።

እርሱ ከማርና ከማር ወለላ ከስኳርም እጅግ የጣፈጠ ነው። እርሱ ከዚህ ዓለም ወደ ሰማያዊ አገር የሚያወጣ መሰላል ነው። እርሱ እውነተኛ አጽናኝና የተስፋ መሪ ነው። እርሱ በጨለማ ጊዜ የሚያበራ ፋና ነው። እርሱ ድንቊርናን የሚያጠፋ ጥበብ ነው። እርሱ ብዙ ምርኮ ከሚካፈል ይልቅ የበለጠ የልብ ደስታ ነው። እርሱ በዚህ ዓለም ባሕር ካለው የመከራ ማዕበል አውጥቶ ድኅነተ ሥጋና ነፍስ ወደሚገኝበት ወደብ የሚያደርስ የማይናወጽ እውነተኛ ሕያው መርከብ ነው።

ለወሃቤ ሠናያት (ለስጦታዎች ባለቤት) አምላካችን ምስጋና ይሁን፤ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ መቼም መች ለዘለዓለሙ፤ አሜን! አሜን! አሜን!

ምዕራፍ 5
ምርጥ ቃላት

የሰሎሞን ምሳሌዎች ምክርና ተግሣጽን ተቀብለው፥ ጥበብና ማስተዋልን ቅን ፍርድና ጽድቅን፥ ጥንቃቄና እውነትን ለሚፈልጉ ሰዎች ተጻፈ:: ጥበብ ለተባለው ሁሉም ምንጩና መሠረቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ንጉሡ ያስረዳናል፤ ምሳ. 1፥1-9::

ልጄ ሆይ! ነገሬን ብትቀበል፥ ጆሮህን ወደ ማስተዋል ብታዘነብለው፥ ጥበብንም ብትሻትና እንደ ተቀበረ መዝገብም ብትመረምራት፥ እግዚአብሔርን መፍራት ትማራለህና:: እግዚአብሔር የተሰወረውን ጥበቡንና ዕውቀቱን ሁሉ ይገልጽልሃል፤ ምሳ. 2፥1-11::

ልጄ ሆይ ነገሬንና ተግሣጼን ስማ፤ እርሱ ሕይወትህ ነውና ያዘው፤ ጠብቀው አትተወውም፤ ምሳ. 4፥7-13::

ሰነፍ ያባቱን ተግሣጽ ይንቃል፤ አእምሮው የበዛ ግን ዘለፋን ይጠብቃል፤ ምሳ. 15፥5::

ተግሣጽን የሚሰማ ይከብራል፤ ተግሣጽን የሚተው ግን ድኽነትና ነውር ይቀበላል፤ ምሳ. 13፥18::

ዋዘኛን የሚገሥጽ ይሰደባል፥ ሕግ ተላላፊውንም የሚዘልፍ ነውረኛ ይባላል:: ስለዚህም ዋዘኛን እንዳይጠላህ አትገሥጸው፥ ብልሃተኛን ብትገሥጸው ግን ይወድሃል፤ ምሳ. 9፥7-9::

ተግሣጽን የሚጠብቅ በሕይወት መንገድ ይሄዳል፥ ዘለፋን የሚተው ግን ይስታል፤ ምሳ.10፥17::

በኃጢአት የተገኘ ገንዘብ ጥቅም የለውም፥ እግዚአብሔር ግን የጻድቅን ነፍስ አያስርብም፥ ጽድቅም ከሞት ታድናለች፤ ምሳ. 10፥1-6::

ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል፥ ዘለፋን የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው፤ ምሳ. 12፥1::

አስተዋይ ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት፥ ሰነፍና አሳፋሪ ሴት ግን ለባልዋ በዐጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ትበላዋለች፤ ምሳ. 12፥4::

አስተዋይ ሰው ትምህርትን ለማግኘት አያስቸግረውም፥ ዋዘኛ ግን ጥበብን ቢፈልግ ከቶ አያገኛትም፤ ምሳ. 14÷6::

መልካም ትምህርት ጸጋ ይሰጣል፥ የቸልተኞች መንገድ ግን በጣም የጨነቀች ናት፤ ምሳ. 13÷15::

ሕግን የሚያቃልል በሕግ ተይዞ ይጠፋል፥ ሕግን የሚፈራ ግን በደኅንነት ይኖራል፤ ምሳ. 13÷13::

የጻድቃን ቤት ታብባለች፥ የሕግ ተላላፊዎች ቤት ግን ይፈርሳል፤ ምሳ. 14÷11::

ዋዘኛ ሰው የሚዘልፈውን ሰው ስለማይወድ ወደ ጠቢባን አይቀርብም፤ ምሳ. 15÷12::

ዘለፋን የሚሰማ አእምሮ ያገኛል፥ ተግሣጽን የሚተው ግን ነፍሱን ያጠቃል፤ ምሳ. 15÷32::

ጠንካራ መንፈስ ያለው ሰው መከራውን ሁሉ ይታገሣል፥ ፍርሃትን የተሞላ መንፈስ ያለውን ግን ማን ያጠነክረዋል? ምሳ. 18÷14::

ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳል፥ አስተዋይ ሴት ግን የእግዚአብሔር ስጦታ ናት:: ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ፤ ምሳ. 18÷22፤ 19÷14::

ትእዛዝን የሚጠብቅ ነፍሱን ይጠብቃል፥ ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል:: ምክር ስማ፥ ተግሣጽንም ተቀበል፥ በፍጻሜህም ብልሃተኛ ትሆናለህ፤ ምሳ. 19÷16-20::

ልቤን አነጻሁ ከኃጢአቴም ጠራሁ የሚል ማነው? ምሳ. 20÷9::

አባት እናቱን የሚሰድብ መብራቱ ይጠፋል፥ ፈጥኖ የተከማቸ ገንዘብ ፍጻሜው አይባረክም፤ ምሳ. 20÷20-22::

እግዚአብሔርን መፍራት ለሕይወት ነው፥ የሚፈራውም ጠግቦ ያድራል እንጂ ክፉ ነገር ከቶ አያገኘውም፤ ምሳ. 19÷23::

ዋዘኛን ሥቃይ ባገኘው ጊዜ አእምሮ የሌለው ሰው ጥበብን ያገኛል፥ ጠቢብም ቢገሠጽ ዕውቀት ይጨምራል፤ ምሳ. 21÷11::

ስንፍና በሕፃን ልብ ታሥሯል፥ የተግሣጽ በትር ግን ከርሱ ያርቃታል:: ለራሱ ጥቅም ለመጨመር ሲል ድኻን የሚጎዳ ለባለጠጋም የሚሰጥ እርሱ ወደ ድኽነት ይወድቃል፤ ምሳ. 22÷15-18::

እውነትና ጥበብን፥ ተግሣጽና ዕውቀትንም ግዛ፥ ከቶም አትሸጣቸው፤ ምሳ. 23፥19-23።

አለንጋ ለፈረስ፥ ልጓምም ለአህያ፥ የተግሣጽ በትርም ለሰነፎች ጀርባ የሚገባ ነው፥ ሐሰተኛ ምላስ ግን የሚገሥጹትን ሰዎች ይጠላል፤ ምሳ. 26፥3-28።

ሰነፍን በሙቀጫ ብትወቅጠው ስንፍናውን ከርሱ አይለይም፤ ምሳ. 27፥22።

ሕግን የተዉ ሰዎች ሕግ ተላላፊውን ያመሰግናሉ፥ ሕግን የሚጠብቁ ግን ይጠሏቸዋል፤ ምሳ. 28፥4።

ባለጸጋ ለመሆን የሚቸኩል ሳይቀሠፍ አይቀርም። ማድላት መልካም አይደለም፥ ሰው ግን ስለ ቍራሽ እንጀራ ሲል ከእውነት ፈቀቅ ይላል። በለዘበ ምላስ ካንገት በላይ ከሚሸነግል ይልቅ በእውነት የሚገሥጽ ኋላ ጸጋ ያገኛል፤ ምሳ. 28፥20-23።

ባልንጀራህ ቢሳሳት በልብህ አትጥላው፥ ነገር ግን በእርሱ ምክንያት ላንተ ኃጢአት እንዳይሆንብህ ባልንጀራህ ነውና ገሥጸው፤ ዘሌ. 19፥17።

ነውረኞች ወንድሞቻችሁን በመንፈስ ገሥጿቸው እንጂ ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤ ኤፌ. 5፥1-11።

አንተ ግን ባለህበት ጸንተህ ሰነፎችን እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ፤ 2ጢሞ. 4፥1-5 ።

የገድልና ተአምር አገልጋዮች ሐሰተኞችና ሆዳሞች ናቸውና፥ በወንጌል ሃይማኖት ብቻ እንዲድኑ ብርቱ ዘለፋ ዝለፋቸው፤ ቲቶ 1፥10-14።

ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል፥ በእግዚአብሔር ብቻ የሚታመን ግን እርሱ ይታደገዋል፤ ምሳ. 29፥25።

የነፍስ ዕውቀት ከሌለበት ዘንድ ከዚያ በጎነት አይገኝም፤ ምሳ. 19፥2።

ተግሣጽ ሁሉ ግን ለጊዜው ያሳዝናል እንጂ ደስ አያሰኝም፥ ለለመዱት ግን ኋላ የሰላምና የጽድቅ ፍሬ ያፈራል፤ ዕብ. 12፥5።

ምዕራፍ 6

ተግሣጽና ምክር

1. ተግሣጽና ምክር ሁለቱ ጓደኛ
ሐሰትን ለመክሰስ ሆነውት ደመኛ
ምን እውነት ቢይዙ አልተገኘም ዳኛ÷
ወንጌል ደጋፊ ግን ወዶአቸው ምንኛ
መንጋው አትፍራ አይዞህ የሱስ ነው እረኛ፤
ሉቃ. 12÷32::

2. ተግሣጽና ምክር መልካም ገሰገሱ
መልክዕና ተኣምር ገድልን እየጣሱ
ሾላ መነጠሩ ተራራ አፈረሱ
በስንት መከራ ካቡን ቤት ደረሱ
እውነት ስለያዙ የትም ተከሰሱ÷
ዳኛው ቅዱስ መጽሐፍ ሲበይን ለእነርሱ
ጽሑፍ መልስ ስጡ ልማድ አትላሱ
ብሎ ነገራቸው ተፈሪ ቅዱሱ÷
መልስማ ለመስጠት የትኛውን ሊጠቅሱ
ማጕረምረም ብቻ ነው ኃይላቸው እነርሱ፤
መዝ. 2÷1-5፤ ኢሳ.8÷9-15::

3. ተግሣጽና ምክር ምንኛ በረቱ
12 ዓመት ታሥረው ቢንገላቱ
ተስፋ ባለመቁረጥ ጨክነው ሞገቱ
የማታ ማታ ግን አቶ እውነት ረቱ÷
በሰገነት ቁመው አፋቸውን ከፈቱ
በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ያምላክ ቸርነቱ
ሰበኩ አስተማሩ አቶ ሐሰት ሞቱ÷
የሰው ሐሳብ ሁሉ በንኖ በመቅረቱ
ይሁዳ ቴዎዳስ እስቲ ተመልከቱ
ምክር ምስጢራቸው በቅጽበት ተፈቱ፤
ኢሳ. 8÷10፤ የሐዋ. ሥራ 5÷34-43::

4. ተግሣጽና ምክር ለሰሚው ጠቃሚ
ለተጠራጣሪው አስረጅና አራሚ
ላልተማሩ ሰዎች በጣም አስገራሚ
እንደበራ ሁሉ በርሱ ተቃዋሚ
መካሪውን (ጠቃሚውን) ይሰቅላል ዓለም አስቀያሚ፤
1ቆሮ. 2÷8፤ ዮሐ. 2 ÷23፤ 3÷12-15::

5. ተግሣጽና ምክር የታሪክ ዋዜማ
ሰነፍ ጠልቶ ጠቢብ እንዲወድህማ
በጠቢብ መጽሐፍ ተመክረሃል ስማ÷
ሐሰት ቢዘረጋ ቢደርስ እስከ ራማ
እውነት ጠቀለለው የወንጌል ዓላማ፤
ምሳ. 9÷7-9፤ ሮሜ 16÷25-27::

6. ተግሣጽና ምክር የክርስቶስ ዕቃ
ጠላቶች ቢቀብሩት በሐሰት ጨረቃ
አእላፍ አእላፋት ወሬ ቢቦረቃ
አንድ ብቻ ይበቃል የእውነት ጠበቃ÷
ወንጌል ተገለጠች እንደ ፀሐይ ደምቃ
እንግዲህ አገሬ ተነሥታለች ወድቃ
ዲያብሎስ አፈረ የሌቦች አለቃ
እግዜር ያጥናህ በሉት ለተዝካር ሰደቃ፤
1ዮሐ. 3÷8::

7. ተግሣጽና ምክር ተደሰቱ በጣም
የእናንተ ደጋፊ ጥቂት ሰው አልታጣም
ቅቤ እንጂ ከወተት ካልተገፋ አይወጣም
በሐሰት ዝክንትል ፍጥረት አይቀጣም÷
አባ ሆድ አምላኩ አስቸገሩኝ በጣም
ሁሉ ቢሰበሰብ ሳንቲም አያወጣም
የእውነት ቅንነቱን ያውቀዋል ጎባጣም
ሰው ለመምሰል ብሎ ቅራሪስ አያጣም
ጥማቱ አይረካለት ይቀራል አለ ጣዕም÷
ግብዝ በሃይማኖት በውነት አልተቀጣም
ክፉ ሠሪ ሁሉ ወደ ብርሃን አይመጣም
እኔ ግን ከወንጌል ብሞትም አልወጣም
ብሰደብ÷ ብጠላ÷ ብታሠር÷ ብገረፍ ዋጋዬን አላጣም
1ጢሞ. 4÷8-10፤ 2ጢሞ. 4÷5-8::

8. ተግሣጽና ምክር የክርስቶስ ሎሌ
አትዘን አትፈራ ተብለሃል ሃሌ
መንግሥቱን ሊሠጥህ ወዶአል ጌታ ጮሌ÷
ጽድቅን ሲመገቡ ያንተ ወገን ቀበሌ
ኀፍረት ሊለብሱ ነው ጠላቶችህ ወይሌ
ሠርቶ መብላት መጣ አለቃ በኃይሌ
እግዚአብሔር ያጥናችሁ የዘኬ ቀበሌ፤
ዘፍ. 3÷17-19::

9. ተግሣጽና ምክር ያነበቡ ሁሉ
የቅዱስ መጽሐፍ ወዳጆች በሙሉ
በጣም ደስ አላቸው ጣዕሙ ኃይለ ቃሉ፥
እነ መምሬ ግን አታንብቡ ሲሉ
ሰው በጠላ ይጸድቃል ብለው ቢያባብሉ
እውነትን በሐሰት ቀብረውት ቢውሉ፥
ጸሐፍት ፈሪሳውያን አሁን ድረስ አሉ
ዘቦችን በገንዘብ ምንም ቢያታልሉ
ምስጢር ነገሯቸው አልተነሣም ሲሉ
በሦስተኛው ቀኑ ታያቸው ለሁሉ፤ ቈላ. 2፥
ከቶ ጣዕመ ወንጌል በምን ነገር ጠሉ
ወየው አለማፈር ታምር ይሰብካሉ
ሐሰትን በሚዛን ከቶ ቢቈልሉ
አንድ ፍሬ ኤልያስ አደላ ከሁሉ፤
1ነገ. 18፥22-40::

10.ተግሣጽና ምክር እንደምን ደፈሩ
ተዝካር አያጸድቅም ብለው ሲያስተምሩ
ምንኩስና ይቅር ሕጋችሁን አክብሩ
ጳጳስም ሚስት ያግባ እያሉ መከሩ፥
ወይ እነመምሬ የሐዋርያትን ቃል እንዳዲስ ቈጠሩ
ተዝካር ከቀረማ አሁን እርሻ ይማሩ
ብለው ነው መሰለኝ በዓላት ሳይቈጥሩ
ሰው እንዴት ይረሳል ታሪኩና ክብሩ
ተሰውሮ አይቀርም ተግሣጽ ቢያማርሩ
የሁሉ ይገለጣል ሥራውና ግብሩ
እሰይ የምሥራች ተዝካር ዝክር ቀሩ፤
ኤር. 16፥17፤ ዕብ. 5፥12-13::

11. ተግሣጽና ምክር ኃይለኛ ነው ብርቱ
ባሕረ ቅዱስ መጽሐፍ ዋኝቶ መውጣቱ
ታምር ዘቅጦ ቀረ በፈርዖን ትዕቢቱ፥
ዐግ ንጉሠ ባሳን ሁኖ ቀረ ከንቱ
ምንም ሳያድነው ያ ሁሉ ጣዖቱ
ሙሴ መሰከረ በጽላት ክልኤቱ፥
ከቶ አያስችለውም የአምላክ ቅንዓቱ
ተግሣጽ ከተኰሰ አይስትም ጥይቱ
እሰይ የምሥራች አቶ ሐሰት ሞቱ
የሥጋ መሣሪያ ሆኖ ቀረ ከንቱ
የወንጌል ወዳጆች ዛሬ ተደሰቱ፤ ዮሐ. 8፥44::

12. ኧረ እነ የኔታን ትንሽ ልምከራቸው
ኧረ እነ መምሬን ጥቂት ልዝለፋቸው
ዛሬ ብቻ ይውጣልኝ ነገ ይቅርታቸው÷
ከሁሉ የቆጨኝ ትልቅ ጥምጥማቸው
በጣም የሚያስጸይፍ ሰፊው እጅጌያቸው
ከሁሉ የሚገርመኝ ረጅም ቀሚሳቸው
ማቴምስ ሃያ ሦስትን ባያነቡ ናቸው÷
መስቀልና ጭራ ይዘው እጆቻቸው
የመስቀል ግብርና ለሥጋ መስሏቸው
አዬ እነ መምሬ ስንቱን ልድፈራቸው
መኾገር ይመስል የሰው ደም ምግባቸው
በሐፊ ገጽከን ምነው መርሳታቸው÷
ሐዋርያትን ጠይቁ ጉልትማ ካላቸው
ሰማዕታትን ጠይቁ ሀብትማ ካላቸው
ድንኳን ሰፍተው ኩርማን ምግበ ዕለታቸው
ያገኙ ነበረ ይላል መጽሐፋቸው፤ የሐዋ. ሥራ 18÷3::
ሕዝብን ማስተማር ግን የግድ ወድቆባቸው
አለ ዋጋ አስተማሩ እርሱ እንዳዘዛቸው
ያላፊ ዓለም ሥጋ ሳያታልላቸው 1ቆሮ. 9÷13-18፤
አገራችን ሰማይ ነበር ኑዛዜአቸው
ወንጌል አስተማሩ እርሱ እንደ ላካቸው
መታሠር መገረፍ ሆነ ዕድላቸው
ባዕድን አታምልኩ ነበር ስብከታቸው
እንኳን የሐር ልብስ ጫማ አልነበራቸው
ሐሰት ጋር ተዋጉ ድል ሆነ ለርሳቸው÷
አዬ እነ መምሬ ምኑን ልንገራቸው
ሠርተው ይመገቡ እንግዲህ ይብቃቸው
ቢጠሉኝ ቢወዱኝ አምላክ ይማራቸው
አለ ዕውቀት በሠሩት ይቅር ይበላቸው÷
ከሐሰት አውጥቶ እውነት ሊሰጣቸው
እመኛለሁ እኔ በቀኝ ሊያቆማቸው
ዛሬ ብቻ ይውጣልኝ ነገ ይቅርታቸው
እቀበለዋለሁ በወጣቶቻቸው፤
ዘኍ. 32÷6-15፤ ዘዳ. 32÷44-52::

13. እንግዲህስ በቃኝ ስንቱን ልለፍልፍ
ስንፍናን እያዩ ዝም ብሎ ማለፍ
አይገባም ከቶ በወገን ልጅ ረድፍ÷
የተሳሳተን ሰው አጥብቆ መዝለፍ
አዞናል ጠቢቡ የእስራኤል መጽሐፍ፤

ዘሌ. 19÷17፤ ምሳ. 2÷7፤ ምዕራፍ ተመልከት::
ወንጌል እንዲገባ የኔውም ጽሑፍ
በዓለም ሊዘረጋ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ
በወገኔ ልጆች በብዙ አእላፍ
ዓቅሜ ትንሽ ቢሆን እንደ ፍሬ ጤፍ
እመኛለሁ ብቻ በሐሳቤ ክንፍ÷
ግብርና ሃይማኖት ረቂቅ ከግዙፍ
የሐሳቤ መግለጫ ትንሽ ቃል ብጽፍ
ስድብ መሰላቸው የክርስቶስ አፍ፤ ኤር. 6÷10::
ያልተማረ ሁሉም መሰለው መንቀፍ
መምሬ አውግዙ ሐሰት እንዲቀሠፍ
የአባት ማለት ይቅር ይተርጐም መጽሐፍ÷
አቶ ልማድ ይውጡ እንድንተቃቀፍ
የአንዲት እናት ልጆች ቤት እንድንደግፍ
ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ ያነጻል ከእድፍ
ሊቃውንት አትለዩን በቋንቋ በአፍ÷
የሰው ባህል ይቅር ጆሮ የሚቀፍ
እስከ መቸ ድረስ ይህን ሁሉ እንቅልፍ
ፀሐይ ወጥቷል ንቁ አትሥሩ ጸያፍ
ተቋጣሪ መጣ የታሪክ ምዕራፍ
ፈተና ካልወጡ አይሰጥም ይለፍ
ተገትረው ቀሩ ደናግል በአፍ
በዐጭር ነገርኋቸው ስንቱን ልለፍልፍ
ታከተኝ ደከመኝ እንግዲህ ልረፍ፤
ኢሳ. 1÷10-20፤ 7÷13::

14. አዬ እነ መምሬ ምን አደረግኋቸው
ከቶ የሚጠሉኝ እኔ ምን ባልኋቸው
ብሉይና ሐዲስ እንግዳ ሁኗቸው
ነቢያት ሐዋርያት እንደ ነቀፏቸው
ምነው ቢጠይቁኝ ቃሉን ላስረዳቸው
ምዕራፍና ቁጥሩን አሁን ላሳያቸው
በገድልና ታምር ተደፍኖ አእምሮአቸው
ተግሣጽና ምክር ሁኖ ጠላታቸው
ቃለ እግዚአብሔር በኃይል መሆኑ ጠፍቶአቸው
ጥቂት ሳያነቡት ቃሉ ሳይገባቸው
«ኃይለኛ መጽሐፍ ነው» ይህ ብቻ ጥቅሳቸው
የተማሪ መጽሐፍ አስደነገጣቸው÷
አላወቁም አንጂ ተግሣጽ ለጥቅማቸው
ተጽፎ ነበረ ለመንፈስ መሪያቸው

ተጽፎ ነበር ሊቀሰቅሳቸው
ለሥጋ እያደሉ እንቅልፍ ይዟቸው
ጥምጥምና ካባ ይህ ብቻ ዕውቀታቸው
ጸሐፍት ፈሪሳውያን ጌታ ቢመክራቸው
በሻኛ ፍርምቢያ ደንድኖ ልባቸው
ናቁና ገረፉት አፌዙ በአምላካቸው
ጠሉና ሰቀሉት ጠፋ መብራታቸው
እስቲ ወደ ኋላ እንመልከታቸው÷
በባዕድ (በእስላም) ሲገዙ ነጻነት የላቸው
አረሚ ከሓዲ ጺቅ ሲልባቸው
ንጉሥና መቅደስ 2ሺ ዓመታቸው
ወና ሁኖ ቀረ ክብር ታሪካቸው÷
አሁንም ያቆሙት የኃይል መንግሥታቸው
የሚጸና አይመስልም እንደ መጽሐፋቸው፤
ኢሳ. 49÷14-26፤ ሆሴ. 1÷7::
15. ዛሬም እነ አባ ሆይ ሳይመሻሽባቸው
ወንጌል ካልዘረጉ ብርሃን ለሕዝባቸው
የገድል ጨለማ ምንም አይጠቅማቸው÷
ያለም መከር ሲደርስ ምነው መርሳታቸው
በማሸን በማጭድ ሊታጨዱ ናቸው
የአውቆ በዳይ ቅጣት እየጠበቃቸው
ወደ ኋላ ቀሩ እንደ አባቶቻቸው
ምክንያት የለውም ለኀጢአታቸው
አቤቱ ብርሃንህን እንድትገልጥላቸው
እለምንሃለሁ እኔ ጠላታቸው፤
መዝ. 78÷1-10፤ ሉቃ. 6÷27-36፤ ዮሐ. 15÷16-27::
16. አዬ እነ መምሬ ምኑን ልንገራቸው
ዐዲስ ዘመን መጣ ሊቆጣጠራቸው
እንዳይገኝ ባዶ የዘይት ማሰሯቸው
ክንብንቡ ይቅር የሥራ ልብሳቸው
አጥልቀው ይነሡ ወንጌል ስብከታቸው÷
ትርፉን ይፈልጋል ኀይለኛው ጌታቸው
ቀብረው ያስቀመጡት ወርቅ መክሊታቸው
የምድር መላእክት አስኬማ ቆባቸው
ከዓለም ሙተናል ነበር መሓላቸው
ከሞቱ በኋላ መግነዝ መጣላቸው (መፍታታቸው)
ርስት አይካፈሉም ከዘመዶቻቸው
ጕልታችን ሪማችን ብቻ ሐሳባቸው
አገር ይገዛሉ አለማፈራቸው

በምድር ለወጡት የሰማይ ርስታቸው፤
ቈላ. 3÷1-10፤ 1ዮሐ. 2÷14-17::
ስለምን ዘነጉት ትልቁን መብታቸው
ወጣቶች በፊዚክስ ተከፍቶ አንጎላቸው
መሪ ወደ ኋላ ተማሪ ቀድሟቸው
የግእዙን ሽፍን ቋንቋ ገልጦላቸው
በአማርኛ እንግሊዝ ሰልቶ ልሳናቸው
ወጣቶች በሳይንስ ረቋል ሐሳባቸው
ከጕዳይ አይቆጥሩት ገድለ ታምራቸው::

17. አዬ . . . እነ መምሬ አለማፈራቸው
ልብስ ማርዘም ብቻ ክብረት ላይሰጣቸው
ዝክር ቀረ ይላሉ የሆድ ስብከታቸው
እረኞች ከተኙ መንጎች ወዮላቸው
የአውሬ እራት ሊሆኑ ማንም ሊነጥቃቸው
በጊዜ ካልዘጉ የዕውቀት በራቸው
ለባዕድ ሊሰጡት ያን ሁሉ ክብራቸው
አዝናለሁ በእውነቱ የእኔ መሆናቸው
ከኒሳ ካቶሊክ ማንም ሲዘርፋቸው
ቁመው ሊቀሩ ነው በባዶ እጃቸው
እነርሱ እየጠሉኝ እኔ ስወዳቸው
ብልሆች ሲያዝኑ ሞኞች ይደምቃል ሳቃቸው
ከእነርሱ ሊፈልግ ደሙን የሕዝባቸው
አላዩትም መሰል ያ ሕዝቅኤላቸው
በሰማይ በምድር ወዮ ወዮላቸው
ጊዜ ይተርጕመው ሕልሜን ነገርኋቸው፤
ሕዝ. 3÷9-13፤ 22፤ 33-34::

ምዕራፍ 7

ስለ አማላጅነት

ወንድሜ ሆይ! የአማላጅነት ነገር የክርስቶስ ሥራና የብቻው ገንዘብ መሆኑን አስቀድሜ ልገልጽልህ እወዳለሁ:: አሁን ግን ይህንኑ የማያሳስት እውነተኛውን የሕይወት መንገድና እርግጠኛ አማላጅ ትተህ ሌላ የስርቆሽ መንገድ ዮሐ.10÷1:: የማይጠቅም ነኪር ባዕድ የፍጡር አማላጅ መፍጠርህ ምን ይባል ይሆን? ይህ ራስህ የፈጠርኸው ሰፊ ጠማማ የማያሳልፍ መንገድ ግን ስሙን ልንገርህ ስማኝ ስሕተት÷ ክዳት÷ ድንቍርናና÷ ልማድ ፍጻሜውም (መድረሻውም) የዘለዓለም ጥፋት ይባላል፤ ኤር. 5÷7፤ 17÷13፤ 18÷15፤ ማቴ. 7÷13::

ወዳጄ ሆይ! ልብ ብለህ ብታስበው ግን ያንተን ዕዳ ሊከፍል ብሎ ኃጢአትህን (ያንተኑ መስቀል) በቀራንዮ ተሸክሞ «አባ ስረይ ሎሙ» «አባት ሆይ ይቅር በላቸው» ብሎ እየጸለየ ተሰቅሎልህ የዋለው ማን ይመስልሃል? ኢሳ. 53÷1-12፤ ሉቃ. 23÷34:: <u>አሁን ግን እውነተኛው አማላጅ ማለት እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ከሰማየ ሰማያት በፈቃዱ የወረደው ከቅድስት ወንጽሕት ማርያም ድንግል የተወለደው ጻድቁ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ዮሐ. 3÷13-18::</u> ሰውን ሰው ሊያድነው ስለማይችል ግን የሰማዩ ንጉሥ ጻድቁ እኛን ኃጥአንን ለማዳን ሲል ፍቅሩ አስገድዶት ከሰማይ ወደ ምድር ሊወርድ ግድ ሆነበት እንጂ ከጻድቃን ሁሉ ይልቅ አብርሃም አበ ምእመናን÷ የእግዚአብሔር ወዳጅ ከሁሉ የበለጠ ጻድቅ ነውና ስለዚህ ጽድቁ ለሰው እንደማይተርፍ አረጋግጥልሃለሁ፤ ዘፍ. 15÷6፤ ዘፀ. 3÷2-10::

የግል ወዳጄ አቶ ማመን ብቻ ሆይ! እነመምሬ ማዘንጊያ ጻድቃን ፈጣሪን ለምነው አማልደው ኃጥአንን ከሲኦል እጅ ያድናሉ÷ ስማቸውን አንሥቶ ጠላ ለጠጣ ሁሉ ከገሃነም ያወጣሉ÷ ጻድቀው ያጸድቃሉ፤ ከሞቱም በኋላ ማናቸውንም ልመናችንን ሊፈጽሙልን ይችላሉ:: ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋልና የፈቀዱትን ይሠራሉ «እያሉ ሥጋቸውን ለመጠገን አስመስለው ቢሰብኩህ እውነት አይምሰልህ:: «እግዚአብሔር አምላክህን ብቻ በሙሉ ልብህ ውደደው::» የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ጥሰው ከሌላ ወዳጅ (የጣዖት ውሽማ) ጋር ሊያጋቡህ መፈለጋቸው ነው እንጂ ፀሓይ ሳለች ሚሊዮን የኤሌክትሪክ መብራትና እእላፋት ጨረቃና ከዋክበት ተሰብስበው እንኳን ብርሃን ሊሰጡ ሊታዩም እንደማይችሉ÷ እንዲሁም ፍጡራን በፈጣሪ ጉዳይ ገብተው ምንም ምን ሊሠሩ

አይችሉምና ይህንኑ ምሳሌ በቂ ማስረጃ እንዲሆንህ አቅርቤልሃለሁ፤ ዮሐ. 1÷1-8::

አሁን ግን በአምላክህ ምሳሌ የተፈጠርህ ክቡርና ዐዋቂ ሰው ነህና÷ የሰዎችን ሰው መሆን በአንተው ሰውነት መዝነህ ታዘበው እንጂ ተብትበው ያሸከሙትን ይዞ ወይም ተጭኖ የሚነዳ እንስሳ ሆነህ እንዳልተፈጠርህ ዐይነ ልቦናህን ግለጥና መርምረህ ዕወቅ::

ወንድሜ ሆይ! ልባዊ የምግባር እንጂ አንድ ፍሬ የሌለው÷ ቅጠሉ የለመለመ ተረጋሚውን በለስ መስለህ አፍኣዊ የስም ክርስቲያን ሆነህ እንዳትገኝ ተጠንቀቅ፤ ማቴ. 21÷18-20::

ድርሳነ ሚካኤል «ስማቸው ገብረ ሚካኤል÷ ወለተ ሚካኤል የሚባሉት ሁሉ ይጸድቃሉ» ይላል፤ (የኅዳር ድርሳን ገጽ 33 ተመልከት):: እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ቃል ግን የእግዚአብሔርን ሕግ አምኖ በመጠበቅ÷ በጎ ሥራ በመሥራት ብቻ ካልሆነ እውነተኛው አምላክ በስምና በሌላ ነገር ሊታለል ከቶ አይችልም፤ ገላ. 6÷7÷8::

ቍርጡን የሚናገር አምላክ «በዚያች ቀን ብዙዎች አቤቱ አቤቱ ይሉኛል፤ እኔም ከቶ አላወቅኋችሁም እላቸዋለሁ::» ብሏል፤ ማቴ. 7÷21-23:: አሁን ግን ወንድሞቼ ሆይ አምላክ አይታለልምና እባካችሁ ሰዎች በፈጠሩት ሕግ አትታለሉ፤ ማቴ. 15÷1-9፤ ገላ.6÷4-8::

መጻሕፍት ግን ከነአካቴው «እስመ ኢይጸድቅ ኵሉ ሕያው በቅድሜከ» መዝ. 143÷2:: «በዚህ ዓለም መልካም የሚሠራ ጻድቅ÷ ኃጢአትም የማይሠራ ሰው አይገኝም::» መክ.7÷20፤ «ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው» ኢሳ. 64÷6፤ «መኑ ይነጽሕ እምርስሐት÷ ወኢመኑሂ» ኢዮ. 14÷4 እያሉ አስተካክለው ይነግሩናል:: ስለዚህ ሰው ሁሉ በአሚነ ምሕረተ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ይጸድቃል እንጂ÷ ከራሱ በምግባሩ ወይም ከማናቸውም ፍጡር ጽድቅ እንደማይገኝም ኢዮብ ሲያስረዳ: - «ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድነው? ወይስ ከሴት (ከሔዋን) የተወለደ ጻድቅ ይሆን ዘንድ እንዴት ይቻላል?» ይላል፤ ኢዮ. 15÷14:: ቅዱስ ዳዊትም «ኵሉ ዐረየ÷ ወኀቡረ ዐለወ÷ አልቦ ዘይገብራ ለሠናይት÷ አልቦ ወኢአሐዱ» «ሁሉ ዐመፁ÷ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም÷ አንድ ስንኳ የለም::» ይላል፤ መዝ. 14÷1-3፤ ኢሳ. 41÷21-28:: «ለምንስ ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ከቶ ሌላ ቸር የለም::» ማቴ. 19÷16-17::

ቸሩ አምላካችን ማናቸውም ፍጡር የአዳምን ዕዳ ከፍሎ ከጌታው ጋር ለማስታረቅና አማላጅም ሆኖ ፍጡር ለፈጣሪው ካሳ መካስ እንደማይቻለው ዐውቆ÷ በገዛ ራሱ ታራቂና አስታራቂ÷ አማላጅም ሆኖ ዕዳችንን በመስቀሉ ከፈለው እንጂ የአድኅኖተ ሰብእን ነገር ፍጡራንን ልኮ እንዳልፈጸመው አቡሊዲስ ዘሮም በሃይማኖተ አበው በ፩ኛው ድርሳኑ እንደሚከተለው ቃል አስረድቷል።

«ኢፈነወ ሐዋርያ÷ ወኢነቢየ÷ አላ ለሊሁ እግዚአብሔር ቃል መጽአ÷ ወአድኀነነ ከመ ኢይኩን ተስፋነ በሰብእ÷ ወኢንኩን ርጉማነ። <u>እስመ ይቤ መጽሐፍ ርጉም ውእቱ ኵሉ ዘይሴፎ ሰብአ ዘወጽአት ልቡናሁ እምእግዚአብሔር ይከውን ከመ ካሄላ÷ ወይትነጸሕ ውስተ ምድር ይብስት እንተ ኢትፈሪ ወኢትሬኢ ሠናየ»</u>፤ ኤር. 17÷5-8።

«አኮ መልአክ ወአኮ ተንባል÷ አላ ለሊሁ እግዚአብሔር ቃል መጽአ ወአድኃነነ÷ ወሕይወተሂ ኮነት ለነ በእንተ ተሰብኦቱ ከመ ኢይኩን ተስፋነ በሰብእ ወኢንኩን ርጉማነ÷ እስመ ይቤ መጽሐፍ መኑ ውእቱ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት÷ ወመኑ ዘያድኅና ለነፍሱ እምእደሲኦል÷ እምከመሰ ኢክህሉ አድኅኖ ርእሶሙ እፎኑመ እንከ ይክሉ አድኅኖ ኪያነ።» እያለ ደጋግሞ ተናግሯል፤ መዝ. 89÷47-48።

«ተስፋችን በሰው እንዳይሆን÷ የተረገምንም እንዳንሆን እኛን ለማዳን ሐዋርያም ሆነ ነቢይ አልላከም÷ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል መጥቶ አዳነን እንጂ÷ መጽሐፍ ልቡ ከእግዚአብሔር የራቀ ሰውን የሚታመን ሁሉ እንደ ዕሩር መሆኑ ነውና የተረገመ ነው ይላልና÷ መልካም ነገርን ወደማታይና ፍሬን ወደማታፈራ ደረቅ ምድር የተጣለ ይሆናል።» ኤር. 17÷5-8።

«ሰው በመሆኑም ሕይወት ለኛ ሆነችልን መጥቶ ያዳነን መልአክ አይደለም÷ አማላጅም አይደለም÷ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ÷ ተስፋችን በሰው እንዳይሆን÷ ርጉማንም እንዳንሆን÷ መጽሐፍ እንደሚል ሞትን የማያይና ነፍሱን ከሲኦል እጅ የሚያድን ማነው? የገዛ ራሳቸውን ማዳን ካልቻሉ እኛን ለማዳን እንግዲህ እንዴት ይችላሉ።» እያለ ደጋግሞ ተናግሯል፤ መዝ. 89÷47-48።

የኢትዮጵያ ብርሃን ሊቀ ጌታዬ አለቃ ታየም ሰው እንኳን ሰውን ማዳን ሊቻለው ይቅርና ነፍሱንም ማዳን እንደ ማይቻለው ምክሐ ምእመናን በተባለው ድርሰታቸው ገልጸው አስረድተውናል።

መወድስ

ወላድያኒነ ቀደምት ድኅረ በኃጢአት ወድቁ፤
ፍትሐ ሞት መጽአሙ ላዕለ አዳም ወደቂቁ፤
እስከነ ወረዱ ውስተ ሲኦል ዘኢይትረከብ ዕመቁ፤
ኖኅ ወአብርሃም ወካልአንሂ እለ በግብሮሙ ተዐውቁ፤
ኢበቁዖሙ ጽድቆሙ ዳእሙ በመርገመ አዳም ወሞት
ኵሎሙ ተሐንቁ፡፡
በጽድቀ ርእስከሙ ቀዊመ እለ ትጽሕቁ፤
እምጸጋ መድኃኒት ኀበ ደይን ከመ ኢትደቁ፤
መጻሕፍተ ብሉይ ወሐዲስ በአስተሐይጾ ጠይቁ፤
እንበለ ክርስቶስ በርእሶሙ ከመ ኢድኀኑ በሕቁ፤
አብርሃም በምግባሩ ወኢዮብ በጽድቁ፡፡

ትርጓሜ፡ - «አዳምና ሔዋን በኀጢአት ሲወድቁ፤
ወደ ሲኦል ጕድጓድ ወረዱ ጠለቁ፤
ሁላችን ተወለድን ከእነርሱ በሩቁ፤
ከኛም መኻል አሉ÷ እነ ኖኅ በበጎነታቸው የታወቁ፤
በአዳም መርገም ሞት እነሱም ታነቁ፤
ዕዳ ሊከፍል አልበቃም የሰው ሁሉ ጽድቁ፡፡
በሥራ ለመጽደቅ የምትናፍቁ፤
ከመዳን ጸጋ ፎቅ ቍልቍል እንዳትወድቁ፤
ብሉይና ሐዲስን መርምሩ ዕወቁ፤
በሥራው አልዳነም አብርሃም ታላቁ፤
ደገኛው ኢዮብም አልዳነም በጽድቁ፡፡»
ምክሐ ምእመናን ቍጥር 49 እና 52 ተመልከት፡፡

ወንድሜ ሆይ! መጻሕፍት እንደዚህ ብለው ገልጸው አጉልተው ተስማምተው ከሰው ንጹሕ የሆነ ሰውን ሊያጸድቅ የሚችል አንድም ፍጡር የለም ይሉሃል፡፡ ስለዚህ ከሰዎች ትራፊ የማይገኘውን የረሃብ ጽድቅ ከመጠበቅ ይልቅ ከመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ማዕድ በእምነት ቀርበህ ሥጋውና ደሙን ብትበላ የዘለዓለም ሕይወት ሰጭ ምግበ ነፍስና በቂ አማላጅ ማለት እርሱ ብቻ ነው፤ ዮሐ. 6÷53-56፡፡ ስለዚህ ልትድን ብትፈልግ እመን፤ የሐዋ. ሥራ 16÷31፡፡

ቅዱስ ዳዊት ሁላቸው የአዳም ልጆች የበዳይ ልጆች በዳዮችና ቁም ነገር የማይገኝባቸው መሆናቸውን አይቶ÷ «ነገር ግን የአዳም ልጆች ሁሉ ከንቱ ናቸው፡፡ እርሳቸው ሁላቸው በሚዛን ተመዝነው ከምናምን የቀለሉ ናቸው፡፡» እያለ በመዝ. 62÷9 ያስረዳናል፡፡

ይህ የመድኃኔ ዓለም አማላጅነት ግን ለዓለም ሁሉ የሚበቃ÷ ላመኑትና ለታዘዙት በእውነትም ለወደዱት ነው:: እርሱ ግን እንኳንስ ለወዳጆቹ÷ ለቸነከሩትና ለሰቀሉት ጠላቶቹም ያለ ዕውቀት እንደ በደሉት ስለ አየ ኃይል ባለው በሚሰማ ጸሎቱ ምሕረት ይለምንላቸዋል:: እንዲሁም ለዘለዓለም ሊቀ ካህናት ሁኖ ኃጥአን ለሆንነው ለሁላችን የአዳም ልጆች በጥምቀት÷ በንስሓና በቁርባን እየተቀበለ ሲያማልደንና ሲያስታርቀን ይኖራል፤ ዕብ. 7÷25:: «ወሶበ እንዘ ፀሩ ለእግዚአብሔር ንሕነ ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ::» «እኛ ለእግዚአብሄር ጠላቶቹ ሳለን÷ በልጁ ሞት ይቅር አለን::» እንዳለ ሐዋርያ፤ ሮሜ 5÷7-11::

«ወውእቱስ ይነብር ለዓለም እስመ ኢይሠዐር ክህነቱ:: ወይክል አድኅኖቶሙ ለዝሉፉ ለእለ ይቀርቡ ኀበ እግዚአብሔር እንተ መንገሌሁ እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ ወይተነብል ሎሙ::» «እርሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፤ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል::» ዕብ. 7÷24-25፤ 10÷11-22:: «ወአንሰ ሰአልኩ በእንቲአክሙ ከመ ኢይድክም ሃይማኖትክሙ::» ሉቃ. 22÷32:: «ወእንሰ በእንቲአሆሙ እስእል፤ አባ ቅዱስ ዕቀቦሙ በስምከ::» «እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤. . . ቅዱስ አባ ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን. . . በስምህ ጠብቃቸው::» እንዳለ፤ ዮሐ. 17÷9፤11::

ስለዚህ ክርስቶስ በቃሉ «ንዑ ኀቤየ ኲልክሙ ስሩሐን ወክቡዳነ ጾር÷ ወአነ አዐርፈክሙ::» «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ÷ እኔም አሳርፋችኋለሁ::» ብሎ ስለ ነገረህ ዕረፍተ ነፍስ እንድታገኝ÷ ዛሬ ቃሉን አምነህ በሠራኸው ኃጢአት እያዘንህ በንጽሐ ሕሊና ወደርሱ ብታለቅስ÷ ኃጥአንን ከአባቱ ጋር ለማስታረቅ የሚቻለው÷ ለዚሁም ሥራ የተመደበው ባለሥልጣን እርሱ ብቻ ነው፤ ማቴ. 11÷28፤ 28÷18፤ ዕብ. 2÷17-18፤ 4÷14-16፤ ራእ. 1÷5-8፤ 5÷1-14::

ወንድሜ ሆይ! ልብ አድርገህ ስማኝ፤ አስቀድሞ ለቸነከሩት ብዬሃለሁ፤ አሁንም ዛሬ የምንቸነክረውና የምንሰቅለው አንተና እኔ÷ ሥጋ አሸንፎን ይልቁንም የኃጥአን ቀዳሚ ከምሆን ከእኔ ጀምሮ ትእዛዙን በማፍረስ ሁላችንም የአዳም ልጆች ሰቃዮቹ መሆናችንን (እስራኤል ብቻ የሰቀሉት አይምሰልህ) አትርሳ:: «እግዚአብሔር ሁሉን ሊምር ስለ ወደደ ግን÷ ሁሉን ካለ መታዘዝ በታች ዘጋው::» ሮሜ 11÷39፤ ዕብ. 6÷4፤ ገላ. 3÷22::

እርሱ ግን ባሕርዩ ርኅራኄ የሆነው አምላካችን፥ አሮጌ ጠባያቸውን በንስሓ ለውጠው ወደርሱ ለሚመለሱ ሁሉ መሐሪ መሆኑን እመንና «ኀበ ሀለወት ብዝኀት ኃጢአት በህየ ትበዝኅ ጸጋ እግዚአብሔር» «ብዙ ኀጢአት ባለችበት በዚያ የእግዚአብሔር ጸጋ ትበዛለች።» የሚለውን ሕያው ቃል በእምነት ተመርኩዘህ ጉዞህን ወደርሱ ቤት እድትቀጥል ዐደራ እልሃለሁ ሮሜ5፥12-21፤ 1ጢሞ.12፥18። «እኔ የበደሉኝን ሁሉ ይቅር እላለሁ።» ይላል፤ ኤር. 33፥1-9፤ 36፥3።

ወዳጄ አንባቢ ሆይ! በሰነፎች ስሕተት ተወስደህ፥ ሃይማኖትን የሚያላላና የፍጡራን አማላጅነት የሚባለውን የሰው ሥርዓት አምነህ መንፈሳዊ ሕይወትህን እንዳታታልል ተጠንቀቅ፤ 2ጴጥ. 3፥17-18።

<u>እውነተኛይቱን አማላጅ ልንገርህ ስማኝ፥ ሕግን ሁሉ መጠበቅ በክርስቶስ ምሕረትም መማፀን ብቻ ናት።</u> ሕግን ከጠበቅህና በኢየሱስ ስም ካመንህ ግን ሕግ ራሱ አማላጅ ሁኖ የገነትን በር ከፍቶ ዓለም ሳይፈጠር ወደ ተዘጋጀልህ የክርስቶስ አዳራሽ እንደሚያገባህ እመን አትጠራጠር፤ ማቴ. 11፥6፤ ዕብ. 4፥14-16። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አማላጅነት ነገር ሲያስተምረን «ልጆቼ ሆይ! ኃጢአት እንዳትሠሩ፥ ከእናንተ ማንም ኃጢአት ቢሠራ ግን ከአብ ዘንድ የሚያስታርቀን እውነተኛ አማላጅ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።» ይለናል፤ 1ዮሐ. 2፥1-2።

ፍጡር ሁሉ እንዳንተና እንደኔ በሕግ አፍራሽነት ተይዞ ዕዳውን መክፈል ስላቃተው ግን ኢየሱስ ብቻውን የተዋረደውን ሥጋችንን ለብሶ፥ የአዳምን ዕዳ ለመክፈል ፍቅሩ አስገድዶት መስቀላችንን ተሸክሞ፥ እጆቹን በችንካር፥ ጎኑን በጦር ተወግቶ ሞቶ ተነሥቶ ከአባቱ ጋር አማልዶ ከጥፋት ያዳነን መድኃኔ ዓለም መሆኑን ልታውቅ ብትፈልግ ጥቅሶቹን በማስተዋል መርምር፥ ብርሃነ ልቡናህን በቅዱስ መንፈሱ ያብራልህ አሜን፤ ማቴ. 27፥22፤ ሮሜ 5፥5፤ ኤፌ. 2፥4-18፤ ቆላ. 1፥10-23።

ምዕራፍ 8

ስለ ፍጡር ጭከናና የአምላክ ርኅራኄ

ወንድሜ ሆይ! ክርስቶስ ጨካኝ ነውና፥ ከፍጡራን አንድ መልአክ ወይም አንድ ጻድቅ አማላጅ ዋስ ጠበቃ በምትፈረድበት ቀን ያስፈልግሃልና፥ ቢሆን ሞግቶ፥ ባይሆን ተውሶ ከገሃነም (ሲኦል ወኀኒ) የሚያወጣህ ወዳጅ ታማኝ ያዝ፥ አብጅ፥ ቢሉህ በከንቱ የሕልም ውሃ እንደ መጠጣት የመሰለ ነገር ነውና አትመናቸው:: ቅዱስ ዳዊት «ሐለሙ ሕልመ ወአልቦ ዘረከቡ::» «ሕልምን አለሙ ያገኙት ግን የለም» (እንደ ግእዙ ትርጉም) ይላል፤ መዝ. 76÷5፤ መክ. 5÷3-7፤ ሲራ. 31÷1-7፤ ኢሳ. 29÷8::

<u>እግዚአብሔር አምላካችን በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ «አኮ በመልአክ ወአኮ በተንባል አላ ለሊሁ ያድኅኖሙ፥ እስመ ያፈቅሮሙ ወይምሕኮሙ ውእቱ ተቤዘዎሙ፥ ወተወክፎሙ ወአክበሮሙ በኲሉ መዋዕሊሆሙ ለዓለም» «በመልአክ አይደለም፤ በአማላጅም አይደለም፤ እርሱ ራሱ ያድናቸዋል እንጂ፥ ይወዳቸዋልና ይራራላቸውማል:: እርሱ ተቤዣቸው፥ ወደ እርሱም ተቀበላቸው፥ በዘመናቸው ሁሉም ያከብራቸዋል::»</u> ይላል፤ (ኢሳ. 63÷1-9 የግእዙን ተመልከት):: ኢየሱስ ራሱ በገዛ እጁ በፍቅር በርኅራኄው ነው እንጂ በለማኝና በአማላጅ እንዳላዳነን <u>«ጻድቅ አምላክ፥ የሚያድንም ከኔ ሌላ የለም::»</u> ይላል፤ ኢሳ. 45÷21:: ስለዚህ አስተውል የሚያድንም ወይም የሚቤዥም ክርስቶስ ብቻ ነው እንጂ ፍጡር ፍጡርን ሊቤዠው ወይም ሊያድነው ከቶ አይቻለውም:: ቅዱስ ዳዊትም «እኅውኒ ኢያድኅን እኅዋሁ፤ ወኢያድኅን ሰብእ፤ ወኢይሁብ ለእግዚአብሔር ቤዛሁ ወኢተውላጠ ሤጠ ነፍሱ» «ወንድም ወንድሙን አያድንም፥ ሰውም አያድን፤ ለእግዚአብሔር ቤዛውን አይሰጥም፤ የነፍሱንም ተለዋጭ ቢሆን::» ይላል፤ መዝ. 49÷7::

ይልቁንም አምላካችን ራሱ ፍቅር ስለሆነ 1ዮሐ.4÷8፤ ተስዓ ወተስዓቱ ነገደ መላእክትን ትቶ አንድ የጠፋ በግ አዳምን ለመፈለግ መጥቶ፥ በዓለም በረሃ ተሰብሮ ወድቆ አግኝቶት ቊስሉን ሳይጸየፈው ስባራውን ጠግኖ፥ እድፉንም ከጎኑ በወጣው ውሃ ዐጥቦ፥ አንጽቶ፥ አድኖ በትከሻው ተሸክሞ፥ ኃጥአንን ገነት መንግሥተ ሰማያት ለማስገባት ተልኮ የመጣው እውነተኛው የነፍሳት እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ቤዛ የሚሰጥ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ሕዝ. 34÷11-25፤ ሉቃ. 15÷1-10:: «እኔ ነኝ

ቸር ጠባቂ፥ ቸር ጠባቂ ራሱን ስለበጎቹ ይለውጣል፥ ምንደኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ጥሎ ይሸሻል::» እንዳለ ጌታ፤ ዮሐ. 10፥1-16::

እንዲያውም ጻድቃን ያማልዳሉ ማለት በፍጹም ሐሰት ነው:: ጻድቃን የምንላቸው ሐዋርያት አንድ ሌሊት እንግዳነት አናሳድራቸውም ላሉአቸው አገሮች (ሰዎች)፥ እነርሱ ተቈጥተው፥ ከሰማይ እሳት አውርደው፥ አቃጥለው፥ ፈጅተው ሊያጠፏቸው እንዳሰቡና ፍቅር ባሕርዩ የሆነው ኢየሱስ ወልደ አምላክ ግን፥ አንድም ሰው እንዲጠፋ ስለማይወድ «ተዉ! የየትኛው መንፈስ እንደ ሆናችሁ አላወቃችሁምን? እኔ ሰውን ላድን እንጂ ላጠፋ አልመጣሁኝም» ብሎ እንደከለከላቸው ሉቃስ በወንጌሉ ገልጾ ይነግረናል፤ ሉቃ. 9፥51-55:: ኤልሳዕ ነቢይም በጭከናው ረግሞ 42 ሕፃናት በጅብ አስገድሏል፤ 2ነገ. 2፥23::

እንደዚሁም ጻድቁ ነቢይ ኤልያስ አክዓብ በነገሠበት ዘመን፥ በጸሎቱ የሰማይን ዝናብ ሦስት ዓመት ዘግቶ ሕዝቡ በረሃብ፥ ሰው ሰውን እስኪበላ ድረስ ዘመዶቹ ሲያልቁ ዓይኑ እያየ፥ እርሱ ግን በዋሻው ውስጥ ገብቶ ተሸሽጎ፥ ሦስቱን ዓመት ሙሉ አንድ ቀን ሳይጎድልበት እንጀራና ሥጋ ጠዋትና ማታ ቁራዎች እያመጡለት ብቻውን እየተቀለበ (እየተመገበ)፥ የወንድሞቹ ጭንቅና ሥቃይ ሳይሰማው (ሳያስደነግጠው) አንዲት ነፍሱን ብቻ ሲንከባከብ እንደነበረ፥ ርኅሩኅ አምላካችን ግን የፍጥረቱን ጭንቅና መከራ አይቶ ራርቶ፥ ለኤልያስ «ና ውጣ ሂድ! ራስህንም ለአክዓብ ግለጥ፥ በምድር ላይ ዝናብ ላወርድ ነውና::» ብሎ ዝናብ እንዳዘነበና ለሕዝቡም ምግብ እንደሰጠ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፤ 1ነገ. 17፥1-14፤ 18፥1:: ጻድቁ ኤልያስ እንደገናም 450 ሰዎች በሰይፈ ጭከናው አርዷል፤ 1ነገ. 18፥40::

ፍጡር ጭከናና ወስላታነት ካልሆነ ርኅራኄና ቅንነት መሥራት እንደማይቻለው፥ ሁለቱ ታላላቆች ነብያት የሠሩትን ተመልክቶ አንድ ሊቅ በሚከተለው ቅኔ አስረድቶናል፤ ርኅራኄንም ለአምላክ ብቻ ሰጥቶ አሳይቶናል::

<u>መወድስ</u>

ገሠጽኮ ለዮናስ በቀስታመ ባሕር
ኅበ ኢዘርዐ ስብከተ ኅጠተ ቃሉ ዘራዒ
ለምድረ ነነዌ ፀርከ በገራህተ እዝና ሰማዒ
ወበቃለ ረኃብ ተዛለፍኮ ለዘኢሐዘነ ኤልያስ ቀናኢ
በእሳተ ረኃብ እንዘ ያውዒ
ኵሎ ገዳመ ቤተ አክዓብ ገፋዒ
አኮኑ አምላከ ፍቅር እንዘ ነደ እሳት በላዒ

ትቌርር ከመ ማይ ድንጋፄ ኃጥአን ሶበ ትሬኢ
ለገብርከኒ ዓለም በበትረ መከራ በቋዒ
ተግሣጸ ውሉድ ተጌሥጸ ወኢትሬስዮ ከመ ጸላኢ።

ትርጓሜ: - «ጠላትህ ለሆነችው ምድረ ነነዌ የስብከት ቃሉን ሊዘራ፥ ዮናስ ፈቃደኛ ባልሆነበት ጊዜ፥ ባሕርን እንደ በትር ተጠቅመህ ቀጣሽው። በአክዓብም ዘመን ምድርን ሁሉ በረኃብ እሳት ሲጠብስ ያላዘነውን ኤልያስን የረኃብን ምንነትና ጉጂነት እንዲያውቅ አደረግሽው።

በባሕርይህ የምትባላ እሳት የሆንከው አንተ ግን የፍቅር አምላክ ነህና የኀጢአተኞችን መደናገጥ (መዋከብ) ስታይ እንደ ውኃ ትቀዘቅዛለህ፤ ከዚህ የተነሣ አገልጋይህን ዓለም (ሰው) በሚጠቅመው የመከራ በትር ትቀጣዋለህ እንጂ (ኤልያስና ዮናስ እንዳደረጉት) የሁልጊዜ ጠላት አድርገህ አትቈጥረውም፤» ብሏል።

እንደዚሁም ፍጡር ጭከና ካልሆነ ርኅራኄ እንደማይገኝበት፥ የጉንደሩ ሊቅ ነጮ ተክለ ሃይማኖት በሚከተለው ቅኔ አስረድተዋል።

መወድስ

አሐደ ዕለተ እምተፈጸምነ
ለፍጥረትከ አምላክ እመ አምላከ ትሬስዮ
ትእምርተ ዝኒ ነገር ሶበ ለነጥበ ማይ ቀነዮ
ኤልያስ ዘፍዳ ሰበኑ ለኤልሳዕ ፈደዮ
ለፍጥረተ ዚአከ ተሐየዮ
እስመ ለፍጥረትከ ዕፅ በእሳተ ረኃብ አውዐዮ
ዳዊትሂ ዘተሠርገወ መንግሥተ ሳዖል ሎግዮ
ግፍዐ ሳዖል ተዘከረ ወጸንዐ በኦርዮ
ሚካኤልኒ ርኅሩኅ ዘጽጋበ ምሕረት ከረዮ
ለሙሴ ኢተራኀርኀ እንዘ ውስተ መሬት ይወድዮ

ትርጓሜ: - «አምላክ ሆይ! ለፍጥረትህ (ፍጡርህን) የአምላክነትን ሥልጣን ብትሰጠው ኖሮ ሁላችንን ባንድ ቀን በጨረሰን ነበር። ይህንንም ነገር እንረዳ ዘንድ፤ መጐናጸፊያውን እንደ ምንዳ ለኤልሳ የከፈለው ኤልያስ የውሃ ጠብታ እንዳይኖር ባዘዘ ጊዜ ለፍጥረት አላዘነም፤ ችላ አለው እንጂ። የሳዖልን መንግሥት የወረሰው ዳዊትም የሳዖልን ግፍ አልረሳም፤ በኦርዮም ጨክኖበት ነበር።

የምሕረት ጥጋብ የፈነቀለው ሚካኤልም፤ (መልአከ ምሕረት ምንም ቢባል፤) ሙሴን በመሬት ውስጥ (በናባው ተራራ) ሲቀብረው ርኅራኄን አላደረገም፤ (አላዘነለትም)፡፡»

ደግሞም ኤልያስ ጻድቁ በጭከናው መቶ ሁለት ሰው እሳት ከሰማይ አውርዶ አስበልቶ አጥፍቷል፤ 2ነገ. 1÷9-12፡፡ የኤርምያስን ጭከናና መርገም አንብብ፤ ኤር. 18÷18-23፡፡

ጻድቁ ዮናስ ነቢይም ነነዌን ያህል ትልቅ ከተማ÷ ከመቶ ሃያ ሺህ የሚበዛ ሕዝብ የያዘ አገር÷ ሰዎቹ ከክፉ ሥራቸው ስለተመለሱ÷ እግዚአብሔር አይቶ ካዘዘው መዓቱ÷ ፍቅር ባሕርዩ ነውና ሳያጠፋው ቀርቶ ቢምረው ዮናስ ግን ይህን ያህል ፍጡር ስላልጠፋና እንደ ሰዶም ስላልተገለበጠ እንዳዘነ÷ እንዳጕረመረመም እንሰማለን (እናነባለን)፤ ዮና. 4÷1-11፡፡

ክርስቶስ ግን ርኅሩኅ ስለሆነ ዕውራንንና ድውያንን ባየ ጊዜ ብርሃንና ጤና እየሰጠ÷ ሁሉንም ይፈውሳል፤ ለሰቀሉትም ሳይቀር ምሕረት ይለምናል፤ ሉቃ. 23÷34፡፡ የፍጡራን ጭከና ግን ቅዱስ ጳውሎስ ለበደሉት ምሕረት በማድረግ ፈንታ የሦስት ቀን ዕውርነቱን ረሳና የሐዋ. ሥራ9÷1-19፤ ያልፈጠራቸውን አዕይንት በዕውርነት ሲቀጣ ነበር፤ የሐዋ. ሥራ 13÷6-11፡፡

ማርያም ድንግል ርኅርኅትና ንጽሕት÷ ጻድቅትና ቅድስት ናትና÷ ክፉን አትወድም በማለት ፈንታ አንድ ጊዜ የሌቦች÷ የዘማውያን÷ የገዳዮችና የሕግ አፍራሾች ሁሉ ዋሻ ናትና አማልዳ ታድናለች፤ አንድ ጊዜ ደግሞ ስደት ስትሄድ እንግድነት አንቀበልሽም ያሏትን አገሮች ረግማ ዝንጀሮና ጦጣ÷ ዐውሬ ሐሪሥም (ጕሽ ወይም አውራሪስ) አደረገቻቸው እያሉ ጠላቶችዋ በሐሰት ጽፈዋል፡፡

ስለዚህ እንወዳታለንና እናከብራታለን ሲሉ÷ አለ ሥራዋ እየሰጡ እርስዋ የማትወደውን እየሠሩ÷ በቁም ነገር ቦታ የጫጉላ ቤት ይመስል ከንቱ የሆነ ቃል መናገራቸው እጅግ ያሳዝናል፡፡ ዝንጀሮና ጦጣ ሌላም እንስሳና ዐራዊት ሁሉ ግን ከሰው ጋራ በ6ኛ ው ቀን እንደተፈጠሩ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፤ ዘፍ. 1÷24-31፡፡

ጻድቃን ያማልዳሉ÷ ሰማዕታት ይራራሉ÷ ቅዱሳንም ስለ ኃጥአን ይለምናሉ ማለት በፍጹም ሐሰት ነው፡፡ በመጨረሻውም ከአቤል ጀምሮ እስከ ምጽአቱ በስመ ክርስቶስ እየተጠሉ የሞቱ ሁላቸው ጻድቃን ምስክሮቹ÷ ስለ ኀጥአን መለመናቸው ቀርቶ «ምነው ጌታችን ሆይ! ቅዱሱ÷ ለፈሰሰው ደማችን በቀል አትበቀልልንምን? በጠላቶቻችንስ ላይ በቶሎ አትፈርድባቸውምን?» እያሉ በታላቅና በሚያስቸኩል ቃል ሰውን ለማጥፋት በጭከና

እያማረሩ÷ እየከሰሱም ሁልጊዜ እንደሚጮሁና ርኅሩኅ አምላክ ግን÷ ተዉ ታገሡ አርፋችሁ ቆዩ ብሎ እንደሚከለክላቸው÷ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በመንፈስ ራእይ አይቶና ሰምቶ አስተካክሎ ነገሮናል፤ ዘፍ. 4÷10፤ ራእ. 6÷9-11፤ ዘፍ. 6÷5፤ 2ዜና. 24÷17-22፤ ራእ. 16÷4-7::

ወንድሜ ሆይ! በአገራችን የሚታወቁት አገርን ለመሰለል የመጡት ባዕዳን ነጮችን (ዲፕሎማቲኮች)÷ እኛ ጻድቃን የምንላቸው አቡነ አረጋዊ÷ ገሪማ÷ አቦ÷ ጊዮርጊስ÷ ተክለ ሃይማኖት ሌሎችም የመሰሏቸው እጅግ ብዙዎች ናቸው:: እነዚህ ሁሉ ከእነርሱ በፊት የሞቱትን ጻድቃንና መነኮሳት÷ ሰማዕታትን እርዱን አማልዱን እያሉ ሰዎችን አምነው ደግ ሳይሠሩ የጸደቁ ይመስልሃልን? አይደለም፤ «ኢትትአመኑ በመላእክት ወኢበዕጓለ እመሕያው÷ እለ ኢይክሉ አድኅኖ::» «ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና በአለቆች አትታመኑ፤» የሚለውን ቃል ስለ ተረዱት÷ እንኳን ለማዳን ለመፍጠርም አጋዥ የማይፈልግ ፈጣሪያቸውን ብቻ አምነው ስላገለገሉት ጸድቀው ይሆናል እንጂ÷ ፍጡራንን አምነው አልጸደቁምና ገድላቸው ወአዕረፈ በሰላም በአሚነ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ (ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን በሰላም ዐረፈ) ይላል፤ መዝ. 146÷1-10፤ የሐዋ. ሥራ 7÷59-60፤ ዕብ. 11÷1-40::

የተወደድህ አንባቢ ሆይ! አምላክ ጨካኝ ነውና እርሱ በተቆጣበህ ቀን÷ ራርቶ የሚያስታርቅህ አንድ ጻድቅ ወዳጅ አማላጅ ዛሬ መያዝ ያስፈልግሃል በሚሉህ ጊዜ÷ ሐሰት ነው አትመናቸው ላልኩህ ማስረጃውን <u>«አልቦ ዘያስተአብዶ ለእግዚአብሔር»</u> አምላክ ሑሩ ብሎ ሲቈጣ የሚሸነግለው÷ የሚያማክረው የሚያታልለው የለም፤ አይገኝም እያሉ መጻሕፍት ይነግሩናል፤ ገላ. 6÷1-7::

ይህ ነገር (ትምህርት) አግራምቢጥ መሆኑን ግን ቅዱስ መጽሐፍን አንብብና ተቀምጠህ÷ ተኝተህም ቢሆን ሳትቸኩል ዝግ ብለህ ተረድተኸው ስታበቃ÷ ነፍስህ የምትድንበት ትልቁ ነገር ስለሆነ÷ ልብህን ዳኛ አድርገህ÷ እውነትን ከሐሰት ለይተህ÷ ሰው ይነቅፈኛል ሳትል በአምላክህና በሰው ፊት በድፍረት እውነተኛውን ፍርድ እንድትፈርድ (እንድትመሰክር) በጲላጦስ ፊት ቁሞ በመልካም ማመን በመሰከረው በኢየሱስ በመድኃኔ ዓለም አማፅንሃለሁ፤ 1ጢሞ. 6÷13-16::

እርሱ የጸጋውን ብርሃን ይግለጽልህና ወደዚያች ሁላችንም ወደምንመኛት አገር÷ ግን÷ ፈሪዎች÷ ኀፍረተኞችና ወላዋዮች እንደማይገቡባት አስተውል፤ ራእ. 21÷8፤ ማቴ. 10÷26-38::

ምዕራፍ ፱

እውነትና ሐሰት

የተወደድህ አንባቢ ሆይ! ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ቅር የሚያሰኝህ ቃላት አታጣበትም ይሆናል። ነገር ግን በእውነተኛ ብርሃናዊ ሕሊናህ ብትመረምረው የኛው አምልኮና (አካሄድና) የአምላካችን ትእዛዝ በጣም የተለያየ መሆኑን ስለ አየሁ፥ እኔም እንዳንተ ብዙ ጊዜ ቅር ብሎኛል፤ እንደምን ብትለኝ ግን ክርስቲያንነታችን በስም ብቻ ነው እንጂ፥ በሕግና በምግባር አይደለም። ከሁሉ ይልቅ የባሰውና የከፋው ግን ያገሬ ሕዝብ የክርስቶስን መድኃኒትነት ከነወንጌሉ ጥሎ፥ እነአባ እገሌን ጻድቅ ብሎ፥ ከነመጽሐፈ ሐሰቱ አምኖ የማያድነውን መድኃኒት መስሎት ተቀብሎ፥ ለስሙ ግን የክርስቶስ ወገን ክርስቲያን ነኝ ይላልና ነገሩ ቅር ያሰኛል፤ በጣምም ያሳዝናል፤ ኢሳ. 29፥10-13፤ ኤር. 25፥4-7፤ ኢሳ. 57፥3-13።

ስለ አትናቴዎስ በቅዳሴው ምዕራፍ 1 ቁ. 9-10 «ገሥጾ ለኃጥእ ከመ እኁከ፥ ዝልፍዎ በግህደት ለእመ ቦቱ አበሳ ዘለሞት መዐድዎ ለዘጌገየ ከመ ይኅድግ ኪያሃ ፍኖተ ወይትጋነይ ለእግዚአብሔር ከመ ይስረይ ሎቱ።» «ኀጢአተኛውን እንደ ወንድምህ ገሥጸው፤ ለሞት የሚያበቃ በደል ያለበትንም በግልጽ ዝለፋት፤ የበደለውንም ምከሩት፤ ያችን ክፉይቱን መንገድ ይተው ዘንድ፥ ለእግዚአብሔር ይገዛ ይቅርም እንዲለው።» ይላል። ቅዱስ ጳውሎስም <u>ወንድምህን ስለጉድለቱ እንዲያፍርበት በግልጽ ገሥጸው»</u>፤ 1ጢሞ. 5፥20፤ 2ተሰ. 3፥14-15 ይላልና፥ እኔም የሀገሬ ሕዝብ የተሰቀለውን እውነተኛውን መድኃኒት ክርስቶስን ብቻ አምኖ እንዲድንልኝ በማለት ነው እስከዚህ ድረስ ደፍሬ የጻፍኩት እንጂ፥ ልሰድብ ወይም ልነቅፍ ብዬ እንዳልጻፍኩት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ብታነበው ቅዱስ ዳዊት «ቅንአተ ቤትከ በልዐኒ።» እንዳለ፥ እኔንም እንዲሁ የጤፍ ፍሬ በማያህል በትንሹ ዐቅሜ፥ የቤቱ ቅንአት አስገድዶ እንዳስጻፈኝ ትረዳዋለህ፤ ዮሐ. 2፥13-17።

ብነቅፍም ቅሉ፥ የሥጋ ቤት ሹመት ተቀብሎ፥ ወይዘሮ ዓለሚቱን አግብቶ፥ ሰፊውንና ረጅሙን የፈረሳውያንን ቀሚስ አጥልቆ በየከተማውና ገበያው እየተኩነሰነሰ ለሚውለው፥ ከሕግ ውጭ ለሆነውና ልማድ በተባለው ለኮ (ገመድ) እየተጕተተ መብቱን ረስቶ ኀላፊውን ዓለም ብቻ እየተመለከተ አምላክና ሰውን እያሳዘነ የሚኖረውን ክፉ (ከባድ ቀምበር) ምግባርን ነቀፍሁ እንጂ፥

ክርስቲያናዊ ሃይማኖትን እንዳልነቀፍሁ ሚዛናዊ ሕሊና ያለው ሰው ሳይረዳው አይቀርም፤ ማቴ. 23÷1-28::

ቁሞ መስበክና ጽፎ መግለጽ እንጂ÷ ተቀምጦ መንቀፍ ለማንም እንደማያዳግተው ማንም ሰው ያውቀዋል:: ይህን ተግሣጽና ምክር የተባለውን መጽሐፌን ያነበቡ አንዳንድ ሰዎች «አዋልድ መጻሕፍትን ለምስክርነት አይበቁም ብሎ ነቅፏቸው ሲያበቃ÷ ራሱ ግን ለምስክርነት ጠቅሷቸዋል» ሲሉ ሳይነቅፉብኝ የቀሩ አይመስለኝም:: እውነት ነው÷ አዋልድ ማለት ትርጓሜው ልጆች ማለት ነው:: ነገር ግን ልጅ ሲባል መልኩና ባሕርይው አባቱን መስሎ ሲገኝ ልጅ ይባላል እንጂ÷ መስሎ ካልተገኘ ዲቃላ÷ በምንዝር የተወለደ÷ ጎደሎ አባቱ ያልታወቀ÷ አንደበራ (ሰነፍ የሴት ልጅ) ማለት ነውና ከመጻሕፍተ ርስት ሊካፈልና ሊቈጠር ከቶ አይገባም ዘፀ. 23÷1-2:: ለምሳሌ ከአንድ ቊና አሸዋ ውስጥ ሁለት ሦስት የወርቅ ቅንጣት ቢገኝ÷ በወንፊቱ ተለቅሞ ወደ ወርቅነቱ ይጨመራል እንጂ÷ ከአሸዋ ጋር ኑረሃል ተብሎ ሊጣል ይገባልን? ሐዋርያው «ሁሉንም መርምሩ÷ ክፉውንም እየተዋችሁ መልካሙን ብቻ ያዙ» ብሎ የሚያስተምረን ለሃይማኖቶች መጻሕፍት ነው እንጂ ለቊሳቊሶቹ የቤት ዕቃዎች አይደለም፤ 1ተሰ. 5÷21-22፤ 1ዮሐ. 4÷1::

ስለዚህ ይህ የእኔው መጽሐፍም አዋልድ (ከብሉያትና ሐዲሳት የተወለደ) ነውና÷ ጸሐፊያቸው ካልታወቀ መጻሕፍት አፍራሾቹን እየተወ÷ አባታቸውን የሚመስሉና ቅዱሳት መጻሕፍትንም የሚደግፉ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ቢጠቅስ÷ በእኔ ሐሳብ የሚያስጸይፍ መስሎ አይታየኝም::

እኔ ግን ተኣምርና ገድላትን በየውሸታቸው ለማጽደቅና ለማጋነን ሲሉ÷ ልጓም እንደሌለው ፈረስ ሁሉም በየፊናቸው ሲጋልቡና በአንድ ቦታ እንኳ÷ ሲጠቃቀሱ ባለመስማቴ እየተደነቅሁ÷ «ሁሉም ወደየመንገዱ አዘነበለ» የሚለውን ቃል እያስታወስሁ በነቃፊዎቹ የሀገሬ ልጆች ሐሰትን እስኪያምኑ ድረስ የስሕተት መንፈስ ስለ ወደቀባቸው ሳዝን እኖራለሁ፤ ኢሳ. 29÷9-14፤ 53÷6፤ 59÷11-16፤ ሮሜ 1÷19-25፤ 2ተሰ. 2÷10-13::

በእውነቱ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ገድልና ተአምሮችን ላስተዋላቸው ሰው÷ እንኳን እንደ አባትና ልጅ ሊመሳሰሉ ይቅርና የባዕድነታቸው መራራቅ በእሳትና ውሃ መካከል ካለው ጠበኝነት ይልቅ የባሰ ሆኖ ይገኛል:: ስለዚህ አዋልድን እንኳን መጻሕፍተ እውነት ብዬ ልጠቅሳቸው÷ ሐሰተኝነታቸው በኔ ሕሊና ውስጥ የምሥራቅና ምዕራብ መራራቅ ያህል መለያየት እንዳለው ስገልጽ

ይብላኝላቸው፥ ሳያውቁ የሚያምኑዋቸውንና የሚመኩባቸውን ወንድሞቼን ይቅር ይበላቸው እንጂ፥ እኔስ ከሐሰታቸው ሸሽቼ የመድኃኒቴን ድምፅ ለይቼ በቃሉ ነጻነትን ስላገኘሁ፥ በወንጌሉ ብቻ አምላኬን ዘወትር እያመሰገንሁ በደስታና ተስፋ እኖራለሁ፤ ዮሐ. 8፥28-37፤ 10፥1-5።

ወንድሞቼ ሆይ እውነትና ሐሰት፥ ጨለማና ብርሃን ግን፥ ምንም እንኳን ጎን ለጎን ሆነው አብረው ሲጓዙ ቢኖሩ አንድም ቀን ተስማምተውና ተግባብተው አያውቁምና፥ «የማታ ማታ እውነት ይረታ» የተባለው የአባቶቻችሁን ምሳሌ ሳትረሱ፥ ሁሉንም እየመረመራችሁ ወደ እውነት ብትገሰግሱ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደምትደርሱ እርግጥ ነው፤ ራእ. 21፥3-8 ።

የክርስቶስ የወንጌሉ ጣዕምም «ኵሉ እንከ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ አአምኖ አነሂ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። ወለዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ አነሂ እክሕዶ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።» «ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ፥ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።» ማቴ.10፥32 ይላልና፥ የሰማሁትንና ያነበብሁትን እንዲሁ ለሀገሬ ልጆች የልማድና የድንቁርናን መጋረጃ ብገልጽላቸው፥ የሕይወት ቃሉንም ባቀምሳቸው በነፍስና በሥጋ እንደሚጠቅማቸው እርግጥ ነው። 1ጢሞ.4፥8። ቅዱስ ዳዊትም «ጠዐሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር» «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም፤» እንዳለ መዝ.34፥8። ሐዋርያትም «ንሕነሰኬ ኢንክል ከቢቶቶ ለዝንቱ ነገር» «እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም፤» ብለዋልና የሐዋ. ሥራ 4፥20፤ እኔም ያየሁትን የተረዳሁትን አቀምሳለሁ (እነግራለሁ) እንጂ አልሸሽግም ማቴ. 10፥27፤ ሉቃ. 8፥16፤ ራእ. 10፥8-11 1ዮሐ. 1፥1-5፤ መዝ. 78፥2-8።

ወንድሞቼ ሆይ! እስከዚህ ድረስ በድፍረት እያማረርኩኝ መጻፌ ግን፥ አባቶቻችን ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት በፍትሐ ነገሥት በሁለተኛው አንቀጸ መጻሕፍት፥ ፹ወ፩ አምላካውያት የተውልን ጠፍተው፥ በመጻሕፍተ ፈጠራ ተቀብረው ተረስተው ስለአየሁና ቸሩ እግዚአብሔርም የጨለማውን ዘመን «በቃህ በኃይለ ሥላሴ ብርሃን ሰጥቼሃለሁ፤ ሐሰት ውጣ እውነት ግባ ብሎ» ዐዋጁ-ምሕረቱን በኢትዮጵያ ስለዘረጋልን ነው። እንዲሁም ዲሞክራሲያ (ሐሳብን በጽሑፍ መግለጽ) ጥንታዊ ዐዲስ ዘመን አመጣሽ ሳይሆን በአገራችን ጥንታዊ መሆኑን እያሳሰብሁ፥ ለምሳሌ ቅዱስ ዳዊት

ሥዕልና ምስልን ሲነቅፍ «ዐይን ቦሙ ወኢይሬእዩ፤ እዝን ቦሙ ወኢይሰምዑ አንፍ ቦሙ ወኢያጼንዉ፥ እድ ቦሙ ወኢይገሥሡ፥ እግር ቦሙ ወኢየሐውሩ ወኢይነብቡ በጐራዒቶሙ፥ ወአልቦ መንፈስ ውስተ አፉሆሙ፥ ከማሆሙ ለይኩኑ ኵሎሙ እለ ገብርዎሙ ወኵሎሙ እለ ይትዌከሉ ቦሙ።» «አፍ አላቸው አይናገሩምም፥ ዐይን አላቸው አያዩምም፥ ጆሮ አላቸው አይሰሙምም፥ እስትንፋስም በአፋቸው የለም፥ የሚሠሯቸው ሁሉ የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደነርሱ ይሁኑ።» እያለ በመዝሙር 115ና 135 ያስረዳናል። አንድ ሰው ደግሞ እውነት መስሎ ስለ ታየውና ሐሳቡንም በጽሑፍ ሲገልጽ «ሥዕል አፍ አውጥቶ ይናገራል፥ ዕንባ ላብና ደምም ይወጣዋል።» ብሎ ጽፏል፤ ይጽፋልም። መስከረም 10 ቀን የሚነበበው የዔዴንያ ተኣምረ ማርያም ተመልከት። እንዲሁም በተአምረ ማርያም ምዕራፍ 8፥31፤ 92፤ 111 አንብብ። እኔም እንደዚሁ <u>ብሉይና ሐዲስ ካልሆነ ሌላ የሕይወት መጽሐፍ ከኢየሱስ ክርስቶስም በቀር ሌላ ሊያድን የሚችል ከቶ የለም</u> ብዬ ሐሳቤን (እምነቴን) ብገልጽ እንደ ድፍረት ወይም እንደ ስሕተት የሚቆጠርብኝ መስሎ አይታየኝም፤ የሐዋ. ሥራ 4፥14፤ ራእ. 20፥13።

ወንድሞቼ ሆይ! እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያን ከሥጋዊና መንፈሳዊ ጉዳት ያደረሳት፥ <u>ከእምላክ ሕግ የተለየ፥ ተጀምሮ የማይፈጸም ምንኵስና የሚባል የሰው ሠራሽ ጽድቅ ነው</u>፤ ማቴ. 19፥1-12፤ 1ቆሮ. 11፥8-12። እግዚአብሔር አምላካችን አዳምን ከፈጠረው በኋላ፥ <u>«ኢኮነ ሠናየ ለእጓለ እመሕያው ይንበር ባሕቲቱ፥ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ» «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።»</u> ብሎ የምትረዳው ሔዋንን ፈጥሮ ሰጠውና ሙሉ ሆነ እንጂ፥ ብቻውንስ ጎደሎ እንደነበረ ጽሑፍ ይነግረናል፤ ዘፍ. 2፥18፤ 1ቆሮ. 11፥11።

ፍጡር የሆነ ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ ደቃቁ ትል፥ የሩካቤ ጠባይና የዘር ማድረጊያ ካለው፥ አምሳያው የሆነ ተደራጊ ባሕርይ እንደሚያስፈልገው ነገሩ ግልጽ ነው። ይህን ሥልጣንና ሥራ ሊያደርጉት የማይሆንላቸው ግን ማድረጊያ የሌላቸው ሕጽዋን (ጃንደረቦች) ብቻ ናቸው። የማይሳሳተው ቸሩ አምላካችን በጥበቡ ዐውቆ፥ በምሥጢሩ ተረቅቆ ለፈጠረው የሩካቤ ሕግ ማድረግያ ተሰጥቷቸው ሳሉ፥ በትምክሕታቸው እሳትን በጨርቅ የሚቋጥሩ መላእክተ ምድር ማለት እኛ ነን፥ ብለው የሚከበሩ መነኵሴዎች ባገራችን በየከተማው ሞልተዋልና፥ አምላክ የፈጠረውንና የወሰነውን ሕግ ሊያፈርሱና ሊሽሩ ሲሞክሩ፥ ሁሉም በጥበባቸው

ተሸረውና በተጸየፉት ዓለማዊ ጭቃ ወድቀው ተጥለቀልቀው መገኘ ታቸውን ስላየሁ በትዕቢታዊ ግብዝነታቸውና በስሕተታቸው አዝናለሁ። ሕግን ሊያጠፋ የሚሞክር ሁሉ ራሱ ይጠፋል፤ ማቴ. 19÷9-12፤ 23÷24-28፤ ሮሜ 2÷7-16፤ 1ቆሮ. 1÷19-31።

እነ መምሬና እነ አባቴ ግን ከዓለም ሙተናል÷ ዓለምም በኛ ዘንድ የሞተች ናት ገላ. 6÷14-17 ብለው ሲያበቁ÷ ለተጸየፉት ዓለም እንደገና ጌቶቹና ዋኖቹ ሁነው÷ አንድ ቀን ሳይሠሩ ከሠራተኛ ሁሉ በግድ እያስገበሩ÷ በጠጅና ጠላ÷ በአረቄና በጮማ÷ በሐርና በኩፍ ጫማ ተነክረው÷ ምዉታኖቹ ከሕያዋን በላይ ከብረው÷ ኀላፊውን የሥጋ ምቾት ይዘው÷ ለሰማያዊና ለሥጋዊ ዳኛ ሳይገዙ÷ መክሊታቸውን ሳያራቡና በሕግ ሕፃናት ወልደው ዘረ አዳምን ሳያበዙ በሥጋና በነፍስ ሸፍተው ከዓለም ዱር ገብተው እስከ ጊዜው ድረስ ተሸሽገው ይኖራሉ።

አንዳንዶቹ ደግሞ ዓለም መራራ ሆኖባቸው÷ ከምድራዊ ሹመትና ከሥጋዊ ጉዳይ ተለይተው በረሃ ገብተው÷ ሰማያዊቱን አገራቸውን እየናፈቁ÷ በጾምና በጸሎት÷ በስጊድና ንቃት÷ ኀይላቸውን አድክመው÷ ከመጠጥና መባልዕት ተከልክለው÷ ፈጣሪያቸውን ዘወትር በመጸለይ ብቻ የሚያገለግሉት ጥቂቶች ዓለምን የናቁ መናንያን እንደማይታጡ አምናለሁ። ቢገኙም ቅሉ እንደኔው አስተያየት «ዘደፈነ ወርቀ እግዚኡ» «የጌታውን ወርቅ የቀበረውን ባሪያ» መስለው ይታዩኛልና÷ እኔስ እነዚህንም ላመሰግናቸው አልደፍርም፤ ማለት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደተመለከትሁት አንዲት ነፍሱን ብቻ ያዳነ ሰው አልተመሰገነምና ነው፤ ማቴ. 25÷13-30፤ 1ቆሮ. 3÷9-15።

በፍትሐ ነገሥት በዐሥረኛው አንቀጸ መነኰሳት የደነገጉት ሕጋቸው ግን÷ ለምሳሌ በትግርኛ ቋንቋ «ፈላሲያ እንተ ሸፈተስ ንኸተማ ይኣቱ፤» «መነኩሴ ሲሸፍት ወደ ከተማ ይገባል፤» ተብሎ ይመሰላልና÷ (መነኰስ ዕድሜ ልኩን ከተማ ሳይገባ በረሃ እንዲኖር÷ ሥጋና መጠጥም ለዘወትር እንዳይቀምስ÷ የጠጉር ሰቅና የቁርበት ልብስ ካልሆነም የሐርና የጥጥ ጨርቅ እንዳይለብስ÷ ተባይ ሲነክሰው እንዳያክ÷ ከወገቡም ስንዝር ወፍራም የቁርበት መታጠቂያ እንዳይለይ÷ በመሬት ካልሆነ ምንጣፍ አንጥፎ ከመደብና ዐልጋ እንዳይተኛ÷ ውሎ ማታ በመጠን በጨው ብቻ በልቶ ውሃ እንዲጠጣ÷ ይህና ሌላውም የመሰለው ሁሉ ብዙ ነው። እንደ ሕጋቸው ሲሔዱና ሲያደርጉ ግን አንድ ቀን አይተናቸው አናውቅምና በድፍረት ለተናገርሁት ይቅርታ እለምናለሁ።

ስለዚህ ከመነኰሱ አይሠሩም፥ ካልሠሩም አይበሉምና ስለ ሥራ እንዲቈጠርላቸው በማለት ለምዉታን ጽድቅ፥ ለናንተም ክብር እንዲሆናችሁ፥ <u>ሳትሠሩ እኛን መግቡን</u> የሚል፥ አግራምቢጥ የሆነ በዓላትን ብቻ የሚቈጥር፥ አትሥሩ የሚል መጽሐፈ ማታለያ አዋልድ የተባለ (ልብ ወለድ)፥ መነኵሴዎች ሰበኩትና፥ ደብተሮችም ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ እያጋነኑ ውሸትን ጨምረው እየጻፉ ከሰከሱት፤ ኤር. 23፥30-31:: ርጎሩት ሕዝባችንም ባሕርዩ እጸድቅ ባይ ስለሆነ፥ ጎዶሎዎቹ ሙሉዎች (ጻድቃን) መስለው ስለታዩት፥ ጽፈው የሰጡትን ውሸት ተቀብሎ ገዝቶ፥ የነገሩትን ብቻ ሰምቶ እንዳዘዙት እነርሱን ፈርቶ በዓላትን እየቈጠረ፥ ሥጋውና ነፍሱ የሚጠቀሙበትን ነገር ሳያገኝ ሥራ ፈት ሆኖ በንዝህላል አጉል ይኖራል 1ነገ.18፥21 መል. ማር ለክሳድኪን ተመልከት::

የአዋልድ አውራቸው መጽሐፈ ሄኖክ የሚባለው ደግሞ፥ «መላእክት ወደ ምድር ወርደው ሴቶችን እየመረጡ አግብተው፥ እርስ በርስ የሚባልሉ፥ ቁመታቸው ሦስት ሺህ ክንድ የሆነ፥ ከነፋስ ጋር የሚሯሯጡ፥ አንድ ዝሆን ባንድ እጃቸው አንሥተው ከፀሐይ አቅርበው ጠብሰው የሚውጡ ወንዶች ልጆችን ወለዱ፤ ስመ ነገዳቸው አዛኤልና አዛዛኤል ይባሉ ነበር::» ይላል፤ ሄኖክ. 2፥1-16::

ሄኖክ ግን ከአዳም 7ኛው ትውልድ ነው፤ ሄኖክ፥ ማቱሳላ፥ ላሜህ፥ ኖኅ፥ በኖኅ ዘመን የማየ አይኅ ጥፋት ሲሆን፥ በአምላክ ትእዛዝ ከተፈጠረው ፍጥረቱ ሁሉ አንድ ሳይቀር በየዘመዱ ከኖኅ መርከብ ገብቶ ለዘር ቀርቶ ስለዳነ ሁሉም እስካሁን ድረስ አለ፤ ዘፍ. 6፥13-22፤ 7፥1-24፤ 8፥15-22::

የነአዛኤልና አዛዛኤል ዘር ግን በዓለም ላይ ስለሌለ፥ ፍጹም ውሸትና የባልቴቶች ተረት መሆኑ በዚሁ ዐጭር ማስረጃ ይታወቃል:: ለመጽሐፈ ሄኖክ ጓደኛውና ምስክሩ ግን ቁርዓን ወይም ማሕዱስ የሚባለው ዋናው የመሐመዳውያን መጽሐፍ «መላእከት ወርደው፥ ሚስቶች አግብተው፥ ሃሩትና ማሩት (አዛኤልና አዛዛኤል) የሚባሉ ረጃጅሞች ሰዎች ወለዱ ይላል::

መጽሐፈ ሄኖክን ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻዋን ለምስክርነት ተቀበለዋለች እንጂ፥ በዓለም ሁሉ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የብሉይ አዋልድ (አፖግራፊ) ስለሆኑ፥ ከ፳ወ፩ ፲፬ቱን ተሩፋት ብለው ለምስክርነት አይቀበሏቸውም (የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ቍጥር 219 ገጽ 98 ተመልከት)::

ውድ ወንድሜ ሆይ! የኢትዮጵያ ሊቅ፥ የጨለማው ፋና ጌታዬ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ «የሰሜን አገር ሰዎች መጽሐፈ

ሊቃውንት እርስ በርሳቸው እየተጣሉ ይካሰሳሉ፥ <u>የደቡብ አገር ሰዎች ደግሞ (አዋልድ) ከእውነተኞቹ ይልቅ ሐሰተኞች ይበዛሉ::»</u> (ወዳጄ ልቤ ምዕ. 18 ገጽ 82) ብለው አስተምረውናል:: ስለዚህ በፍትሐ ነገሥትም መጽሐፈ ሄኖክ አልተቈጠረምና ማመን አይገባም:: አባቶቻችን ፸፱፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት የተውልን ፹ወ፩ ብቻ ይበቁናል እንጂ፥ እውነትና ሐሰት፥ እምነትና ክሕደት ደበላልቀን ብናምን ዋጋችን ምናምንቴ መሆኑን እንገንዘብ፤ ኢዮ. 15÷31:: ለምስክርነት የማይበቁት አዋልድ የሚባሉት መጻሕፍት ሁሉ ግን፥ የሐሰትና የማታለያ ቃላት፥ መንፈስ የሌለው ሬሳ መሆናቸውን ከላይ የተጠቀሱትን ቃላት በመንፈስ መርምረህ፥ መዝነህ ከንቱና ውሸት መሆናቸውን አይተህ አምዘግዝገህ ጥለህ፥ በእሳት አቃጥለህ አጥፍተህ፥ ቃለ እግዚአብሔር የሆነውን ቅዱስ መጽሐፍን ብቻ አጽንተህ ያዝና ለነፍስህ ዕረፍት ታገኛለህ፤ ማቴ. 11÷28-30፤ የሐዋ. ሥራ 19÷13-20::

ወዳጆቼ ሆይ አዋልድ የሚባል ሁሉ ውሸት ነው ስላችሁ ግን፥ ዋናው መጽሐፈ መነኵሳት ደግሞ አርድዕት የሚባል ነው:: እርሱ ሲዋሽ ሰዶምና ገሞራን ሐዋርያት አቃጠሉት ይላል (አርድዕት ዘኀሙስ ተመልከት):: ከሎጥ እስከ ዘመነ ሐዋርያት ሁለት ሺህ ዓመት ነው:: ይህን ያህል ዘመን እየዋሸ ግን መነኰሴዎች እውነተኛ መጽሐፍ ብለው፥ ለጸሎታቸው ተቀብለው፥ ከመጻሕፍት ሁሉ በላይ አድርገው አምነው ይዘውት ይኖራሉ፤ ሮሜ 1÷21-25:: ከዚህ ሁሉ ጥፋትና ስሕተት ያደረሰን ግን በባዕድ ሕዝብ መመራት ነው:: «ወትሠይም ለከ መልአከ ዘኀረየ እግዚአብሔር አምላክከ እምውስተ አኀዊከ፥ ወኢትክል ሠዪመ ለከ ብእሴ ነኪረ እስመ ኢኮነ እኁከ::» «አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሣለህ፤ ከወንድሞችህ መካከል የሆነውን በአንተ ላይ ንጉሥ ታነግሣለህ:: ወንድምህ ያልሆነውን፥ ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም::» ዘዳ.17÷15:: «ለምንት ተሐውሪ በፍኖተ ግብጽ ከመ ትስተዪ ማየ ሕሙገ» «አሁንስ የሺሆርን ውሃ ትጠጪ ዘንድ በግብጽ ምን ጉዳይ አለሽ?» ኤር. 2÷18 የሚለውን የአምላክ ቃል መመልከት ነው:: «ምስር (ግብጽ) ሰው ነው፤ አምላክም አይደለም::» ኢሳ. 31÷1-3::

አባቶቻችን እግዚአብሔር ፈጥሮ፥ ኢትዮጵያ ባሳደገቻቸውና «አባታችሁ በሰማይ ያለው አንድ ብቻ ነውና ማንንም አባታችን ብላችሁ አትጥሩ» የሚለውን ቃልም በመዘንጋታቸው፥ ማቴ. 23÷8-11 አባቴ ማርቆስ፥ እናቴም እስክንድርያ ናት እያሉ በምስር ይመካሉ:: የምስር ረዳትነት ግን በከንቱ እንደሆነ መጽሐፍ

ይነግረናል፡፡ ሕዝባችንን ገደል ያገባው ማን መሆኑን አስተዋይ ልብ ያለው ሰው ሳያውቀው አይቀርም፤ ኢሳ. 16÷26፤ 20÷7-8፤ 23÷8፤ 29÷6-9፤ 30÷13፡፡

«ወእቤሎሙ ግድፉ ኵልክሙ ርኵሰክሙ እምቅድመ አዕይንቲክሙ÷ ወኢትርኰሱ በጣዖቶሙ ለግብጽ÷ አነ እግዚአብሔር አምላክክሙ፡፡ ወዐለዉኒ ወአበዩ ሰሚዖትየ ወኢገደፉ ርኵሰ እምአዕይንቲሆሙ፡፡ ወኢኀደጉ ጣዖቶሙ ለግብጽ÷ ወእቤ እሰውጥ መዓትየ በላዕሌሆሙ፡፡» «እኔም ከእናንተ እያንዳንዱ የዐይኑን ርኵሰት ይጣል፤ በግብጽም ጣዖታት አትርከሱ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ አልኋቸው፡፡ እነርሱ ግን ዐመፁብኝ፤ ይሰሙኝም ዘንድ አልወደዱም፤ ሁሉም እያንዳንዱ የዐይኑን ርኵሰት አልጣለም፤ የግብጽንም ጣዖታት አልተወም፤ በዚህም ጊዜ በግብጽ ምድር መካከል ቍጣዬን እፈጽምባቸው ዘንድ መዓቴን አፈስስባቸዋለሁ አልሁ፡፡» ሕዝ. 20÷7-8 ይላል፡፡

አንባቢ ሆይ! ለወደፊቱ ግን ለኢትዮጵያዊ ሕዝቤ እንደ ክህነተ አሮንና እንደ ጳውሎስ ትእዛዝ ዘፀ. 6÷23 አንዲት ሚስት ያለችው÷ የቤቱን ሥርዐትና የልጆችንም አቀጣጥ ያሳመረ በኑሮውም ፍጹም የሆነ ጳጳስ «ወአፍቅሩ ሐሊበ ነባቤ ዘአልቦቱ ቱስሕት» «ያልተቀላቀለ የቃልን ወተት ውደዱ» ተብሎ እንደታዘዘውና «ረዐዩ ዘሀሎ ኀቤክሙ መርኤቶ ለእግዚአብሔር እንዘ ተዐቅብዎሙ ወኢትቅንይዎሙ በኵርህ÷ አላ አርአያ ኩንዎሙ ለመርዔቱ፡፡» «በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን÷ . . . ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ፡፡» 1ጴጥ. 5÷1-4 እንደሚለው÷ ለሕዝቡ ድብላቂ የሌለውን የክርስቶስን የጸጋ ወንጌል ተግቶ የሚመግበውና የሚገሥጸው÷ ወደ ሕይወትም የሚመራውን እውነተኛውን እረኛ ባርያውን እንዲልክለት እግዚአብሔርን እየለመንሁ እመኘለታለሁ፤ 1ጢሞ. 3÷1-13፤ ቲቶ 1÷1-9፤ 1ጴጥ. 2÷1-3፡፡

መከሩ ሰፊ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ስለ ሆኑ÷ «እንደ ልቤ ጠባቆች እሰጣችኋለሁ፤ በዕውቀትና በማስተዋልም ይጠብቋችኋል፡፡» ኤር. 3÷11-16 የተባለውን ቃል ዛሬ እንዲፈጽምልን ሁላችን በአንድነት ቸሩ አምላካችንን እንለምነው፤ ማቴ.6÷8፤ 9÷36-38፡፡

ምዕራፍ 10

ሕያዋንና ምዉታን አይተዋወቁም

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! የአማላጅነት ነገር ሁለት ዐይነት መሆኑን ልገልጽልህ እወዳለሁ:: እርሱም ዐጸደ ሥጋና ዐጸደ ነፍስ ይባላል:: ስለዚህ አንዳንድ ዐውቆ አበዶች የሐሰትን ትምህርት የተከተሉ÷ ሳይሠሩ በዓላትን እየቈጠሩ ቦዘን (ሥራ ፈትተው) የሚውሉ÷ «እለ ከርሦሙ ያመልኩ ወአኮ ለእግዚእነ» የተባሉ ሮሜ.16÷18፤ በጻድቃንና ቅዱሳን ስም ለክብራቸው እያልን አመካኝተን እንብላ እንጠጣ የሚሉ÷ ሕዝባቸውን ስለ ጭብጥ ገብስና ቁራሽ እንጀራ እያታለሉ የሚኖሩ ኢሳ. 3÷12፤ ሕዝ. 13÷17-23፤ ጻድቃን ከሞቱ በኋላ ብንጠራቸው ይሰሙናል÷ ብንለምናቸው ይሰጡናል፤ ስለኛ ሲሉም ከአምላክ ምሕረት ይለምኑልናል ቢሉህ ውሸታቸውን ነውና አትመን:: ተፈራጆቹ እንኳንስ ከሞቱ በኋላ በፍርድ ቀን ሊያማልዱ÷ በሕይወተ ሥጋ ሳሉም ሕዝባቸውን ወደ ባቢሎን ከመማረክና በባዕድ ከመገዛትም ሊያድኑ ሊያማልዱም ብለው ቢጸልዩ እግዚብሔር ለኤርምያስ «አንተ ስለዚህ ክፉ ሕዝብ አትጸልይ፤ ስለርሳቸውም ጸሎትና ልመና መማለድም አታድርግ አትነዝንዘኝም፤ እኔ አልሰማህምና::» ይለዋል፤ ኤር. 7÷16-20፤ 14÷11-18:: ነቢዩ ኢሳይያስም «የመከረውንና ያሰበውን ያስተወው (ይከለክለው) ዘንድ የሚችል የለም::» ይላል፤ ኢሳ. 14÷27:: ረአዩ ኅቡአት ኤር. 23÷23-24:: ከሀሌ ኵሉ የሆነ አምላካችን ሰዎች በነገሩትና ባስታወሱት ሰምቶ አይፈርድምና÷ ባገራችን ያለው አማላጅነት የሚባል በሐሰት የተደነገገብንን (የተለመደ) የሰው ሥርዓት አትመን ያልኩህ ስለዚህ ነው:: ለሙሴም እንኳን ስለ ሕዝቡ ለራሱም ሊያማልድ ቢጸልይ «በዚህ ነገር ሁለተኛ እንዳትናገረኝ» ብሎ እግዚአብሔር ተቈጥቶታል፤ ዘዳ. 3÷23-26::

ከነገደ እስራኤል ስድስት መቶ ሺህ እግረኛ (ጦረኛ) በኃጢአቱ ምክንያት ከምድረ በዳ ላይ በመቅሠፍት ሙቶ ሲያልቅ÷ ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ በጽድቃቸው ምድረ ከነዓንን ብቻቸውን ወረሱ እንጂ÷ በአማላጅነታቸው አንድ ሰው እንኳ ይዘው እንዳልገቡ ልትረዳ ብትወድ የሚከተለውን ጥቅስ አንብብ፤ ዘፀ. 12÷37፤ ዘኍ. 14÷26-38፤ ዘዳ. 1÷35-39::

ትልቆቹ ሰዎች እኛ ጻድቃን የምንላቸው ሙሴና አሮንም እንኳን ሌሎችን አማልደው÷ ከሞት አትርፈው (አጽድቀው) ከነዓን (ገነት) ሊስያገቡ ይቅርና÷ በጉድለታቸውና በኃጢአታቸው ምክንያት

የገዛ ራሳቸው በድን በምድረ በዳ ወድቆ እንደቀረ መጻሕፍት ይነግሩናል፤ ዘኍ. 14÷1-32፤ 20÷1-29፤ ዘዳ. 34÷1-7፤ 32÷48-52::

አንባቢ ሆይ! ቅዱሳን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ አማላጅነታቸው ግን ዛሬ ቂሱ በኛ በሕዝቡ ላይ «ስረይ ኃጢአትየ ወኃጢአተ ሕዝብከ» ብሎ እንደሚጸልይልንና እንደሚያማልደን የመሰለው ነው እንጂ ሌላ ዐይነት ልመና አይምሰልህ፤ ኤር. 42÷1-6:: «ተአመኑ በበይናቲክሙ ኃጢአተክሙ፤ ወጸልዩ ላዕለ ቢጽክሙ ከመ ትሕየዉ ብዙኃ ትረድእ ጸሎቱ ለጻድቅ ትክል ወታሠልጥ::» «ከኃጢአታችሁና ሕመማችሁ እንድትፈወሱ አንዱ ላንዱ ይጸልይለት ወይም ይማልድለት» ይላል ሐዋርያው ያዕቆብ 5÷13-20:: ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ማማለድ (መለመን) ስለ ዓለም ሁሉ ዘወትር ጸሎት እንዲደረግ አዝዞታል፤ 1ጢሞ. 2÷1-8::

ጻድቃን የሞት እንቅልፍ ይዟቸዋልና ስንለምናቸው አይሰሙንም፤ ከሞት በኋላ በዐጸደ ነፍስ አይቻላቸውም እንጂ ሙሴና ኢዮብም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ግን አማልደዋል፤ ዘኍ. 16÷44-48፤ ዘፀ. 32÷9-14፤ ኢዮ. 42÷7-9:: አብርሃምም በሕይወተ ሥጋ ሳለ በበደሉ ከታዘዘበት መቅሠፍት ለአቢሜሌክ አማልዶ ጸልዮ ከሞት አድኖታል፤ ዘፍ. 20÷1-18:: በዐጸደ ነፍስ ሆኖ ከሞት በኋላ መማለድ ስለማይሆንለት ግን÷ ያንን ባዕል (ነዌን) እንኳን ከሲኦል አውጥቶ አማልዶ ወደ ገነት ሊያገባው ይቅርና ጉሮሮውን የሚያጠልበት አንድ ጠብታ ውሃም ሊሰጠው አልቻለም፤ ሉቃ. 16÷23-25::

አሁን ግን እኛ በዐጸደ ሥጋ ያለነው በዐጸደ ነፍስ ያለውን ነገር እንደማናውቀው÷ እንዲሁም በዐጸደ ነፍስ ያሉት ሟቾች ባዕዶቹ ይቅርና አባት እናቶቻችን እንኳ ለኛ በሥጋ ላለን ልጆቻቸውና ቤተሰቦቻው ምን እንደምንሆንና እንዴት እንዳለን ምንም አያውቁም፤ ኢዮ. 7÷9-10፤ 14÷21:: ስንጠራቸው እንደማይሰሙንና መልስ እንደማይሰጡን «ከፀሐይ በታች ፈንታ የላቸውም::» መክ. 9÷3-6:: እንኳን እኛ ስንጠራቸው ሊሰሙን ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ ሁሉም ተኝተዋልና ፈጣሪያቸውንም አያመሰግኑትም፤ ኢዮ. 14÷12:: «ዘአኮ ምዉታን ይሴብሑከ እግዚኦ» እንዳለ ሕዝቅያስ ንጉሥ ኢሳ. 38÷10-18::

ፈጽሞም ከአዳም ልጅ ሁሉ ጻድቅ ስለማይገኝ መጻሕፍት «ሁሉም ዐመፁ፤ አንድ መልካም የሚሠራ ጻድቅ እንኳ የለም::» ሮሜ 3÷10-18 «ወኮነ ኵልነ ርኩሳነ» «ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል» ኢሳ. 64÷6:: «ከርኩስ ንጽሕናን ሊያመጣ የሚችል

ማነው? አንድም የለም።» ኢዮ. 14፥4 ይላሉ። አትናቴዎስ በቅዳሴው ምዕ. 4 ቁ.1 «ሰብእሰ ጽቡረ ኃጢአት ውእቱ።» «ሰውስ በኀጢአት ጭቃ ተለውሶ ያለ ነው፤» ብሏል። ያዕቆብ ዘሥሩግም ም.2 ቁ.5 «አልቦ ዘተረክበ ዘኢኀደጎ ለሥርዐትከ እምቀዳሚ አዳም እስከ ይእዜ።» «ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ዘመን ድረስ ሥርዐትህን ያላፈረሰ (ሳያፈርስ) የተገኘ የለም፤» ይላልና፥ ይህ አልቦ ማለቱ ፈጽሞ ከቶና አካቶ የሌለ የማይገኝ በመሆኑ እንደሆነ አስተውል፤ ኢሳ. 41፥26-28።

ወንድሜና ወዳጄ ሆይ! መጻሕፍት ግን «አሁንም ብትበሉ ብትጠጡ ወይስ ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉንም ስለ እግዚአብሔር ክብር አድርጉት።» ይላሉ እንጂ ስለ ፍጡራን ክብር አድርጉት አይሉም፤ 1ቆሮ. 10፥31። ከጳውሎስ የበለጠ እስከ ሦስተኛ ሰማይ የተመሰጠ ጻድቅ ወዴት ይገኝ ይሆን? ምንም አይገኝም። ለጳውሎስና በርናባስ ክብርና ዝክር (መሥዋዕት) እንዲሆናቸው ብለው ድግስ ላቀረቡላቸው ሰዎች በቁጣ ቃል እንዲህ አሏቸው «ወሰሚያሙ ሐዋርያት ወይቤልዎሙ አንትሙ ሰብእ ምንትኑ ዝ ነገር። አኮኑ ከማክሙ ሰብእ ንሕነ ዘንመውት፤ ወንሜህረክሙ ከመ ትኅድጉ ዘንተ ከንቶ፤ ወትትመየጡ ኀበ እግዚአብሔር ሕያው ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ወባሕረ ወኵሎ ዘውስቴቶሙ።» ለኛ ለአምላክ ባሮች ክብር አይገባንምና ይህን ከንቱ የሆነ ሥራችሁን (ፍጡራንን ማምለክ) ተዉት። ሰዎች እንደማይጠቅሙም «ኢዘተከለ ወኢዘሰቀየ አልቦ ዘበቍዐ ዘእንበለ ዳእሙ ዘአልሀቀ ሀቡ ዕበየ ለአምላክነ» እያሉ አስተማሩ እንጂ፥ ለኛ ለሐዋርያት ለጻድቃን ክብር፥ ለናንተም ጽድቅ፥ እንዲቈጠርላችሁ የኛን ስም አንሥታችሁ ብሉ ጠጡ ብለው አላስተማሩም፤ የሐዋ. ሥራ 14፥13-18፤ 1ቆሮ. 3፥6-10። <u>እነርሱስ «አልቦ ካልእ ስም ዘየሐዩ ሰሰብእ በታሕተ ሰማይ ዘእንበለ ስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ናዝራዊ</u> የሐዋ. ሥራ 4፥10-18 ብለው ነው ያስተማሩት።

ሰዎች ከሞቱ በኋላ ሰዎችን እንደማይረዱና እንደማያማልዱ አምላክ «ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም።» ብሎ በቍጣ ፈርዶ ካሰናበተም በኋላ እንደማይለመን <u>«እበቀላለሁ ሰውም አይለምነኝም።»</u> ይላል፤ ኢሳ. 47፥3። ደግሞም በነቢዩ በሕዝቅኤል አፍ «ወነበበኒ እግዚአብሔር ወይቤለኒ ኦ ወልደ እጓለ እመሕያው ምድር እመ አበሰት ሊተ፥ ወስሕተት ወኔገየት አነሥእ እዴየ ላዕሌሃ፥ ወአጠፍእ እምኔሃ ሰብአ ወእንስሳ ወለእመ ሀለዉ እሉ ፫ እደው ማእከላ ኖኅ፥ ወኢዮብ፥ ወዳንኤል ሕያው አነ ይቤ እግዚአብሔር ከመ ኢያድኅኑ ደቂቆሙ፥ ወአዋልዲሆሙ ዘእንበለ ለባሕቲቶሙ ያድኅኑ ነፍሶሙ በጽድቆሙ።» «የእግዚአብሔር ቃል

ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ የሰው ልጅ ሆይ! ምድር በማመፅ በእኔ ላይ ኃጢአት ስትሠራ÷ እኔም እጄን ስዘረጋባት÷ የእንጀራዋንም በትር ስሰብር÷ ራብን ስሰድባት÷ ሰውንና እንስሳውንም ከእርሷ ሳጠፋ÷ እነዚህ ሦስት ሰዎች ኖኅና ዳንኤል÷ ኢዮብም ቢኖሩባት በጽድቃቸው የገዛ ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ:: . . . እኔ ሕያው ነኝና እነርሱ ብቻቸውን ይድናሉ እንጂ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን አያድኑም::» ይላል፤ ሕዝ. 14÷12-20:: «አልቦ አሜሃ ቤዛ ነፍስ÷ ወኢተውላጠ ብእሲ በብእሲት አብ በወልዱ ወእም በወለታ አላ ፩ ፩ ይነሥእ ፍዳ ምግባሩ::» «ያን ጊዜ የነፍስ ቤዛ የለም፤ ባል በሚስቱ÷ አባት በወንድ ልጁ÷ እናትም በሴት ልጇ መለወጥም ቢሆን የለም፤ ሁሉም እያንዳንዱ የሥራውን ዋጋ ይቀበላል እንጂ::» እንዳለ አትናቴዎስ. 3÷28-31:: ዳዊት ልበ አምላክም «ኢትትአመኑ በመላእክት ወኢበእጓለ እመሕያው እለ ኢይክሉ አድኅኖ÷ ትወጽእ ነፍሶሙ ወይገብእ ውስተ መሬቶሙ፤ ውእተ አሚረ ይጠፍእ ኵሉ ምክሮሙ::» «ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና በአለቆች አትታመኑ፤ ነፍሱ ትወጣለች ወደ መሬቱም ይመለሳል፤ ያን ጊዜ ምክሩ ሁሉ ይጠፋል::» ይላል፤ መዝ. 146÷1-4:: ደግሞም «መኑ ሰብእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት ወመኑ ዘያድኅና ለነፍሱ እምእደ ሲኦል» «ሕያው ሆኖ የሚኖር ሞትንስ የማያይ ማነው? ነፍሱንስ ከሲኦል እጅ የሚያድን ማነው?» ይላል፤ መዝ. 89÷48:: ስለዚህ ሰዎች ነፍሳቸውን ከሲኦል እጅ የማያድኑ ከሆነ÷ የሌሎችን ነፍሳት እንዴት በመሰለ ዘዴ ሊያድኑ ይሆን? ሐሰት ነው ምንም ቢሆን ፍጡራን ፍጡራንን ከቶ ሊያድኗቸው አይችሉም፤ ራእ. 5÷1-5:: አንድ ሸክላ ቢሰበር ያ ሠሪው ካልሆነ÷ እንደርሱ ያሉ ብዙ ሸክላዎች ተሰብስበው መልሰው ሊሠሩት ከቶ አይቻላቸውም፤ ሮሜ 9÷18-23:: «ወእምዝ ሶበ ርእየ ከመ ኢበቊዐ ለአድኅኖተ ዓለም ደመ ነቢያት ቅዱሳን እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ፤ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኅነ ወመቤዝወ ከመ ይባልሕ ወይቤዙ ወያብእ ቅድሜሁ ተዝካረ ሕያዋን ወምዉታን::» «ከዚህም በኋላ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ÷ አዳኝ መድኀኒት የሚሆን ልጁን ሰደደልን፤ ፈጽሞ ያድን ዘንድ÷ በፊቱም የሕያዋንንና የሙታንን መታሰቢያ ያገባ ዘንድ::» እንዳለ ኤጲፋንዮስ 2÷28:: የቅዱሳን ነቢያት የፈሰሰው ደማቸው ዓለምን ለማዳን እንደማይረባና እንደማይጠቅም ስላየ አንድ ልጁን ልኮ በልጁ ደም ብቻ አዳነን፤ 1ጴጥ. 1÷18-20::

ወንድሜ ሆይ! ፍጡርን ፍጡር ሊያድን እንደማይችል፥ አንድ ጠብታ ደሙን ወይም ላቡን ለሰው መድኃኒት እንዲሆን ብሎ በምድር ያፈሰሰ አንድ ጻድቅም እንደማይገኝ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትና ኤጲፋንዮስም የነገሩህን ቃላት አጥብቀህ ችላ ሳትል መርምር:: ስለዚህ ጻድቁ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ «ዘበልዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም»:: ያለውን ሕያው ቃል በቂ አማላጅና እውነተኛ መድኃኒት መሆኑን በልብህ ብታምን ትድናለህ:: ይህ በሀገራችን ያለ ከንቱ የሆነ (በልማድ ለማያድን መድኃኒት እየተባለ) ዋና ሁኖ የሚኖር የምዉታን ምዉት ተስፋ አይኑርብህ፤ ኢዮ. 15÷31፤ 1ጴጥ. 1÷3::

ፍጡራን ከሞቱ በኋላ ስለ ሕያዋን ጥቅም ወይም ጉዳት ማሰብና መሥራት፥ መገናኘትና መረዳዳትም እንደማይችሉ ኤልያስ ነቢይ ሲያስረዳ «ስአለኒ ዘትፈቅድ እግበር ለከ ዘእንበለ እዕርግ እምኀቤከ::» 2ነገ. 2÷9-14:: ካንተ ከተለየሁ ልሰጥህ ወይም ላደርግልህ ከቶ አይቻለኝምና አሁን ሳንለያይ የሚያስፈልግህን ንገረኝ ማለቱ ሰዎች ካረፉና ካንቀላፉ ምንም ምን እንደማይሠሩ ያሳያል:: ኢዮ. 3÷11-18፤ 14፡1-22:: ከዚሁ ቃል ጋራ የሚከተለውን የሊበን ወልታው ጎጋሚ ግጥም ብንጠቅሰው ይስማማል:: ንግሥት ዘውዲቱ በሞት ደጃዝማች ገብረ ሥላሴን በስምንት ወር ቀድመው ስለ ነበር::

እንጉርጉሮ

ንግሥት ዘውዲቱ አጀቡ ቢያንሳቸው
ጌታዬን አስጠሩት በስምንት ወራቸው::
ምን ይረባኝ ብለው በሰማይ አሽከር
መገናኘት የለ አይረዳ ምክር::

እያለ እውነት የሆነ ብዙ ብዙ ቃል በጋዜጣ ታትሞ አንብበን ነበር::

ነቢዩ ኤርምያስ «ርጉመ ለይኩን ኵሉ ዘይትአመን በፍጡር (በእጓለ እምሕያው)፥ ወያሰምክ ቦቱ መዝራዕቶ ወእም እግዚአብሔር ይርኅቅ ልቡ፥ ወይከውን ከመ ኲሄላ በውስተ ገዳም፥ ወኢይሬኢ ሠናየ ወይነብር ወስተ ምድረ ጼው ወበድው::» «በሰው የሚታመን፥ ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ፥ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው፤ በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል፤ መልካምም በመጣ ጊዜ አያይም፤ ሰውም በሌለበት፥ ጨው ባለበት ምድረ በዳ በደረቅ ስፍራ ይቀመጣል::» ኤር. 17÷5-10:: ይላልና ጽድቅ ወይም ማዳን አማላጅነት በኢየሱስ ስም ካልሆነ ከቶ በፍጡራን ስም አይገኝም:: ፍጡር ሞያተኛ ስለ

ሆነ ነፍሱን ቤዛ አባግዕ አሳልፎ ሊሰጥ አይችልም። እንደ ጴጥሮስ ሊክድ ወይም እንደ ዮሐንስ ነጠላውን ጥሎ ሊሸሽ ካልሆነ ከቶ የሚጠቅመው ነገር የለውም፤ ማቴ. 26÷56-75፤ ማር. 14÷50-72፤ ዮሐ. 10÷12፤ 1ቆሮ. 3÷6።

ጠቢቡ ሰሎሞን «ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉ ምዉታን ግን አንዳች ነገር አያውቁም።» ይላል፤ መክ. 9÷3-6። ኢሳይያስም «አብርሃም ኢያእመረነ ወእስራኤልኒ ኢጠየቀነ።» «አብርሃም አላወቀንም እስራኤልም አልተረዳንም (አልተገነዘበንም)» (እንደ ግእዙ) ኢሳ. 63÷16። «በውኑ ስለ ሕያዋን ጥቅም ብለው ምዉታንን ይጠይቃሉን?» ብሏል፤ ኢሳ. 8÷19።

መጻሕፍት እንደዚህ አድርገው ተስማምተው ምዉታን ተኝተዋልና እኛ ስንለምናቸው አይሰሙም÷ አያውቁም÷ አያማልዱም÷ ከቶውንም ያሉበት ቦታ የመርሳት ምድር ይባላል ይላሉ፤ ኢዮ. 3÷11-22፤ 10÷18-22፤ መዝ. 88÷10-12።

ስለዚህ እንደ መጻሕፍቱ ቃል ሙቶ የተነሣው ሕያው መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው። ስንለምነው የሚሰማንና የሚያማልደን እንጂ ወደማይሰሙንና ወደማያውቁን ምዉታን ተስፋ ብናደርግ ግን ተስፋችን ሁሉ ዋጋ የሌለው ዜሮ አልቦ ሆኖ ይቀራል። ፍጡራን ከሞቱ በኋላ ለሕያዋን እንደማይረዱና እንደማይጠቅሙም ሳኦል ንጉሠ እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ጭፍራ ተከቦና ተጨንቆ ሳለ÷ በሟርተኞችና ጠንቋዮች መንፈስ ምዉት ሳሙኤልን አስቀስቅሶ «ጠላቶች ሊወጉኝ ተነሥተውብኛልና የምሠራውን ታስታውቀኝና ትረዳኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ቢለው÷ እግዚአብሔር ጠላትህ ከሆነ ስለምን እኔን ትጠይቀኛለህ? እነሆ እግዚአብሔር ለጠላቶችህ አሳልፎ ይሰጥሃልና÷ አንተና ልጆችህም ትሰየፋላችሁ።» ብሎ በተናገረው ቃል እንረዳዋለን፤ 1ሳሙ. 28÷1-19፤ 31÷1-13።

ኢዮብ «ሰው በምናምን ነገር አይመን፤ እርሱ ይስታል ዋጋውም ምናምንነት ይሆናልና።» እያለ ይመክራል፤ ኢዮ. 15÷31፤ ኢሳ. 59÷4-6፤ ዮና. 2÷9።

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! እንደ አገራችን ባህልና ልማድ ግን÷ እምነታችን ተስፋችን መድኃኒታችን የሚሆኑ የማይሰሙ ምዉታን ጻድቃን ሰማዕታት ቅዱሳን እያልን÷ እየሸምን÷ እርዱን÷ አማልዱን÷ ለምኑልን÷ ንገሩልን÷ የሚሉት የሰው ሥርዓትና የስሕተት መንገድ አለና÷ በዚሁ ሰፊ የማታለል ጎዳና እንዳትሄድ ተጠንቀቅ፤ ማቴ. 7÷13-19፤ ቈላ.2÷8። አሁን ግን ይህን ፍሬ

የሌለውና ጥቅም የማይገኝበትን የሰው ሕግ ትተህ ጳውሎስ «ወኀደግነ ዘቀዲሙ ትምህርተነ ከመ ንትቀነይ በሕገ መንፈስ ወአኮ በብሉይ መጽሐፍ::» «አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለሞትን ÷ ከሕግ ተፈትተናል÷ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም::» ሮሜ 7÷6:: «ዘበእንቲአሁ ገደፍኩ ኵሎ÷ ወረሰይክዎ ከመ እዳው ከመ እርብሖ ለክርስቶስ» «አዎን÷ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ ዕውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለእርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፤» ፊልጵ. 3÷8-15:: ያለውን ቃል ተመልክተህ አሮጌውን ልማድ (ውሸቱን) በእውነተኛው ቃለ እግዚአብሔር ይመትር ነደ እሳት በተባለው ሰይፉ ቈርጠህ ከነ ሥሩ ነቅለህ ጣለው፤ ማቴ. 10÷32-39፤ 1ቆሮ. 13÷11-13፤ ዕብ. 4÷12:: እውነተኛው አማላጅ÷ ሲነግሩት የማይረሳ÷ ለምነውት የማይነሣ÷ ቊስለ ሕሊናህን ለመዳሰስ÷ የዓለምን ኃጢአት ለመደምሰስ ሥልጣን ያለው አንድ ብቻውን ሕያው መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን አምነህ በክቡር ደሙ ብቻ ታጥበህ ዳንና ጽደቅ እንጂ ሌላ ሊያድን÷ ሊያማልድ÷ ሊያጸድቅ የሚችል ስም ከሰማይ በታች ለፍጡር (ለምዉት) እንዳልተሰጠ እንደሌለም ሐዋርያትን ጠይቅ:: ሐዋርያት ልኡካኑ በእርሱ እጅ የተካኑ ያሉህን ስማ፤ እመን፤ ታዘዝ፤ አድርግም ትድናለህ፤ የሐዋ. ሥራ 4÷12፤ 16÷27-34፤ ዮሐ. 20÷21-23::

ወንድሜ ሆይ፤ <u>ነቢያትና ሐዋርያት የኢየሱስ ስም ካልሆነ በቀር ሌላ ሊያድን የሚችል ስም ከሰማይ በታች ከቶ የለም አይገኝም፤</u> ብለው እየነገሩህ÷ አንተ ግን ሌላ የማይጠቅም የማያድን ስም በራስህ ፈጥረህ መጥራትህ÷ ማመንህም አለማወቅህ ወይም እልኸህ ነውና÷ ፈጣሪውን ተወዳድሮ÷ እያወቀ ዐይነ ልቡናውን አሳውሮ÷ በእልኹ ከባሕር ሰጥሞ÷ ሥጋና ነፍሱን አጥፍቶ ከንቱ ሆኖ የቀረውን ፈሪያንን እንዳትመስል÷ አሁን ዛሬ ድምጹን በሰማህበት ቀን እሺ ብለህ የየሱስን ስምና ቃል አምነህ÷ ከአምላክህ ጋር በኢየሱስ ስም ብቻ ታረቅ፤ ዘፀ. 14÷1-31፤ 2ቆሮ. 5÷17-21::

ወዳጆቼ ሆይ! ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ከመልበሱ በፊትም ቢሆን÷ አዳማውያንን ተልኮ ለመርዳት የተመደበው እርሱ ብቻ ስለሆነ በሚከተለው ስሙ እንረዳዋለን:: «መልአከ ገጹ÷ እደ መዝራዕቱ÷ ኃይሉ ወጥበቡ÷ መልአከ ምክሩ የዓለም ካህን÷ መልአከ ኪዳኑ÷ ጻድቅ ባርያው» እያሉ መጻሕፍት ይመሰክሩለታል፤ ዘፀ. 23÷20፤ 33÷11-23፤ ኢሳ. 59÷16፤ 62÷1-10፤ ዘካ. 6÷9-15፤ ምሳ. 8÷1-36::

አባታችን ቅዱስ ያሬድም «ሚካኤል ብሂል መኑ ከመ እግዚአብሔር÷ ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአብሔር ። የሚለው ለክርስቶስ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። ከምስር ባርነት መሪ ሆኖ ያወጣቸው እርሱ ብቻ ነው። በባቢሎን ተማርከው ሲኖሩም «አቤቱ ይቅር አትላቸውምን?» ብሎ አማልዶ ያወጣቸው እርሱ ነው። ስለዚህ ጥቅሶቹን አስተውለህ መርምርና አማላጅነት የክርስቶስ የብቻው ሥራ መሆኑን የተረዳህ ሁን፤ ዘካ. 1÷7-16፤ ዘፍ. 16÷7-11፤ ዘፀ. 23÷20፤ 32÷30-35፤ መሳ. 2÷1-4፤ ኢዮ. 23÷23፤ ኢሳ. 48÷16-19፤ ዘፍ. 21÷17-20፤ 22÷11።

ቅን የሆነውን የአምላክ ትእዛዝ ትተህ ጠማማውን የሰው ሥርዐትና አሮጌ ልማድ መጠበቅ ግን መድረሻው (ፍጻሜው) ጸጸትና ጥፋት ብቻ ነው፤ ማቴ. 7÷13፤ ቈላ. 2÷20-23። ይልቁንስ ጳውሎስ ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን <u>«ወባሕቱ አንተሙሰ እምሰማይ ለእመ መሀረክሙ ካልአ እምዘመሀርናክሙ ንሕነ ውጉዘ ለይኩን።»</u> «ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ÷ ከሰብክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ÷ የተረገመ ይሁን።» ብሎ የሐዋርያት ካልሆነ በቀር ሌላ ሕግና መጽሐፍ÷ ትምህርትና ሃይማኖት እንኳንና ሰዎች መላእክትም ቢሆኑ÷ ቢናገሩና ቢያስተምሩ እንዳናምናቸው እንዳንቀበላቸው አውግዞናል። ገላ.1÷6-10። ስለዚህ ያባታችንን የጳውሎስን ግዝት ሰምተን ትምህርቱን÷ ትእዛዙን÷ ሃይማኖቱን÷ መጻሕፍቱን አይተንና መርምረን «ኢታምጽኡ ካልአ ነኪረ ትምህርተ» «ልዩ ልዩ ዐይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤» ብሎ ያዘዘንን የኑዛዜ ቃሉን ማጽናት ይገባናል። ዕብ.13÷9፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ምዉታን በመካነ ዕረፍት ተኝተዋልና÷ ለፍርድ ቀን እስቲቀሰቀሱ ድረስ በምድር ያለውን አንዳች ነገር ከቶ አያውቁም፤ አይሠሩም፤ አይሰሙም እያሉ ያስረዱናል፤ ኢዮ. 3÷11-19፤ 7÷6-10፤ 14÷7-22፤ መዝ. 39÷4-13፤ 88÷10-12፤ 103÷14-16፤ 115÷17፤ መክ. 9÷5-6፤10፤ ኢሳ. 38÷9-20፤ ዳን. 12÷1-13፤ ዮሐ. 5÷25-29፤ 1ተሰ. 4÷13-18፤ ጥቅሶቹን በውል መርምራቸው።

የሀገሬ መሪዎች ግን አንድ ዋንጫ ቅራሪ ለመጠጣት ሲሉ በስመ ጻድቅን ብቻ ጠቅሰው÷ «ምዉታኖቹ ጻድቃን በዐጸደ ነፍስ ሁነው ለናንተ ለሕያዋን ጸሎት ያደርጉላችኋል።» እያሉ ያስተምራሉ። ቅዱሳን በሰማይ ወይም በሲኦል ሁነው ጸሎት ያደርጋሉ ካሉዋቸው ግን÷ ከሦስቱ ትእዛዝ አንዱን ብቻ መርጠው ቢይዙ ዐመፅ መስሎ ይታያልና ጾም ምጽዋትም ያዘወትሩ ይሆናል ለማለት አያዳግትም፤ ማቴ. 6÷1-18።

ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ በመንፈስ ራእዩ አይቶ የጻፈልን ግን «በዙፋን ዙሪያ የሚኖሩት ጻድቃን ሁላቸው ዘወትር በደስታ ሃሌ ሉያ እያሉ ፈጣሪያቸውን ብቻ ሲያመሰግኑ አየኋቸው።» ይለናል እንጂ÷ በምድር ስለሚኖሩ ኃጥአን ወንድሞቻቸው በሐዘን እየተሠቃዩ ጸሎት ሲያደርጉላቸው አየሁ ብሎ ከቶ አልጻፈልንም፤ ራእ. 5÷6-14፤ 7÷9-17፤ 15÷2-4፤ 19÷1-9 ።

ውድ ወዳጄ ሆይ! የምዉታንን ዕውቀትና ተስፋ ትተህ ሕያው ዘኢይመውት ኢየሱስ መድኃኔ ዓለምን በወንጌሉ ተወዳጀው። እርሱ በጸጋው ይርዳህ። አሜን!

ምዕራፍ 11

ስለ ቃል ኪዳን

ወዳጄ አንባቢ ሆይ! ቅድም እንደ ነገርኩህ አሁንም «እለ ከርሦሙ ያመልኩ» «ሆዳቸውን የሚያመልኩ» እና «ወእለ አልባሲሆሙ ያነውኑ» «ቀሚሳቸውን የሚያስረዝሙ» ፊልጵ. 3÷17-21፤ ማቴ. 23÷5-7:: ለሥጋዊ ጥቅማቸው ሲሉ የደነገጉትን÷ የጻድቃንና የቅዱሳንን ስም አንሥታችሁ ከፍጡራን አንዱን መርጣችሁ አምናችሁ÷ በፍርድ ቀን ዋስና ጠበቃ እንዲሆኗችሁ ድግስ ደግሳችሁ በስመ እገሌ እያላችሁ እኛን አብሉን አጠጡንና በሕፍነ ማይ ገነት ትገባላችሁ እያሉ በ፹ወ፩ መጻሕፍት ውስጥ ነቢያትና ሐዋርያት ያልተናገሩትን ይሰብካሉ:: እግዚአብሔር ጻድቃንን ጸድቀው እንዲያጸድቋችሁ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል:: ስለዚህ በነርሱ ስም አምናችሁ ለኛ ካበላችሁንና ካጠጣችሁን ሳትኮነኑ እንበለ ንስሐ ገነት ትገባላችሁ፤ (ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተመልከት) ብለው በሐሰት ያስተምራሉ:: መንግሥተ ሰማያት በኛ ካልሆነ በሌላ አይገባም እያሉ እየተመኩ÷ ሕዝባቸውን በከንቱ እያታለሉ ይበሉታልና እንደዚህ የመሰለ ከንቱ የሆነ የውሸት ፍጻሜ ሲኦል መሆኑ ካሁን በፊት እንደተነገረ እነዚህን ቃላት አንብበህ ትረዳዋለህ፤ ሕዝ. 13÷1-23፤ 34÷1-31፤ ሚክ. 2÷8-11፤ ማር. 12÷40:: እግዚአብሔር ግን ለሁሉ ቃል ኪዳን አትበሉ ይላል፤ ኢሳ. 8÷12፤ 30÷1::

አንድ የሸክላ ዕቃ ቢሰበር ያ ሠሪው ብቻ በዕውቀቱ እንደገና ካልሠራው በቀር እንደርሱ ያሉ ብዙ ሸክላዎች ተሰብስበው ሊሠሩት አይቻላቸውም:: ስለዚህ ትልቁን የአድኅኖን (የማዳንን) ነገር ፍጡራን የሆኑ መላእክትን ወይም ቅዱሳንን ልኮ መፈጸም ቢቻል ኖሮ አምላክ ከሰማያዊ ዙፋኑ መውረድ ለምን አስፈለገው? ሰው ሆኖ ወደ ሞትና የመከራ ውርደት የደረሰውስ ተሳስቶ ይሆን? እንዲያውም እንኳንስ ኃጢአተኞቹ የአዳም ልጆች ይቅሩና ንጹሓን መላእክትም ቢሆኑ ስንፍናና ጌጋይ (በደል) ይገኝባቸዋል:: ስለዚህ ትልቁ የአድኅኖ ነገር በባለቤቱ በራሱ አማካይነት ካልሆነ በፍጡራን በኩል ስለማይፈጸም÷ እነርሱን ለድኅነተ ዓለም አላካቸውም፤ ኢዮ. 4÷17-21፤ 15÷14-16፤ ኢሳ. 63÷1-9:: በሐሰት ነው እንጂ «በእናንተ ያመነ ይዳን» ብሎም ቃል ኪዳን አልገባላቸውም፤ ኤር. 23÷30-32 ::

ወንድሜ ሆይ! በወንጌል «ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻደቅ ዐስበ ጻድቅ ይነሥእ፤» «ጻድቁን በጻድቅ ስም የተቀበለ የጻድቁን

ዋጋ ይወስዳል፤» የተባለው ቃልም÷ ጻድቅ በሆነው በስመ ክርስቶስ ተጠልተው÷ በመታሠርና በመገረፍ ተንገላተው÷ እንደ ሐዋርያት ቤትና ንብረትን ትተው÷ ከሀገር ሀገር እየዞሩ «ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ በጸጋ» «በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ስጡ፤» ብሎ እንዳዘዛቸው ወንጌልን ያለ ዋጋ ለሁሉ የሚያስተምሩትን÷ እንኳን ጉልት ቀላድ ሪም÷ የመሬት ሲሶ አንድ ሳንቲም ቢሆንም በኪሳቸው የማይቋጥሩትን÷ ዓለመኞች (ጌቶች) ሆነው ሐርና ኩፍ ጫማ ለብሰው በዘመነ አመጣሽ መኪና የማይንሸራሸሩትን÷ አገር እየገዙ ድሃን የማያስሩትን÷ የፍየል ቆዳና የበግ ደበሎ ለብሰው በዱርና በዋሻ የሚሰፍሩትን÷ በዕብነ በረድ የተሠራ ፎቅ ቀርቶ ራሳቸውን የሚያስጠጉበት የወፍ ጉጆ የሚያህል ቤት (ማደሪያ) በዚህ ዓለም የማይሠሩትን÷ አገራችን የምትመጣው ዓለም ናት እያሉ የሚፎክሩትን÷ ውሸትና ዲያብሎስ በነገሡበት ሀገር ያለውን የጨለማ እሾኽ (አምልኮ ጣዖትን) በሰይፈ ቃሉ ቈርጠው እየጣሉ የወንጌሉን ብርሃን የሚያበሩትን÷ ነግደ ኮንኩ ወተወከፍክሙኒ (እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል) ብለው የሚያስተምሩትን÷ ዛሬ ያሉትንና የሚገኙ ሕያዋን አገልጋዮችን ተወከፉ (ተቀበሉ)÷ ለድሆች ወንድሞቼ አጠጡ፤ አልብሱ፤ አብሉ አለ እንጂ÷ እርስ በርሳችሁ ተሰብስባችሁ የሚያሰክር አልኮልና መርዝ እየጠጣችሁ÷ የማይሰሙ ምውታን (የሬሶችን) ስም ብታነሡ ትጸድቃላችሁ አይልም፤ ማቴ. 10÷1-41፤ ሉቃ. 9÷57-82፤ ፊልጵ. 3÷20፤ ዕብ. 11÷1-40::

የሀገሬ ሕዝብ ከነመሪዎች እውነተኛውን የክርስቶስን ቃለ ወንጌል ትቶ ድርሳንና ተአምር÷ ገድልና መልክዕ የሚባሉ የሐሰት መጻሕፍትን በራሱ ፈጥሮ÷ ወንጌል ጸባብ አንቀጽ (ጠባብ በር) ናት «ኢትስርቅ÷ ኢትቅትል÷ ኢትዘሙ÷ ኢትኩን ስምዐ በሐሰት÷ አፍቅሩ ጸላእተክሙ÷ ሠናየ ግበሩ ለኵሉ» «አትስረቅ÷ አትግደል÷ አታመንዝር÷ በሐሰት አትመስክር÷ ጠላቶቻችሁን ውደዱ÷ ለሁሉ መልካምን አድርጉ» እያለች የሰውን ሕሊና እያሳቀቀች ታስቸግራለችና÷ ለሥጋዊ ጠባይ ደስ የሚያሰኝና «ሰራቂ÷ ሐሳዊ÷ ዘማዊ÷ በላዔ ሰብእ÷ ወኵሎሙ ዓላውያነ ሕግ በሕፍነ ማይ ይበውኡ ገነተ ትፍሥሕት::» «ሌባ÷ ሐሰተኛ÷ አመንዝራ÷ ሰው በላውና ሕግ ተላላፊዎች ሁሉ በእፍኝ ውሃ ወደ ደስታ ገነት ይገባሉ::» የሚል የሐሰት ትምህርት በማስተማር÷ 78 ሰው የሚያህል አርደውና ቀቅለው ቢበሉም÷ እግዚአብሔር ከወዳጆቹ ከፍጡራን ጋር ቃል ኪዳን ገብቷልና÷ «ገነት ለኃጥአን ክፍት ነው (ዝግ ነው፤ አትበድሉ በማለት ፈንታ) አትሰቀቁ፤ ብቻ ጠላ

ጥመቁ፤ ዛሬ እንብላ እንጠጣ፤ ነገ እንሞታለንና ዛሬ ደስታና ስካርን እናብዛ፤» እያለ ራሱን በማታለልና በዐውቆ አበድነት አጉል በስሕተት ይኖራል:: ይህን የማታለል አሮጌ ልማድ ግን ጌታችን በወንጌለ ማቴዎስ 5ኛ ምዕራፍ ከተናገረው ቃላት ጋር እንደምን ሊስማማ ይችላል? 2ቆሮ. 6÷14-18፤ ኢሳ. 22÷13፤ 56÷10-12፤ ኤር. 5÷31::

እኛ ግን ሰባት ልጆቹን÷ ሚስቱንና ሰባ ባዕዳን ወንድሞቹን በድምሩ 78 ሰው በጭከና እያረደ ሲመገብ የኖረውን የዲያብሎስ ልጅ÷ ያለንስሐ ምሕረት ሊያገኝ ይቅርና ወንድሙን ጨርቅ ለባሽ ብሎ ሰድቦ ያሳዘነውም÷ በገሃነም እንደሚፈርድበት ስለ አነበብን÷ «አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ» «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤» እያልን እናስተምራለን እንጂ÷ ሰው በሰው እንዲጨካከንና በአምላካዊ ሕግ ላይም ቀልድና ዋዛ እንዲለምድ አንሰብክም፤ ማቴ. 5÷21-30::

እውነተኛው የአምላክ ቃል ውሾችና አስማተኞች÷ አመንዝራዎችና ነፍሰ ገዳዮች÷ ጣዖት አምላኪዎችና ሐሰትን ወዳጆች የሆኑ ሁሉ÷ ከመንግሥተ ሰማያት በውጭ ይቀራሉ የሚለውን ትምህርት አምነን እንሰብካለን እንጂ÷ ዐመፀኞች በእፍኝ ውሃ አምላክን አታልለው ገቡ የሚለውና ቃኤላውያን (የቃኤል ወገኖች) የጻፉት መጽሐፈ መንግሥተ ሰይጣን÷ በእኛ ዘንድ የተወገዘ ነውና ከቶ አንቀበለውም፤ ገላ. 1÷6-12፤ ራእ. 22÷15::

እኛ ግን የሃይማኖታችን መሠረት ፍቅር ስለሆነ÷ አዳማውያን ወንድሞቻችንን እንወዳለን:: እርስ በርስ መዋደድንና በችግር መረዳዳትንም እናስተምራለን:: የሚያየውን ወንድሙን እየጠላ ያላየውን እግዚአብሔርን እወዳለሁ የሚል ዋሾ ግን በዘለዓለማዊ ሕይወት ዕድል ፈንታ የለውምና እንደ ነፍሰ ገዳይ እንቈጥረዋለን:: በተቻለ መጠን ክፉ አመልህን ተው እያልን እንመክረዋለን እንጂ÷ የፈቀድከውን ኃጢአት ሠርተህ ሕፍነ ማይ (እፍኝ ውሃ) ብትሰጥ ትጸድቃለህ እያልን የሚያታልልና ሐሰትን የተሞላ ግብዝነት አንሰብክም፤ 1ዮሐ. 3÷6-7::

ወዳጄ ሆይ! ይህ የማታለል ነገር ዐዲስ እንዳይመስልህ፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ700 ዓመት በኢሳይያስ ዘመን ሕዝቡ ነቢያትን «የእስራኤልን ቅዱስ ከነሕጉ ወዲያ ፈቀቅ አድርጉት፤ ቅን ነገርም አትዩልን ለሥጋዊ ሐሳባችን ብቻ ደስ የሚያሰኘንን የጣፈጠውን ቃላትና ማታለልን ንገሩን::» የሚሉ እምቢተኞች ሰዎች እንደ ነበሩ መጻሕፍት ይነግሩናል፤ ኢሳ. 30÷8-14፤ ኤር. 23÷9-40::

ሐዋርያትም በኋለኛው ዘመን ሐሰተኞች መምህራን: - በደሙ የገዛቸውን ጌታ የሚክዱ፥ የሥጋን ፈቃድ ተከትለው የሚሄዱ ደፋሮችና ትዕቢተኞች፥ ርኩሶችና ነውረኞች፥ በማታለላቸው ራሳቸውን የሚያወፍሩ ሴሰኞችና የተረገሙ ልጆች እንደሚነሡ ጽፈው ተተውልናል፤ 2ጴጥ. 2፥1-22፤ ይሁ. 4-19።

እውነተኛዋና ቅን የሆነችው የክርስቶስ የቃል ኪዳኑ እጮኛ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ማለት ግን፥ ዝሙትና ርኩሰት፥ ትዕቢትና ስስት፥ ሐሰትና ፍትወት፥ ስካርና ቅትለት፥ ዛር፥ ቃልቻና ክሕደት፥ ጥንቆላና ጣዖት፥ ጠብና መቃናት፥ ቍጣና መለያየት ገላ.5፥13-26 የሌለባትና ነውር የማይገኝባት፥ ቅድስት፥ ንጽሕት፥ ድንግል፥ ለክርስቶስ የምትገባው በውዴታ የታጨችው፥ በሕገ ወንገል ብቻ የተቀጣችና ትእዛዙንም በሙሉ የጠበቀች ፍጽምት ልትሆን ይገባታል፤ 2ቆሮ. 11፥1-4፤ ኤፌ. 5፥22-32፤ ሆሴ 1፥2-3።

ትእዛዙን ሳትፈጽም ችላ በማለት ሌሎችን ያልፈጠሯትንና የማይጠቅሟትን ውሽሞችና ጣዖቶች የለመደች ሴሰኛ ነፍስ ከሆነች ግን፥ መች ከንጹሕ ከክርስቶስ ጋራ ትዋሐዳለች? እርሱ ግን ስሙን ብቻ ይዛ በትእዛዙ ለምታላግጥ ነፍስ «አንቺ ዋሾና አመንዝራ፥ ቃል ኪዳንዋን የማትጠብቅ፥ ሕግ አፍራሽ፥ ከዳተኛ» ብሎ ተቀይሞና ተቈጥቶ፥ ዓለም ሳይፈጠር ከተመደበላት ዘለዓለማዊ የጸጋ ክብር አባርሮ፥ ተጸይፎ፥ ወደ ሲኦል ወደ አባትዋ አዳራሽ ይሰዳታል እንጂ ሕግ አፍራሽቱን ነፍስ፥ በእንተ ስመ እገሌ፥ በእንተ ሕፍነ ማይ ተታልሎና የቃል ኪዳን ሚስቴ ነበርሽ ብሎ፥ ወደ ሰማያዊ የደስታ መንግሥቱ እንደሚያስገባት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ወንጌላውያን አርድእት ከቶ አልተናገሩም፤ ኤር. 3፥1-25፤ ሕዝ. 16፥1-43።

«ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌኪ፥ ወስፋሕኩ እደውየ ላዕሌኪ፥ ወከደንኩ ኃፍረተኪ፥ ወመሐልኩ ለኪ፥ ወቦእኩ ኀቤኪ በሕግ፥ ወኮንኪ ሊተ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር።» «ቃል ኪዳኔን ካንቺ ጋር አቆማለሁ፤ እጆቼን በላይሽ ዘረጋሁ፤ ኀፍረትሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽ፤ ካንቺ ጋርም ቃል ኪዳን ገባሁ፤ አንቺም ለኔ ሆንሽ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።» ሕዝ. 16፥1-8፤ 34፥27፤ 37፥26።

ያገራችን ቃል ኪዳን ግን ከማናውቃቸው ኀላፊዎች ከሆኑና ቁጥር ከሌላቸው ፍጡራን ሁሉ ጋር ነውና፥ በቀናተኛው በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ ያሳዝናል ያስፈራልም፤ ዕብ. 10፥26-31፤ ኢሳ. 57፥3-8።

አሁን ግን የአምላካችንን እውነተኛውን ቃል ኪዳን ስማኝ ልንገርህ:: እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች በሙሉ÷ እስራኤል ዘመንፈስ ለሆኑ (ሁለተኛ ለተወለዱ) ዐሠርቱ ቃላትን በጽላት ላይ በጣቱ ጽፎ በሙሴ እጅ ሰጣቸውና÷ ሰዎች እነዚህን ቃሎች ሊጠብቁ÷ እግዚአብሔርም ሰማያዊት ከነዓን ገነትን ሊያወርሳቸው ቃል ኪዳኑን ከሕዝቡ ሁሉ ጋር በአንድነት ተዋዋለ እንጂ÷ ለይቶ መርጦ ከሙሴ÷ ከአሮን÷ ከአልዓዛር÷ ከፊንሐስ÷ ከዔሊ÷ ከሳሙኤል÷ ከጻድቃን÷ ከቅዱሳን÷ ከሰማዕታትና ከመነኩሴዎች ብቻ ጋር ቃል ኪዳን አልገባም፤ ዘዳ. 29÷9-15:: «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ::» «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» ብሎ ለፍጥረቱ ሁሉ ጠቅልሎ ቃል ኪዳን ገብቷል፤ ሕዝ. 16÷59-62፤ ዘሌ. 11÷44-45:: አምላካችን አድሎአዊ አይደለምና ስሙም «እስመ ኢኮነ አምላከ ዘዐመፃ ያፈቅር::» «ዐመፃን የሚወድድ አምላክ አይደለምና» ይባላል፤ የሐዋ. ሥራ 10÷34፤ ሮሜ 2÷11::

አንባቢ ሆይ! ይህን ከንቱ የሆነ የማታለልና የሰው ሥርዓት እያልኩኝ የምነግርህ የሐሰት መምህራንና የፈጠራ መጻሕፍትም ሁሉ÷ ዛሬ የመጣ ዐዲስ ነገር አይምሰልህ:: ከነቢያትና ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ስለነበረ÷ ጴጥሮስ ሐዋርያው እንዲህ ብሎ ያስረዳናል:: <u>«ወቦቱ ባሕቱ ሐሳውያን ነቢያት ማእከለ ሕዝብ ከመ እለ ሀለው ማእከሌክሙ ወውስቴትክሙ እለ ሐሰተ ይሜህሩ፤ . . . ወይትከሐዱ በቃል ዘለሊሆሙ ፈጠሩ ወቦቱ የሐውሩ</u>::» «ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፤ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ::» 2ጴጥ. 2÷1-22:: «አኮኑ ራእየ ሐሰት ርኢክሙ፤ ወትቤሉ ይቤ እግዚአብሔር፤ ወአነ ኢነበብኩ::» «እኔም ሳልናገር እግዚአብሔር እንዲህ ብሎአል ስትሉ ከንቱ ራእይን ያያችሁ ውሸተኞችንም ምዋርት የተናገራችሁ አይደላችሁምን?» ሕዝ. 13÷1-7 ይላሉ መጻሕፍት::

ስለዚህ ከንቱ በሆነ ልማድ ወደሚባል ገደል በሚያገባው መንገድ÷ አባቶቻችን ያቆዩት ነው እያልን ብንጓዝ ጥፋቱ የኛ÷ መድረሻው ገሃነም መሆኑን አስተውል::

ይህንን ባገራችን ያለውን «ሕግ ላፈረሱ÷ ድምበር ለጣሱ ጽድቅ ይገኛል÷ እግዚአብሔር ለጻድቃን ጸድቀው እንዲያጸድቁበት ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል::» እያሉ ለሚሰብኩት ማታለል ግን ቁርጡን የሚናገር አምላካችን አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ «እናንተ ፌዘኞች የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ ከሞት ጋር ቃል

ኪዳን አድርገናል፥ ከሲኦልም ጋር ተማምለናልና መቅሠፍት አይነካንም ትላላችሁና፥ ይህ ከሞትና ሲኦል ጋር የተማማላችሁት ቃል ኪዳን ይጠፋል እንጂ አይጸናላችሁም። እናንተም በኔ ላይ የምታፌዙ በጽኑ ታሥራችሁ እየተገረፋችሁ ለኀፍረትና ለመረገጫ ትሆናላችሁ።» እያለ ደጋግሞ እያማረረና እያሰማ ጮኾ ተናግሮታል፤ ኢሳ. 28፥14-22፤ 30፥1፤ 8፥9-16።

ወዳጄ ሆይ! አባቶችን ጣዖት የሚያመልኩ በሥዕልና ምስል የሚመኩ፥ ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃወሙ፥ ዕንጨትና ደንጊያን የሚሳለሙ፥ የሚገድሉ፥ የሚሰርቁ፥ የሚያመነዝሩ፥ እየዋሹ በዛርና ጠንቋይ የሚመሩ ቢኖሩም እንኳን፥ ይህን ክፉ ሃይማኖት (ልማድ) አባቶቻችን ያቆዩልን ነው ብለን ልንሠራውና ልንጠብቀው ይገባናልን? ለዚህ መልሱ አይገባንም ብቻ ነው። አባቴ ታንቆ ሙቷልና እኔም ታንቄ ልሙት የሚል ሰው አይገኝምና ያባቶቻችን ሃይማኖት «ዘጸውዐ ስመከ ወዘገብረ ተዝካረከ እምሕር ለከ።» «ስምህን የጠራውን፥ ተዝካርህን (መታሰቢያህን) ያደረገውን እምርልሃለሁ።» ብቻ ነው። ይህም ከቅዱሳት መጻሕፍት የማይገኝ ነገር ነውና፥ አንተ ግን ለነፍስህ ከእውነትና ከሐሰት የሚጠቅማትን ነገር ለይተህ ያዝላት እንጂ፥ አባትህ ስላንተ ነፍስ መድኅን ሆነው አያልፉም። አብርሃም አበ ምእመናን የታራ የመምለኬ ጣዖት (የጣኦት አምላኪው) ልጅ እንደነበር ጽሑፍ ይነግረናል፤ ኢያ. 24፥1-5። በታሪክ ታራ ጣዖቱን እየሠራ፥ አብርሃምም ጣዖቶቹን ተሸክሞ እየሸጠ ይመገቡ እንደነበር ይነገራል። ለአብርሃምም ሕያው አምላክ በተገለጠለት ጊዜ ግን «ሲርብ የማያበላ፥ ሲጠማም የማያጠጣ፥ ሲደክምም የማያበረታ፥ ሲቸገርም የማይረዳ፥ ደንቆሮ አምላክ ግዙ» እያለ ሲቀልድበት ነበር ይባላል። የአባቱን አምላክ አመልከዋለሁ ብሎ ሕያው አብርሃም ምዉቱን ጣዖት ሥዕልንና ምስልን፥ ፍጡር የፈጠረውን አላመለከም። የሰው ይሉኝታና ልማድ ሊያታልለውና ሕሊናውን ሊያሳርፍለት አልቻለምና፥ የአባቱን ልማድ እምቢ፥ የፈጣሪውን ሕግ እሺ ስላለ፥ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ እየተባለ ሲጠራ ይኖራል፤ ኢሳ. 41፥1-14። «ስለ እኔና ስለ ወንጌል ብሎ አባት እናቱን ያልተወ፥ የኔ ተማሪ ሊሆንና ሊባል አይችልም።» የተባለው ቃል የሚፈጸምበት ጊዜ እንደዚህ በመሰለው ሰዓት መሆኑን እንዳንዘነጋው በውል እናስብበት፤ ማቴ. 10፥32-39።

አምላካችን ሃይማኖት ለሰው ሁሉ፥ ለያንዳንዱ የግል ገንዘብ መሆኑን ሲያስረዳ «ኢትሑሩ በግዕዘ አበዊክሙ፤ ወኢትዕቀቡ ሥርዐቶሙ፤ ወኢትደመሩ በጌጋዮሙ ወኢትርኵሱ» «በአባቶቻሁ

ሥርዐት አትሂዱ፤ ወጋቸውንም አትጠብቁ፤ በጣዖቶቻቸውም አትርከሱ።» ሕዝ. 20÷13-20፤ ዘካ. 1÷1-5። «ወልድ ኢይትፈደይ በኀጢአተ አቡሁ÷ ወአብ በኃጢአተ ወልዱ። ወጽድቁ ለጻድቅ ለርእሱ ወኃጢአቱ ለኃጥእ ላዕሌሁ።» «ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም÷ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፤ የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል÷ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል።» ብሎ ያስረዳናል፤ ዘዳ. 24÷16፤ ሕዝ.18÷1-20።

ይልቁንስ ደጎች ጻድቃንና ቅዱሳን ሰዎች ክርስቶስን ብቻ አምነው÷ መከራ መስቀሉን ተሸክመው÷ ያዘዛቸውን ፈጽመው «ነስሑ ወእመኑ በወንጌል እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት።» «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ።» እያሉ እስከ ዛሬ ስላስተማሩ በዓለም ዘንድ ተጠልተው÷ ክፉ ስም ተሰጥቷቸው እየተናቁ÷ እየታሠሩ÷ እየተወረሱ÷ እየተገረፉ÷ እየተሰየፉ የዓለም ጨውና ብርሃን ለመሆን የበቁት÷ በጠባቡ መንገድ ስለሄዱ ነውና÷ ፍለጋቸውን ተከትለን እነርሱ በሄዱበት መንገድ ልንሄድ ይገባናል እንጂ÷ አባቶቻችን ቅዱሳንን መስለን እነርሱን ተከትለን እንደሠሩት የጽድቅ ሥራ ሳንሠራ÷ ድነው ያድኑናል÷ ጸድቀው ያጸድቁናል ብለን እየተታለልንና እያወራን በከንቱ ሐሳባችን አለሥራቸው ማዳንን ለነርሱ እየሰጠን÷ አማልክት (ጣዖታት) ልናደርጋቸው አይገባንም፤ 1ቆሮ. 3÷1-7፤ ዕብ. 12÷1-14። ዐዲሱን መጽሐፍ ጸሎት ገጽ 45 መመልከት ነው።

ምዕራፍ 12

የማይመስል ምሳሌ

ወንድሜ ሆይ! ይህን «እመዐር ወሦከር ጥዕመኒ ለአፋየ» «ከማርና ከማር ወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» የተባለውን የመድኃኔ ዓለምን ቃልና አማላጅነቱን ስነግርህ÷ የሌለና የማይመስል መራራ ምሳሌ «ዘተሠርዐ በምድር ተሠርዐ በሰማይ::» «በምድር የተሠራው በሰማይ ተሠርቷል::» ተብሏልና÷ ምነው በምድራዊ ንጉሥ ዘንድ ሕግ ያፈረሰ÷ የሰረቀ÷ የገደለ በአማላጆች ይድናል ትለኛለህ? እንዳንተው ሐሳብና እንዳየኸውም ሁሉ÷ ሀብታም ቢበድል በአማላጅ ሲድን ድኻ ግን በጭንቅ ተይዞ በፍርድ ሲቀጣና ሲጠቃ ሁላችንም እናያለን:: በሰማያዊ ዳኛ ፊት ግን እንደዚህ እንደ ዋሾውና ዐመፀኛው ዓለም አይምሰልህ:: «በዚህ ዓለም የሚሠራው ሥራ ሁሉ ከንቱ ነው፤ የኃጥአን ድርሻ የሚደርስባቸው ጻድቃን አሉ፤ የጻድቃን ድርሻ የሚደርስላቸው ኀጥአንም አሉ:: በጽድቅ ስፍራ ኃጢአት በኃጢአት ስፍራም ጽድቅ አየሁ::» መክ. 3÷16፤ 8÷9-14፤ 9÷11 የሚለውን ቃል አስተውለህ አንብብ:: በሰማይ ንጉሥ ዘንድ ግን ሀብታምና ድኻ ትልቅና ትንሽ እንደሌለ አትናቴዎስ «ኢየኀፍሮ ለባዕል እንበይነ ብዕሉ አላ በከመ ተሐሰበ ሎቱ:: ወኢይምሕሮ ለነዳይ እንበይነ ንዴቱ ለእመ ኢኮነ መሥመሬ ሎቱ:: አሜሃ ብዑላን ይነድዩ፤ ወነዳያን ይብዕሉ:: አሜሃ ይፈትሕ ንጉሥ በኵነኔ ርትዕ ዘአልቦ አድልዎ::» «ባለጸጋውን ስለብልጽግናው ሲል አያፍረውም፤ እንደተገመገመለት መጠን ነው እንጂ:: ድኻውንም ስለድኽነቱ ሲል አይራራለትም፤ እርሱን ደስ ያሰኘው ካልሆነ በቀር:: በዚያን ጊዜ ባለጸጎች ይደኸያሉ:: ድኾችም ባለጸጋ ይሆናሉ:: በዚያን ጊዜ ንጉሥ አድልዎ በሌለበት ቅን ፍርድ ይፈርዳል::» እያለ አስረድቷል (ቅዳ. አት. ቁ.28-46)::

ይህ ዓለም መከረኛና ዐመፀኛ ነውና÷ ሕግ አፍራሾቹ ትልልቆቹና ሀብታሞቹ ሆነው ሳለ ታፍረውና ተፈርተው ይኖራሉ፤ በሕግ አፍራሽነትም ከቶ አይያዙም:: ንጉሥም በእነርሱ ምክር ስለሚነግሥ የሠሩትን ቢሠሩ አይደፍራቸውም:: ስለዚህ ምድራዊ ንጉሥ ከሰማያዊ ጋር ሊመሳሰል አይገባም፤ ኢሳ. 46÷5-9፤ ዳን. 6÷12-15::

ይህ ዋሾ ዓለም የሐሰትና የክፋት÷ የዐመፃና የውሸት÷ የአድልዎና የሕጸት (ጉድለት) ገበያ መሆኑንም ብዙ ሊቃውንትና መጻሕፍት ተስማምተውበታል::

ከሊቃውንት አንዱ አክሱማዊው አፈ ንቡረ እድ ተፈሪ በሚከተለው ቅኔ አስረድተውናል።

መወድስ

ምሥያጠ ዐመፃ ዓለም ሕጽጽተ አእምሮ
ኢረከብነ ብኪ ረባሐ ሥጋ ወነፍስ
አምጣነ ኅዳጥ ሤጥኪ፤ ወመድሎትኪ ንኡስ
ዓዲ በላዕለ ዝንቱ ጥዒናኪ ደዌ ወፍቅርኪ ባእስ
እምዝኒ ዘይብእስ ዘረከበኪ ይጼዓር ወዘኢረከበኪ ይጼነስ
ንሕነሂ እንዘ ናንሶሱ ዲበ ፍቅርኪ ተሥላስ
እፎ ከመ ጸላኢ ሞጣሕተ ዘለፋኪ ንለብስ
ቦኑ ትክል ትፍረይ በወርኀ ማእረር ሐዲስ
መሪረ ወጥዑመ አሐቲ ዕፀ በለስ። ያዕ .3÷6-12።

ትርጓሜ: - «አእምሮ የሌለሽ የዓመፅ ገበያ ዓለም!
ለሥጋም ለነፍስም የለብሽም ጥቅም፤
ሽያጭሽ ጥቂት ነው፤ ትንሽ ነው ሚዛንሽ፤
የጤና ስጦታሽ በሽታ፤ ጥላቻ ነው ፍቅርሽ፤
ደግሞ ሲታይ አለ ከዚህም የሚብስ ፤
ያገኘሽ ሲጨነቅ፤ ይቸገራል ያጣሽ፤
በፍቅርሽ አዳራሽ የምንኖረውንም፤
ጠላት አርገሽናል ትሰድቢናለሽም፤
ባዲስ ኪዳን ዘመን እንደዚህ አይሆንም፤
አንዱ የበለስ ዛፍ መራራና ጣፋጭ ከቶ አያፈራም።»

ስማኝ! ምድራዊ ንጉሥ ሌላው ሁሉ ይቅርና ከራስ ማዕረግ ጀምሮ እስከ ተራው ወታደር ላለው ሠራዊቱ÷ ስለ መዓርጉ (ሹመቱ) ወይም ደመወዙ ምን ያህል መስጠት እንደሚገባውና እንደሚበቃው ሊደነግግ ቢፈልግ÷ ከአማካሪዎች ጋር ካልተማከረ ብቻውን ሊያከናውን የሚችልበት ሥልጣን÷ ዕውቀትና ችሎታ የለውም። ምንም እንኳ እርሱ ቢሠራና ቢበይን ሰሎሞን «የእግዚአብሔር ብይን በንጉሥ ከንፈር ነው፤ ልቡናውንም እግዚአብሔር ወደ ወደደው ያዘነብለዋል።» እንደሚለን÷ ለጊዜው ተመርጦ ቢቀባ እርሱ የፈቀደውን ስለማይሠራ ማድረጊያ (መሣሪያ) ነው እንጂ አድራጊ አለመሆኑን አስተውል፤ ምሳ. 16÷10፤ 21÷1፤ 29÷26፤ ጥበብ 6÷1-27።

ምድራዊ ንጉሥ ማናቸውንም የግዛቱን ነገር የተደረገውንና ሊደረግም የሚገባውን የአስተዳደር ጉዳይ÷ ሹማምንቶቹ ካልነገሩት÷ እንዳይረሳውም ደግመው ደጋግመው ካላስታወሱት÷ አስፈላጊውንም ነገር ሁሉ ካላማከሩት÷ አይሰማውም÷ አያየውም÷

አያውቀውምና የአምላክ ምሳሌ ሊሆን አይገባውም:: አምላካችን ግን ሰማይና ምድርን ሲፈጥር ከቶ ያገዘውና ያማከረው የለም፤ ሮሜ 11÷33-36::

ወንድሜ ሆይ! ቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያትም ድዉይ እየፈወሱ÷ ምዉት እያነሡ÷ ሌላ ብዙ ብዙ ተአምራትን በስሙ እየሠሩ «በምን መሰላችሁኝ? ከማንስ ጋር ታስተካክሉኛላችሁ? ይላል ቅዱሱ::» ይላልና የተመረጡ ባሮቹም ምሳሌው ሊሆኑ ወይም ሊባሉ አይገባም፤ ኢሳ. 40÷25-31::

ንጉሥ የአምላክ ማድረጊያ (መሣሪያ) ነው ብዬሃለሁ እንዲሁም በጠቢብ የሚሠሩ ማረሻና ማጭድም÷ ለገበሬ ማድረጊያው ስለሆኑ ገበሬ በማረሻና ማጭድ አይመሰልም:: እንኳን ሕይወት በሌለው መሣሪያው÷ ሕይወት ባለው ማድረጊያው በበሬም አይመሰልም:: ዘመን አመጣሽ አስደናቂቱ በአንድ ሰዓት ከዐዲስ አበባ ወደ አሥመራ የምትገባው አውሮፕላን እንኳ÷ በጠፊ÷ ባላፊ÷ በረጋፊ በብረት እንጂ በሰው ልትመሰል አይገባትምና አይቻልም:: ይህን ሁሉ ስነግርህ አምላካችን በቃሉ «ምሳሌ የለኝም፤ ያየኝም ከቶ የለም::» ብሎ ስለ ተናገረ ነው እንጂ የኔ ሐሳብ አይምሰልህ፤ ዘፀ. 33÷17-23፤ ዘዳ. 4÷13-24፤ ኢሳ. 40÷18-25፤ 44÷6-22፤ 46÷4-9፤ ዮሐ. 1÷18፤ 5÷37:: እነዚህን ጥቅሶች ሳትሰለች አስተውለህ ብታነባቸው ቃሎቹ ይረቱሃል::

ስለዚህ የሚመስለውንና የተደረገውንም ቃላት መመሰል ይገባል እንጂ የሌለውንና ያልተደረገውን÷ የማይገባውንና የማይመስለውን ምሳሌ መመሰል ከቶ የማይገባና ተደርጎ የማያውቅ ነገር ነው::

ዓለም የወንጌልን ብርሃን ተቀብሎ እውነተኛ ክርስቶስን እንዳያመልክ የአታላዮች ልማድና ጨለማ አስሮ ስለያዘው÷ ግዙፉን የሮማውን ምስል (ምስለኔ) ሲያመልክና የኃጢአት ስርየት በገንዘብ ገዝቶ ሲመካበት÷ በዐይነ ሕሊና ለተመለከተው ሰው በጣም የሚገርምና የሚያሳዝን ነው:: ክርስቶስም ለዚሁ ሰው «እኔ በአባቴ ስም መጣሁ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ::» ብሎ አስቀድሞ ተንብዮለታል፤ ዮሐ. 5÷43፤ ራእ. 17÷1-18 ተመልከት::

አንባቢ ሆይ! ንጉሥና ጳጳስ የአምላክ ምሳሌ ሊሆኑና ሊባሉ ከቶ አይገባም:: ሌላው ሁሉ ቀርቶ ከፍጡር አንዲት የጤፍ ፍሬ መፍጠር ወይም አንዲቷን ጥቁር ጸጕር ነጭ ለማድረግ የሚችል አይገኝም:: ስለዚህ ምንም ትልቅ መስሎ የሚታየውን ነገር እንኳ ቢሠሩ÷ ክፉም ቢሆን በጎ በአምላክ ታዘው አሳላፊዎች ሆነው ነው

እንጂ ከራሳቸው በፈቃዳቸው አንድ ነገር ለመሥራት ሥልጣን የላቸውምና፥ ኀላፊዎቹ ንጉሥና ጳጳስ የአምላክ ምሳሌው ቢባሉ ድፍረትና ስሕተት ነው፤ ዮሐ. 19፥9-11፤ ማቴ. 5፥36።

ሕያው አምላክ አንዜ ዓለም ግን ሳይደክምና ሳይታክት ሰማይና ምድርን በቃሉ ብቻውን የፈጠረ ኢሳ.44፥24፤ 40፥12-31፤ ልብና ኩላሊትን የሚመረምር፥ ለሁሉም እንደሥራው ሳያዳላ የሚከፍል ራእ.2፥23፤ ነገርን ሁሉ ከመደረጉ በፊት አስቀድሞ የሚያውቅና የሚፈጽም ስለሆነ፥ እንኳን ከዐፈር የተፈጠሩ፥ ከባሕረ ኃጢአት የተነከሩ የአዳም ልጆች ቀርቶ፥ ረቂቃን መላእክት ቅሩባኑ ኪሩቤልና ሱራፌልም ምሥጢሩን ስለማያውቁት ምሳሌው ሊሆኑ፥ ሊባሉም አይገባም፤ ኢሳ.46፥8-11። ዳዊት «አልቦ ዘይመስለከ እምነ አማልክት፤ ወአልቦ ዘከመ ምግባሪከ።» «አቤቱ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፤ እንደ ሥራህም ያለ የለም።» ብሎታልና፥ ሸክላ የሚሠራ ሰው በሠራው ዕቃ እንደማይመሰል እንደዚሁ ፈጣሪም በፍጡር አይመሰልም፤ መዝ. 86፥8፤ ኢሳ. 45፥9-12፤ 29፥16። «እግዚአብሔርን በሰማይ የሚስተካከለው ማነው? ከአማልክት ልጆችስ ለእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር የሚመሰል ማነው? እንደርሱ የበረታና የተፈራ፥ እንደ እርሱ ኀይለኛና ግሩም የግሩም ግሩም የሆነስ ማው?» መዝ. 89፥6-13፤ አንድም የለም፤ ኢሳ. 41፥21-28።

ከነአካቴውም መላእክት በአምላክ ዘንድ ሰነፎች፥ ዕውቀት የሌላቸው፥ ስንዴና እንክርዳድን እንኳ ለይቶ ማወቅ የማይችሉ ተሳሳቾች መሆናቸውን ክርስቶስ በቃሉ ነግሮናል፤ ኢዮ. 4፥17-21፤ ማቴ. 13፥27-29።

የታዘዙትንም ነገር መቅሠፍትና መዓት ለማውረድ ሲላኩ ተሳሳቾች ስለሆኑ፥ የማይሳሳተው ወልድ ቃል የሚጠፉውንና የማይጠፉውን ለመለየት በገዛ እጁ ምልክት ያደርግለታል እንጂ፥ እነርሱስ (መላእክት) ከቶ ዕውቀት እንደሌላቸው ጥቅሱን ተመልከት፤ ዘፀ. 12፥1-27፤ ሕዝ. 9፥1-11፤ 15፥14-16፤ ማቴ. 13፥29፤ ራእ. 7፥2-8። ከአዳም በፊትም ኃጢአትን የጀመሩ መላእክት መሆናቸውን አስተውል 2ጴጥ. 2፥1-7። ስለዚህ ከፍጡር የማይሳሳትና ጉድለት የሌለበት፥ ፍጹምነትና ጽድቅን የሚሠራ አንድ አይገኝምና ፈጣሪን በፍጡራኑ መመሰል ትልቅ ኃጢአት ነው፤ ኢሳ. 46፥5-9፤ ሚክ. 7፥2።

የማማለዱ ነገር ደግሞ መላእክት «ንዑ» እና «ሑሩ» በምንባልበት ቀን ማማለዳቸውና ስለኀጥአን መለመናቸው ቀርቶ፥

ኃጥአንን እያዳፉ ወደ ዘለዓለማዊው እሳት (ገሃነም) የሚያስገቡ÷ እያምዘገዘጉም የሚጥሉ መላእክት መሆናቸውን አንብብ፤ ማቴ.13÷36-49::

መላእክት በፍርድ ቀን በዕውቀታቸውና በርኅራኄአቸው÷ ለምነውና አማልደው÷ አምላክ የፈረደውን አስለውጠው÷ አንድ ወዳጃቸውን እንኳ ገነት አስገቡ የሚል በመጻሕፍተ ነቢያትና ሐዋርያት (ብሉይና ሐዲስ) አንድ ቃል ተጽፎ አይገኝም:: የተጻፈውስ የታዘዙትን ብቻ ይሠራሉ እንጂ ሊምሩ ወይም ሊያስምሩ÷ ሊያድኑና ሊገድሉ ኃይል÷ ዕውቀትና ሥልጣን የላቸውም የሚል ነው፤ 1ዜና. 21÷14-27፤ ኢሳ. 37÷36::

ወንድሜ ሆይ! በክፋትና በኃጢአት የረከሰውን÷ ዐፈርና ሚቹን ሰው (ኢዮ. 15÷14-16) ንጉሥን ወይም ጳጳስን ከዘለዓለም ሕያው÷ ንጹሕ÷ ፍጹም÷ ቅዱስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከልህ÷ ምሳሌውም ማድረግህ ስሕተት ወይም ድፍረት ነውና ተጸጸትበት:: ደግመህም በዚህ ስሕተት አትውደቅ፤ ሳታውቅ ለበደልከውም ምሕረትን ከመሐሪው ጌታ ለምን፤ መዝ. 19÷12-14፤ ኢሳ. 46÷3-13::

ብዙ ነገሥታት በስሕተታቸውና በኃጢአታቸው መንግሥታቸውንና ሕይወታቸውን እያጠፉ ይኖራሉ:: ሕያው÷ ከሃሌ ኲሉ አምላክ ግን÷ ሕጉ አይለወጥም፤ ሚዛኑ አያደላም፤ አይሳሳትም፤ ለዘለዓለም ዓለም ነዋሪ ስለሆነም÷ አማልክት (ነገሥታት) ከተባሉት ሁሉ አንድ እንኳን የሚመስለውና የሚስተካከለው የለም፤ ዳን. 4÷34-37፤ 6÷26-27፤ መዝ. 86÷8::

አንባቢ ሆይ! ከልበ አምላክ ዳዊት የበለጠ ንጉሥ ማን አለ? (ነበረ?) ሲባል ትሰማለህ:: እርሱ «አንሰ ዕፄ ወአኮ ሰብእ» «እኔ በአምላክ ፊት ትል ነኝ እንጂ ሰው ለመባል አልበቃም::» ይላል መዝ.22÷6:: አብርሃምም «አንሰ መሬት ወሐመድ አነ::» «እኔ ዐፈርና አመድ ነኝ::» ብሏል፤ ዘፍ. 18÷27:: ስለዚህ ምድራዊውን ንጉሥ ሊቃውንትና ካህናት÷ ሕዝብና መሳፍንት መክረው÷ መርጠው ይሾሙታል፤ ጉድለት ቢያገኙበት ደግሞ ወዲያው ይሽሩታል:: ሕያው አምላክ÷ አኀዜ ኲሉ ግን መለኮቱን እደ መዝራዕቱ÷ ኃይሉ÷ ጥበቡ÷ ምስሉ÷ መልአከ ገጹ÷ ወልዱ ቃሉና መንፈሱ ካልሆነ የሚረዳውና የሚያገለግለው÷ የሚያስታውሰውም÷ ወይም ዓለምን ያህል ትልቁን ነገር ሲፈጥር ያማከረው÷ ያነገሠውና የሚሽረው÷ ምክሩን የሚቃወመውም ከቶ የለም፤ ዳን. 4÷35፤ ዘፀ. 23÷20፤ 33÷14 ኢሳ. 63÷9::

ወዳጄ ሆይ! ነገር በሰምና ወርቅ ይመሰላል ቢሉም ሰም በሐሳብ ፈጥሮ ወይም ምስሉን አይቶ ቅጂ (ኮፒ) ማንሣት ነው:: አምላክን ግን ፍጡራኑ በሐሳባችን እንዳንፈጥረውና እንዳንወስነው «ወመለኮትሰ ኢይትከሀል ይትበሀል ዘንተ የአክል ወዘንተ ይመስል::» «መለኮት ግን ይህን ያህላል÷ ይህንንም ይመስላል ይሉት ዘንድ አይቻልም::» ይለዋል ሕርያቆስ 5÷14:: ወይም አይተነው እገሌን ይመስላል እንዳንለውም ከቶና አካቶ ያየው ስለሌለ ምሳሌ የለኝም ብሏል፤ ኢሳ. 46÷9፤ የሐዋ. ሥራ 17÷24-31፤ ዮሐ. 1÷18፤ ሮሜ 11÷33-36::

ምዕራፍ 13

ንስሓ፥ ሐዘን፥ ልቅሶ

ወንድሜ ሆይ! እውነተኛው አማላጅ ማለት ግን ፈጣሪህ መሐሪ መሆኑን አምነህ በንስሓ፥ በኀዘንና በልቅሶ ነቅተህ፥ እነዚህን ሦስት አማላጆች አጥብቀህ ይዘህ ብትፈልገው፥ ጎልጎታ ድረስ ሳትደክም ይቅርታውንና በረከቱን፥ ጸጋውንና መሐሪነቱን ከልብህ ውስጥ ታገኘዋለህ፤ ዘፍ.32፥24-29፤ ዘዳ.4፥29-36:: «ኢተአምሩኑ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ፤» «እስመ እንተ ውስጡ ለሰብእ የኀድር ክርስቶስ በሃይማኖት ውስተ ልብክሙ በተፋቅሮ::» «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን?» «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኀይል እንድትጠነክሩ፥ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር፥ እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ::» 1ቆሮ. 3፥16፤ ኤፌ. 3፥17 የሚለውን ቃል አይተህ፥ የማን (የክርስቶስ ወይም የዲያብሎስ) ማኅደር መሆንህን ለልብህ በልብህ አንተ ራስህ መርምረው መዝነው 2ቆሮ.13፥5:: እንዳንተ ፍጡራን የሆኑት ቄስና ጳጳስ ቢሆኑም ቅሉ ምንነትህንና ማንነትህን አያውቁትም:: ምንም እንኳን አንተ ሳታውቅ ይፍቱኝ ብትላቸው፥ «እኔ አልችልም፤ እግዚአብሔር ይፍታህ::» ይሉሃልና አሳሪና ፈቺ ማን መሆኑን አስተውል፤ ራእ. 5፥1-5:: ዳዊት ግን «እግዚአብሔር ይፈትሖሙ ለሙቁሓን፤ ወሰበርከ መዋቅሕትየ» «እግዚአብሔር የታሰሩትን ይፈታል፤ ሰንሰለቴንም ሰበርህ» መዝ.146፥7፤ 116፥16 ይላል::

ስለዚህ ሁልጊዜ ኃጢአትህ መብዛቱን በኀዘን እያሰብህ ከእግዚአብሔር እጅ በታች ዝቅ ዝቅ ብትል እርሱ በጊዜው ከፍ ከፍ ያደርግሃል 1ጴጥ.5፥5-9:: አምላካችን የተሰበረውን መንፈስና የተደቈሰውን ልብ አይንቅም:: ቅሩብ ለየዋሃነ ልብ (በልባቸው የዋህ ለሆኑ ቅርብ) ስለሆነም፥ የሰውን ትእዛዝ ትተህ እርሱ ባዘዘውና በአዘጋጀው መንገድ ብትሔድ፥ «<u>አነ ውእቱ አንቀጽ ዘበአማን፥ ዘቦአ እንተ ኀቤየ ይድኅን::» የሚል የጽድቅ በር ኢየሱስ ብቻ መሆኑን በቃሉ ታገኘዋለህ፤</u> ዘዳ. 4፥29፤ መዝ. 51፥1-17፤ ዮሐ. 10፥9::

ቅዱሱ ወልደ እግዚአብሔር ሥጋችንን ለብሶ መገረፉ፥ መሰቀሉ፥ መሞቱና ይህን ሁሉ መከራ መቀበሉ ኃጢአት ኖሮበት ይመስልሃልን? «ያለ ኃጢአት ከመሆኑ በቀር በሁሉ እንደኛ የተፈተነ ነው::» ዕብ. 5፥15 ተብሏልና፥ እርሱ ወደዚህ ዓለም

የመጣበት ዋና ዐላማው፥ እኔና አንተን የመሳሉትን ጎጕላን (የጠፉ) ኃጥአንን ፈልጎ ከዲያብሎስ እጅ ነጥቆ ለማዳንና ከአባቱ ዘንድ አማልዶ፥ በደሙ ዐጥቦ፥ አንጽቶ፥ አጽድቆ ገነት ለማስግባት ነው 1ዮሐ. 1፥7።

ዳዊት በስሕተቱ፥ ምናሴ በኃጢአቱ፥ ጴጥሮስ በክሕደቱ፥ «ለከ ለባሕቲትከ አበስኩ» «አንተን ብቻ በደልሁ።» ብለው ወደ እርሱ ቢያለቅሱ፥ መራራ ሐዘናቸውንና ፈሳሹን እንባቸውን አይቶ ራርቶ፥ ስርየት ሰጣቸው እንጂ በመልአክ ወይም በጻድቃን፥ በፍጡር፥ በአማላጅ ተለምኖ አልማራቸውም። ኃጢአታችሁንም ለቄስ ንገሩ አላላቸውም። ስለምን ብትል ኢሳይያስ «እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ለማዳን ዐጭር አይደለችም፤ ጆሮውም ከመስማት አልደነቈረችም።» ይላልና፥ ስለዚህ በገዛ እጅህ (አፍህ) የምትፈልገውን ሁሉ ለእርሱ መንገር ይገባሃል። ምክንያቱም እርሱ ስማ በለው (ኢንተርፕሪተር) አይፈልግም፤ 2ዜና. 33፥1-33፤ መዝ. 51፥1-12፤ ኢሳ. 59፥1፤ ዳን. 9፥1-11፤ ማቴ. 26፥69-75።

እግዚአብሔር በመልአክ ተለምኖ የሚምር፥ መላእክትም መለመኑ የሚቻላቸው ቢሆን ኖሮ፥ ኃጢአት የተጀመረው ገና ከመጀመሪያው አዳምና ሔዋን በነበሩበት ገነት ወስጥ ነውና፥ በቀላሉ ሁለቱን ብቻ አማልደውና ለምነው፥ ወደ ነበሩበት አገር መልሰው ማስገባት በተቻላቸው ነበር። ነገር ግን ስለማይቻላቸውና ሥራቸውም ስላልሆነና የታዘዙትን ብቻ ስለሚሠሩ፥ የሚያንበለብል ሰይፈ እሳት ይዘው እያጣደፉ ወደ ምድረ ፍዳ ያወጧቸው መላእክት መሆናቸውን አስተውል ዘፍ.3፥24። <u>ሰው እግዚአብሔርን ቢበድል ስለእርሱ የሚለምንለት ከቶ አይገኝም</u>፤ <u>1</u>ሳሙ. 2፥25።

ባለፈው ዘመንህ ሳታውቀው የሠራኸውን ኃጢአት ይቅር የሚልህ፥ ኃጢአትህን ለመሻር፥ ለመደምሰስም ሥልጣን ያለው አንዱ እውነተኛው አማላጅህ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ነውና፥ እርሱ ስለአንተ ኃጢአት ኃጥእ መስሎ፥ ጻድቅ ሲሆን እንደ ክፉ አድራጊ በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ፥ ዕዳህን ፈጽሞ ከፍሎ፥ ሥጋውን ቆርሶ፥ ክቡር ደሙን ኡፍስሶ፥ ሕይወቱን ሰጥቶ፥ ሙቶ ተነሥቶ፥ የተቤዠህና የገዛህ መሆኑን እመንና ትድናለህ፤ ዳን. 9፥24፤ ገላ. 3፥10-13፤ 1ጴጥ. 1፥18-25። «<u>በደልህን እንደ ደመና፥ ኃጢአትህንም እንደ ጉም አጠፋዋለሁ፤ ስለዚህ እባክህ ወደኔ ተመለስ፤ እኔ ተቤዥቼሃለሁና።» ብሎ</u> ይመክርሃልና ስማው። የተቤዠህ የሚቤዥህም ሌላ የለምና እባክህን እሺ በለው። እውነተኛ መድኃኒትና መካሪ፥ አዳኝና አጽዳቂ ኢየሱስ ብቻ ስለሆነም እርሱን ብቻ አምነህ ጽደቅ፤ ኢሳ. 44፥22፤ ኤር. 4፥1-4።

ወንድሜ ሆይ! የምነግርህን ልብ አድርገህ ስማኝ፤ «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ» «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፤» ብሎ ሲፈጥረን አንድ አምላክ ብቻ እንደሆነ አንተም ታውቃለህ:: አሁንም እንዲሁ እኛን ለማዳን የተሰቀለልን ኢየሱስ ብቻ መሆኑን አትጠራጠር:: በፈጠረን ጊዜ አጋዥ፥ ረዳት፥ ጭቃና ውሃ አቀባይ ካላስፈለገው፥ ለመዳናችንም ረዳትና አማላጅ እንደማያስፈልገው አስተውል፤ ኢሳ. 40፥12-14:: «ኢየኀሥሥ መርድአ በእንተ ኪን ዘኀለየ፤ ወኢይፈቅድ እንከ መምክረ በእንተ ምግባር ዘፈተወ::» «ያሰበውን ለማድረግ ረዳት አይሻም፤ የወደደውንም ለመሥራት አማካሪ አይፈልግም::» ኤጲፋንዮስ.1፥13፤ ስለዚህ በስም ብቻ ሳይሆን በእውነት ክርስቶሳዊ (የክርስቶስ ወገን) ክርስቲያን ከሆንህ፥ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ «የክርስቶስ መስቀል ካልሆነ በቀር አንዳች ሌላ መድኃኒት አላውቅም» በል፤ 1ቆሮ. 2፥2፤ ገላ. 6፥14-16:: «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ፈዋሽህ ነኝ::» ዘፀ.15፥26 ብሎሃልና፥ እርሱን ብቻ አምነህ፥ በደሙና በመገረፉ ቍስል ተፈወስ እንጂ ሌላ የአታላዮች መድኃኒት መሰብሰቡ ከቶ አይጠቅምህም፤ ኢሳ. 47፥12-15፤ 1ጴጥ. 2፥24፤ ኢሳ. 57፥13::

አንባቢ ሆይ! እነ አባ፥ አማላጅ ያድናል ብለው ያስተምሩሃል:: ነገር ግን ፈያታይ ዘየማን (በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ) ብቻውን ወደ ገነት ሲገባ፥ ጓደኛውና ወዳጁ ፈያታይ ዘጸጋምን (በጌታ ግራ የተሰቀለውን ወንበዴ) አማልዶና አምላክን ለምኖ ይዞት ወደ ገነት አለመግባቱ፥ በእንተ ተዝካሩ ለፈያታይ (ስለወንበዴው መታሰቢያ) ብሎ፥ ሕፍነ ማይ ቈሪር (ቀዝቃዛ እፍኝ ውሃ) ለድዉይ አለ ማጠጣቱ ይሆን? ወይም ከዐሥሩ ደናግል አምስቱ ጠባባት (ልባሞች) ሙሽራው ክርስቶስን ተከትለው ሲገቡ፥ አምስቱ አብዳት (ዝንጉዎች) ጓደኞቻቸው በደጅ ቁመው «እግዚኦ አርኅወነ» «አቤቱ ክፈትልን» ብለው እያለቀሱ ሲያዩአቸው፥ ንጉሡ «ኢየአምረክን» «አላውቃችሁም» ባላቸው ጊዜ፥ «አንተ እኮ ባታውቅ ነው፥ እነርሱ ዘይት አልቆባቸው ሊገዙ ሄደው ነው ሳይገቡ የቀሩት እንጂ፥ ከኛ ጋር ሆነው አብረውን ሲጠብቁህ አምሽተዋል:: ስለዚህ አሁን ዘይት ገዝተው መብራታቸውን አሰናድተዋልና እባክህን ስለኛ ብለህ በሩን ከፍተህ አስገባቸው::» ብለው አምስቱ ጻድቃን ስለአምስቱ ኃጥአን ጓደኞቻቸው አማልደው ገነት መንግሥተ ሰማያት ያላስገቧቸው ምን ሆነው ይሆን? ብለህ ጠይቅና መልስ ጠብቅ:: አምስቱ ጻድቃን ግን በማማለድ ፈንታ ኃጥአኑ «ዘይት ስጡን እባካችሁ» ብለው ቢለምናቸው «ኢየአክል ለነ ወለክን» «ለኛና ለእናንተ አይበቃንም» አሏቸው እንጂ በምንም

መንገድ ሊረዷቸው አልቻሉም:: ስለዚህ የሰው ጽድቅ ለሰው እንደማይተርፈው አስተውል፤ ማቴ. 25÷1-13፤ ሉቃ. 23÷39-43::

እንዲሁም ሉቃስ በወንጌሉ በ15ኛው ምዕራፍ ገልጸ እንደሚነግረን÷ ያንን ከአባቱ ቤት ከድቶ ወደ ሩቅ አገር ከዓለም በረሃ ሸፍቶ ሲኖር የነበረ የጠፋውን ልጅ÷ ልጅነቱን ስለአጠፋ ተጸጽቶ ወደ አባቱ ቤት በተመለሰ ጊዜ ማን የሚባል ካህንና ጻድቅ ለማኝ÷ አማላጅና አስታራቂ ይዞ መጣ ይሉሃል? ይዞት የመጣውን አማላጅስ ልንገርህ፤ ዕንባውን÷ ጥፋቱን÷ ችግሩን÷ ስሕተቱን÷ ሐዘኑን÷ ኃጢአቱን÷ ረኃቡን÷ ጥማቱን÷ ዕርቃኑንና ኀፍረቱን ይዞ ብቻውን ወደ አባቱ ቤት መጣ:: አባቱም ርኅራኄው ወሰን ስለሌው በሩቅ ሲመጣ ባየው ጊዜ ተነሥቶ በደስታ ተቀብሎ÷ በኃጢአት የተበላሸ አካሉን በጽድቁ ወልውሎ÷ ሳይጸየፈው አቅፎ እየሳመ÷ ያንን ዱሮ በሕፃንነቱ ያጠፋውን ልጅነት መልሶ ሰጥቶ÷ የንጉሥ ልጅ አደረገው እንጂ ባዕድ አማላጅ ካልያዝህ ወደ ቤቴ አላስገባህም፤ ሂድ! ውጣ! አስታራቂ ይዘህ ና! ብሎ አላባረረውም::

ስለዚህ አንተም እግዚአብሔር ያለፈውን ኃጢአትህን የማይቈጣጠር÷ «ዳግመ ኢተአብስ» «ደግመህ አትበድል» የሚል መሐሪ የምሕረት አባት መሆኑን አምነህ÷ በሐዘን÷ በልቅሶና በንስሓ ክፉ ጠባያቸውን ለውጠው ወደርሱ የሚመለሱትን ሁሉ በደስታ የሚቀበል ቸር ጌታ መሆኑን ተገንዝበህ÷ ዛሬ ድምፁን ሰምተህ ካልተመለስህ ነገ ቅጽበትን ያህል የንስሓ ጊዜ ብትፈልግ ከቶ አታገኝም፤ ዘፀ. 16÷25-27:: ወዳጄ ሆይ! ቸሩ አምላካችን «እኔ ነኝ ክፉትህን የምደመስስ፤ ኃጢአትህንም ስለኔ ብዬ አላስባትም፤ ሕዝቤ ሆይ ትመለስ እንደሆነ ወደኔ ተመለስ::» ይልሃል፤ ኢሳ. 43÷25፤ ኤር. 4÷1፤ ሉቃ. 23÷39-43:: እነሆ! የሚቀበልበት ጊዜ ዛሬ ነው፤ እነሆ! የመድኃኒቱ ቀን ዛሬ ነው፤ ስለዚህ እግረ ነፍሳችሁ በኃጢአት የሚያነክስባችሁ ሰዎች ብትኖሩ ዛሬ እንድትፈወሱ ወደርሱ ተመልሳችሁ የቀናውን መንገድ (ሃይማኖት) ያዙ፤ 2ቆሮ. 6÷2፤ ዕብ. 12÷12-13 በመንፈሱ ይምራችሁ አሜን::

ምዕራፍ 14

ስለ መምረጥ፤ ሰው የፈለገውን መርጦ ለመውሰድ በራሱ ሥልጣን አለው

አንባቢ ሆይ! ስለ አማላጅነት ነገር ደግሜ ደጋግሜ እነግርህ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። ቢሆንም «ለጠቢብሰ አሐቲ ቃል ትበቁዖ» «ለጥበበኛ ሰው አንዲት ቃል ትበቃዋለች» የሚባለውን ምሳሌ ስታስብ ከአሁን በፊት የነገርኩህ በበቃህ ነበር። ነገር ግን መምህራነ ሐሰት ከንቱ የሆነ ፍሬ የሌለው ልማድ የሚባል ትምህርት፥ እያታለሉ መግበው ስላሳደጉህና ጽምአተ ነፍስን ሊያረካ በማይችል፥ ቃለ እግዚአብሔር ባልሆነ፥ ነቢያትና ሐዋርያት ባላቄዩትና የደፈረሰ ውሃ በሚመስል አዋልድ በሚባለው በመጻሕፍተ ፈጠራ ልቦናህ (አንጐልህ) ስለደነዘዘ፥ ቅዱስ መጽሐፍን በስማ በለው (በተርጓሚ) ሳይሆን በቋንቋህ ራስህ አንብበህ እውነቱን ከሐሰት እስክትለይ ድረስ፥ ካነበበ ይሰማኝ ይሆናል ብዬ ሳልሰለች ከተኛህበት ልቀሰቅስህ ግድ ሆነብኝ፤ ኤር. 2÷6-13፤ አሞ. 8÷11፤ ሉቃ. 14÷23፤ ኤፌ. 5÷6-11። «ወገኖቼ ሆይ! የሚመሯችሁ እነርሱ ያስቷችኋል፤ የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ።» ኢሳ. 3÷12፤ «የዚህ ሕዝብ መሪዎች አሳቾች ናቸው፤ ተመሪዎቹም ይጠፋሉ።» ኢሳ. 9÷16 የሚለውን ምክር ሰምተህ፥ ልማድ የሚባለውን አተላ ትተህ «ዘይመጽእ ኀቤየ ኢይርኀብ፤ ወዘሂ የአምን ብየ ኢይጸምእ ለዝሉፉ።» «ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም።» የሚለውን ሕይወት ሰጥቶ ጥማት የሚያረካ የክርስቶስን እውነተኛና መልካሙን ቃለ ወንጌል ብቻ ዛሬ ብትማርና ብትመገብ፥ በነፍስህና በሥጋህ ተጠቅመህ የዘለዓለም ሕይወት ወራሽ፥ የስሙም ቀዳሽ ትሆናለህ፤ ኢሳ. 55÷1-3፤ ዮሐ. 6÷29-37።

ፍጡራን መላእክትና ጻድቃን ያማልዳሉ ማለት በፍጹም ሐሰት ነው። እንደምን ብትለኝ ግን አበ ምእመናን የተባለ አብርሃም ጻድቁ ያን ባለ ጸጋ ከሲኦል ውስጥ ገብቶ በእሳት ነበልባል ሲቃጠል እያየው፥ ፈጣሪውን ለምኖ ገነት ማስገባት ይቅርና፥ «አባ አብርሃም ተሣሃለኒ» «አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ» ብሎ እያለቀሰ ሲለምነው፥ ያን የተለመነውንና ጉሮሮውን የሚያርስበትን አንድ ጠብታ ውሃ እንኳ ሊሰጠው እንዳልቻለና እንዳላገኘለትም እናነባለን። እርሱስ ጨክኖ «<u>ተዘከር ወልድየ ዘከመ ፈጋዕከ በሕይወትከ ወምስለ ዝንቱ ኵሉ ጸድፍ ዐቢይ ይከልአነ ማእከሌነ ወማእከሌክሙ ከመ እለሂ ይፈቅዱ እምለፌ ይኅልፉ ኢይክሉ መጺአ ኀቤክሙ</u>

ወእለሂ መንገሌክሙ ኢይዕድዉ ኀቤነ።» «ልጄ ሆይ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ፤ . . . ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል።» ብሎ መለመንና ማማለድ ስለሌለ፥ ኃጥአንና ጻድቃንም መደባለቅ ስለማይችሉ፥ «አይሆንልኝም፤ አይቻለኝም፤ ቢቻለኝም እንኳ እኛንና እናንተን የማያገናኝና ለያይቶን የሚኖር ትልቅ ገደል (የአምላክ ሥልጣን) በመካከላችን አለ።» ሲል ቁርጥ ያለ መልስ ሰጠው እንጂ፥ በማናቸውም ነገር ሊረዳውና ሊያማልደው እንዳልቻለ ሉቃስ በወንጌሉ ገልጾ ይነግርሃልና ሳትሰለች ልብ አድርገህ አንብብ፤ ሉቃ. 16፥19-31።

መጻሕፍት ግን «በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ምግባራቸውም ትከተላቸዋለች።» ራእ. 14፥13፤ «እስመ አንተ ትፌድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።» «አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራ ትከፍለዋለህ።» መዝ.62፥12፤ ብለዋልና አንተም ዛሬ «ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘድልው ለክሙ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም።» «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።» የሚያሰኝህን እውነተኛውን የክርስቲያን ምግባር መርጠህ መያዝና ማድረግ ያስፈልግሃል። ስንቅህን ዛሬ ወደፊት ካላሳለፍህ ምንም ቢሆን በኋላ የተውሶ ጽድቅ ከቶ አታገኝም፤ ማቴ. 25፥31-40፤ መክ. 9፥10።

ወንድሜ ሆይ! ነፍስህን ግን ብታድናትም ብታጠፋትም ከሁለቱ አንዱን መምረጡ የአንተ ሐሳብና ፈቃድ ስለሆነ፥ «አቅረብኩ ለከ ማየ ወእሳተ ሞተ ወሕይወተ ደይ እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ» «እሳትና ውሃን፥ ሕይወትና ሞትን፥ አቅርቤልሃለሁ፤ እጅህን ወደ ወደድከው ጨምር።» ብሎ ሁለቱን አገሮች (ገነትና ገሃነምን) አቅርቦልሃልና ያማረህን፥ ደስ የሚልህን ዛሬ መርጠህ ውሰድ። ዘዳ. 30፥5-20፤ ሲራ. 15፥14። ፍቅር ባሕርዩ የሆነ፥ አንድ ኃጥእ ሰው እንዲጠፋ የማይወድ ቸሩ አምላካችን ግን፥ እባክህን ሕይወትን እንጂ ሞትን አትምረጥ እያለ ይለምንሃል፤ ይመክርሃልምና ዛሬ እሺ ብለህ እርሱን ብቻ አምነህ፥ ምክሩን ሰምተህ ብትታዘዘው ትድናለህ እንጂ፥ ትእዛዙንና ሕጉን ሳትፈጽም ቅዱሳን ሰዎች ብዙ መከራና ሥቃይ ታግሠው ያፈሩትን ጽድቅ፥ «እኔ ሳልደክም ሳልሠራ፥ በሰዎች ድካም ገነት እገባለሁ ወይም ያስገቡኛል» ብለህ ማሰብህ፥ ከንቱ የሆነ የሞተ ተስፋ፥ ነፋስ እንደ መጨበጥ የመሰለ ነገር ነውና ቀልዱ በማን ቤት ነው? መክ. 1፥14።

ወዳጄ ሆይ! ባለቤቱ ንጉሡ ደግሞ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ከቶ አላውቃችሁም፤ እናንተ ኃጢአትን የምትሠሩ ከኔ ራቁ::» ብሎ ቊርጡን የሚናገር፥ ፊት አይቶ የማያደላ፥ ፈርዶ ካሰናበተ የማይጸጸት፥ እውነተኛና ቅን የሆነ ዳኛ ነው እንጂ ዋዘኛ አይምሰልህ፤ ሕዝ. 24÷14፤ ማቴ. 7÷21-23፤ 25÷31-46:: እህልን ሠኔ ካልዘሩት ምርት በኅዳር እንደማይገኝ፥ እንዲሁም ጽድቅን የታዘዙት ካልሠሩና ካላገለገሉ፥ ካልደከሙ፥ በእምነትም ዓለምና ዲያብሎስን ተዋግተው ድል ካላደረጉ ከቶ በሰው ድካምና በዋዛ «ዘጸውዐ ስመከ፥ ወዘገብረ ተዝከረከ፥ እምሕር ለከ» «ስምህን የጠራውን፥ መታሰቢያህን ያደረገውን፥ እምርልሃለሁ::» እንደሚሉት በዋንጫ ጠላ አይገኝም:: እንደዚህ ማለታቸው ግን «ወዘሰ ይገብሮ ለኵሉ ሕግ ወይስሕት በአሐቲ ኮነ መኣብሰ በኵሉ::» «ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል::» የሚለውን ቃል አለማወቃቸው ነውና፥ መንግሥተ ሰማያት ዐሠርቱ ቃላተ ኦሪትንና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ካልሠሩና ካልጠበቁ በጽዋዐ ማይ ብቻ ምንም አይገኝም፤ 1ጴጥ. 5÷8-11፤ ያዕ. 2÷8-13::

ይህ የሕይወትና የጽድቅ መንገድ ግን ኢየሱስ ብቻ ነው እንጂ ሌላ አይደለም:: ኢየሱስ ማለትም ትርጓሜው አዳኝ የሚያድን ማለት ነው:: «ስሙ ይመርሖ ኀበ ግብሩ» እንደሚሉ ኢየሱስን እውነተኛውን መድኃኒትህን ትተህ፥ እንዳንተ በኃጢአት የተወለዱ ሰዎች የሚያድኑህ መስሎህ፥ ፍጡርን አምነህ እንዳትታለልና እንዳትጠፋ ብሎ እግዚአብሔር አምላክህ በነቢዩ በኤርምያስ አፍ «ርጉመ ለይኩን ኵሉ ዘይትአመን በዕጓለ እመሕያው (በፍጡር)፥ ወያሰምክ ቦቱ መዝራዕቶ፥ ወእምእግዚአብሔር ይርኀቅ ልቡ::» «በሰው የሚታመን፥ ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ፥ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው::» እያለ አስተካክሎ ነግሮሃል፤ ኤር. 17÷5-10:: ይህንን አምላካዊ መርገም ግን ወደህ፥ በገዛ እጅህም ወደ ራስህ አምጥተህ የማይሰማውንና የማይረዳውን፥ የማያድነውንና የማይጠቅመውን፥ እንዳንተው ፍጡር የሆነውን አምነህ፥ በፈቃድህ ነፍስህንና ሥጋህን በሲኦል (ገሃነም) በከንቱ እንዳታጠፋው፥ እውነተኛውን መድኃኒተ ነፍስ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ዛሬ መርጠህ ያዝ:: «ናሁ ሤምኩ ቅድሜከ ሕይወተ ወሞተ፤ ወኅረያ ለከ ለሕይወት ከመ ትሕየው አንተ ወዘርእከ» ብሏልና፤ ዘዳ. 30÷19፤ ምሳ. 1÷7-33፤ መዝ. 49÷7-20:: ግራ ከሚያጋባው ሐሰት አውጥቶ በቀኙ ለመቆም የሚያበቃህ ቃሉን ለመምረጥ ዛሬ በኃይሉ ይርዳህ፤ አሜን::

ምዕራፍ 15

እውነተኛ የሚያድን ተስፋ

ምእመን ወንድሜ ሆይ! እግዚአብሔር አምላካችን መጀመሪያ ለአባታችን ለአዳም ሕግ አቁሞለት ወይም ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር:: አባታችን አዳምም በዲያብሎስ ስሕተትና በሥጋ ደካማነት ተሸንፎ ይህን ቃል ኪዳኑን ስለአፈረሰ ሐዘንና ልቅሶ÷ ሞትና የዘለዓለም ኲነኔ የሚባለውን ብርቱ ቅጣት ተቀብሎበታል፤ ዘፍ. 2÷6-17፤ 3÷1-9፤ ዕብ. 9÷27::

በዚሁ አዳም ባፈረሰው የቃል ኪዳን ውል ምክንያት በአምላክና በሰው መካከል ቁሞ ሁለቱን ለማስታረቅ÷ የፈረሰውን ሕግ እንደገና ለማደስ÷ የአዳምንም ዕዳ ለመክፈልና ከአምላኩ ጋራ ለማዋሐድ የተቻለው ግን÷ ከሰማይ የወረደውና ከድንግል ተወልዶ ሰው የሆነው አንዱ አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ 1ጢሞ. 2÷5፤ ኤፌ. 2÷11-22::

ከአሁን በፊት እንደ ተናገርነው አሁንም ቢሆን አንድ ሸክላ ቢሰበር÷ አእላፋት ሸክላዎች ተሰብስበው ሊሠሩትና ሊጠግኑት እንደማይቻላቸው ሁሉ÷ አእላፋት መላእክትና ቅዱሳን የሚባሉት ነቢያትና ሐዋርያት÷ ጻድቃንና ሰማዕታት÷ ደናግልና መነኰሳት÷ ፍጡራን የሆኑት ሁሉ የአዳምን ዕዳ ለመክፈልና ሰባራውንም ለመጠገን ከቶ አይቻላቸውም:: «መጽሐፉን ገልጦ ያየው ዘንድ ለማንም አልተቻለውም::» ራእ.5÷1-14:: «ኢክህለ አድኅኖተነ ኢመልአክ ወኢብእሲ ዕሩቅ፤ ባሕቱ አምላክ ሥግው ዘክህለ ዘንተ::» «መልአክም ሆነ ዕሩቅ ብእሲ እኛን ማዳን አልቻለም፤ ነገር ግን ይህን ማድረግ የቻለ ሰው የሆነው አምላክ ብቻ ነው::» ተብሏል፤ (መጽሐፈ ሰዋስው ገጽ 253 ቊ.235 ተመልከት)::

ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ለሚያምኑት ሁሉ በአንድ ሰው (በአዳም) አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ÷ እንዲሁም በአንድ ሰው (በክርስቶስ) መታዘዝ ሁሉም ጻድቃን ይሆናሉ::» እያለ ያጽናናቸዋል፤ ሮሜ 5÷16-21:: ይህንኑ ትልቅና እውነተኛ ዋጋ ያለውን የክርስቶስን እምነት ጥለን ለራሳቸው አዳኝ የሚፈልጉትን ፍጡራንን ማመናችን ግን ከንቱ ድካምና አለ ዋጋ የሚያስቀረንም ነው፤ ዕብ.10÷3-39:: አለዋጋ መቅረታችን ብቻም ሳይሆን «እነ ውእቱ አምላክ ቀናኢ» «እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ::» የሚለውን ቃል ማፍረሳችንም ጭምር ስለሆነ÷ በሕግ አፍራሾች ቅጣት እንቀጣለን:: ስለዚህ እውነተኛውን አዳኝና አማላጅ÷ የዕዳችንን ከፋይና የሰው

ወዳጅ፥ መስቀላችንን ብቻውን የተሸከመልንን ኢየሱስ ክርስቶስን ብናምን ይበቃናል፡፡ እኛ ግን የዘለዓለም ሕይወት በክርስቶስ ብቻ እንደሆነች አምነናል፤ ዐውቀናልምና እምነትን መነጠልና መቀጠል አይገባንም፤ ዮሐ. 6፥66-69፡፡

እኛ ግን በሰው የተናቀውንና በአምላክም ዘንድ ለማዳን የተመረጠውን፥ እውነተኛውንና የማይናወጠውን መሠረት፥ ለሚያምኑትም የማያሳፍረውን ክቡር የማዕዘን ራስ ደንጊያ (ዐለት) ሕያው ክርስቶስን ብቻ እናምናለን እንጂ፥ አንዳንድ ማኅበራት «አንተ ኰኵሕ» «አንተ (ጴጥሮስ) ዐለት ነህ» የሚለውን ንባብ ይዘው፥ ኰኵሕነትን ለጴጥሮስ እየሰጡ በጴጥሮስ ድኅነተ ነፍስ እናገኛለን እያሉ እንደሚሰብኩት፥ ዐለትነትን እንደኛ ከጭቃ ለተፈጠረው ለምዉቱ ለጴጥሮስ አንሰጥም፡፡ ኰኵሕ ቢሆንማ ኖሮ እንደፎከረው ይፈጽመው ነበር እንጂ መች ሦስት ጊዜ እየማለ ፈጣሪውን ይክድ ነበር፤ ማቴ. 26፥33፤ 69-75፡፡

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! «ወኰኵሕሰ ክርስቶስ ውእቱ» «ያም ዐለት ክርስቶስ ነበረ» 1ቆሮ. 10፥4 እንደተባለው፥ ያቺ ሰዓት ደርሳ ጠላቶቹ ሊይዙት በመጡ ጊዜ «ማንን ትፈልጋላችሁ?» ብሎ ሲጠይቃቸውና «ኢየሱስን እንፈልጋለን» ሲሉት፥ «እኔ ነኝ» ብሎ ኰኵሕነቱን ገለጸ፡፡ አለቃ ጴጥሮስ ግን ከእርሱ ጋር ነበርህ ቢሉት፥ ከቶ አላውቀውም እያለና ራሱን እየረገመ ጌታውን በመካዱ ጭቃነቱን አሳይቶናል፤ ዮሐ. 18፥15-27፡፡ በግእዙ «አንተ ኰኵሕ» የሚለውን ቃል በጽርዕ ቋንቋ «ዘኰኵሕ» የሚል መሆኑንም ዐዋቂዎችን መጠየቅ ነው፤ ማቴ. 15፥18፡፡

ቢሆንም «ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕያው ያደርጋል» ተብሏልና፥ የመጽሐፍን ጠቃሚነት በመንፈስ እየመረመሩ መንፈሱን ለይቶ መያዝ ያስፈልጋል እንጂ፥ የፊደሉ ወይም የንባቡ ግዘፍ ከቶ ጥቅም ሊሰጥ አይችልም፤ 2ቆሮ. 3፥1-8፡፡

«ፔትራ» ድንጋይ ማለት ሲሆን «ስ»ን ሲቀጥል ግን በጽርዕ ቃል «ፔትሮስ» «የደንጊያ ነህ» ማለት ነው እንጂ «ደንጊያ ነህ» ማለት እንዳልሆነ ሊቃውንት አስረድተውናል፡፡ ጴጥሮስም ራሱ «በእምነት የቀረባችሁትም አናጢናዎች ወደ ናቁት፥ በእግዚአብሔር ግን ወደ ተመረጠ የሕይወት ደንጊያ ነውና፥ እናንተም የሕይወት ደንጊያዎች ሆናችሁ ብትሠሩ አምላካችሁ መሥዕዋታችሁን በክርስቶስ እጅ ይቀበላችኋል፥ በርሱ የሚያምንም አያፍርም» በማለቱ ፍጡርን አምኖ የሚመካ ዋጋው ኀፍረትና ሐዘን መሆኑን ገልጾ አስረድቶናል፤ 1ጴጥ. 2፥1-10፤ ኢሳ. 28፥16፡፡

ቀጥሎ ቅዱስ ጳውሎስም «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ እንጂ ከእናንተ ማንም በሰው እንዳይመካ።» 1ቆሮ. 1÷31፤ እንደሚለን <u>የሕይወታችን ትምክሕትና መድኃኒት አንዱ ልጁ ጌታችን÷ ወንድማችን÷ ወዳጃችንና ፈጣሪያችን ኢየሱስ ብቻ ነው።</u> ለርሱ ብቻ ክብር ምስጋና ይሁን፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ አሜን፤ 2ጴጥ. 3÷18።

ወዳጄ ሆይ! ሕግ አፍራሽ ልጆችንና የማይጠግኑንን ሽክላዎች 2ቆሮ.4÷5-7፤ አምነን ያድኑናል÷ ይረዱናል÷ ያማልዱናል እያልን ብንቀባጥር ግን÷ ለድኅነታችን ተመድቦ በጎልጎታ የፈሰሰውን ንጹሑን የክርስቶስን ደም ማቃለላችንና መርገጣችን ነው፤ በክርስቶስ ብቻ የቆመውንም የዕርቅ ውል ማፍረስ ይሆንብናል፤ ዮሐ. 3÷31-36፤ ማቴ.27÷33-54። እንግዲህ ይህንኑ በቂ የኪዳን ደም ብናፈርሰው÷ በየልቦናችንም የጥርጥር እንክርዳድ ብናበቅል÷ ዋጋችን «ሑሩ ውስተ እሳት» የሚባል ዘለዓለማዊ ሥቃይና ሐዘን ነው እንጂ÷ እንደገና የሚሠዋልን በግና ዕዳችንን ከፍሎ ለያስታርቀን የሚችል መድኃኒት ሊገኝልን ከቶ አይቻልም፤ ማቴ. 25÷41-46፤ ዕብ. 6÷4-8።

ስለዚህ በኛና በአምላክ መካከል ከጥንት ቁሞ የነበረው አባታዊ የፍቅር ሰንሰለት ባለ መታዘዛችንና ሕግ በማፍረሳችን ምክንያት ስለቈረጥነው÷ እስከ ጊዜው ድረስ ተጥለን ቈየን። የምሕረቱ ጊዜ ሲደርስ ግን እግዚአብሔር አምላካችን የጥንቱን ልጅነታችንን ሊመልስልን ስለ ፈቀደ÷ ከሴት የተወለደውን አንድያ ልጁን ልኮ ከኦሪት መርገም በተባረከው ደሙ ገዛንና ተቤዠን፤ ገላ. 4÷1-7።

ይህንኑ ተቈርጦና ተለያይቶ የነበረውን የፍቅር ሰንሰለት ግን÷ ዓለም ሳይፈጠር ለዚሁ ሥራ የተመደበው ከአብ ባሕርይ የተወለደው መለኮታዊ ጥበብ÷ ጻድቅና ንጹሕ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ካልሆነ ሌላ ሊቀጥለውና አስታርቆ ሊያድሰው የሚችል ከፍጡር ወገን አንድ ስንኳ ከቶ አልተገኘምና አልተቻለም፤ ዮሐ. 8÷57-58፤ ሮሜ 16÷25-27፤ ኤፌ. 1÷14፤ ቈላ. 1÷23። ስለዚህም «ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር÷ ወቦቱ ሠመርኩ፤ አሐዱ ውእቱ ኅሩይ ማእከለ እግዚአብሔር ወሰብእ።» «በእርሱ ደስ የሚለኝ÷ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤. . . በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ።» ማቴ. 3÷17፤ 1ጢሞ. 2÷5፤ ተብሎ የተሠየመና የተመረጠ እውነተኛ አስታራቂ ስለ ተገኘልን÷ በርሱ ብቻ የጥንቱ ልጅነታችን እንደገና ተመለሰልን፤ ሉቃ. 15÷11-32።

እርሱን ብቻ አምነን የወንጌሉን ቃል ከፈጸምን ግን ከርሱ ጋራ መንግሥተ ሰማያት ገብተን የብርሃን ሉል ጨብጠን÷ የሚያንፀባርቅ ዘለዓለማዊ ዘውድ ደፍተን÷ በቀኙ ለማቆም የሚያበቃን ባለሥልጣኑ የተሰቀለልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ራእ. 2÷7-17፤ 2ጢሞ. 4÷8::

ወደ መንግሥተ ሰማያት በፍጡራን አማላጆች አማካይነት መግባት የሚቻል ቢሆን÷ አምላካችን «በአማላጆች በኩል አድርጋችሁ ኑ!» ለማለት ምን ያዳግተው ነበር? እስከ መስቀል ሞትስ ምን ያደርሰው ነበር?

እርሱ ግን «ኃጢአታችሁ እንደ ከሰል ቢጠቁር እንደ ነጭ ባዘቶ ጥጥ÷ እንደ ደም ቢቀላም እንደ በረዶ አድርጌ አነጻዋለሁና÷ የኃጢአት ሸክም የከበዳችሁ ሁላችሁም ወደኔ ኑ! እኔ አሳርፋችኋለሁ:: የሰርየት ማእድም አዘጋጅቼላችኋለሁና አሳርፋችሁ ዘንድ ወደኔ ኑ!» እያለ ይናገራል እንጂ÷ ከቶ ወደ እናቴና መላእክቴ÷ ወደ ጻድቃኔና ወደ ሰማዕታቴ ሂዱ አላለም፤ ኢሳ. 1÷18፤ ማቴ. 11÷28፤ 22÷1-4::

ኢየሩሳሌም አምላኳን ትታ ሌሎች የማያድኑ አማልክትን ለማምለክ ስትባክን ስለአያት÷ በመንገድሽ ብዛት ብትደክሚ÷ የነፍስሽን ጽምአት የሚያረካ የሚያሳርፍሽ ፈውስ ከቶ አላገኘሽም::» እያለ ሲዘልፋት ነበር፤ ኢሳ. 57÷5-13::

ስለዚህ ለዓለም ሁሉ የሚበቃውን የክርስቶስን የደሙን መድኃኒትነት ትቶ ሌላ መፈለግና መጨመር ግን÷ የክርስቶስ የጸዕሩና የሥቃዩ ፍሬ ሳይሆኑ መቅረትና ከጸጋውም ጎድለው የኪዳኑን ደም እያቃለሉ ማየት÷ አምላክንም እያሳዘኑና ሳይታረቁት በጥርጣሬ ሥቃይና ሐዘን ውስጥ ተውጦ ለዘለዓለሙ እያለቀሱ መኖር ይባላል፤ ዕብ. 6÷4-8::

መጽሐፉ የሚለው ግን «የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል፤ በመስቀሉ ደምም በምድርና በሰማያት ያሉትን ፍጥረቶቹን ለራሱ ታረቃቸው:: ኢየሱስ ወደደን፤ ከኃጢአታችንም ሁሉ በደሙ ዐጠበን፤ ልብሰ ኃጢአታቸውንም በበጉ ደም ዐጥበው አነጹት::» ብቻ ነው፤ 1ዮሐ. 1÷7፤ ቈላ. 1÷20፤ ራእ. 1÷5-7፤14::

ከነጹና ከዳኑ ወዲያ ሌላ የሚያነጻና የሚያድን ፈውስ በሐሳብ መፍጠርና መፈለግ ግን ከአምላክ ጋር እየተላለኩ ፍሬ የማይገኝበትን ከንቱ ሐዘንና ድካም መጨመር ነው፤ ኤር. 18÷11-16፤ ማቴ. 21÷33-40፤ 23÷37-39፤ ኢሳ. 1÷3-8::

ወንድሜ ሆይ! ሸክላስ ሸክላ ነው፤ ያመነባትን ሁሉ የምታድን የሕይወት ምንጭና የደስታ ዕረፍተ ነፍስን የምታስገኘው የክርስቶስ ወንጌል ብቻ ናት እንጂ፥ ለማታለያ የተፈጠሩት ሌሎች ፈውሶች ሁሉ ውሃ ይይዙ ዘንድ የማይችሉ፥ በኃጢአት የተቀደዱ ጉድጓዶች ናቸው፤ ኤር. 2፥13፤ ዮሐ. 4፥13፤ መዝ. 36፥9::

ስባረ ነፍሳችንን ጠግኖ፥ በዕፀ በለስ ሽምጥና ጋሬጣ የተቀደደውንና ያረጀውን ልብሳችንን አስወግዶ፥ ስለ አዳም ዕዳ ቤዛችን ሆኖ፥ የፊተኛውን ቃል ኪዳናችንን በደሙ አድሶ ጽድቁን የሚያለብሰንና ዘለዓለማዊ መንግሥቱንም የሚያወርሰን ግን መድኃኔ ዓለም ብቻ ነው፤ ኤፌ. 1፥4-11፤ 4፥20-24::

ስለዚህ እውነተኛውንና የሚያድነውን ሕያው ተስፋ መርምሮ፥ ተገንዝቦና ይዞ፥ ወደ ሰማያዊ አገራችን በሙሉ እምነት ሳንወላውል በወንጌልና በክርስቶስ ጎዳና መጓዝ ይገባናል:: እርሱም እጃችንን ይዞ እንደሚመራን እርግጠኛና ታማኝ ነው፤ ዘፍ. 19፥16፤ ዘዳ. 32፥1-14፤ መዝ. 139፥10::

ከፍጡር ወገን ለፍጡር አዳኝና ገላጋይ፥ መጠጊያና ረዳትም ለመሆን የሚችልና የሚበቃ እንዳልተፈጠረና እንደማይገኝም አንድ ሊቅ በሚከተለው ቅኔ አስረድቶናል: -

መወድስ

አይቴ ናሰምክ ውሉደ ዐመፃ
ዘተመዝበረ ልብነ በግብረ ዐመፃ ነፉስ
እምትዕይንቱ ሰማይ አመ ይመጽእ ንጉሥ
በንጥረ መብረቅ ረዋጺ ፈረስ
እንዘ መደንግጽ ይለብስ
ከመ ዐማፅያነ ያጥፍእ በግብረ ተሰናን ወባእስ
ኀዳጠዊ ኢንጸወን በደብረ ጽዮን ሐዳስ
ጽዮን ለርእሳ ጸወነ ተኀሥሥ
ወበውስተ ሰማይ ኢንግበር ማኅደረ ሥጋ ወነፍስ
ሰማይ ለርእሱ ምስለ ምድር ይደመሰስ
ኢሳ. 13፥6-16፤ 24፥1-23፤ ራእ. 6፥12-17፤

ትርጓሜ: - «በዐመፅ ሥራ ነፋስ ልባችን የተመዘበረብን (የፈራረሰብን) የዐመፃ ልጆች ንጉሡ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በዳግም ምጽአቱ በዐመፀኞች ላይ ሊፈርድ፥ ከሯጭ ፈረስ ይልቅ በሚፈጥን የመብረቅ ብልጭታ፥ በሚያስደነግጥም ግርማ ከሰማይ ሲገለጥ በዐመፅ ሥራ ነፋስ ልባችን የተመዘበረብን (የፈራረሰብን) የዐመፃ ልጆች ምን መጠጊያ እናገኛለን? ወዴትስ እንጠጋለን? እምባ መጠጊያ ናት ብለን

ወደ ጽዮን እንዳንጠጋ ጽዮንምኮ በዚያን ጊዜ ለራሷ መጠጊያ ፈላጊ ናት። ማደሪያችንን ከምድር ጋር በተፈጠረው ሰማይ እንዳናደርግም ራሱ ሰማይ ከምድር ጋር የሚደመሰስ (የሚያልፍ) ይሆናል።»

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም በ146ኛው መዝሙሩ «ተአኰቶ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፤ ኢትትአመኑ በመላእክት ወኢበእጓለ እመሕያው እለ ኢይክሉ አድኅኖ ትወጽእ ነፍሶሙ፤ ወይገብኡ ውስተ መሬቶሙ፤ ውእተ አሚረ ይጠፍእ ኵሉ ምክሮሙ። ብፁዕ ብእሲ ዘአምላከ ያዕቆብ ረዳኢሁ፤ ወትውክልቱኒ ላዕለ እግዚአብሔር አምላኩ። ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ወባሕረ ወኵሎ ዘውስቴቶሙ። ዘየአቅባ ለጽድቅ ዘለዓለም።» «ነፍሴ እግዚአብሔርን አመስግኚ፤ . . . ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና በአለቆች አትታመኑ፤ ነፍሱ ትወጣለች፤ ወደ መሬቱም ይመለሳል፤ ያን ጊዜ ምክሩ ሁሉ ይጠፋል። የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ፥ ተስፋውም በአምላኩ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ምስጉን ነው፤ እርሱም ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ በእነርሱም ያለውንም ሁሉ የፈጠረ፥ እውነትን ለዘለዓለም የሚጠብቅ ነው።» እያለ መናገሩ ያባቶቹ የኖኅንና የአብርሃምን፥ የይሥሐቅንና የያዕቆብን ጽድቅ ረስቶ ይመስላችኋልን? የአዳም ልጆች በሙሉ በኃጢአት እርሾ የተቦኩ ሸክላዎች ስለሆኑ፥ በሞታቸው ጊዜ ምክራቸው ሁሉ የጠፋባቸው ሰባራዎች ብቻ መሆናቸውን ስላወቀ አይደለምን? ስለሆነም «በፍጡራን አትታመኑ፤ ጽድቅን ለዘለዓለም የሚጠብቃትን አንድ እግዚአብሔር ብቻ እመኑ በርሱ ተወከላችሁ (ተስፋ አድርጋችሁ) ዳኑ» ይለናል።

ስለዚህ ትልቁ የአድኅኖ ነገር ዋጋው ምን ያህል እንደሆነና ባለቤቱም ማን እንደሆነ መርምረንና ለይተን፥ ዐውቀንና ተረድተን፥ እውነተኛውን የመድኃኒት መስቀል የተሸከመውን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን ብቻ ብንይዝ ይበቃናል። በእርሱ ላይ ሌላ መጨመር ግን ርኵሰትና ግልሙትና ይባላል፤ ኢሳ. 57፥3-8።

ይህ ሁሉ የሚሆነውና የሚገኘው ግን፥ ከመንፈስ ዳግም ተወልደው፥ ከአርያም ኃይልን ለብሰው፥ የመንፈስ ቅዱስ ኩል ተኩለው፥ ዓይነ ልቦናን አጥርተው በቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ አምነው ሲመሩ ነው። አለበለዚያ የፍጡርንና የፈጣሪን፥ የሚያድነውንና የማያድነውን መድኃኒት፥ የጽድቅንና የኃጢአትን፥ የእውነትንና የሐሰትን፥ የሲኦልንና የገነትን ጣዕም ለይቶ ለማወቅ ከቶ አይቻልምና ዕውቀቱን በመንፈሳዊ ኃይሉ ይግለጽልን አሜን፤ ዮሐ. 3፥1-12፤ ሉቃ. 24፥45-49፤ 2ጢሞ. 3፥14-17፤ ራእ. 3፥14-22።

ምዕራፍ 16

መጠርጠርና መመርመር

የግል ወዳጄ ሆይ! ሰው የተፈጠረው ጽድቅና ኃጢአት የሚዋጉበት የመከራ ዐውድማ እንዲሆን ነውና፥ ጸሎትና ትዕግሥት የሚባሉትን ሁለት መሣሪያዎች ይዘህ፥ ነቅተህና ታጥቀህ ጠብቀው:: ፈተና አደጋ ጣይ ወንበዴ መስሎ በድንገት ማርኮ የሕሊና ረመጥ በሕይወትህ እንዳያፈስብህ መከላከያውን ዕወቅበት፤ ያዕ. 1፥1-15:: የወርቅን ዝገት እሳት ለይቶ እንደሚያጠራው እንዲሁም በጥርጣሬ ውስጥ ለሚኖረው የግብዝ ሰው አምልኮ ባለቤቱ በአስፈለገው ጊዜ ከእቶን መከራ አግብቶ ይታዘበዋልና በውል አስብበት፤ ኢሳ. 48፥10፤ 1ጴጥ. 1፥5-7:: ፈተናን የሚያመጣው ግን ሥጋዊ ምኞትና ዓለማዊ ፍትወት ቢሆንም ቅሉ፥ ሰው የሚፈተነው በዐቅሙ ልክ ነው እንጂ ከዐቅሙ በላይ እንደማይፈተን አስተውል፤ 1ቆሮ. 10፥13:: ስለዚህ ለማናቸውም ነገር የምትጐመጅ አትሁን፤ መጐምጀት በልብህ ከበቀለ ግን የገሃነምን ቁልፍ በእጅህ ይዘሃልና ከፍቶ ለመግባቱ ምንም እንዳልቀረህ አትዘንጋ:: የጨለማው ጌታ (ሰይጣን) አንተን ለማታለል መልኩን ለውጦ የብርሃን መልአክ መስሎ፥ እንደ ዮናስ ቅል በቅጽበት የሚጠወልገውን የዓለም ብልጭልጭታና ውበት ይዞ፥ ለጥፋትህ የሚሆን አሽክላ ለመዘርጋት ይመጣልና፥ ማንነቱን አውቀህ፥ የጥፍር መግቢያ ታህል ቀዳዳ አጥቶብህ፥ ኀፍረት ምሱን ለብሶ እስከሚሸሽ ድረስ ጠንክረህ መዋጋት አለብህ:: በዚህ ጊዜ የሚያስፈልግህ ግን ከምትወዳቸው አካላቶችህ ዐይንና እጅ፥ እግር ወይም ሌላ አካልህንም ቢሆን በሐሳብ ቈርጦ መጣል ካልሆነ ሌላ ድል የምትነሣበት መሣሪያ ከቶ አታገኝም፤ ማቴ. 5፥27-32፤ 2ቆሮ. 11፥13-15::

ወንድሜ ሆይ! ሀብት ፈልጎ ሲያገኝህ መልካም ነው እንጂ ከዐቅምህ በላይ በሆነ ድካምና ሐሳብ ፈልጌ አገኘዋለሁ ብለህ አትድከም:: ቢሆንም ተስፋ አትቍረጥ፤ ድሃ ወይም በሽተኛ ብትሆንም ሁሉም ነገር ስጦታ ነውና፥ ፈጣሪህን አመስግንበት እንጂ ዕድልህን እየረገምህ አታማርር:: የዓለምን አኗኗር ቻልበት፤ ሁሉንም በለይኩን ፈቃድከ (ፈቃድህ ይሁን በማለት) ወስነው:: ኀዘንና ደስታም ለሰው ሕይወት ድርና ማግ መሆኑንም አትርሳ:: የገንዘብ ጌታ ነህና የገንዘብ ባሪያ እስክትሆን ድረስ አትሰስት:: ለዘወትር እኖራለሁ እያልህ ምድራዊውን ሀብት በትጋት አትሰብስብ፤ ነገ እሞታለሁ ብለህ እያሰብህም በሰማይ የምትሰበስበውን ሰብል (ስንቅ) ዛሬ በከርሠ ርኁባን (በተራቡ ሰዎች

ሆድ) ዝራ:: በኀላፊው አገር ለጥቂት ጊዜ ስትኖር÷ ፀሐዩ የማይጠልቅ ብርሃኑ የማይለወጥ÷ ዘወትር ደስታ የሚፈልቅበት÷ ኀዘንና ልቅሶ የማይገባበት÷ ረኀብና ጥማት የሌለበት÷ ኪራይ የማይከፈልበት÷ መሠረቱ ኢያስፒድ÷ ጠፈሩ አሜቴስጢኖስ ተብሎ የተሠየመ÷ በወርቅና ሉል የተሸለመ አስደናቂ የሆነ ዘለዓለማዊ ቤት ዛሬ በጥቂት ገንዘብ ሥራ፤ ራእ. 21÷10-27::

ጌታው አቶ ምእመን ሆይ! ይህንኑ ከዚህ በላይ የጻፍኩልህን ቃል ሁሉ÷ በሕገ ተፈጥሮ ቋሚነት ያለውና በሰው ልቡና ውስጥ (በአንተና በእኔው ሕሊና)÷ በአምላካዊ ምስጢር ጉልህ ሆኖ ተመዝግቦ የተጻፈውን አነበብኩልህ እንጂ÷ በሥጋዊ መጠበብ ከሕግ ውጪ የተለቃቀመ ወሬ አለመሆኑን የተረዳኸው ሁን:: እንደዚህም ብዬ ስነግርህ ይልቁንም መንፈሳዊና ነፍሳዊ የተባለው ነገር ጥልቅና ረቂቅ ቢሆንም ቅሉ÷ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈሳዊ መራቀቅ እየተመሩ የጻፉትን ቅዱስ መጽሐፍ መስተዋትና መሪ መነጽር አድርገህ÷ አንተ እኔን÷ እኔም አንተን ብንነባበብ እውነቱን በየሕሊናችን ለማግኘት እንችላን እንጂ÷ «ማየ ሰሊሆም ዕውር ኀበ ወሰድዎ የሐውር» «ዕውር የሰሊሆም ውሃ ወደ ወሰዱት ይሄዳል::» እንደ ተባለው ተረት ሰው ነህና÷ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ካልሆነ የሰውን መሪነትና ምክር ከማመኑ ይልቅ መጠርጠሩ ይሻልሃል:: ስማኝ ሰዎች ውሸትን ደብለቅ እያደረጉ ጽፈው ያቀረቡልህን ወሸካታ ወሬ ሁሉ ሳትመረምርና በልቡናህም ውስጥ አግኝተህ ሳትረዳው ዓለምን ለመምሰል በዘልማድ ብትቀበለው÷ ሃይማኖት የግል ናት የተባለውን ትምህርት መርሳትና ማፍረስ ይሆንብሃል:: ይህን የኔውን ምክርም ቢሆን ጠርጥረውና መርምረው::

ትዕቢት የእግዚአብሔር ጠላት÷ የዲያብሎስ መሣሪያ÷ የድንቁርና ዘውድ ናትና÷ ትሕትና በተባለው ሰይፍ ቈርጠህ ከነሥርዋ ነቅለህ ከሕይወትህ ውስጥ አውጥተህ ጣላት፤ 1ጴጥ. 5÷5-7::

የሀገሬ ልጅ ሆይ! አስቀድመህ እውነተኛውን የወንጌል መብራት አብርተህ÷ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን በዚህ በጨለማ ዓለም ውስጥ ተግተህ ፈልጋት:: እርስዋም ይኸውና በአንተው እጅ ውስጥ ስለሆነች÷ ወደ ሰማይ ወጥቶ ወይም ባሕርን ተሻግሮ ሊያመጣልኝ ማን ይችላል? ብለህ እንዳትጠይቅ ጥቅሶችን በጥንቃቄ ተመልከትና መርምር፤ ዘዳ. 30÷8-20፤ ማቴ. 6÷31-34::

ሊቁ ዘርዐ ያዕቆብ ሲመራመር «እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ሃይማኖቶችን ያበዛቸው ስለምንድር ነው? አንድ ሃይማኖት ማድረግ አቅቶት ነው?» ብሎ ጠይቆ ሲያበቃ «አይሳነውም፤ ነገር ግን ስዎች ሐሰትን አምነው ሐሳበ አልቦ ሆነው ዝም እንዳይሉ÷ ወደ

እውነተኛው አምላክ የሚያቀርብአቸው እውነተኛው ሃይማኖት፥ የትኛው መሆኑን እንዲመረምሩና መርጠው እንዲይዙ ብሎ ነው ያበዛው:: ነገር ግን ሰው ለሥጋው እያደላ፥ እውነተኛውንና መንፈሳዊውን ነገር ችላ ባይ ስለሆነ፥ በሥጋው በኩል ተስማሚ የሆነውን ሁሉ ሃይማኖቴ ብሎ ይኖርበታል::» (ዘ.ያ.ክ.4 ገጽ 8 ክፍል 7 ገጽ 13 ተመልከት) ሲል ራሱ በራሱ መልስ ሰጥቶበታልና፥ አንተም የዐቅምህን ያህል ከመረመርህ እውነተኛ ይቱን ነገር እውነተኛው አምላክ እንደሚገልጽልህ በመረዳት፥ ሁሉንም ጠርጥረው፤ መርምረውም:: «ለሥጋው የዘራ ጥፋትን፥ ለነፍሱ የዘራ ግን የዘላለም ሕይወትን ያጭዳልና::» የነፍስ እንጂ እንደ እንስሳ የሥጋ ደጋፊ ብቻ እንዳትሆን ተጠንቀቅ ገላ.6፥1-9::

በዛሬው ጊዜ የኢሳይያስ ትንቢት ተፈጽሞበትና የእንቅልፍ መንፈስ ወድቆበት ካልሆነ፥ እውነትን ከሐሰት ለይቶና መርምሮ ለማወቅ ማንም ሰው ያዳግተዋል ብዬ አልጠረጥርም፤ ኢሳ. 29፥9-16::

ስለዚህ ልግም በገላ እንጂ በነፍስ ስለማያስፈልግ፥ በግብር ያልተገለጠ ዕውቀትና ሊቅነት ከበጎ ምግባርና ከክርስቲያናዊ ፍሬና ጸጋ ሊያደርስ ከቶ የማይቻል ነገር ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ የስም ክርስቲያኖችን (ወረተኞችን) ሲዘልፍ፥ «መጀመሪያ ልማድ ከተባለው ሕግ ለጊዜው ተለይተው፥ የወንጌልን ብርሃን ተካፍለው ሲያበቁ፥ እንደገና በግብዝነት አተላ ወደ ተቦካው ጨለማዊ የሰው ሥርዐት የሚነከሩና ወደ ኋላ የሚመለሱ ሰዎች የእርያና የአሳማ ባሕርይ አድሮባቸዋልና ዱሮውንም ባያውቁት ይሻላቸው ነበር::» ሲል አስደናቂ ምክሩን ትቶልናል፤ 2ጴ. 2፥9-22::

ሃይማኖትህን ግን የሃይማኖት ጌታ ብቻ ይወቅልህ እንጂ አንተን የመሰሉ ልቡሳነ ሥጋ ቢነቅፉህ ወይም ቢያመሰግኑህ ከእነርሱ ጥቅምና ጉዳት እንደማታገኝበት በጥልቀት ዐስብ:: ሃይማኖት ሲባልም ዐላማውና ግቡ ሰውን ሁሉ እንደ ራስ አድርጎ ማየት፥ ጠላትንና ወዳጅን ሳይለዩ ሁሉንም በችግሩ ጊዜ መርዳት ብቻ ነው፤ ማቴ. 19፥16-21፤ ያዕ. 1፥27፤ ሉቃ. 10፥25-37::

ወደጄ ሆይ! መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝና፥ የሚከተለኝም ሁሉ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይሄድም::» ብሏል፤ ዮሐ. 8፥12:: ስለዚህም እንኳን የዛሬዎቹና የዱሮዎቹም ሐዋርያት ምንም ለጊዜው «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ቢባሉ፥ አሕዛብን አስተምረው ከአምልኮ ጣዖት ወደ ክርስትና ስለ መለሱ የብርሃንን መንገድ አሳዩ (አመለከቱ) ይባላል እንጂ፥ ለሰው ሁሉ የሚያበሩ እውነተኞች ብርሃን ናቸው ማለት አይደለም:: «ከሴቶች ልጆች ከሚወለዱት

ሁሉ ዮሐንስን የሚመስለው የለም።» የተባለው መጥምቁ ዮሐንስ እንኳ፥ ብርሃን እንዳይደለ ራሱ ወንጌሉ መስክሯል ዮሐ. 1፥9። አሁን ግን ቅዱስ ዳዊት «የሕይወት ምንጭ በአንተ ዘንድ ነውና፥ በአንተውም ብርሃን ብርሃንን እናያለን።» መዝ. 36፥9፤ 43፥3፤ ብሎ እንዳስተማረን፥ እውነተኛውን ነገር ለመረዳት ልባችንን በትጋት ከፍተን «ወደ መቅደስህ እንዲመሩኝ ብርሃንህንና እውነትህን ላክልኝ።» መዝ. 43፥3 ብለን ብርሃን የሆነ ጌታን ብንለምነው፥ እርሱ ጸጋውን ሊሰጠን እጁ የተዘረጋ፥ ጆሮውም ሊሰማን ዘወትር የተከፈተ መሆኑን አትርሳ፤ ኢሳ. 59፥1። ቢሆንልህ ዘወትር፥ ያም ቢቀር ለዕረፍተ ሥጋ የተመደበችውን ቀን እሑድን ስለነፍስህ ነገር በውል ዐስብባት፤ አንብብ፤ መርምር፤ አስተውል። ለኀላፊውና ለማይጠግበው ሥጋህ ብቻ አትሳሳ፤ ዮሐ. 6፥25-30። እንደ አምስቱ ሰነፎች ደናግል የጸጋ ሰዓት እንዳያልፍብህና የምሕረት በር እንዳይዘጋብህ ተጠንቀቅ፤ ንቃም። የተኙትንም ቀስቅስ፤ ማቴ. 25፥1-13።

አምላካችን የተወልንን ቃል ስማኝ ልንገርህ፤ «እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህና በምትሄድበት መንገድ የምመራህ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ።» ኢሳ. 48፥17። «እንደርሱ የሚያስተምር የለም።» ኢዮ.36፥22። «መምህራችሁ አንድ ብቻ በሰማይ ያለው ነውና፥ እናንተ ግን ከቶ መምህራን ተብላችሁ እንዳትጠሩ፤ ከኔ ብቻ ተማሩ።» ማቴ. 11-29፤ 23፥8። «መንፈስ ቅዱስን እሰድላችኋለሁ፤ እርሱ ካደረባችሁ ያስተምራችኋል፤ ወደ እውነትም ይመራችኋል፤ ያልኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል።» እያለ ይመክረናል፤ ዮሐ. 14፥26።

አቶ ምእመን ሆይ! ይህን እውነተኛ ቃሉን ተቀብለህ በእርሱ መሪነትና አስተማሪነት እውነተኛውን ነገር መርምረህ አግኘው እንጂ፥ ሰማያዊውን ምስጢር በምድራውያን ዘንድ አገኘዋለሁ ብለህ ብታስብና ብትዳስስ፥ ነፋስን እንደ መጨበጥ እንዳይሆንብህ በውል ዐስብበት። የክርስቶስ ማደሪያ መሆንህንና በእውነተኛው ሃይማኖት መቆምህን ግን ራስህን በራስህ መርምረው፤ 2ቆሮ. 13፥3-7፤ ሰቆ. ኤር. 3፥39-41።

ወዳጄ ሆይ! እንግዲህ ሰው መሆንህን አትርሳ። ክርስቶስ በብርሃነ ወንጌሉ ነጻ አውጥቶሃልና ለሰው ሥርዐትና አሮጌ ልማድ ከቶ እንዳትገዛ በአምላካዊ ነጻነት ብቻ ጽና፤ ዮሐ. 8፥31-32፤ ገላ. 5፥1። አንተን ባለአእምሮና ዐዋቂ አድርጎ የፈጠረህ ጌታ «ይህ ሰው፥ በሰው ሥርዐትና ትእዛዝ እየተመላለሰ በከንቱና ግብዝ በሆነ ከንፈሩ ያመልከኛል። ልቡ ግን ከኔ በጣም አስረዘሞ የራቀ ነው።» ብሎ እንዳይነቅፍህና በዘለዓለም ኵነኔ እንዳይፈርድብህ፥ ዛሬ

ክርስቲያናዊ ስምህ በመጽሐፈ ሕይወት የሚጻፍበትን ዘዴ ነቅተህ ፈልግ (ዐስብ) ተጠንቀቅም፤ ማቴ. 15÷1-9:: ልዝቡንና ቀላሉን የክርስቶስን ቀምበር በጋለ ፈቃድና ፍቅር ብትሸከም÷ በነፍስህና በሥጋህ ዕረፍት ታገኛለህ፤ የሰው ሥርዐትና ልማዳዊ የጥርጥር ትብትብ ብትከተል ግን÷ ስቃይና ሐዘን ካልሆነ ከቶ ሌላ ጥቅም እንደማታገኝበት በቃሉ አረጋግጥልሃለሁ፤ ማቴ. 11÷28-30፤ 23÷1-4፤ ራእ. 20÷11-15::

ወንድሜ ምእመን ሆይ! እንካ ይህን እውነት የሆነውን÷ ከቃለ እግዚአብሔር የተጠቀሰውንና የመነጨውን መጽሐፍ አዘውትረህ አንብብ፤ ጠጣ፤ እርካ:: አሁን በሥጋዊ ሐሳብህ ከእሬትና ኮሶ ይልቅ መራራ መስሎ ቢታይህም÷ በመንፈሳዊ ሕሊናህ ብትመረምረውና ብታስተውለው ግን÷ መናፍስተ ሐሰት በሕይወትህ ውስጥ ያበቀሉትን የእንክርዳድ ትል ሁሉ ገድሎ÷ ጤነኛና ሕያው መንፈስ ሰጥቶ÷ ወደ ዘለዓለማዊው የሕይወት አገር የሚያደርስህ መሪና ፍቱን መድኃኒተ ነፍስ ነውና÷ በትጋትና ቅንዓት አንብበህ ከተረዳኸው በኋላ÷ ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፈጠው፤ ከማርና ከማር ወለላም ይልቅ ለአፌ ጣመው እያልህ ፈጣሪህን ፍቅርና ደስታ በተሞላ ልብህ እንደምታመሰግነው አምኜ÷ ለበረከት እንዲሆንህ እየተመኘሁ በብዙ ድካም ጽፌ ለሀገሬ ልጆች ገጸ በረከት ማቅረቤ÷ ያለኝን መስጠቴ መሆኑን እገልጽልሃለሁ፤ የሐዋ. ሥራ 3÷6::

ወዳጄ ሆይ! ዓለም መካሪውን እንደሚጠላ ሁላችሁም በክርስቶስ ላይ የደረሰውን ሁሉ አይታችሁታልና÷ እኔም ደግሞ በትንሹ ዐቅሜ አገሬ÷ ይልቁንም ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያናችን ከእንቅልፏ ተነሥታ÷ የወንጌልን መብራት አብርታ÷ የቤቷን ጉድፍ ጠርጋና አሰናድታ÷ በቃለ እግዚአብሔር ሳሙና÷ በልማድ ያደፈውን ልብስዋን ዐጥባ÷ ንጽሕት ሁና እንድታምርና እንድታጌጥ ብዬ÷ ሕፃናዊ በሆነው ትምህርትና በአልበሰለው አእምሮዬ ጥቂት ኃይለ ቃላትን ጨመር አድርጌ ስለ ዘለፍኋት÷ ባለማወቋ ክፉ ስም ሰጥታ እንደምታዝንብኝና እንደምትጠላኝ አልስተውም:: እኔ ግን «እናትህ በአረጀች ጊዜ አትናቃት::» ምሳ. 23÷22፤ «ክፉውን በበጎ አሸንፉት እንጂ አትቃወሙት::» ሮሜ 22÷18-21፤ «ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግምዋችሁን ባርኩ፤ ስለሚያሳድዱዋችሁና ስለሚጠሏችሁ ጸልዩ::» ማቴ. 5÷44 የሚለውን ቃል ተምሬአለሁና ከቶ አልቀየማትም:: የሐሳቤ መነሻና መገስገሻ÷ መድረሻና መመለሻም እናቴ መንፈሳዊና ሥጋዊ ዓይኗን ከሰማይ በወረደው ኵል ተኵላ÷ በቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ተወልውላ÷ ባለማወቅ ስለሠራችው ኃጢአትዋ በክርስቶስ እጅ ስርየት ተቀብላ÷

ወደማያልፈው ርስቱ እንዲያስገባትና ለሰማያዊ መንግሥቱ እንዲያበቃት ጸሎቴን ወደ ፈጣሪዬ በማቅረብ፥ በጎውን ነገር ብቻ እመኝላታለሁ እንጂ፥ እርሷ ብትጠላኝ «አባት እናቱን ያልተወ የኔ ተማሪ ሊሆን አይችልም።» ሉቃ.14፥26፤ የተባለውን ባታውቅ ነውና እኔ አልጠላትም። ብትጠላኝስ እኔ በማን ጡት አደግሁና ነው እርሷን የምጠላ! እውነት ነው ንጹሕና ነጭ የሆነውን የጤፍ እንጀራ (ወንጌልን) ባገኘሁ ጊዜ፥ የተፍረቀረቀውን የዘንጋዳ ቂጣዋን (ገድል ተአምርዋን) አምዘግዝጌ በመጣሌ ብትቀየመኝ፥ ይቅርታዋን ብቻ ከምለምናት በቀር ሌላ የምጠይቃትና የማደርግላት ነገር እንደሌለኝ ሕሊናዬና አምላኬ ያውቃሉ፤ መዝ. 137፥5-6። ጳውሎስ ከሕግ ውጪ የሆነው ነገር ይጠቅመኛል ብዬ ይዤው ነበር፤ ነገር ግን ክርስቶስን ከአገኘሁት በኋላ የአባቶቼን ሥርዓት ሁሉንም እንደ ጉድፍ ቈጠርሁት ይላል፤ ፊል. 3፥4-10።

ዛሬ ግን የዓለም ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን መረጡ። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ሥራው እንዳይዘለፍ ሲል ወደ ወንጌል ብርሃን አይመጣምና፤ የሚዘልፈውንም ሰው ይጠላል፤ ዮሐ. 3፥19-21። ዓለም ወገኑን ይወዳልና እናንተ ግን ከዓለም ወገን ስለአልሆናችሁ ዓለም ይጠላችኋል። ዓለም ቢጠላችሁም በዚህ አትደነቁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ፤ ዮሐ. 15፥16-21። የእናቴ ልጆች በወደድኋቸውና ተግሣፅና ምክርን በጻፍሁላቸው ፈንታ ያለምክንያት በከንቱ ጠሉኝ፤ መዝ. 109፥1-5። እኔ ግን ስለ ወገኔ ልጆች ጨነቀኝ፤ ታድያ ለማን እነግራለሁ? ለማንስ እስመሰክራለሁ? ይሰሙ ዘንድ እነሆ ጆሮአቸው ስላልተገዘረች መስማት አይቻላቸውም። ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ፥ ከተማሪው እስከ ሊቁ ድረስ ሁሉም በንፍገትና በተንኰል፥ በሐሰትና በማታለል ይመላለሳሉ፤ የእግዚአብሔርም ነገር ስድብና ነውር ሆኖባቸው አይወዱትም፤ ሌትና ቀንም አይመረምሩትምና ፈሪሳውያንንና ጸሐፍትን ያገኘው ፍርድ እንዳያገኛቸው ቸሩ ፈጣሪ የልብ ጆሮቻቸውን በሕያው ቃሉ ከፍቶ እንዲፈውሳቸውና እንዲምራቸው እየለመንሁ በሙሉ ልቤ በጎውን ነገር እመኝላችኋለሁ፤ ኢሳ. 6፥8-10፤ ኤር. 6፥10-17፤ 2ቆሮ. 3፥3-18።

ወንድሜ ሆይ! የዕድሜ ልክና የልብ እንጂ የወርና የዓመት የዘመንና የዕለት (የስም) ክርስቲያን እንዳትሆን ተጠንቀቅ። ይህንንም ስልህ በአንተ ውስጥ ምን ዐይነት ሕይወት እንዳለ መርምር። ለነፍስ እንጂ ለሥጋ ሳታደላ ራስህን በራስህ መዝነህ ዕወቀው። መንገዳችንን እንመርምርና ወደ እግዚአብሔር እንመለስ። እርሱም በኃይሉ ይርዳን፤ አሜን፤ ሰቆ. ኤር. 3፥40።

ምዕራፍ 17

ስለ ማሠርና መፍታት

«ዘአሠርክሙ በምድር ይከውን እሡረ በሰማያት::» «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል::» ማቴ. 18÷15-18::

ማሠርና መፍታት ማለት ለንጹሓን ሐዋርያት የተሰጠ ሥልጣን ነው:: ይህንኑ መንፈሳዊ ሥልጣን ግን ሐዋርያት እንደሠሩትና እንዳስተማሩት ድዉይ እየፈወሱ÷ ምዉት እያስነሡ÷ አስቀድሞ እነርሱ ሕግን ጠብቀው ንጹሐን ስለሆኑ በሕግ የማይሄዱትንና ክርስቶስን የሚክዱትን ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ምስጢራት እንዲለዩ የተሰጣቸው ሲሆን÷ ዛሬም አሰራቸውን ተከትለው ለሚሄዱ ቀሳውስት የተሰጠና የሚገባም ነው::

ፊተኞቹ የክርስቶስ ተከታዮች ሐዋርያት ግን የበደለውንና የተሳሳተውን እንኳንና አውግዘው (አስረው) ከማኅበር ከመለየት ይልቅ ታግሠው በዕውቀትና ርኅራኄ÷ በፍቅርም አስተምረውና አስረድተው እንዲድኑልን በማለት ከሁሉ ሰው ጋር እንደነርሱ ሆንን 1ቆሮ. 9÷19-23 እያሉ÷ ይመልሷቸው ስለነበር «ሁሉም አማኞች በአንዲት ነፍስ ነበሩ::» የሐዋ. ሥራ 4÷32 ሲል እናነባለን እንጂ÷ ዐሥራ ሁለት ዐይነት ስምና ማኅበር ነበራቸው የሚል አንድ ጽሑፍ ከቶ አይገኝም:: እምቢ ብለው ሥራቸውን ለማፍረስ ቢበድሏቸው÷ «እግዚአብሔር ይመልስላቸው::» 2ጢሞ. 4÷14 ይሉ ነበር እንጂ አንድን ሰው እንኳን እንክርዳድ (ኀጥእ) ነህና ከማኅበራችን ውጣ ብለው ክርስቶስ የሞተለትን ኃጥእ አባል መንጋ አውግዘው ለዐርዌ አሳልፈው አልሰጡም (አላባረሩም) ሉቃ. 15÷1-10:: ክርስቶስ የመጣበት ዐይነተኛ ጉዳይ ግን የተበተኑትን በጎች ዐርዌ (ዲያብሎስ) እንዳይበላበት አዝኖ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን (በረት) ውስጥ ለመሰብሰብ ነው፤ ማቴ. 9÷13-36::

የዛሬው ዘመን ሐዋርያት (ቀሳውስት) ግን «እኛ የክርስቶስ ምስለኔዎች ስለ ሆንን÷ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ በእጃችን ናት፤ እኛ ፈርደን በምድር ካሰርነው በሰማይም የታሰረ ነው::» ብለው የሚመኩ÷ በትዕቢት ጭቃና ግብዝነት የተቦኩ÷ ወገን÷ ሠራዊትና መባእን ለማብዛትና ሥጋዊ ጥቅማቸውን ብቻ ለማግኘት እያታለሉ የሚሰብኩ ናቸው:: ስም በመያዝ ብቻ ነው እንጂ በግብራቸውስ እንኳን የክርስቶስ ምስለኔዎች የሐዋርያት ተከታዮችም ለመሆን አልበቁም::

ስለዚህ ሰው የሰውን አፍኣውን (ውጪውን) አይቶ ኃጥኡንና ጻድቁን ለይቶ፥ አውግዞ፥ ፈርዶ ካሰረው፥ እውነተኛው ጻድቅና ፈራጅ፥ ልብና ኵላሊትን የሚመረምረው ጌታ ታዲያ ምን ሊሠራ ነው? ፍርድን ፍጡራኑ ከፈጸሙት፥ ኃጥእና ጻድቅ ብለው ከለያዩ እርሱ ለፍርድ አይመጣም እንደ ማለት ነው፡፡ የእርሱ የመጨረሻ ቃሉ ግን ሌላ ሳይሆን «እነሆ! ለሁሉ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እሰጠው ዘንድ ፈጥኜ እመጣለሁ፤ ዋጋዬም ከኔ ጋራ ነው፡፡» ራእ. 22፥9-13 የሚል ብቻ ነው፡፡

የዘመኑ ቀሳውስት ግን ሐዋርያት የሠሩትን ሥራ ሳይሠሩ፥ ስማቸውን ከግብራቸው ሳያስተባብሩ ቢፈቱ ወይም ቢያስሩ እንዲያው በከንቱ ነው፡፡ ነፋስንም እንደ መጨበጥ ማለት ነው፡፡ ታላቁ እስክንድር በጦርነት ውስጥ ገብቶ በድፍረት ሲዋጋ ሳለ አንድ ፈሪ ወታደር ሲሸሽ አየና «አንተ ሰው ስምህ ማን ይባላል?» ብሎ ጠየቀው ቡቡው ወታደርም «እስከንድር እባላለሁ» አለው፤ እርሱም «እስክንድር ከሆንህ ተዋጋ አለበለዚያ ስሜን ልቀቅልኝ፡፡» አለው ይባላል፡፡ ስለዚህ ስምና ምግባርን ሳያስተባብሩ (ሳያዋሕዱ) የሌላ ሥልጣን ነጥቆ መጨበጥ ግን፥ ዘናም እንደሌለው ጉምና ሕይወት እንደሌለው መልኩ ያማረ ጣዖት፥ ክንፍ እንደሌለው አሞራና እንጀራ እንደሌለው መሶብ፥ ጨው እንደሌለው ምግብና ወንጌል እንደሌለው ቤተ ክርስቲያን፥ ዘውድና ዐላማም እንደሌለው ንጉሥ መምሰል ነው፤ ራእ. 3፥14-19፡፡

ይህንን እየተወጋገዙ ማሰርና መፍታት በከንቱ ነው ስል ግን፥ ለምሳሌ ሉተር ጀርመናዊ የሰውን ሥርዐትና የፍጡራን አማላጅነት፥ ተባሕትዎና ምንኵስና የሚሉትን ፈጠራ አምዘግዝጎ ጥሎ፥ በምግባር ሳይሆን በክርስቶስ እምነት ብቻ የሚገኘውን የጸጋ ድኅነተ ነፍስ በድፍረት ስለአስተማረ፥ (እምነት መጽደቅያ መልካም ምግባር ግን የሃይማኖት መግለጫ ነው ብሎ መስክሯል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 349-370፡፡) በሮማው ጳጳስ ሕግ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ እርሱና ተማሪዎቹ ጽሉዓንና ውጉዛን፥ እሱራንም ናቸው፡፡ እንዲሁም የሮማው ጳጳስ ልዮን በእስንድርያው ጳጳስ በዲዮስቆሮስ ሕግ (ሥልጣን) ውጉዝና እሱር ነው (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የእግዚአብሔር መንግሥት ገጽ 247-250 ተመልከትና መርምር)፡፡

እውነተኛው ዳኛ ሐሰተኞቹ የአዳም ልጆች በየሥልጣናቸው አስረውና ፈትተው የሰጡትን ዝም ብሎ የሚቀበል ይመስልሃልን? አይደለም፤ ይህስ እውነት አይመስልም፤ እርሱ «ዐይን እንደሚያየው አይፈርድም፡፡» ኢሳ. 11፥1-3፡፡ «ሰው አፍአዊውን

ፊት ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል።» 1ሳሙ. 16÷7። «የእግዚአብሔር መብራት የሰው መንፈስ ነው፤ እርሱ የሰውነቱን ውስጣዊ ክፍሎች ሁሉ ይመረምራል።» ምሳ. 20÷24-27። «የእርሱን ፍርድ ሰው መርምሮ አያገኘውም።» ሮሜ 11÷33-36። እርሱ ግን እንኳን ከአዳም ልጆች ንጹሕ የሆነ ሊያገኝ ይቅርና በመላእክቱም ስንፍና (ጉድለት) ያገኝባቸዋልና አያምናቸውም፤ ኢዮ. 4÷18፤ 25÷1-7።

እርሱ ፍርዱን (ማሰርና መፍታት) ለሰዎች ሰጥቶ ካበቃ÷ ዛሬ በኛ በኢትዮጵያውያን ውስጥም ክርስቶስና ክርስትና አንድ ብቻ ሲሆን÷ የሜራና የመለያየት ስም ግን ተዋሕዶ÷ ፕሮቴስታንት÷ ከኒሻ÷ ካቶሊክ÷ አድቬንቲስት÷ ይሆዋ÷ ኦርቶዶክስ÷ ጸጋ÷ ቅብዓት÷ ካራ÷ አንድ ባሕርይ÷ ሁለት ባሕርይ÷ ሦስት መለኮት÷ ኀድረት የሚባሉ ሰው የፈጠራቸው ሃይማኖቶች ሞልተዋል። የሃይማኖት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ ሆነው በተከማቹበት በመካከላቸው ሁኜ እገኝላቸዋለሁ።» ማቴ. 18÷20 ብሎ ተስፋ ሰጠ እንጂ÷ የግጠም አሸከር÷ የገሥጥ ሎሌ÷ የጉበን ሰው እያሉ በየስመ ሜራቸው አውጥተው እየፎከሩ በሚጣሉና በሚወነጋገዙ ማኅበሮች እንደሌለ ይህ ቃሉ ያስረዳል።

የክርስቶስን አንድነት የሚያስረውን የፍቅርና የሰላም ማሰርያ በአንድ ልብና ዐሳብ ጠብቆ በመፈጸም ፈንታ÷ ሮሜ 13÷10፤ ቈላ. 3÷12-17 ይህንን ማሰሪያ በዲያብሎሳዊ ጠብና ጕሕሉት (ሸንገላ) ቈርጠው ከተለያዩ÷ «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ዐዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን በእርስዋ (በፍቅር) ሰው ሁሉ ያውቃችኋል።» ዮሐ.13÷34-35 ብሎ ያስተማራቸው የፍቅር መምህር ክርስቶስ÷ በሁሉም ዘንድ እርሱ በመካከላቸው እንደሌለና÷ ተማሪዎቹም እንዳልሆኑ÷ እርስ በርስ ተጣልተው በመለያየታቸውና በመወጋገዛቸውም የሌላ (የሰይጣን) ተማሪዎች መሆናቸውን በምግባራቸው ይገልጻሉ፤ ሉቃ. 22÷31። ቅዱሱ አምላካችን ግን የአንድነት እንጂ የመለያየት ጌታ አይደለም፤ 1ቆሮ. 13÷33።

አሁን ግን «ዘአሰርክሙ በምድር ይከውን እሱረ በሰማያት» የተባለው ቃል ትርጓሜውና ሞያው ይህ ከሆነ÷ ይልቁንም የሃይማኖትን ሥልጣን በእጃችን ጨብጠን ይዘነዋል እያሉ የሚመኩ ሰዎች÷ ገነትን በመወጋገዛቸው ዘግተውታልና ከቶም እነርሱ የሚገቡበት አይመስሉም። ስለዚህ በክርስቶስ የሰርግ ቀን ወደ ድግሱ ያልተጠሩ እንጂ የተጠሩ እንዳልቀመሱት ሉቃ. 13÷16-24 እንዲሁም ሌሎች ብዙዎች ፍጥረቶቹ÷ ከምሥራቅና ከምዕራብ

መጥተው ወደ ገነቱ እንደገቡና የቤቱ ልጆች ግን ወደ ሜዳዊ ጨለማ እንደተጣሉ የሚናገረውን ቃል ማስተዋል ይገባናል፤ ማቴ. 8÷5-13።

ክርስቶስ ለሐዋርያቱ የሰጣቸው ሥልጣን ግን «አሕዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ በስሜ አሳምናችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንዲሆኑ የወንጌልን የንስሓና የምሥራች ቃሌን እየነገራችሁ ወደ ቤቴ ሰብስቡልኝ።» አላቸው እንጂ÷ (ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ንባቡን ብቻ ይዛ በአፍኣ እንደምትተረጉመውና <u>የጴጥሮስ መክፈቻም የኔ ብቻ ነው</u> ብላ እንደምትመካበት) የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ሰጥቻችኋለሁና ኃጥእንና ጻድቅን እየለያችሁ የወደዳችሁትን አስገቡ÷ የጠላችሁትንም አስወጡ (ከልክሉ) አላላቸውም። መክፈቻ ያላትም ቃለ ወንጌሉ ብቻ ስለሆነች ለሰው የሚዘጋበትና የሚከፍትለት ምግባሩ ነው። ከነአካቴውም መንግሥተ ሰማያት ሌትና ቀን የላትም፤ ደጆችዋም አይዘጉም፤ ኢሳ. 8÷11። ከፍጡራንም ሊዘጋና ሊከፍት የሚችል አንድ ንጹሕ ከቶ አልተገኘም፤ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ከቶ ኃጢአትን ማስተስረይ ማን ይችላል? ማር. 2÷7፤ ኢሳ. 22÷22፤ 41÷25-28፤ ራእ. 3÷7፤ 5÷1-5፤ 21÷21-27።

ምንም እንኳ እንደ ሰው አነጋገር ለአምስቱ ሰነፎች በሩ ተዘጋባቸው፤ ማቴ. 25÷10 ተብሎ ቢጻፍም÷ ትርጓሜው የጸጋንና የንስሓን ጊዜ ሳይሠሩበት (ሳይጠቀሙበት) አባክነው አሳለፉት ማለት ነው። አልሠራችበትም እንጂ የንስሓ ጊዜ ለነቢዪቱ ኤልዛቤልም ተሰጥቷት እንደ ነበረ አስተውለህ አንብብ፤ ራእ. 2÷18-23፤ 2ጢሞ. 2÷25-26።

ሐዋርያት ከጌታ ዘንድ የተቀበሏቸው መክፈቻዎችም ንስሓ÷ ጥምቀትና ቊርባን ናቸው እንጂ÷ በቁሙ ሮማውያን «የሰማይ ቊልፍ በጴጥሮስ (በቫቲካኖች) እጅ ብቻ አለችና÷ ካቶሊክ ያልሆነ ከቶ አይጸድቅም።» ብለው እየሰበኩና ስርየትን በዋጋ እየሸጡ÷ ግንዘት <u>«አልክፍዎ ለበድን» «አስከሬንን አቊርቡት»</u> እንደሚል÷ እነርሱም ነፍሳቸውን ያልመረመሩትን ምእመናን በፉሲካ ወራት በግድ እያቈረቡ÷ በየሥዕልና ምስሉ እጅ ቊልፎችን አስይዘው÷ የዋሃንን እያታለሉ÷ የሥጋቸው መጠገኛ የሚሆን መባእን ለመሰብሰቢያ እንዳደረጉት አይምሰልህ፤ 2ጴጥ. 21÷22፤ ይሁ. 25።

የቀሳውስት ሥልጣን ማሠርና መፍታት ማለትም ማናቸውም ሰው ሥጋዊ ጠባይ አሸንፎት በኃጢአት ጭቃ ከወደቀ በኋላ÷ ተጸጽቶ አልቅሶ÷ እድፉን በክርስቶስ ደም እንዳያጥበው «እምቢ አልነሣም፤ ክፉውን ግብር መተውም ከቶ አይሆንልኝም።»

ቢል ካህኑ ሊመክረውና ሊገሥጸው ይገባዋል:: እስከ ሦስት ጊዜ መክሮት እምቢ ካለው ግን ለማኅበሩ አበሳውን አስታውቆ÷ ስሙንም ከመዝገበ ጥምቀቱ ፍቆ እንደ አረሚ ሊቈጥረውና ለምእመናንም ክፉ አርአያ እንዳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ሊከለክለው (ሊያስረው) ይገባዋል፤ ማቴ. 18÷15-22፤ 1ቆሮ. 5÷1-5፤ 2ተሰ. 3÷6-16:: እንዲሁም በበደሉ ተጸጽቶ ለተመለሰ «ዳግመ ኢተአብስ፤ ተንድገ ለከ ኀጢአትከ» «ደግመህ አትበድል፤ ኀጢአትህ ተሰረየልህ::» ብሎ አጽናንቶ ሊቀበለው (ሊፈታው) ይገባዋል እንጂ፤ ሉቃ. 15÷11-24:: ፍጡር እንኳንና ከሰው ሕሊና ገብቶ ሊፈርድ÷ ለራሱም ቢሆን ስሕተቱን ስለማያውቀው አያስተውለውም፤ መዝ. 19÷12:: ሐዋርያት ግን ፍርድ የሚጀመረው በእኛ በዐዋቂዎች ነው ብለዋል፤ 1ጴጥ. 4÷17፤ ሕዝ. 9÷5-7::

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! በዚህ በኀላፊው÷ ጽድቅና ኀጢአት በተፈራረቀበት ዋሾ ዓለም እስከ ጊዜው በእውነት ወይም በሐሰት ሊፈርዱ ቢሾሙ÷ ጽድቅ በሚኖርባት ኋለኛይቱ ዓለም ግን እንኳን በሰው ሊፈርዱ በየራሳቸው ላይም ምን እንደሚፈረድባቸው አንዳች አያውቁም፤ 1ቆሮ. 4÷1-5::

ስለዚህ ጥቅሶቹን እየተመለከትህ ነገሩን መርምረህ አስተውለው:: በኃጢአቱ ወዶ የታሰረውን ወደ ሲኦል÷ በንስሓ ወዶ የተመለሰውንም ወደ ገነት የሚያስገባ ረቂቁ ባለ ሥልጣን÷ መክፈቻውን በእጁ ይዞ የፈቀደውን የሚሠራ÷ የሚቋቋመው የሌለ ዳን. 3÷35፤ አንድ ብቻውን ጻድቅ የሆነ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ መሆኑን አስተውል፤ ራእ. 3÷7:: ከአዳም ልጆች ግን አንድ ንጹሕ አልተገኘምና ሮሜ 3÷10-12 ኃጥእ ኃጥእን ሊያስረውና ሊፈታው÷ ሊያጸድቀውና ሊኰንነው ከቶ አይቻለውም:: ካህን አስተምሮና መክሮ ኃጢአተኛውን ከክፉ ሥራው ቢመልሰው ግን÷ መክሊቱን ስለአራባ ከጌታው ዘንድ ዕጥፍ ክብርና ደስታ ይቀበላል፤ ማቴ. 25÷23-24::

የዘመኑ ቀሳውስት ግን በምድር ያሰርነው በሰማይም እሱር ነው፤ ከነአካቴውም ጌታ ሐዋርያትን «በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ትፈርዳላችሁ::» ማቴ. 19÷26-30 ብሏቸዋልና÷ በሰማይም ለመፍረድ ሥልጣን ተሰጥቶናል እያሉ ይመካሉ፤ 2ቆሮ. 10÷15-18:: ይህን ቃል ጌታ ለሐዋርያት ሲነግራቸው እነርሱ ገና በጥርጥር ያሉ÷ በየጊዜው የሚያምኑና ተመልሰውም የሚክዱ÷ ገና መንፈስ ቅዱስ ያላደረባቸው ሥጋውያን ስለነበሩ÷ ምድራዊ ንጉሥም ይመስላቸው ስለ ነበረ÷ ስለሚያገኛቸው መከራ በተስፋ

እንዲጸኑ ብሎ እንደዚህ አላቸው እንጂ፥ በሰማይ ሙግትና ጻዕር፥ ጠብና ክርክር የለም:: የቀደመው ሥርዐትም (ምድራዊው) አልፏልና በሰማይ ሰዎች ለፍርድ ተቀምጠው የሚዳኙ ሆኖ አይደለም:: የገብረ መንፈስ ቅዱስ ገድል ግን በሰማይ ጦርነት አለ፤ እንዲያውም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአንድ ኃጥእን ነፍስ ለማዳን ሲሉ ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር በሰማይ ተዋግተው ሁሉንም በመባርቅት ፈጇቸው ብሎ ይዋሻል፤ ራእ. 7፥9-17፤ 21፥1-7:: ደግሞም ጳውሎስ «አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ በክብር ይበልጣል::» 1ቆሮ. 15፥41 እንዳለ፥ ስላገለገሉ ማዕረግና ክብር ወይም ደረጃ ቀጠሉ ማለት ስለሆነ ከእርሱ ጋር ነገሡ ራእ. 22፥3-4 ቢባል፥ በቀኙ ለመቆም በቁ (ከበሩ) ማለት ነው:: «አብ እንኳ በማንም አይፈርድምና ፍርዱን ሁሉ ለልጁ ብቻ ሰጠው::» ዮሐ. 5፥22 ሥልጣኑ የማይለየው የሁሉ ፈራጅ ግን እርሱ ብቻ ነው ዳን. 7፥9-14፤ ራእ. 11፥15-19::

ወንድሜ ሆይ! ከጳውሎስ የበለጠ አገልጋይ አልተገኘም:: እርሱም «ሁላችን እያንዳንዳችን ምላሽ ለመስጠት በክርስቶስ ወንበር ፊት ለፍርድ እንገለጣለን (እንቆማለን)::» ሮሜ 14፥6-13፤ እንዲሁም «ፍርዱ የማትገኝ፥ መንገዱም የማትመረመር ናት::» ሮሜ 11፥32-36 ይላል እንጂ፥ ሁላችን በየዐቅማችን ግዛት ተቀብለን እንፈርዳለን አይልም፤ ማቴ. 25፥31-46፤ ተመልከት መርምር፤ 2ቆሮ. 5፥10::

ሃይማኖት አለን የሚሉ የሤራና የስም ክርስቲያኖች ሁሉ ግን፥ ዕዳቸውን ለመክፈል የተሰቀለላቸውን አንዱን ክርስቶስን ብቻ አምነው በመስበክ ፈንታ፥ ኀላፊው የሥጋ ጉልትና ሹመት እንዳይቀርባቸው ሲሉ አንዱ የጳውሎስ፥ አንዱ የጴጥሮስ ነኝ፥ አንዱ የማርቆስ፥ አንዱም የዲዮስቆሮስ ነኝ፥ አንዱ የድሜጥሮስ ነኝ፥ አንዱም የንስጥሮስ ነኝ፥ አንዱ የአርዮስ ነኝ፥ አንዱም የሰባልዮስ ነኝ፥ አንዱ የልዮን አንዱም የሉተር ነኝ፥ አንዱ የእምዬ፥ አንዱ የአቡዬ ነኝ፥ አንዱ የጊዮርጊስ፥ አንዱ የተክልዬ ነኝ እያሉ የማያውቋቸውንና የማይጠቅሟቸውን ጌቶች በየሐሳባቸው እየፈጠሩና በሰው ባህልና ትርጓሜ እየተመሩ፥ የኔ ይበልጥ የኔ ይበልጥ ብለው ራሳቸውን እያታለሉ፥ አለቆቻቸውን ለማጋነን ሲሉ ሁሉም ከአምላካዊ አንድነት ተለይተው፥ እውነተኛውን የክርስቶስን ፍቅር አጥተው በዐይነ ጸብእ እየተያዩና ክፉ ስም እየተሰጣጡ በምቀኝነት ጸንተው ይኖራሉ፤ 1ቆሮ. 1፥10-13፤ 3፥1-9::

አንባቢ ሆይ! እነዚህን ሰዎች አንድ በግ አርደው ከተካፈሉ በኋላ፥ የኔ ይሰባል የኔው ይሰባል በማለት በየገበያው ተቀምጠው የሚጣሉ ወረተኞችና የአእምሮ ሕፃናትን ይመስላሉ፤ ማቴ.

11÷16-19:: አንተ ግን ራሱንና የማኅበሩን ስም ሳይሆን ለዓለም መድኃኒት እንዲሆን የተሰቀለውን አንዱን ክርስቶስን ብቻ የሚሰብክ 2ቆሮ. 4÷1-6 እውነትን የተከተለ÷ ክርስቶሳዊ ፍሬ ያለውንና ስብከቱና ምግባሩ የተስተካከለውን ወገን መርምረህ መከተል ይገባሃል::

እንዲህ ብዬ ስነግርህም «በሰው የሚታመን ሰው ርጉም ነው::» ተብሏልና በአምላክ እንጂ በሰው መሪነትና ማኅበር እንዳትመካ ተጠንቀቅ:: መሪህና አስተማሪህ÷ እረኛህና ጠባቂህ÷ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን በውል ዐስብ እንጂ÷ ባዕዳን ይሁኑ ወይም የአገር ልጆች የሙዳየ ምጽዋት ማዳበሪያ እንድትሆናቸው በመዝገባቸው ጽፈው እንዳይደልሉህ አስተውል:: ስምህ በመጽሐፈ ሕይወት ተጽፎ የሚገኝበትን ዘዴ አንተው ፈልግና አግኝ፤ ቅዱስ መጽሐፍን የሕይወትህ ዐምድ አድርገህ ይዘህ ሌትና ቀን መርምረው:: በእርሱ ውስጥም የተቀበረ ሕያው የሆነ ወርቅ ታገኝበታለህ፤ መንገድህም ሁሉ የቀና ይሆንልሃል፤ ዘዳ. 32÷12፤ ኢያ. 1÷5-9፤ መዝ. 19÷7-14:: የክርስቶስ ቤት አንተው መሆንህን አትርሳ፤ 1ቆሮ. 3÷11-18::

ቤተ ክርስቲያን ማለትም ስንዴና እንክርዳድ÷ ገለባና እብቅም ጭምር የያዘች የእህል ክምር÷ (ገሪፍ÷ መረብ÷ ወጥመድ) ስለ ሆነች ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ኅድግዎሙ ኅቡረ ይልኅቁ እስከ ማዕረር::» «ተዉአቸው እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ::» እንዳለ ማቴ. 13÷30፤ እርሱ በመከር ወራት መጥቶ÷ በአውድማው ላይ ወቅቶ በመንሽ እስኪለያየው ድረስ÷ ዛሬ ጻድቅና ኃጥእ÷ አማኝና ከሐዲ ተባብለው እየተወነጋገዙ አለጊዜው መፍረድ ከቶ አይገባም፤ 2ቆሮ. 4÷1-6:: ከአዳምስ ልጆች ኃጢአተኛውንና ጻድቁን ለይቶ ማወቅ የሚችል ማን የሚባል ፍጹም ጻድቅ አለ? አንድስ እንኳን አልተገኘም፤ መዝ. 14÷1-3፤ ሮሜ 2÷1-6::

አንባቢ ሆይ! እንደዚህ እያልኩኝ ስነግርህ ግን «ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ እለ ኢየአምኑ፤ ፃኡ እማእከሎሙ ወተፈለጡ እምኔሆሙ::» «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤. . . ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ::» 2ቆሮ. 6÷14-16፤ «አእትቱ እምላዕሌክሙ እኩየ::» «ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት::» 2ቆሮ. 5÷1-13፤ የሚሉትን ቃላት የረሳሁኝ አይምሰልህ:: ተለዩ ማለቱ ግን ክርስቶስን ከማያምንና የክርስቶስን ትምህርት ያልሆነ ሌላ ትምህርት÷ <u>የመሐመድ ቊርዓንን ከሚመስል ፈጠራ</u> ተለዩ ማለቱ ነው እንጂ÷ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ ከሚያምን ወንድም ተለዩ አላለም፤ 1ዮሐ. 4÷1-6፤ 2ዮሐ. 7÷11:: ስለዚህ ክርስቲያኖች ሲባሉ በክርስቶስ ተጣልተው

እየተወገጋገዙ እንደየስማቸውና ባህላቸው ብዛት ከተለያዩ፥ ሁሉም የክርስቶስ መንፈስ እንደሌላቸውና አለቆች የተባሉትም ሁሉ የሚናጠቁ ጅቦች፥ የመንጋው በታኞችም እንደሆኑ በመለያየታቸው ይታወቃሉ፤ የሐዋ. ሥራ 20፥26-30:: ቸሩ ጠባቂ ግን ቤተ ክርስቲያንን አንዲት የኔ መንጋ ይላታል እንጂ፥ ዐሥር ወይም ሃያ ዐይነት መንጋ አላላትም ዮሐ.10፥14-16:: አንዱ የሃይማኖት ጌታ እግዚአብሔርም ያንድነትና የዕርቅ አምላክ ነው እንጂ የጠብና የመለያየት አለቃ እንዳልሆነ አንብብ፤ የሐዋ. ሥራ 2፥38-47፤ 1ቆሮ. 14፥33::

አሁን ግን ሃይማኖት አለኝ የሚል እውነተኛ ክርስቲያን፥ የጳጳሳት ውግዘት፥ ሥጋዊ ጥቅም፥ የወገን ማብዛት፥ የመለያያትና የሤራ መበታተን ካለው የሰው ሥርዓትና ማኅበር ተለይቶ፥ እንደነ ሄኖክ፥ ኖኅ፥ አብርሃም፥ ሎጥ፥ ኢዮብ፥ ዳዊት፥ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ዳንኤልና ሠለስቱ ደቂቅን መስሎ፥ የዓለምን (የሰውን) ባህልና ምግባር አምዘግዝጎ ጥሎና ሁሉንም ነገር በውል ተመልክቶ፥ <u>የግሉን ሃይማኖት (ሕገ አምላክን) በልቡ ይዞና አጽንቶ</u> ለሁሉ ሰው ወዳጅና አስተማሪ፥ ታጋሽና ንጽሕና አፍቃሪ፥ ምእመን ወንድሙን ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅር ባይ ሆኖ ሳይቀየም ሊኖር ይገባዋል፤ ማቴ. 18፥21-22፤ 2ጢሞ. 2፥24::

ያንዱ ሰው ሐሳብና ትርጓሜ ከሌላው ሰው ጋር ስለማይስማማ፥ ሰው አስቀድሞ በሰው ላይ ከመፍረዱ በፊት በራሱ ላይ መፍረድ ይገባዋል:: «በራሳችን ላይ ብንፈርድ ባልተፈረደብንም ነበር::» 1ቆሮ. 11፥31:: «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ::» ማቴ. 7፥5:: «በወንድሙ የሚፈርድ ፈጽሞ በሕግ ላይ ይፈርዳል፤ በሕግም ከፈረድህ አንተ ሕግን አድራጊ አይደለህም:: በሕግ ፈራጅ የሆነ፥ ለመግደልና ለማዳንም ችሎታ ያለው ግን አንድ ብቻ ነው:: አንተስ በባልንጀራህ ላይ የምትፈርድ ማነህ? ያዕ. 4፥1-12፤ 5፥7-9:: «እንግዲህ እርስ በርሳችን አንፈራረድ::» ሮሜ.14፥7-13:: የበደሏችሁን ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ ይቅር አይላችሁም::» ማር. 11፥24-26:: «ማንንም የምንከስበት ቢኖር፥ ክርስቶስ እናንተን ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ ይቅር በሉ::» ኤፌ 4፥29-32::

ወንድሜ ሆይ! ከኛ አስተዋይና ጠቢብ ሆኖ ሃይማኖት አለኝ የሚል ሰው ማነው? በመልካም አካሄዱ ሃይማኖቱን በሥራው ይግለጥና ያሳይ፤ ያዕ. 3፥13-18 «በወንጌል የተሰበከልን ቃል ይህ ብቻ ነው::» 1ጴጥ. 1፥13-25:: ክርስቲያን ሆይ! እውነትን ከሐሰት፥ ትሕትናን ከትዕቢት ለይቶ ለማወቅ ብርሃነ ወንጌሉ ያብራልህ፤ አሜን::

ምዕራፍ 18

ስለ መድኃኒትነቱ

በኃጢአት ቊስል ለታመመ ሰው መድኃኒት ወይም ሐኪም እንደሚያስፈልገው እርግጠኛ ነገር ነው። ይህ ሲሆን ግን ሰው አስቀድሞ ቊስለ ኃጢአቱ ቢታወቀውና እውነተኛውን መድኃኒት (ጽድቅን) ለመፈለግ ሕሊናው (ነፍሱ) ቢጨነቅ፥ «ልጄ ሆይ! ኃጢአትህ ቀረልህ፤ ሃይማኖትህ አዳነህ።» የሚል የምሥራች አምላካዊ ቃል በእዝነ ልቡናው ሊሰማና ሊያገኝ ይችላል። ይህንንም ስርየት ከአገኘ በኋላ ቀላሉንና ልዝቡን የክርስቶስ ቀምበር ተሸክሞ፥ በእውነተኛው የነፍሳት ሐኪም ታክሞና ድኖ፥ «ልበስዎ ለክርስቶስ» እንደተባለው የጻድቃንን ልብስ ቢሶስ ለብሶ ከቊስለ ኃጢአቱ ተፈውሶ እፎይ ብሎ ዐርፎ በደስታ ይኖራል፤ ማቴ. 12÷18-30፤ 1ጴጥ. 2÷24-25፤ ዮሐ. 5÷14፤ ኤፌ. 6÷1-18።

ወዳጄ ሆይ! የመድኃኒትነቱን ስም ስማ «ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ፤ ሕዝቡንም ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።» ማቴ.1÷21። «መድኃኒት ከጽዮን ይመጣል፤ የያዕቆብንም ኃጢአት ያርቃል።» ሮሜ 11÷26። «በጌታ ኢየሱስ ጽድቅ፥ ቅድስና መድኃኒትም ሆነልን።» 1ቆሮ. 1÷30። «ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ ስለኃጢአታችን ራሱን ለወጠ።» ገላ. 1÷4። «በእርሱ ደም መድኃኒት ተቀበልን።» ኤፌ. 1÷7። «ኢየሱስ ክርስቶስ ወደደን፤ ከኃጢአታችንም በደሙ ዐጠበን።» ራእ. 1÷5፤ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ።» ዮሐ. 1÷29። ይኸውልህ እውነተኛና እርግጠኛ የነፍሳት መድኃኒት ማለት ኢየሱስ ብቻ ነው።

ቸሩ አምላካችን እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት አዳምና ሔዋን በስሕተታቸው እንደሚወድቁ ቀድሞ ስለ ዐወቀ፥ ከውድቀታቸው ለማንሣትና ወደ ጥንቱ ገነታዊ ንብረታቸው ለመመለስ፥ የጠላታቸውን የዲያብሎስን ራስ ጨፍልቆ፥ ኃጢአታቸውን በምሕረቱ አርቆ፥ ከእሥራታቸውም ፈትቶና በመስቀሉ ዕዳቸውን ከፍሎ፥ በደሙም ዐጥቦ፥ አንጽቶና አስታርቆ ገነት የሚያስገባቸውን አንድ አማላጅ ፍጹም እግዚአብሔር እንደ መሆኑ ፍጹምም ሰው ሆኖ በመካከለኛነቱ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያገናኝ መካከለኛ እንዲሆን በምክረ ሥላሴ መወሰኑ፥ ኃጥአን የሆኑ የአዳም ልጆች ሁላቸው እርሱን በማመን ብቻ እንዲድኑና እንዲፈወሱ ነው። የአምላካዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንዲያደርጋቸው ስለዐሰበም፥ <u>እርሱን ዓለም ሳይፈጠር አስታራቂና አዳኝ፥</u>

<u>መድኃኒትም አድርጎ ለቆመው::</u> «ወውእቱ ህልው እምቅድመ ኵሉ፤ ወኵሉ ቦቱ ቆመ::» «እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል::» ቈላ. 1÷12-23:: «በከመ ኀረየነ ሎቱ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ከመ ይረስየነ ቅዱሳነ ወንጹሓነ በቅድሜሁ በተፋቅሮ::» «ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን::» ኤፌ.1÷3-14፤ ዘተአምረ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወአስተርአየ በደኀሪ መዋዕል በእንቲአነ::» «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ፤. . . በዘመኑ መጨረሻም ተገለጠ::» እንዳለ፤ 1ጴጥ. 1÷20::

ወንድሜ ሆይ! የጻድቁ የክርስቶስ መድኃኒትነት ርኅራኄው ፍጹም አማላጅነቱን መጻሕፍት ሲገልጹ <u>«ወይክል አድኅኖቶሙ ለዘሉፉ ለእለ ይቀርቡ ኀበ እግዚአብሔር እንተ መንገሌሁ÷ እስመ ለግሙራ ሕያው ውእቱ÷ ወይተነብል ሎሙ::»</u> «እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል::» ዕብ.7÷22-28፤ ብለው መስክረውለታል:: ይህ የሥጋ ጥቅም እንዲገኝበት በሐሰት የተደነገገብን የፍጡራን አማላጅነት ግን ሐሰት መሆኑን እነዚያ መምህራነ ሐሰት ቅዱስ ዳዊት «ወከንቱ ተአምኖ በሰብእ:: ኢትትአመኑ በመላእክት ወኢበዕጓለ እመ ሕያው እለ ኢይክሉ አድኅኖ:: <u>እኍኒ ኢያድኅን እኅዋሁ፤ ወኢያድኅን ሰብእ::»</u> «የሰውም ማዳን ከንቱ ነው፤ ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና በአለቆች አትታመኑ፤ ወንድም ወንድሙን አያድንም፤ ሰውም አያድንም፤» መዝ. 108÷12፤ 49÷7፤ 146÷1-5 በሚለው ቃሉ ብቻ ሐሰተኛነታቸውንና አታላይነታቸውን ይገልጻል::

<u>ስለዚህ ክርስቶስ ሕያው ዘኢይመውት አማላጃችን ነውና ልትድኑ ኢየሱስን ብቻ እመኑ</u> በማለት ፈንታ ፍጡራን ሙታን ያድናሉ (ያማልዳሉ) ቢሉ÷ መጻሕፍትን (ብሉይና ሐዲስን) ብቻ ብታነብ ቃላቸው ሐሰት መሆኑን ትረዳዋለህ:: የክርስቶስ ታላቅነት ፍጡራን ከተባሉ ሁሉ ብልጫ አለው:: «ዝንቱ ወእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ ወሎቱ ሠመርኩ::» «ፈጽሜ አከበርኩት፤ ደግሜም አከብረዋለሁ::» ማቴ. 3÷17፤ ዮሐ. 12÷23-36 ብሎ እግዚአብሔር አብ የመሰከረለት÷ ከመልከ ጼዴቅና ከአሮን የበለጠ ለዘለዓለም የሚኖር÷ የማይሻርና የማይለወጥ ዘለዓለማዊ ክህነት ያለው እውነተኛው አዳኝና አማላጅ ማለት ኢየሱስ ብቻ ነው:: አሁን ግን ሕያው ሆኖ የዘለዓለም ሕይወትን ላመኑት የሚሰጠውን እርሱን ብቻ መድኃኒቴ÷ አማላጄ ብለህ በእምነትና በተስፋ እጅ አጽንተህ ያዝ እንጂ ዕብ. 2÷16-18፤ ምዉታንና እንደ አንተ

ፍጡራን የሆኑ ሰዎችን ላያድኑህ ያድኑኛል ያማልዱኛል ማለትህ በክርስቶስ ከተገኘው ጸጋና ክብር መውደቅህና መለየትህ÷ የማይፈወስም ቍስል ማውጣትህ ስለሆነ «ዛሬ እኔስ የክርስቶስን ጸጋ አልክድም» በል ገላ. 2÷16-21:: «እፎ እንከ ትቄስሉ እንዘ ትዌስኩ ኃጢአተ በዲበ ኃጢአት::» «ደግሞስ ዐመፃ እየጨመራሁ ለምን ትቀሠፋላችሁ?» ኢሳ. 1÷2-9፤ የሚለው ቃል እንዳይፈጸምብህ÷ የጸጋ ጊዜም ሳያልፍብህ ዛሬ በንስሓ ወደእርሱ ተመለስ::

ወዳጄ ሆይ! ፍጡር በፍጡር መዳን የሚችል ከሆነ ከአቤል እስከ ዘካርያስ ያሉት ደጋጎች ሰዎች ያነሱ መሰለህን? እግዚአብሔር ሰውን ሰው ሊያድን እንደማይችልና የሰው ጽድቅም ለሰው እንደማይተርፍ ስለአየ አንድ ልጁን ወዳጁን ክርስቶስን ከሰማይ ልኮ በፍቅሩ አዳነን:: ፍጡር ሁሉ ኃጢአት ካልሆነ የጤፍ ፍሬ የሚያህል ጽድቅ ያፈራም ሆነ አንድ ሕግ እንኳ ያላፈረሰ ፍጹም ሰው አይገኝም:: ምንም ልጸድቅ ብሎ እንኳ የጽድቅን ሥራ አንዲት ቢሠራ÷ ወዲያው መቶ ጊዜ ደግሞ ኃጢአት እንደሚሠራ እርግጥ ነው:: ኢሳይያስ ይህን በኃጢአት የተነከረ ፍጥረታችንን አይቶ <u>«ወኲሉ ጽድቅነ ከመ ፀርቀ ትክቶ::» «ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው::»</u> ብሎታል 64÷5-9:: ቅዱስ ዳዊትም «እግዚአብሔር ከሰማይ የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚሻ ሰው እንዳለ ያይ ዘንድ የሰውን ልጆች ተመለከተ:: ሁሉ ግብዝ ሆኑ፤ አብረውም ወደ ኋላ ተመለሱ:: አንድስ ስንኳ በጎ የሚያደርግ የለም::» ይላል፤ መዝ. 53÷1-3::

ስለዚህ ሰው ሰውን ሊያድነው ወይም ሊያጸድቀው ከቶ አይችልም:: እንኳን ሰውን ሊያጸድቁ ራሳቸውም መጽደቃቸው የሚታወቀው በትልቋ በፍርድ ቀን ነው:: እኛ ግን ሁሉን ጻድቃን እያልን መጥራታችን (መሾማችን) በዐይነ መጻሕፍት ያልታየ ነገር ስለሆነ ወደ ጥርጥር መግባታችን ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ «ወባሕቱ በዝየ ኢያጸድቅ ርእስየ እስመ እግዚአብሔር የሐትተኒ::» «ነገር ግን በዚህ አልጸድቅም፤ እኔን የሚፈርድ ግን ጌታ ነው::» ይላል፤ 1ቆሮ. 4÷1-6:: ስለዚህ ኃጥእና ጻድቁ የሚታየው የሊቀ መላእክትን የመለከት ድምፅ በምንሰማባትና ከእንቅልፋችን ተነሥተን የፈጣሪያችንን ፊት በምናይባት÷ ንዑና ሑር በምንባልባት በታላቋ ቀን ነው:: ከአሁን በፊት ግን አብርሃምና አልዓዛር÷ ፈያታይ ዘየማንም ሦስቱ ብቻ ካልሆኑ በቀር ሌላ እገሌ የሚባል ጻድቅ ወደ ገነት ገባ የሚል ቃል በመጻሕፍት የለም፤ ከቶም አላየንም፤ ዳን. 12÷1-13፤ ሉቃ. 16÷19-31 ፤23÷39-43 ፤1ቆሮ. 2÷6-11::

ወንድሜ ሆይ! ሁላችንም የኃጥኡ የአዳም ልጆች ሁለተኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ተወልደን ሕያዋን (ጻድቃን) ሁነን እንድናለን እንጂ፥ ፍጡራንስ እንደ አንተና እንደኔ በኃጢአት ጭቃ ተንከባልለው የረከሱ ስለሆኑ የማይሰሙ፥ የማይረዱ፥ የማያማልዱ፥ የማያድኑ፥ በሞት የተቀጡና ትንፋሽ የሌላቸው የደረቁ ሬሳዎች መሆናቸውን አስተውል፤ ሕዝ. 37፥1-8፤ ሮሜ 6፥4-23:: ከሰዎች ደግ የሠሩ ቢገኙባቸውም «ወኵሎሙ ዐስበሙ ይነሥኡ በአምጣነ ጻማሆሙ::» «ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል::» 1ቆሮ. 3፥8 እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፥ በፍርድ ቀን ሁሉም ፍዳ ምግባሩን (የሥራውን ብድራት) ሊቀበል ከእንቅልፉ በሰማያዊ ድምፅ ተቀስቅሶ ይነሣልና፥ አንተም እንደ ሰው ሁሉ በምሳሌው ፈጥሮ ዕውቀቱን ስለሰጠህ ከአሁን ጀምረህ ምን ይፈረድብኝ ይሆን? ብለህ በኃጢአትህ እያዘንህና አምላክህን እየፈራህ በዐቅምህ ካገለገልኸው፥ ለአንተም ሳያደላ ዋጋህን ይሰጥሃል፤ 1ተሰ. 4፥13-18፤ ራእ. 22፥12:: ፈራጅህና ዋጋ ሰጭህ፥ አዳኝህና አማላጅህ፥ ዲያብሎስን አሽከሮ የማያምኑትንና የማይታዘዙትን ጠላቶቹን በብረት በትር ሊያደቃቸው ለሚታዘዙት ወዳጆቹ ግን ቦታን ሊያዘጋጅላቸው ሄዶአል:: እስኪመጣ ድረስም በባቱ ቀኝ ተቀምጦ ዘወትር ምሕረት ሲለምንላቸውና ሲያማልዳቸው የሚኖር መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ መሆኑን አስተውል:: <u>ሰው በሰው ወይም በምግባሩ የሚድንና የሚጸድቅ ከሆነ ግን እንግዲያስ ክርስቶስ ለከንቱ የሞተ ነዋ!</u> ገላ. 2፥16-21፤ ዕብ. 4፥14-17፤ 7፥18-28 ::

ወዳጄ ሆይ! በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ ዕዳህን የከፈለልህ ወንድምህና ጌታህ፥ ነገረ ፈረጅህና ጠበቃህ፥ አንዱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው:: ፍጡራንስ ቅዱስ ጳውሎስ <u>«አልቦሙ ዘይበቍዑ::» «የሚጠቅሙት ነገር፥ የሚሞሉት ጉዳይ የላቸውም::»</u> ብሎሃልና፤ 1ቆሮ. 3፥7:: ማማለድ ማዳን የማይቻላቸውን ፍጡራንን ትተህ፥ አዳኝ ጠቃሚ የዘለዓለም ሕይወት ሰጪና ነሺ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን አምነህ፥ ትእዛዙን እየጠበቅህና ሥጋ ወደሙን እየተመገብህ «ዛሬ ድምፁን በሰማችሁበት ቀን ልባችሁን አታጽኑ::» ዕብ. 3፥12-19 እንደተባለው፥ ዛሬ በዚህ በኃላፊው ዓለም ሳለህ የማያልፈውን ነዋሪ አገር የዘላለም ድነት ማደሪያህን ሥራ፤ ዮሐ. 14፥1-23:: እውነተኛ ውን የሚያድን መድኃኒት ዐውቆና መርጦ ሥፍራ መያዝ፥ ዛሬ በኃላፊው ዓለም ሁኖ ነው እንጂ፥ ነገ ሰው ከሞተ በኋላ ጽድቅ ወይም ኃጢአት ሊሠራ ከቶ አይቻለውም፤ መክ. 9፥10፤ ገላ. 6፥7-10፤ ራእ. 22፥10-15:: ኋላ ቢጸጸቱ፥ ቢያዝኑና ቢያለቅሱም

ዘኢይበቍዕ (ከንቱ፥ ዋጋ የሌለው) የአኪጦፌልና የገብር ሐካይ (የስነፉ ባሪያ)፥ የይሁዳ አስቆሮታዊ ጸጸት ዐይነት ማለት ነው፤ 2ሳሙ. 17፥1-23፤ ሉቃ. 12፥35-48፤ ማቴ. 24፥43-51፤ 27፥3-5።

እውነቱን ከሐሰት ለይቶ ዐውቆና ሠርቶ ለመዳን ሰማያዊ ኃይልን ይስጥህ፤ አሜን።

ምዕራፍ 19

የአዳም መድኃኒት ከመጽሐፈ ብሉት ክርስቶስም አዳምን ለማዳን እንደሚመጣ በመጻሕፍተ ብሉያት ስለተነገሩለት ቃላተ ትንቢት

«እርሱ የእባብን ራስ ይቀጠቅጣል።» ዘፍ. 3÷15፤ «የሰላም ንጉሥ እስኪመጣ ድረስ በትር ከይሁዳ አይጠፋም፤ ለርሱም የአሕዛብ መታዘዝ ይሆናል።» 48÷8-12። «እነሆ እኔ መልአኬን ይጠብቅህ ዘንድ በፊትህ እሰደዋለሁ፤ ወዳዘጋጀሁት ስፍራም ያስገባሃል።» ዘፀ. 23÷8-27፤ «ፊቴ በፊትህ ይሄዳል፤ አሳርፍህማለሁ።» 33÷14፤ «አውራ ፍየሉም ኃጢአታቸውን ሁሉ ወደ በረሃ ይሸከም።» ዘሌ. 16÷22፤ «አየዋለሁ ዛሬም አይደለም፤ ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል፤ በትርም ከእስራኤል ትነሣለች።» ዘኍ. 24÷17፤ «እግዚአብሔር አምላክህ ከአንተ መካከል እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃና እርሱን ስማው።» ዘዳ. 18÷15-19፤ «እነሆ የምድር ሁሉ ጌታ በፊታችሁ ይሄዳል።» ኢያ. 3÷11።

«ጌዴዎንም የእግዚአብሔርን መልእክተኛ ፊት ለፊት አየሁ አለ።» መሳ. 6÷11-24፤ «እግዚአብሔር እንደልቡ የሆነ ሰው መርጧል።» 1ሳሙ. 13÷14፤ «እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል፤ እርሱም ለስሜ ቤት ይሠራልና የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘለዓለም አጸናለታለሁ።» 2ሳሙ. 6÷8-16፤ «በፊቴ በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው ካንተ አይታጣም።» 1ነገ. 8÷25፤ «በቤቴና በመንግሥቴም ለዘለዓለም አቀመዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል።» 1ዜና. 17÷6-14፤ 2ዜና. 6÷16፤ «ከብዙ ሺህ አንድ መልአክ መካከለኛው ቢሆን አድነው ይለዋል።» ኢዮ. 33÷14-28።

«እግዚአብሔር አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወለድሁህ አለኝ።» መዝ. 2÷7፤ «ስሙ ለዘለዓለም ይኖራል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉም በርሱ ይባረካሉ።» መዝ. 72÷17 «እርሱን የበኵር ልጄ አደርገዋለሁ፤ ኪዳኔም ለርሱ ይሆናል፤ ከምድር ነገሥታት ሁሉ በላይም አደርገዋለሁ።» መዝ. 89÷20-29፤ «ጌታ ጌታዬን በቀኜ ተቀመጥ አለው።» መዝ. 110÷10።

«እነኋት ድንግል ትፀንሳለች÷ ወንድ ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ኢሳ. 7÷14። «ሕፃን ተወልዶልናል፤ ልጅም ተሰጠን ስሙንም ድንቅ መካር÷ ብርቱ አምላክ÷ የዘለዓለም አባት÷ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» ኢሳ. 9÷1-7፤ «እርሱንም ተስፋ አደረግነው፤ ሞትንም ለዘለዓለም

ይውጣል፤ ዕንባንም ሁሉ ከፊት ያብሳል፤ ያድነናልም።» ኢሳ. 25÷7-9፤ «በትር ከእሴይ ሥር ይወጣል፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ ያርፍበታል።» ኢሳ. 11÷1-10፤ «የዳዊትን ቤት መክፈቻም በጫንቃው ላይ እሰጣለሁ፤ እርሱ ይከፍታል፤ የሚዘጋ የለም፤ ይዘጋል የሚከፍትም የለም።» ኢሳ. 22÷22፤ «እርሱ ስብራትን ይጠግናል፤ ቍስልንም ሁሉ ይፈውሳል።» ኢሳ. 30÷26፤ «እነሆ የምቀበለው÷ የመረጥሁት ባርያዬ÷ ነፍሴ የወደደችው» ኢሳ. 42÷10-16፤ «እኔ እርሱን በጽድቅ አነሣሁት፤ እርሱም ምርኮኞዬን ያወጣል።» ኢሳ. 45÷13፤ «እግዚአብሔር የሁላችንን ኃጢአት በርሱ ላይ አኖረበት፤ እርሱ ጻድቅ ባሪያዬ በዕውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል።» ኢሳ. 53÷1-22፤ «ተነሽ ብርሃንሽ መጥቷልና፤ አብሪ የእግዚአብሔርም ክብር መጥቶልሻልና።» ኢሳ. 60÷1-2፤ «የእግዚአብሔር መንፈስ በላዬ ነው፤ ለተሑታን የምሥራችን÷ የተሰበሩትን እጠግንና ለታሰሩትም መለቀቅን እነግር ዘንድ ቀብቶኛል።» ኢሳ. 61÷1-11፤ «በፍቅሩና በርኅራኄው ተቤዣቸው፤ መድኃኒትም ሆነላቸው።» ኢሳ. 63÷1-9፤ <u>እነሆ ዘመን ይመጣል፤ ለዳዊትም የጽድቅ ጫፍ አበቅላለሁ፤ እግዚአብሔር ጽድቃችን ብለውም ይጠሩኛል።»</u> ኤር. 23÷1-6፤ «በዚያም ቀን እስራታችሁን እፈታለሁ፤ ለእኔ ለአምላካቸው እግዚአብሔር÷ ለማስነሣላቸው ለንጉሣቸውም ለዳዊት ይገዛሉ።» ኤር. 30÷8-9፤ የደኅንነት ቃል ኪዳን እገባላችኋለሁ፤ ዳዊት ባሪያዬም በመካከላቸው አለቃ ይሆናል።» ሕዝ. 34÷1-28።

«ከሽህ ሰዎችም አንድ ብቻ አገኘሁ።» መክ. 7÷27-29፤ «እኔ ስለ ታላቁ ስሜ ራርቼ ነው እንጂ÷ ስለናንተ የምሠራ አይደለሁም። ከርኵሰታችሁም ሁሉ አነጻችኋለሁ።» ሕዝ. 36÷25-32፤ «የአራተኛውም መልክ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል፤ እንደ እርሱ ማዳን የሚችል ሌላ አምላክ ከቶ የለም።» ዳን. 3÷25-29፤ <u>«ከኔ ሌላ አምላክ አታውቅም፤ ከኔም በቀር የሚያድን የለም።» ሆሴ. 13÷4፤ «ያልጠራውንም ደማቸውን እኔ አጠራዋለሁ።» ኢዩ. 3÷21 «እኔን እሹኝ ትድኑማላችሁ» አሞ. 5÷4 «በጽዮን ተራራ ግን መድኃኒት ይሆናል።»</u> አብድ. 1÷17፤ «አንቺ ቤተልሔም ከአንቺ አለቃ የሚሆን ይወጣልኛል።» ሚክ. 5÷1-4፤ «ኃጢአታቸውንም ሁሉ ወደ ጥልቅ ባሕር ትጥላለህ።» 7÷18-20።

«እነሆ የምሥራች ነጋሪ እግር በተራሮች ላይ መጥቶ ዘለዓለምነትን ያወራል።» ናሆ. 1÷15፤ «የቀባኸውን ሕዝብ ለማዳን ወጣህ፤ እኔ ግን በርሱ ደስ ይለኛል። በመድኃኒቴም አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።» ዕንባ. 3÷13-18፤ «እንደ ቃል ኪዳኔ መንፈሴ

በመካከላችሁ ይኖራልና አትፍሩ።» ሐጌ. 2÷5፤ «አንቺ የጽዮን ልጅ እነሆ ወዳንቺ መጥቻለሁና ደስ ይበልሽ።» ዘካ. 2÷10-11፤ «በዚያ ቀን በኔ ላይ ተላልፈሽ በሠራሽው ሥራ ሁሉ አታፍሪም።» ሶፎ. 3÷9-17፤ «እርሱ የእግዚአብሔርን መቅደስ ይሠራል፤ በዙፋኑም ላይ ካህን ይሆናል።» ዘካ. 7÷9-12፤ «አንቺ የጽዮን ልጅ እነሆ ጻድቅ ንጉሥሽና መድኃኒትሽ ድኻ ሆኖ÷ በአህያ ላይ ተቀምጦ ይመጣልሻል።» ዘካ.9÷9-12፤ «በዚያ ቀን በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ከኃጢአትና ከርኵሰት የምታነጻ ምንጭ ትከፈታለች።» ዘካ. 13÷1-9፤ «እነሆ መልእክተኛዬን እልካለሁ፤ እናንተ የምትሹትና የምትወዱት የቃል ኪዳን መልክተኛ መጣ።» ሚል. 3÷1።

የተወደድህ ወንድሜ ሆይ! ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል የሆነውን ክርስቶስን÷ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ጋራ ትክክል መኖሩንና ለአዳም (ለሰው ልጆች) አስታራቂ÷ ለዓለምም መድኃኒት እንዲሆን መመደቡን ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ የተነበዩለትንና የመሰከሩለትን ለመረዳት ከፈለግህ÷ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእየ ዮሐንስ የተጻፈውን ቃል በሥጋዊው ጠባይህ ሳይሆን ÷ በመንፈሳዊ ሐሳብና ኅሊናህ አስተውለህ መርምር፤ ምሳ. 8÷1-36፤ 2ጢሞ. 3÷16፤ 2ጴጥ. 1÷21።

«ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው። ሥጋዊ ሰው በርሱ ዘንድ ስንፍና መስሎ ስለሚታየው የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት አይቀበለውም። መንፈሳዊ ሰው ሁሉን ይምረምራል፤ እርሱ ግን በማንም አይመረመርም።» የሚሉትን ቃላት አጥብቀህ መርምራቸው ዮሐ. 3÷6፤ 1ቆሮ.2÷10-16። ቅዱስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ተጻፈ ሌትና ቀን በትጋት እየመረመረ ለሚያስተውለው ሰው÷ ለትምህርት÷ ለተግሣጽ÷ ለጽድቅ÷ ለማስተማርና ልብንም ለማቅናት ይጠቅመዋል፤ 2ጢሞ. 3÷12-17። እርሱ በኃይሉ ይርዳህ፤ አሜን።

ምዕራፍ 20

ስለ ጥምቀትና ቊርባን

ጥምቀትና ቊርባን ለሰው ሕይወት መሠረትና ጠፈር ስለሆኑ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ የሠራቸው ማኅተመ ጸጋና መድኃኒተ ነፍስ ናቸው። ሥርዐተ ጥምቀት የጸጋ ልጅነትን የሚያስገኝ ሲሆን፥ ፍሬ ነገሩ ግን ሰው ከማኅፀነ ቤተ ክርስቲያን ለማደር፥ ከሥጋ ቤት ወጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ዳግም ከመንፈስ ለመወለድና ለመታደስ፥ በስመ ሥሉስ ቅዱስ የሚገኝ ሀብትና በውሃም የሚደረግ ረቂቅና ትልቅ ምስጢር መያዣ ነው፤ ዮሐ. 3፥1-11፤ ኤፌ 1፥7-14።

ይህንኑ ምስጢር ግን መጥምቁ ዮሐንስ በኃጢአታቸው እየተጸጸቱ የተናዘዙትን አጥምቆ <u>ንስሓ ግቡ፤ በወንጌል እመኑ</u> እያለ የጥምቀትን ውል እየሰበከ እንደነገራቸው፥ ተጠማቂዎቹም ትምህርቱን ተቀብለው ስርየተ ኃጢአታቸውን አምነው፥ ከአሮጌው የዓለምና የሥጋ ልደት ተለይተው፥ በጎውንና ዐዲሱን የንስሓ ፍሬ ለማፍራት የሚችሉበት ጥልቅ ምስጢር ነው። መድኃኒታችንም የመጣበትን ጉዳይ ከመጀመሩ በፊት፥ ለትስብእቱ የሚያስፈልገውን ኃይል የሚሰጠው ምስጢር ስለሆነ፥ በ30 ዓመቱ በእደ ዮሐንስ ስለ ተጠመቀ ዲያብሎስን ተዋግቶ ድል ነሥቶታል፤ ማቴ. 3፥1-17፤ 4፥1-10፤ 10፥7፤ 1ዮሐ. 3፥8።

ሆኖም የሕፃናትን ጥምቀት በተመለከተ፥ በሕገ ኦሪት በ8ኛው ቀን ግዝረት እንደ ተሠራ፥ እንዲሁም በዘመነ ሐዲስ መድኃኒታችንና ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ኢትክልእዎሙ ለሕፃናት ከመ ይምጽኡ ኀቤየ» «ሕፃናትን ተዉአቸው፤ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው።» ብሎ እጆቹን በራሳቸው ላይ ጭኖ ሲባርካቸውና ሲጸልይላቸው እንደነበረ ማቴዎስ በ19ነኛው ምዕራፍ ላይ ቁ.13-15 ገልጾ ነግሮናልና፥ በዚሁ ቃል መሠረት በሕፃንነት ጊዜ ሊጠመቁ ይገባል እንጂ፥ አንዳንድ ማኅበሮች እንደሚሉት እስከ 30 ዓመት ዕድሜያቸው ወደርሱ መጥተው ጸጋውንና ሀብተ ወልድነቱን ሳይቀምሱ፥ ባዕዳን ሆነውና ተከልክለው ሊኖሩ ከቶ አይገባም፤ ሮሜ 5፥7-21፤ ማር. 10፥13-16።

ጉባኤ ዘሐዋርያት <u>«ነአምን በአሐቲ ጥምቀት» «በአንዲት ጥምቀት እናምናለን»</u> ይላል። እኛም ወላጆቻችን እንደአጠመቁን ከአመንን በቂ ነገር ነውና፥ የያኢሮስ ልጅ አባትዋ ስለ አመነ ድናለች፤ ሁሉንም ነገር የምትሠራ ግን ወይዘሮ እምነት ነች።

ጥምቀት እንደ ልብስ የማያረጅ መሆኑን አንርሳ፤ ማር. 5÷21-42፤ 9÷17-29::

ሕፃን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለመቀበል ችሎታ እንዳለው ግን እንኳን ተወልዶ ዮሐንስ መጥመቁ ከተፀነሰ በ6 ወሩ በከርሠ እሙ (በእናቱ ማኅፀን) ሆኖ ኢየሱስን በዐይነ መንፈስ አይቶ በደስታ መዝለሉ ይታወቃል ሉቃ.1÷44:: ኤርምያስና ጳውሎስም በእናቶቻቸው ማሕፀን ሳሉ በመንፈስ ቅዱስ ተመርጠዋል፤ ኤር. 1÷5፤ ገላ. 1÷15::

አሁን ግን ጽሑፍ «ዘአምነ ወዘተጠመቀ ይድኅን» «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ቢል ጥምቀትን መልካም ምግባር ለመሥራትና ትእዛዛትንም ጠብቆ የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር ለመሆን የተመደብንበት የጸጋ ውል ነው እንጂ ኤፌ. 4÷29-32፤ <u>በእምነት የዐዲስ ልደት ሕግን ሳንፈጽም ጥምቀት ብቻውን የሥጋ እድፍ በማጠብ የሚያድነን አይደለም::</u> የመድኃኒትነቱ ዐላማ ግን ሰው በበጎ ኅሊና የክርስቶስን ትንሣኤ አምኖ÷ ከኃጣውእና ከሥጋ ፍሬ ገላ. 5÷13-26፤ ተለይቶ÷ ዘወትር በጸሎትና ንጽሕና ነቅቶ ወደ እግዚአብሔር በመለመን ብቻ ተግቶ ቢያገለግል ነው 1ጴጥ. 3÷21:: ይህንኑ የጸጋ ዐረቦነ ጥምቀትና ቊርባንን ቸሩ አምላካችን ወሰን በሌለው ፍቅሩና የልግስና ምሕረቱ ያፈሰሰልን ስጦታ ነው እንጂ÷ ጽድቅ ስለ ሠራን የተሰጠን ደመወዝና ዋጋ አለ መሆኑን ለማወቅ ብትሻ ጥቅሱን ተመልከት፤ ሮሜ 3÷19-31፤ ቲቶ 3÷1-7::

ጥምቀትና ቊርባን ለሰው ሕይወት መሠረቱና ጠፈሩ ናቸው ብለናል:: ክርስቲያን የእምነቱን መሠረት በማኅተመ ጥምቀቱ ላይ ይመሠርተዋል:: ከዚሁ መሠረት ላይ ጸንቶ ቆሞ ቢኖርም÷ ከዓለም ፍትወትና በዲያብሎስ ቅንዓት ተዘርግቶ የሚቈየውን ፈተና ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና እምነት ድል ያደርገዋል 1ዮሐ.4÷4:: በእምነትና ጥምቀት ዐዲስ ሆኖ የሚኖር የእግዚአብሔርን ሀብተ ወልድና ያገኛል:: «እናንተ በክርስቶስ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁታልና÷ በክርስቶስ እምነትም የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን በቅታችኋል::» ገላ. 3÷26-27::

እውነተኛው ክርስቲያን ቅዱስ ቊርባንን አዘውትሮ ቢመገብ÷ ቊስለ ልቡናው ይፈወሳል፤ የደከመው ኅሊናውም ይጐለምሳል፤ ዐዲስ መንፈሳዊ ኃይልና ፍጹም የዕረፍት ሕይወትና የኃጢአት ስርየት ያገኛል ዕብ.10÷12-23:: ቈራቢ በኃጢአቱ አዝኖና ተጸጽቶ÷ ከዓለምና ከሥጋ ፍሬ ተለይቶ ቢቈርብ÷ ከስል የመሰለውን ኃጢአቱንና ደም የሚመስለውን ርኵሰቱን በረዶና ጥጥ

አስመስሎ፥ ዐጥቦና ቀድሶ የሚያነጻው የኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሕ ደሙ ብቻ ነው፤ ኢሳ. 1፥18፤ 1ዮሐ. 1፥7፤ ራእ. 1፥5::

ቅዱስ ቊርባን ምንም እንኳ በግዙፉ ኅብስትና ወይን ቢደረግ፥ አምነው ለሚቀበሉት ሁሉ ግን ሦከ ኃጢአትን አቃጥሎ የሚያጠፋ፥ ባሕረ ሲኦልን አሻግሮ ገነት የሚያገባ መለኮታዊ የእሳት መርከብ ነውና፥ ሳይጠራጠሩ ሕይወት ያለው የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን በእምነት ኃይል ጸንቶ፥ በኀሊና ተረድቶ ፈውሰ ነፍስ ነው ብሎ አምኖ መቍረብ ይገባል፤ ማቴ. 26፥26-28::

ይህንኑ ትልቅ የስርየት መሣሪያ የሆነውን ምስጢረ ቍርባንን ግን፥ ሰው አስቀድሞ ከጣዖታዊ ርኵሰትና ከዓለማዊ ፍትወት ተሰናብቶ፥ መድኃኒትነቱ በቂ መሆኑን አምኖና መርምሮ፥ ለይቶና በራሱ ላይ ፈርዶ ሊቀበለው ይገባዋል:: ምንነቱን ሳያውቅና ከምድራዊ ሕብስትና ወይን ሳይለይ፥ ለመቍረብም መብቃቱን በመንፈሱ ፈርዶ እሳተ መለኮትነቱን በእምነት ሳይረዳው ቢቈርብ ግን፥ ፈውሰ ኃጢአት በመሆኑ ፈንታ ከፍዳና ኵነኔ የሚያገባ ደፋር ከሳሽ ስለመሆኑ፥ የጳውሎስን ምክር አስቀድሞ ማድመጥና መገንዘብ ይገባል፤ ያስፈልጋልም፤ 1ቆሮ. 11፥23-31::

የምሕረት አባትና ጌታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ፥ የዘለዓለም ሕይወት አለው::» ብሎ ሲያበቃ፥ ለሐዋርያቱ «የሰማይና የምድር ሥልጣን ተሰጥቶኛ ልና ሂዱ፤ አሕዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ፥ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፤ <u>በርሱም ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤</u> እኔም እነሆ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ከእናንተ ጋራ ነኝ::» ማቴ. 28፥16-20 ብሏል:: ስለዚህ እርሱ ከኛ ጋራ መኖሩን የምናውቀው፥ ሥጋውና ደሙን በእምነት እየተመገብን ከእርሱ ጋር ብንዋሐድ ነው:: በዚህም የአምላካዊ ባሕርይ ተካፋዮች ለመሆን እንበቃለን፤ 2ጴጥ. 1፥4:: ይህን የማይታበለውን ቃሉን ግን በእምነት ታንኳ፥ ከዐመፀኛው ባሕረ ዓለምና ጥርጣሬ ከሚባለው የማዕበል ወንዝ ተሻግሮ (ወጥቶ)፥ ኢየሱስ ብቻውን የዓለምን ኃጢአትና የዲያብሎስን ክፋት የሚደመስስ እውነተኛው አዳኝና አስታራቂ፥ ከሰማይ የወረደ ንጹሕ የፋሲካ በግ መሆኑን አምኖና በደሙ ታጥቦ መንጻትና መጽደቅ ካልሆነ፥ ሕይወትን ሊሰጥ የሚችል ከቶ ሌላ ፈውስ በዓለም አይገኝም፤ ኢሳ. 63፥1-19፤ 1ዮሐ. 1፥7፤ 3፥8::

«ኢየሱስ ክርስቶስ ወደደን ከኃጢአታችንም ሁሉ በደሙ ዐጠበን::» ራእ. 1፥5:: «ሌቦችና ስስታሞች፥ ሰካሮችና ተሳዳቢዎች፥

ነጣቂዎችና አመንዝራዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሷትም:: እንደዚህ የመሰሉም ከናንተ ውስጥ ነበሩ፤ ነገር ግን ሰው ወዳጅ አምላካችን በዘለዓለማዊ ፍቅሩና በክቡር ደሙ ስለ ገዛችሁ በመንፈሱ ታጥባችሁ በቃሉም ተቀድሳችሁ ጸድቃችኋል::» 1ቆሮ. 6÷9-20::

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! የጥምቀትና የቍርባን ምስጢር በእደ እምነት ተጨብጦ የሚያዝ እርግጠኛ መድኃኒት መሆኑን አስቀድመህ «ዘየአምን በወልድ÷ ዘበልዐ ሥጋየ÷ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም» «በወልድ ያመነ፤ ሥጋዬን የበላ÷ ደሜንም የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤» የሚሉትን ሁለት ቃላት በልብህ ጽላት ቀርጸህ መያዝ አለብህ:: ለዚህ ለክርስቶስ ደምም ምሳሌው በሕገ ኦሪት የእንስሳ ደም ለሕዝቡ የኃጢአት ማስተስረያ እንደ ነበረ አንብብና አስተውል:: ደም ሳይፈስ ግን ከቶ ስርየት የለም፤ አይገኝም፤ ዘፀ. 24÷6-8፤ ዕብ. 9÷1-15፤ ዘሌ. 17÷11:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዕዳ ሊከፍል ብሎ በፈቃዱ በብዙ የላብ ጸሎትና ጻዕር÷ መከራና ሥቃይ÷ ጭንቅና ፍርሃት ውስጥ አልፎ እኛን አዳነን፤ ሉቃ.22÷39-44፤ ዕብ.5÷7-10::

ይህም ስላልበቃ በሕግ አፍራሽነት የሞተውን ሕይወታችንን ለማዳን ብሎ በፈቃዱና በፍቅሩ÷ በሞቱም ተቤዠን፤ ወይም ዕዳችንን በመስቀሉ ከፍሎ ከአባቱ ጋር አስታርቆ÷ ድሮ በስሕተታችን ያጠፋነውን የአምላክ ልጅነት አስመልሶ ሰጥቶ አከበረን፤ ዮሐ. 17÷14-26:: ይህም የሕይወት ምንጭ በባዕዳን÷ በመልአክና በፍጡር÷ በጻድቃንና ቅዱሳን ድካም ሳይሆን÷ በራሱ አካልና ሕይወት «ይህ ስለእናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ነው፤ ይህ ስለ ብዙ ሰዎች ኃጢአትን ለማስተስረይ የሚፈስ የአዲስ ሥርዐት ደሜ ነው::» ብሎ በቂ የሆነ የማያወላውል እውነተኛ መድኃኒተ ነፍስና ሥጋ ሰጠን፤ ማቴ. 26÷26-30፤ ማር.14÷22-26፤ ሉቃ. 22÷14-20፤ 1ቆሮ. 11÷23-31፤ ዕብ. 10÷4-23፤ ራእ. 7÷17::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችንና ወንድማችን ስለሆነ÷ ሞታችንን በሞቱ ድል ነሣልን፤ በኃጢአት የረከሰውን ሥጋችንንም በንጹሕ አካሉ አንጽቶ አደሰልን፤ በሰሪቀ ዕፀ በለስ ከገባንበት ወኅኒ (እስር ቤት) አወጣን፤ በክቡር ደሙም እስራታችንን ፈታልን፤ የጨለማውን ሥልጣንና የተጻፈብንን የዕዳችንን ጽሕፈት በመስቀሉ ደምስሶ ነጻ አወጣን፤ ቈላ. 1÷13-20፤ 2÷8-15::

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! ይህን የመሰለ የማይቀየም ቸር ዘመድና ወዳጅ÷ እውነተኛ መድኃኒትና አማላጅ ትተህ÷ የማይጠቅምና የማያድን÷ በነኪርና (በባዕድና) በፈጠራ መድኃኒት

ተታልለህ ብታምን ግን፥ ዋጋህ ረኃብና ሥቃይ፥ ሐዘንና ወዮታ፥ ብርቱ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት፥ ርስትህም እሳቱ የማይጠፋ፥ ትሉ የማያንቀላፋ፥ ጨለማው የማይገፋ መሆኑን ዛሬ ዕወቀው፤ ማር. 9፥43-48፤ ሉቃ. 13፥24-28፡፡

ስለዚህ ድምፁን ከሰማህበት ቀን ጀምረህ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መድኃኒትህን የምታገኝበትን ነገር ዛሬ አድርግ ፊልጵ.2፥5-15፡፡ በጥምቀትና ቊርባን ብቻ ከእርሱ ጋር ታረቅ፤ ሰላምም ሁን፤ ከዚያ ወዲያ በጎነቱንና ጽድቁን ታገኘዋለሁ፡፡ ክርስቲያን ሆይ ትእዛዛቱን ብትጠብቅ እነርሱም አንተን ይጠብቁሃል እንጂ፥ አንተ ጻድቅ ብትሆን እግዚአብሔርን ምን ትጠቅመዋለህ? ኢዮ.22፥1-30፡፡ «አሁን ግን የምመጣበትን ሰዓት አታውቅምና ንቃ፤ ንስሓም ግባ፤ እነሆ እኔ እንደ ሌባ እመጣለሁ፤ ዕራቁቱን እንዳይሆንና ኀፍረቱም እንዳይታይ ብሎ ልብስ ንጽሕናውን ሳያሳድፍ ተጠንቅቆ የሚጠብቀኝ ሰው ብፁዕ ነው፡፡» የሚል ምክሩን በልብህ ጽላት ጽፈህ ያዝ፤ ራእ. 3፥1-3፤ 17፥15፡፡

ወንድሞቼ ሆይ! እግዚአብሔር አንድያ ልጁን አሳልፎ እስኪሰጥለት ድረስ ዓለምን ወዶታልና፥ በእርሱ ያመነ ሁሉም የዘለዓለም ሕይወት ያገኛል እንጂ ከቶ አይጠፋም፡፡» ዮሐ. 3፥16፡፡ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኗልና ኃጢአታቸውን ሳይቈጥርባቸው ዓለሙን ለራሱ ታርቆታል፤ እኛም በክርስቶስ ፈንታ ከእግዚአብሔር ጋራ በንስሓ ብቻ ትታረቁ ዘንድ እንለምናችኋለን፡፡» 2ቆሮ. 5፥17-21፡፡ ወዳጆቼ ሆይ! እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ የወደደን ከሆነ፥ እኛም ሁላችን በአንድ ጌታ፥ በአንዲትም ጥምቀትና ቊርባን እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል፤ ኤፌ. 4፥1-7፤ 1 ዮሐ. 4፥7-21፡፡

«አሁን ግን የሥጋ ሥራና የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይብቃችሁ፡፡» 1ጴጥ. 4፥1-7፡፡ «ዓለምን አትውደዱት ኃላፊውን ዓለም በሚወድ ሰው ዘንድ የእግዚአብሔር ፍቅር የለበትም 1ዮሐ. 2፥13-17፡፡ «ለመድኃኒታችሁ ቀን በጥምቀትና ቊርባን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈሱን አታሳዝኑ፡፡» ኤፌ. 4፥30 «እርሱ ግን የሚያሳዝኑትን ሁሉ ወዳጅና አፍቃሪ በመሆን ፈንታ ተመልሶ ጠላት ይሆናል፡፡» ኢሳ. 62፥8-10፡፡

«ወንድሜ ሆይ! ሕይወታችሁንና ሥጋችሁን እግዚአብሔርን ደስ የምታሰኝና ተቀባይነት ያላት ሕያዉት መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቧት ዘንድ በእግዚአብሔር ምሕረት እለምናችኋለሁ፡፡» ሮሜ 12፥1-2፡፡

መንፈስ ቅዱስ የጸጋውን ብርሃን ይስጣችሁ፡፡ አሜን፡፡

ምዕራፍ 21

ስለ ተዝካርና ዝክር

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! «እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንስሓ» «ሰው ከሞተ በኋላ ንስሓ የለውም::» እንዳለው መጽሐፈ ግንዘት፥ አንተ ከሞትህ በኋላ ነፍስህ ከሁለቱ ቦታ በአንዱ ማለትም በሕፅነ አብርሃም በገነት፥ ወይም ከዚያ ባለ ጸጋ ጋራ በሥቃይ ቦታ ገሃነም ውስጥ ከገባች፥ ከዚያ አውጥቶና አምላክ የፈረደውን ገልብጦ ስፍራ ሊለውጥላት የሚችል ፍጡር እንደማይገኝ አስተውል፤ ማቴ. 25፥46፤ ሉቃ. 16፥25-26:: አምላክ ካሰረ የሚፈታ፥ ከፈታም የሚያስር ከቶ እንደሌለ ዮሐንስ በራእዩ «ዘነቤሁ ይነብር ኲሉ መራኁተ ቤተ ዳዊት አልቦ ዘያርኁ፥ ወአልቦ ዘየዐጹ ዘእንበሌሁ::» «የዳዊት መክፈቻ ያለው፥ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፥ የሚዘጋ የሚከፍትም የሌለ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል» ብሎታል፤ 3፥7-13:: እንዲያውም ገነት አጋፋሪና መዝጊያ የላትም፤ ራእ. 21፥21-26::

እንደ አገራችን መሪዎች የነመምሬ አታለሉ ልማድና *ሥርዓት* ግን፥ አንተ ከሞትህ በኋላ «ወዮላችሁ እናንተ የሕዝብ እረኞች፥ በጸሎት አመካኝታችሁ የምውታንንና የመበለቶችን ቤት ትበላላችሁ፤ ትውጣላችሁ፤ ስለዚህ ከሁሉ የባሰና የከፋ ፍርድ ይፈረድባችኋል::» ማቴ. 23፥13-14፤ ማር. 12፥38-40 ብሎ ጌታ በቃለ ወንጌል የዘለፋቸው ቀሳውስት፥ መበለቱን ወይም መበለቲቱን ከሐዘናቸው በማጽናናትና ችግራቸውን በማቅለል የምዉቱ ቤተሰቦች ከረኃብና ሥቃይ የሚድኑበትን፥ ሕፃናቱም የሚያድጉበትን ዘዴ በመፍጠር ፈንታ፥ ቤተሰዎቹን ሟቹ ከሞተ ከ7 ቀኑ ጀምረው፥ ሌላው ይቅርና በሥጋሁ ወደሙ ተወስኖ የዳነውን ቈራቢ እንኳ ሳይቀር፥ ከገነት ወይም ከገሃነም ወደ የትኛው ቦታ እንደገባ ሳያውቁ፥ «የሚያጸድቀው መድኃኒተ ነፍስ ከእኛ ዘንድ አለና ጸሎት ጸልየን፥ ዳዊት ደግመን፥ ከሲኦል አውጥተን አጽድቀን ገነት ልናስገባላችሁ የድካማችንን ዋጋ (ዐስበ ከናፍር መብልና መጠጥ) ማሰብና ማደራጀት አለባችሁ (ይገባችኋል)::» ብለው «ወየአስሩ ጾረ ዐቢየ፤ ወክቡደ ወያሰክምዎ ለሰብእ ዲበ መታክፍቱ::» «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ::» ማቴ. 23፥4 እንደ ተባለው፥ አበ ንስሓው (የንስሓ አባቱ) ለሐዘኑ መጨመሪያ የሚሆን ከባዱን የብረት ቀምበር በሐዘንተኛው ላይ በጭከና ይጭኑበታል::

እንዲሁም የሞት ዋጋ የማኅለፍተ ነፍስ፥ የግንዘት፥ የድልዋንና የሐዲገ ቊርባን እያሉም ቢያንስ ከመቶ እስከ አምስት መቶ ብር ድረስ ጥሎሽ ዕዳ ይጥሉበታል።

የሚቹም ልብሶችና ምንጣፉ ለልጆቹ የብርድ መከላከያና የአባታቸውን ጠረን እያሸተቱ ተስፋ እንዳይሆናቸው፥ አበ ንስሓው በጭከና እየገፈፉ፥ ሕፃናቱን ከመሬት አፍስሰው አልጋውንና ጀንዲውን፥ ጫማውንና ጭራውን፥ መሣሪያውንና ልብሱን፥ መጻሕፍቱንና በርኖሱን አንድ ሳይቀር ይህን ሁሉ በመንፈሳዊ አታላይነት አለ ፍርድ ይወርሱታል፤ ሕዝ. 34፥1-8፤ ቲቶ 1፥2፤ 2ጴጥ. 2፥12-22፤ ይሁ. 10-19።

የሀገሬ መንፈሳዊ መሪዎች ሰላም ሰላም እያሉ የወገኔን ልጆች ስብራት በሐሰት ይፈውሳሉ። እውነተኛው ሰላም ግን ያለ ክርስቶስ ወንጌል ከቶ ሊገኝ አይቻልም። ወይ እነ አባ፥ ርኩስ ነገር ስለሚሠሩና ስለሚያስተምሩሳ አፍረው ይሆን? የለም ኀፍረትን አያውቁትምና ከሚወድቁት ጋራ ይወድቃሉ፤ «የጉም ሌባ፥ ጉም ሲሸሽ ከምን ይገባ» እንጃ! ኤር. 8፥5-13።

እኛ የወንጌልን ሽታ የቀመስን ሰዎች ሕዝባችን ሮብዓማዊ (የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ የሮብዓም የአገዛዝ ቀምበር ለማለት ነው) የብረት ቀምበር ወርዶለት፥ ልዝብና ቀላል የሆነውን የክርስቶስን ቀምበር መች ያገኝ ይሆን? እያልን በሐዘንና ተስፋ ስንጠባበቅ፥ ስለ ተዝካር ጉዳይ መጀመሪያ በ24/11/29 ዓ.ም ለሕዝብ እንዲቀልለት ዕዳው በገንዘብ ይሁን ተብሎ ነበር። እንደ ገና ዛሬ <u>«ከዐሥር እስከ ተዝካር ባሉት ቀኖች ሁሉ የማቹ ቤተሰብ ሟቹን በገንዘብ ማጽደቁ ቀርቶ፥ ድግስ ተደግሶ እንዲሰከርበት ዐውጀናል።» የሚል የጭከና ቃል</u> አሥመራ በሚታተመውና «ፍኖተ ብርሃን» በተባለው መንፈሳዊ ጋዜጣ ስናነብ፥ መንታ ዕንባ ከማፍሰስ በቀር ሕዝባችንን የምንረዳበት ሌላ ዘዴና ኃይል አልነበረንም፤ ፍ.ብ.ቁ.13 25/4/45 ዓ.ም ተመልከት።

«እኔም ከፀሓይ በታች የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ፤ እነሆም ተጨናቂዎች እንባ ያነቡ ነበር፤ የሚያጽናናቸውም አልነበረም፤ በሚጋፏቸው እጅ ኃይል ነበረና ማንም ሊያጸና ናቸው የቻለ የለም።» ምሳ. 29፥1-2፤ መክ. 4፥1-3፤ 10፥1-7።

ሮብዓም የሰሎሞን ልጅ በነገሠበት ዘመን ሕዝበ እስራኤል ተሰብስበው «አባትህ ያከበደብንን ቀምበር አንተ እንድታቀልልን እንለምንሃለን፤» ቢሉት፥ እርሱም መልሶ «አባቴ የዕንጨት ቀምበር ጭኖ በአለንጋ ሲገርፋችሁ ነበር፤ እኔ ግን የብረት ቀምበር ጭኜ

ጊንጥ በሚባለው ከጭራ በተሠራ ጅራፍ እገርፋችኋለሁ::» አላቸው ይባላል፤ 1ነገ. 12÷1-14::

ወንድሞቼ ሆይ! ሀብታሞቹ ጽድቅን በድግስ ሲገዟት÷ ምግበ ዕለት እንኳ የሌላቸው ድኾች ወንድሞቼስ እንዴት ሊሆኑ ይሆን? እንደ መጻሕፍቱ ቃል ግን ሀብታሞችን «ወዮላችሁ!»÷ ድኾችን ግን «መንግሥተ ሰማያት የእናንተ ናትና ደስ ይበላችሁ::» የሚለውን ስናነብ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ሉቃ. 6÷20-25፤ 16÷19-25፤ ያዕ. 5÷1-5::

ወንድሞቼ ሆይ! ይህን ከመንፈሳዊ መሪዎቻችን የመጣልንን የጭከና ዐዋጅ ስንመለከተው ግን÷ በሕዝባችን ላይ ከፋሺስታዊ ቀምበር የከፋ ወይም የከበደ ተጫነ እንላለን እንጂ÷ በአዲሱ ዘመን የሚስማማና የተሻለ የሃይማኖት ነጻነት አግኝቷል ለማለት ከቶ አያስደፍርም:: ሀገራችን ግን ዱሮ የነካው ካማዊ መርገም÷ እስከዛሬ ድረስ በሴማዊው ክርስቶስ ለበረከታዊ ነጻነት ስለ አልተለወጠለት በጣም ይገርማል፤ ያሳዝናልም:: ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ማቴ. 11÷25-30፤ ገላ. 3÷7-29::

ቅዱሳን ሐዋርያት ግን ምዉት እያነሡ÷ ድዉይ እየፈወሱ÷ ለምጻም እያነጹ÷ አንካሳ እያሮጡ÷ ብዙ ብዙ ተአምራት ሠርተው ሕዝባቸውን ከሥቃይ እያዳኑ በእጃቸው ሠርተው ይመገቡ ነበር እንጂ÷ ሲያስተምሩ የክርስቶስን ጸጋ በዋጋ እየሸጡ በሕዝብ ላይ ዕዳ አልጣሉበትም:: «ወንሠርሕ እንዘ ንትቀነይ በግብረ እደዊነ፤ ታአምሩ ከመ ኢተሰቀቀ ንዋየክሙ፤ ኢወርቀ÷ ወኢብሩረ÷ ወኢአልባሰ÷ ኢነሣእኩ፤ ወኢኀበ አሐዱሂ እምኔክሙ::» «በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም::» እንዳለ ሐዋርያው፤ 1ቆሮ. 4÷9-13፤ የሐዋ. ሥራ 20÷32-36::

ሥጋዊ ዳኛን የበደለ÷ ሕጉንም ያፈረሰ ሰው ቢሞት የበደሉ ቅጣት (መቀጫ) እርሱ ከሞተ በኋላ ይሻራል (ይቀራል) እንጂ የሟቹ ቤተሰብ አይጠየቅበትም:: (ወንጀለኛ መቅጫ 9ኛ ምዕራፍ 152 ቁጥር ተመልከት) መንፈሳውያን ዳኞች የአገሬ ካህናት ግን÷ ሰው ስለ ሞተ የሟቹን ዕዳ በቤተሰቡ ላይ ይጥላሉ እንጂ÷ ሟቹን ገና በሕይወቱ ሳለ «በክርስቶስ እመን፤ ከሞትህ በኋላ የምትመገበውን ስንቅ ዛሬ ቋጥር፤ አምላክህንና ወንድምህን አፍቅር፤ ጾም ጸሎት ምጽዋት አዘውትር፤ በሥጋህ ወደሙ ተወሰን፤ በወንጌሉ ያለውን የክርስቶስን ሕግ ፈጽም፤ ይህን ካልፈጸምህ ግን ከቤተ ክርስቲያን ተከልከል::» ብለው በሥልጣናቸው አያስሩትም፤ ማቴ. 18÷15-18:: «እጥምቃችሁ

ሕግን መጠበቅ አስተምሯቸው።» ተብለው እንደታዘዙትም ወንጌልን ተግተው አያስተምሩትም። ማቴ. 10÷1-42፤ 28÷16-20፤ ማር. 1÷14-21፤ 1ጢሞ. 4÷6-16፤ 6÷13-20፤ 2ጢሞ. 4÷1-8።

እግዚአብሔርን ለምነን የሚቑን ነፍስ ልናጸድቅላችሁ እንችላለን ብለው የሚጸልዩት ጸሎትም እንደሚከተለው ነው። «ሀቦሙ በከመ እከየ ምግባሮሙ፤ ፍድዮሙ ፍዳሆሙ ላዕለ ርእሶሙ፤ ንስቶሙ፤ ወኢትሕንጾሙ፤ ወኢይባኡ በጽድቅከ፤ ወይደምስሱ እመጽሐፈ ሕያዋን÷ ወኢይጸሐፉ ምስለ ጻድቃን፤ ይጽለማ አዕይንቲሆሙ ወኢይርአያ፤ ወስኮሙ ጌጋየ በዲበ ጌጋዮሙ፤ ወይርከቦሙ መቅሠፍተ መዓትከ፤ አምላኪየ ረስዮሙ ከመ መንኰራኵር፤ ወከመ ሣዕር ዘቅድመ ገጸ እሳት፤ ከማሁ ስድዶሙ በዐውሎከ፤ ወሁኮሙ በቅሠፍትከ ምላዕ ውስተ ንጾሙ ኀፍረተ ወኀሣረ፤ ይምጽኦሙ ሞት ወይረዱ ውስተ ሲኦል ሕያዋኒሆሙ፤ ወኢትሣሃሎሙ ለኵሎሙ ገበርተ ዐመፃ፤ ወጻማ ከናፍሪሆሙ ይድፍኖሙ ወይደቅ ላዕሌሆሙ አፍሐመ እሳት፤ አንተ እግዚኦ አጽድፎሙ ውስተ ዐዘቅተ ሞት፤ ወኢታድኅኖሙ ወኢበምንትኒ፤ ከዐው መዓተከ ላዕሌሆሙ፤ ቀጥቅጥ መዝራዕቶ ለኃጥእ ወለእኩይ፤ ዝርዎሙ በኃይልከ፤ ለይኩኑ ከመ ጸበል ዘቅድመ ገጸ ነፋስ፤ ወይሠገሩ በትዕቢቶሙ፤ አጽድፎሙ አምላኪየ ወረዳእየ፤ ወይሤሬው ትራፋቲሆሙ ለኃጥአን፤ ይግብኡ ኃጥአን ውስተ ሰኦል፤» «እንደ ሥራቸው÷ እንደ አካሄዳቸውም ክፋት ስጣቸው፤ እንደ እጃቸውም ሥራ ስጣቸው፤ ፍዳቸውን ወደ ራሳቸው መልስ፤ ወደ እግዚአብሔር ሥራ ወደ እጆቹም አደራረግ አላሰቡምና ያፈርሳቸዋል እንጂ አይሠራቸውም፤ መዝ. 28÷4-5፤ በጽድቅህም አይግቡ፤ ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፤ ከጻድቃን ጋርም አይጻፉ፤ ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፤ መዓትን በላያቸው አፍስስ፤ የቍጣህ መቅሠፍትም ያግኛቸው፤ መዝ. 89÷23-24፤ 27-28፤ አምላኬ ሆይ እንደ ትቢያ በነፋስ ፊትም እንደ ገለባ አድርጋቸው፤ እሳት ዱር እንደሚያቃጥል÷ ነበልባልም ተራሮችን እንደሚያነድድ እንዲሁ በቁጣህ አሳድዳቸው፤ በመቅሠፍትህም አስደንግጣቸው፤ ፊታቸውን እፍረት ሙላው፤ መዝ. 83÷13-16። ሞት ይምጣባቸው፤ በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ይውረዱ፤ መዝ. 55÷15። ዓመፅ የሚያደርጉትን ሁሉ አትማራቸው፤ መዝ. 59÷5። የሚከብቡኝን ራስ የከንፈራቸው ክፋት ይክደናቸው፤ የእሳት ፍም በላያቸው ይውደቅ፤ መዝ. 140÷9፤ አንተ ግን አቤቱ ወደ ሞት ጕድጓድ ታወርዳቸዋለህ መዝ. 55÷23። በምንም ምን አታድናቸው፤መዝ. 55÷7። መዓትህን በላያቸው አፍስስ፤ መዝ. 69÷24። የኃጢአተኛንና የክፉን ክንድ ስበር፤

9÷35:: በኃይልህ በትናቸው፣መዝ. 59÷11:: በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይሁኑ፣ መዝ.35÷5:: በትዕቢታቸው ይጠመዱ፣ መዝ. 59÷12:: አቤቱ ጋሻዬ አዋርዳቸው፣ መዝ. 59÷11:: የኃጢአተኞች ቅሬታ ይጠፋል፣ መዝ. 37÷38:: ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፣ መዝ. 9÷17::» እንደዚህ የመሰለውንና ሌላውንም ሁሉ ንጉሥ ዳዊት ጠላቶቹን የረገመበትን ብቻ ሲራገሙ አድረው፥ «ዘነሣእክሙ በጸጋ ሀቡ በጸጋ» «በከንቱ ተቀብላችሁ በከንቱ ስጡ» ማቴ. 10÷8:: የሚለውን ቃል ወደ ኋላ ጥለውና ዋሽተው፥ እግዚአብሔርን ለምነን የሚቱን ነፍስ ከሲኦል አውጥተን፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለ አስገባናት ዋጋችንን በቶሎ ስጡን ይላሉ:: ይኸውም ንዋየ ዐመፃን፥ እክለ ሕማምን (የመከራ እንጀራን) ዘለዓለም እየበሉ አንድ ቀን ስንኳ ጠግበው አያውቁም፣ ኢሳ. 56÷10-12::

ሀብታሙንስ እንኳ አታልለው ቢበሉት ምንም አልነበረም፥ ከሁሉ የባሰውና የከፋው ግን ድኻው ሚች አንድ በሬ ቢኖረው ለልጆቹ ማሳደጊያና ተስፋ እንዳይሆን፥ «ሕፃናቱ በዕድላቸው ያድጋሉ፣ በሬውን ግን ለኛ ዋጋ አድርጋችሁ ስጡን::» ብለው፥ በጭከና አሳርደው ሰውየው ከሞተ በ30 ወይም በ40 ቀኑ ይበሉታል:: ሕፃናቱ ግን በረኃብና ችግር ሞተው ያልቃሉ:: ስለዚህ የሀገሬ ካህናት ራሳቸውን ብቻ የሚያስማሩትንና በዘመነ ሕዝቅኤል የነበሩትን የሕዝብ እረኞች (ካህናት) ይመስላሉ:: እግዚአብሔር አምላክ የሚቾችን ቤተሰብ፥ የመበለቲቱንና የሕፃናቱን ደምና ዕንባ ከማን እጅ ይፈልገው ይሆን? ሕዝ. 3÷16-21፣ 34÷1-31:: እግዚአብሔር ያየዋል ይሻውማል፣ 2ዜና. 24÷19-22፣ ማቴ. 23÷23-39::

አምላካችን «በመቅደሴ የሚያገለግሉ ካህናት ከቶ ጠጅ እንዳይጠጡ፣ ቅዱሳን ይሁኑ፣ ሕጌንና ትእዛዜን በእውነት ይጠብቁ፣ ለሕዝቤም ጽድቅ ያስተምሩ፣ የቅዱስና የርኩስ ልዩነት ምን እንደሆነ በምግባር ያሳዩ፣ ንጹሐንም ይሁኑ፣ እንደ ፍርዴም ይፍረዱ፣ ርስታቸውና ግዛታቸውም እኔ ነኝና ግዛትና ርስት ከቶ አይሁንላቸው፣ አትስጧቸው::» ብሎ ተናግሮ ነበረ፣ ሕዝ. 44÷15-28::

መንፈሳዊ መሪዎቻችን ግን ሰማያዊ ክብራቸውን ዘንግተው በምድራዊው ለወጡት፣ በጠጅና በስካር ምክንያት ሳቱ፣ ነቢዩና ካህኑ፥ ቄሱና ዲያቆኑ ከስካር የተነሣ ምንም አላወቁም፣ በጠጅ ውስጥ ጠለቁና ዘቀጡ፣ ከስካርና ስስትም የተነሣ ተቅበዝብዘው ተሳሳቱ፣ «ሰካራሞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሷትም»

የሚለውን ቃል ረሱ፤ በፍርድም ተሰናከሉ፤ የፈሪሳውያንን መንገድ ተከተሉ፤ የምዉታንን ቤት ዋጡ፤ በሉ፤ ስለዚህም ማዕዳቸው ሁሉ ትፋትና ርኵሰትን ስለተሞላ ከቶ ንጹሕ ስፍራ ወይም ቅዱስ ሰውና ካህን የለም፤ ኢሳ. 28÷7-13::

ለሕዝባቸው መልካም አርአያ እየሆኑ÷ ምእመናን በጎቻቸውን በቅዱስ መጽሐፍ መስክ እያሰማሩ÷ ዐውሬ ዲያብሎስ እንዳይበላባቸው÷ በጥንቃቄና በትጋት ነቅተው የሕይወትን ቃል እየመገቡና እየመከሩ÷ ምንም ምን ያልተደባለቀበትን የወንጌልን ወተት ብቻ እያጠቡና እያስተማሩ÷ ነፍሳትን የሚያድኑ የእውነት ካህናት ቢገኙ ግን 1ጴጥ. 2÷1-12 ሐዋርያ ጳውሎስ «ለሠራተኛው ዋጋው ይገባዋል::» 1ጢሞ. 5÷17-18 እንዲል÷ ምእመናኖቻቸው ፈቅደው የሰጧቸውን እውነተኛውን የድካም ዋጋቸውን ተቀብለው÷ በመጠን እየተመገቡ ሊኖሩ ይገባቸዋል እንጂ÷ ሱቅ እንደከፈተ ነጋዴ በማታለልና በግዴታ የገዛ ወንድሞቻቸውን ጨቍነው ይዘው እያጭበረበሩ÷ ሥጋዊ ጥቅማቸውን ብቻ በማሰብ እየተጨነቁ÷ የእግዚአብሔርን ቃል መናገጃ ሊያደርጉት ከቶ የማይገባና የሚያስጸይፍ ነገር ነው፤ የሐዋ. ሥራ 20÷28-34፤ 1ጴጥ. 5÷1-9፤ ይሁ. 1-19፤ ቲቶ 2÷1-8::

«ተግሣጽና ምክር በማትቀበል በዐመፀኛይቱ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ መኳንንቶች እንደሚያገሡ አንበሶች ናቸው፤ ፈራጆችዋም እስኪነጋ ድረስ አንዲት ምታሪ እንደማያቈዩ እንደ ማታ ተኵሎች ናቸው:: ነቢያትዋ መቅደሴን የሚያረክሱ÷ ካህናትዋም በሕጌ ላይ ግፍ የሚያደርጉ ተንዳጆችና ተንኰለኞች የኃጢአትም መሪዎች ስለ ሆኑ ኀፍረትን ከቶ አያውቁትም::» ሶፎ. 3÷1-5::

«እጃቸውን መልካም ነው እያሉ ወደ ክፋት ይዘረጉታል፤ አለቃውም መማለጃ ይሻል፤ ፈራጁም በብድራት ይፈርዳል፤ ታላላቆች የሚባሉትም ሁሉ ክፋትን እየጐነጐኑ እንደ ነፍሳቸው ፈቃድ ይናገራሉ፤ ከእነርሱ እሻላለሁ የሚለው እንደ አሜኬላ÷ ቅን የተባለውም እንደ አቃቅማ (ኵርንችት) ነው::» ሚክ. 7÷1-4::

«ወገኖቼን በሚያስቱ በነቢያት ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በጥርሳቸው የሚነክሱ÷ በሰላምም የሚጠሩ÷ በአፋቸውም አንዳች በማይሰጥ ሰው ላይ ሰልፍ ያስቡበታል፤ አለቆች በመማለጃ ይፈርዳሉ፤ ካህናትዋም በዋጋ ያስተምራሉ ነቢያትዋም በብር ትንቢት ይናገራሉ:: ከዚህም ሁሉ ጋር እግዚአብሔር በመካከላችን ነውና መከራ አይመጣብንም እያሉ ይታመናሉ፤ እግዚአብሔር ግን ፊቱን ከርሳቸው ይሰውራል::» ሚክ. 3÷1-12::

ወንድሜ ሆይ! ይህን የካህናተ ኦሪት ማታለል የሆነውን፥ ለነፍስና ሥጋም የማይጠቅመውን አሮጌውን ልማድ፥ ማቴዎስ በ23ኛው ምዕራፍ እንደ ጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስም የነቀፈው ነውና፥ «ወየአስሩ ጾረ ዐቢየ ወክቡደ ወያስክምዎ ለሰብእ ዲበ መታክፍቲ፡፡» «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤» (ማቴ. 23፥4) የተባለው፥ እግዚአብሔር ያላዘዘውን፥ ለመሸከምም የማይመቸውን አሮጌውን ጽድቅ፥ ከባድ የሆነውን የሰው ሥርዐት (ቀምበር) በቃለ እግዚአብሔር (ቅዱስ መጽሐፍ) ማሕጼ (መጥረቢያ) ቈርጠህ ጥለህ፥ ዛሬ ክርስቶስ በወንጌሉ ብቻ ያዘዘውንና ለመሸከም የሚመቸውን ቀላሉንና ልዝቡን አምላካዊ ቀምበር ብትሸከም ግን ለነፍስና ሥጋህ ዕረፍት ታገኛለህ፤ ማቴ. 11፥25-30፤ የሐዋ. ሥራ 15፥8-11፡፡

አንተ ከሞትክ በኋላ ግን አበ ንስሓህን ከነማኅበሩ፥ ያገርህን ሹም ከነ ገባሩ፥ አታላዮችና አላጋጮች ሁሉ ተሰብስበው «በእንተ ተዝካሩ ለእገሌ» ብለው በልተው ጠጥተው ቢሰክሩ፥ በውሸት ነው እንጂ ከሲኦል እጅ አንድ ነፍስ ነጥቆ ለማዳን የሚችል ፍጡር የለም፤ ከቶም አይገኝም፡፡ ዓለምና ሞላዋ ብትገመትም የነፍስ ዋጋ ለመሆን አትበቃም፤ ሉቃ. 9፥23-26፡፡

እግዚአብሔር አምላክም በዘመነ እስራኤል የነበሩትንና፥ ሕዝባቸውን በእውነትና አምላክን በመፍራት የማይጠብቁትን፥ ድኾችን የሚበድሉትንና የሚንቁትን ባለሥልጣኖች፥ «በውስጥዋ ያሉት ነቢያት እንደሚጮህና እንደሚሰብርም አንበሳ መስለው ነፍሶችን በማታለል ሊበሉ በአንድነት ሆነው ተማማሉ፡፡ ካህናትዋም ንጹሕና ርኩስን እንዳይለዩ ዐይኖቻቸውን አሳወሩ፤ መቅደሴንም አረከሱ፤ ሕጌንም አቃለሉ፡፡ አለቆችዋም እንደ ጅቦች ደም ለማፍሰስና ነፍሶችን ለማጥፋት፥ ትርፍ ለመሻትና የሰውንም ገንዘብ ለመንጠቅ ይነቃሉ፡፡ ነቢያትዋም እግዚአብሔር ያልተናገረውንና ያላዘዘውን እያስተማሩ ሕዝባቸውን ገለባ በሌለው ጭቃ እየለሰኑ በኔ ላይ ዐመፅ ይሠራሉ፡፡» እያለ በሚያስፈራና በሚያስደንቅ ቃል ሲዘልፋቸው እንደነበረ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል፤ ሕዝ. 22፥23-31፡፡

በዘመናችን የተገኘውና የገነነው «ፖለቲካ» የሚባለው የታላላቆቹ ሰዎች ትምህርትና መብትም፥ እንደኔው አስተያየትና ሐሳብ ትርጓሜ ስሰጠው፥ ያው ማታለል ማለት ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ፤ ዳን. 11፥27-34፡፡

ከአሁን በፊት ወገኔ ዕውቀት ቢያንሰው በአላዋቂዎች ተማረከ ኢሳ.5፥9-13፡፡ ከዐዲሱ ዘመን ጀምሮ ለወደፊቱ ግን የሀገሬ

ወጣቶች በእውነተኛው የወንጌል ብርሃን ተመርተው፥ የነፍሳቸውን ዕረፍትና የሥጋቸውን ነጻነት አግኝተው፥ ልዝቡንና ቀላሉን የክርስቶስን ቀምበር ብቻ ተሸክመው፥ ራሳቸውን አድነውና ጠቅመው፥ ሀገራቸውን ያድናሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ እንጂ፥ በተዝካርና ዝክር፥ በአሮጌው ልማድና በከባዱ የፈሪሳውያን ቀምበር ይጠመዳሉ (ይማረካሉ) ብዬ ከቶ አልጠረጥርምና እባክህን መርምር፤ ማቴ. 11፥28-30፤ 23፥1-10።

ወዳጄ ሆይ! ከሲኦል እጅ አድኖ በቀኝ ለማቆም የሚያበቃህ ግን «አቅድሙ ስንቀክሙ።» «ስንቃችሁን አስቀድሙ» እንደ ተባለው፥ እውነተኛው በልብ ያለው ሃይማኖትህና መልካሙ ምግባርህ ብቻ ነው። ነፍስ ሊያድን የሚችል ሌላ መድኃኒት እግዚአብሔር እንዳላዘዘ መጻሕፍትን ጠይቅ፤ ማቴ. 6፥19-21፤ ያዕ. 2፥14-26፤ 1ጴጥ. 3፥18-22፤ ዕብ. 10፥1-31።

አንባቢ ሆይ! ከአንተ የምሸሽገው ምስጢር ስለ ሌለኝ ከዚህ አስከትዬ ስለ በዓላት የሚናገር ዐጭር ቃል ጽፌልህ አለሁና ሳትቸኩል አስተውለህ አንብብ፤ ማቴ. 10፥26-27። ክርስቶስ እውነትና ሐሰት የሚለይ ብሩህ ልቦና ይስጥህ፤ አሜን።

ምዕራፍ 22

ስለ በዓላት

በዓላት ማለት መታሰቢያ÷ ዝክር ወይም የደስታ ቀን ጉባዔ ቀን ማለት ነው፤ ዘፀ. 12÷1-14፤ 2ዜና. 8÷13፤ ነህ. 8÷6-14::

ይኸውም በመጽሐፈ ብሉይ እንደ ተጻፈው የሚዘከረው እግዚአብሔር ብቻ÷ ቀኖቹም በዓመት ሦስት ስማቸውም ናእት (የቂጣ በዓል)÷ ሠዊትና (የመከር በዓልና) መጸለት (የዳስ በዓል) ነው፤ 2ዜና. 8÷13::

እንዲሁም በመጽሐፈ ሐዲስ እንደ ተገለጸውና በፍትሐ ነገሥትም በ19ኛው አንቀጽ እንደ ተደነገገው÷ በዓላተ ወልድ የተባሉት በአንድ ዓመት ውስጥ 9 ቀናት ብቻ ናቸው:: አባ ገብረ ወልድና መምሬ ተክለ ዮሐንስ የተባሉ ሰዎች ግን÷ ተአምረ ማርያምና መርሐ ዕውር በሚባል በ1934 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ባስጻፉት መጽሐፋቸው በገጽ 127÷ በፍትሐ ነገሥት የሌለውን «በአንድ ዓመት ዐርባ አንድ ቀን ታዟል::» ብለው በውሸት ጽፈዋል:: እንደ ሀገራችን ባህልና ልማድ ግን ፫፻፲ወ፳ ርቱዓነ ሃይማኖት ያላወጁት÷ በአንድ ወር ዐሥራ ስምንት ቀን በዓላት እየተባለ የማይሠራበት ለመላእክት÷ ለቅዱሳን÷ ለጻድቃን÷ ለሰማዕታት÷ ለአባሆይ እገሌና ለእማሆይ እገሊት ለክብራቸው ተብሎ ተደግሶ የሚሰከርበት÷ ፈጣሪን ትቶ ፍጡር የሚመለክበት በአንድ ዓመት ከሁለት መቶ የሚበዛ በዓል ይደረጋል:: ስለዚህ ይህን ዋጋ የሌለው የሰው ሥርዐት ከንቱ የሆነ ስሕተት ስለተከተልን÷ ዋጋችን ያ ክፉ ጠላት የሰው ልጆች ደመኛ የሆነው ማጣት ወይም ረኅብ ብቻ ነው (ሆኗል)፤ ምሳ. 6÷9-11፤ 13÷4፤ 20÷13::

ወዳጄ ሆይ! ሥራ ወዳጆች የሆኑት ወንድሞቻችን በኑሮአቸው÷ በምግብና በልብሳቸው እንዴት እንዳሉ÷ እኛ ግን ሳንሠራ÷ በዓላት ስንቈጥርና የሚሠራውን ወንድማችንን ቡዳ÷ ፋቂ÷ ሸማኔ÷ ቀጥቃጭ÷ አንጥረኛ÷ ሸቃጭ÷ ሠራተኛ÷ ነጋዴ÷ ወታደር÷ ገበሬ (ዓኺይ)÷ ጩዋ÷ ባሪያ ብለን እየተሳደብን የምንኖር÷ ሕገ ክርስቶስ «ሰዱሰ መዋዕለ ተገበር ተግባረከ» «በስድስት ቀን ተግባርህን አከናውን» የሚለውን ሳንፈጽም÷ በስም ብቻ ክርስቲያኖች የምንባለው እንዴት ያለ ኑሮ እንደምንኖር ልብ ያለው አስተዋይ ሰው አይስተውም ይሆናል፤ ዘዳ. 28÷43-45:: «ፍትወት ይቀትሎ ለሃካይ፤ እስመ ኢይፈቅዳ እደዊሁ ምንተኒ

ይግበራ፡፡» «እጆቹ ይሠሩ ዘንድ አይፈቅዱምና፥ ኃጥእ ቀኑን ሁሉ ምኞትን ይመኛል፡፡» ይላል ጠቢቡ ሰሎሞን፤ ምሳ. 21፥25፡፡

አሁን ግን ይህን የሰው ሥርዐት አሮጌ ልማድን ተከትለን፥ ለጻድቃን ዝክር፥ ክብር፥ መታሰቢያ እያልን የምንበላውና የምንጠጣው ሁሉ፥ እግዚአብሔር አምላካችን እንደ መሥዋዕተ ጣዖት አድርጎ የሚጸየፈው ርኩስ ነገር ስለሆነ፥ በባሪያው በሙሴ አፍ «ከአንዱ አምላክ በቀር ለሌላ የሚሠዋ ሰው ፈጽሞ ይጥፋ፡፡» ይላል፤ ዘፀ. 22፥20፤ 2ነገ. 17፥35-39፡፡

ደግሞም ሦዑ ለአጋንንት፤ ወአኮ ለእግዚአብሔር፤ ለአማልክት እለ ኢያአምሩ፤ ለአማልክተ ግብት እለ ኢይበቍዑ፤. . . አይቴ እሙንቱ አማልክቲክሙ እለ ትትዌከሉ ቦሙ፤ ወእለ ትበልዑ መሳብሕተ መሥዋዕቶሙ፤ ወትሰትዩ ወይነ ሞጻሕቶሙ፤ ይትነሥኡኬ ወይርድኡክሙ፤ ወይኩኑክሙ መድኀኔክሙ፤ አእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ፤ አነ እቀትል ወአሐዩ፤ እቀሥፍ ወእሣሃል፤ ወአልቦ ዘያመሥጥ እምእዴየ፡፡. . . . ምንተ ይበቍዕ ሠዊዕ ለአማልክት ኢእሙንቱ ይበልዑ ወኢእሙንቱ ያጼንዉ «እግዚአብሔር ላልሆኑ አጋንንት፥ ለማያውቋቸው አማልክት፥ በቅርብ ጊዜ ለተነሡ ለዐዲሶች፥ አባቶቻቸውም ላልፈሯቸው አማልክት ሠዉ፡፡ . . . አማልክቶቻቸው የት ናቸው? ይታመኑባቸው የነበሩት አማልክት፤ የመሥዋዕታቸውን ስብ የበሉ፤ የመጠጥ ቍርባናቸውን የወይን ጠጅ የጠጡ፤ እነርሱ ይነሡ፤ ይርዷቸውም፡፡ መጠጊያም ይሁኑላቸው፤ አሁንም እኔ ብቻዬን እንደሆንሁ፥ ከኔ በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፡፡ እኔ እገድላለሁ፤ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፤ እፈውስማለሁ፤ ከእጄም የሚያድን የለም፡፡ . . . እነርሳቸው አይበሉ፤ አይጠጡ፤ አያሸቱ ለጣዖት መሥዋዕት መሠዋት ምን ይጠቅማል፡፡ » እያለ አስተካክሎ ይነግረናል፤ ዘዳ. 32፥15-39፤ ሲራ. 30፥19፤ 1ቆሮ. 10፥19-22፡፡ አገሬ ኢትዮጵያ ሆይ! አማልክቶችህ መብዛታቸው እንዳገርህ ቁጥርና መንገድ ናቸው፤ ኤር. 11፥9-14፡፡

ወንድሜ ሆይ! ቸሩ አምላካችን እንደዚህ አድርጎ አስተካክሎ ገልጾ እየነገረን፥ የርሱን ሕያው ቃል ወደ ቀኝ ጥለን ወደ ግራ (ገሃነም) በሚያስገባው በሰዎች ሥርዐት ስሕተት ወይም ጥፋት በሚባል ጎዳና መጓዛችን ይገርማል፡፡ «ዕውርን ዕውር ቢመራው ሁለቱም ተያይዘው ገደል ይገባሉ፡፡» የሚለው አምላካዊ ቃል በእኛ በኢትዮጵያውያን እንዳይፈጸም እጅግ በጣም ያስፈራል፤ ኢሳ. 9፥16፤ ማቴ. 15፥12-20፡፡

ስለዚህ ክርስቲያን ከሆንህ አሕዛብ ከሚሠሩትና ከደነገጉት ሁሉ መለየት ይገባሃል፡፡ «ወተደመሩ ምስለ አሕዛብ ወሰገዱ ለግልፎ፤ ወተምህሩ ምግባሮሙ፤ ወተንቀንዩ ለግልፎሆሙ ወበልዑ መሥዋዕተ ምውተ፤ ወሦዑ ለግልፎ ከነዓን ወዘመዉ በጣዖቶሙ፡፡» «ከአሕዛብ ጋር ተደባለቁ፤ ሥራቸውንም ተማሩ፤ ለጣዖቶቻቸውም ተገዙ፤ ወንዶች ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠዉ . . . በማድረጋቸውም አመነዘሩ፡፡» መዝ. 106÷19-43፤ የሚለውን ቃል ለማን እንደ ተነገረ በማስተዋል ተጠንቅቀህ መርምር፤ 1ዮሐ. 4÷1፡፡

የስሕተታችንንም ማስረጃ ስማኝ ልንገርህ፤ መላእክት፥ ጻድቃን፥ ቅዱሳንና ሰማዕታት በሚዘከሩበት ቀን ሥራ ብንሠራ አትሥሩ እያሉ የሚቈጡን ከሆነ፥ (እነርሱ ግን «ስዱሰ መዋዕለ ተገበር ተግባረከ» የሚለውን አምላካዊ ዐዋጅ ፈጽመው የጸደቁ ይመስለናል) እኛም ለአንድ ጻድቅ ክብር ብለን አንድ ቀን ሥራ ከፈታን፥ የአንድ ዓመት ቀኖች 365 ናቸው፡፡ ጻድቃንና ቅዱሳን፥ ሰማዕታት፥ መላእክት አገልጋዮቹና ባሮቹ ግን ሰው ሊቈጥራቸው የማይቻለው ከባሕር አሸዋ የሚበዙ አእላፋት ናቸው፤ መዝ. 104÷4፤ ዳን. 7÷10፡፡

ስለዚህ የዓመቱን ቀናት ለምናውቃቸው ቅዱሳን ብቻ ብናካፍልና በአንድ ቀን ቢያንስ ለመቶ ጻድቃን መታሰቢያ ቢደረግ፥ በአንድ ዓመት ውስጥ ሥራ የሚሠራበት አንድ ደቂቃ ያህል ጊዜም ባልተገኘ ነበር፡፡ አእምሮ ባላቸው ሰዎችና አገሮች ግን በአንድ ዓመት ውስጥ አንድ ቀን ብቻ ለቅዱሳን ሰዎች መታሰቢያ ተብሎ የሕይወት ታሪካቸውና ሥራቸው ለሕዝብ ማጽናኛ እንዲሆን እየተነገረ በዓል ይደረጋል፤ የሐዋ. ሥራ 5÷17-42፤ ዕብ. 11÷1-40፡፡

የአገራችን በዓላት ግን እነ መምሬ ሃኬት፥ እነ ቄስ ስንፍና፥ እነ አባ አታለሉ፥ እነ ርእሰ ደብር ሳትሠሩ አብሉን፥ እነ ግራ ጌታ ዓለማየሁ፥ እነ አለቃ ሆድ አምላኩ ተሰብስበው ለሥጋዊ ጥቅማቸው ብቻ ሲሉ፥ ጌታ በወንጌሉ «ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ፤ ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ በአተ ፈያት ወሰረቅት» «ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፏል፡፡ እናንተ ግን የሌቦችና የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት፡፡» እንዳላቸው፥ አምልኮን ተጠግተው በሐሰት የደነገጓቸው በዓላት ስለሆኑ ከንቱ ስሕተት ነውና አትመናቸው ያልኩህ ስለዚህ ነው፤ ኤር. 23÷11-16፤ ሕዝ. 13÷1-23፤ ሉቃ. 19÷46፡፡

የስሕተቱ መጨረሻም የልጆች ጨዋታ ይመስል በበዓል ቀን «ኢታንሥእ እደዊከ ወእገሪከ» «እግርህንም እጅህንም አታንሣ።» ይባላል፤ ኢሳ. 58÷13። ጠማማው የሰው ሥርዐት ግን ከሁለት ተከፍሎ እኩሌታው በሥራ ቀን የሚሠራ፥ እኩሌታው ደግሞ በበዓል ቀን የሚሠራ ተብሎ ተደንግጓል። በሥራ ቀን ብቻ የሚሠራው እርሻ፥ ጉልጓሎ፥ ዐጨዳ፥ ቁፋሮ፥ መፍተልና ወፍጮ ነው። በበዓል ቀን ሊሠራ የተፈቀደው ደግሞ እሾኽ እየቈረጡ ዐጥር ማጠር፥ የተጕለጐለውን ማውጣት፥ የታጨደውን መከመር፥ አውድማ ማውጣት፥ የተወቃውን ማጥራት፥ ገለባ መሸከም፥ የጥጥ ፍሬ መፈልቀቅ፥ እህል ማበጠር፥ ወፍጮ መውቀር ነው። ይህ ሁሉ ግን ሥራ መባሉ ቀርቶ በሰንበትም ሳይቀር በስርቆሽ ሲሠራ ይውላል። እኩሉ የሚሠራበት እኩልም የማይሠራበት ሆኖ ከታዘዘ ግን፥ ይህ መሰሉ ነገር የልጆች መጫወቻና የጫጉላ ቤት መዘባበቻ የሆነው የሰው ሥርዐትና ሕግ ሁሉ የእምቧይ ካብ መሆኑን አስተውል፤ ኢሳ. 28÷7-18።

ወዳጄ ሆይ! የአምላክን ትእዛዝና ሕግ ከሐሰተኛው የሰው ሕግ ለይተህ ልታውቀውና ልትፈጽመው ከፈለግህ ግን፥ እውነተኛው ሕግ «በስድስት ቀን ሥራህን ሁሉ ሥራ፤ በሰባተኛው ቀን ግን የአምላክህ ሰንበት ነውና አክብረው፤ ምንም አትሥራበት።» ብሎ ሕያው ዘኢይመውት ቅዱስ አምላካችን በድንጋይ ላይ በአፍአ ሳይሆን፥ በጣቱ በልባችን ውስጥ ጽፎ ለዘለዓለም ተጠንቅቀን እንድንጠብቀው አጥብቆ አዝዞናል፤ ዘፀ. 20÷8-11፤ ዘዳ. 5÷12-15፤ ኤር. 17÷19-25፤ ሉቃ. 13÷14፤ ሕዝ. 36÷26።

አንባቢ ሆይ! ጻድቁ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ግን እንኳን ለስድስት ቀናት ቦዝነን ልንውል፥ ሰባተኛውንም ቀን ሰንበትንም ሰው የሚጠቀምበትን ሥራ እንድንሠራበት አዝዞናል። «ይከውንኬ በሰንበት ገቢረ ሠናይ።» «በሰንበት መልካም ሥራ መሥራት ይገባል።» ማቴ12÷12፤ «ሰንበት ስለ ሰው እንጂ፥ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም።» ማር. 2÷27 ይላል።

ስለዚህ አምላካችን የሚደሰትበትን መልካም ሥራ ሁሉ ዘወትር፥ አንድ ደቂቃ እንኳ ሳናጕድል እስከ ዘለዓለም እንድንሠራ ፈቅዶልናል። ፈጣሪያችን የከለከለው ኃጢአት የተባለውን ክፉ ሥራ ሁሉ መሥራት ግን በዓል ሆነም አልሆነም፥ ለዘለዓለም እንዳንነካውና እንዳንሠራው ከልክሎናል። ለዘለዓለም የተከለከለውን ልታውቀው ብትፈልግ ግን በማር. 7÷8-23 እና ገላ. 5÷19-21 ተጽፎ ያለው፥ ከልብ እየወጣ ሰውን የሚያረክስ የሥጋ ፍሬ የተባለውና በ28 መደብ የተቀመረውን ኃጢአት ብቻ ነው። አንድ

ቀን ሳናጎድል እስከ ዘለዓለም እየሠራነው እንድንኖር የታዘዘው ግን በማቴዎስ 5ኛው፥ 6ኛውና 25ኛው ምዕራፍ፥ ገላ. 5፥22 የተጻፈው «አፍቅሩ ጸላእተክሙ፤ ባርክዎሙ ለእለ ይረግሙክሙ፤ ርኀብኩ ጸማዕኩ፤ ዓረቁ፤ ተፋቅሮ፥ ፍሥሐ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ የሚለውን ሌላም ይህን የመሰለውንና የመንፈስ (የነፍስ) ፍሬ የተባለውን ነው።

አሁን ግን በዓል ለማክበር ብለን ተሰብስበን አምላካችን የከለከለውን የሲኦል ጎዳና ቂምና በቀል፥ ሐሜትና ዝሙትን ለብሰን፥ ሰክረን ሰንፈናከትና ስንጋደል ብንውል ነው ኃጢአት የሚቈጠርብን እንጂ፥ የእኛና የወንድሞቻችን ሕይወት የሚድንበትን በእውነተኛው ነገር መልካም ሥራ ከሠራን፥ በእሑድ ቀንም ቢሆን እንደ ጽድቅ እንጂ እንደ ኃጢአት እንደማይቈጥርብን በትምህርቱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል፤ ራሱም በሰንበት ቀን ሠርቶ አሳይቷል፤ ማቴ. 12፥1-14፤ ዮሐ. 5፥1-18። እውነተኛው ክርስቲያን ግን በእሑድ ዕለት ዐይነተኛ ግብሩ አድርጎ እስረኛንና በሽተኛን በመጠየቅና በመርዳት ቢውል፥ እግዚአብሔር የሚደሰትበት የተለየ የሥራ ቀኑ ነው።

ዛሬ በሀገራችን እንደምናደርገው ልማድ ግን፥ በዓላትን እየቈጠርን ቦዝነን ብንውል «በሐፌ ገጽከ ብላዕ» የሚል አምላካዊ ዐዋጅ ማፍረሳችን ነውና፥ አምላክ እዳያዝንብን መጠንቀቅ ይገባናል። ሐዋርያትም «ዘኢይፈቅድ ይትቀነይ ኢይሴሰይ።» «ሊሠራ የማይወድ አይብላ።» ብለው አዘዋልና፥ እነርሱ ግን እንዳስተማሩት ወንጌልን አለ ዋጋ ለሁሉ እያስተማሩ፥ ስለምግባቸውም ሲሉ በእጃቸው እየሠሩ፥ በደመወዝ ድንኳን እየሰፉ ይመገቡ ነበሩ እንጂ፥ እንደ ሀገሬ ካህናት በዓላት እየቈጠሩ ድግስ ደግሳችሁ፥ ፍጡራንን አክብሩ ብለው ሥራ ፈትነትን ከቶ አላስተማሩም። ከምእመናኑም አንድ ሳንቲም ሳይቀበሉ፥ በብርቱ ድካም ሳይሰለቹ ሌትና ቀን ይሠሩ ነበር። «ወተዘከሩ አኀዊነ ጻማነ፤ ወስራሐነ፤ መዐልተ ወሌሊተ ኮነ ንትጌበር ከመ ኢናክብድ ላዕለ አሐዱሂ እምውስቴትክሙ።» «ወንድሞች ሆይ! ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።» ብለዋል፤ 1ተሰ. 2፥1-12፤ የሐዋ. ሥራ 20፥33-35።

ወንድሜና ወዳጄ ሆይ! ቸሩ አምላካችን በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የድንቍርናና ወራትን አሳልፎታል፤ የሐዋ. ሥራ 17፥22-30። እንግዲህ ግን ዛሬ የአምላክህን ድምፅ ከሰማህበት ቀን ጀምረህ፥ አሮጌ የማይጠቅም ፍሬ የሌለው የሰው ትእዛዝ ከመጠበቅ ይልቅ፥ ዐዲሱንና እውነተኛ ዋጋ ያለውን የአምላክን ሕግ መስማትና ማድረግ ዐውቀህና ተምረህ፤ የሐዋ. ሥራ 4፥15-35

ልብህን ሳታጸና (ሳታደነድን)፥ በእውነተኛው ንስሓ ጠባይህን ለውጠህ፥ ከኃጢአት ተለይተህ የፈጣሪህን ትእዛዝ ብቻ በልብህ ውስጥ አጥብቀህ ይዘህ «ወሕገ አምላኩ ውስተ ልቡ» «የአምላኩ ሕግ በልቡ ውስጥ ነው።» መዝ. 37፥26-31 የተባለው ሰው ሆነህ፥ በስድስቱ ቀን ውስጥ ትንሽና ትልቅ ሳትል የሥጋህን ሥራ ሁሉ ሥራ። ሰባተኛውን ቀን ግን የአምላክህ ሰንበት ነውና አክብረው፤ ማለት ለነፍስህ ስንቅ የሚሆን መልካሙን ሥራ ሥራበት፤ ዘሌ. 23፥2-8።

ቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማሩን እውነተኛውንና ንጹሑን አምልኮ (ሃይማኖት) ልንገርህ፡ - «ራስህን በዓለም ካለው ርኵሰት ዘወትር እየጠበቅህ፥ ድኻችንና መበለቶችን በመከራቸው ጊዜ መርዳት፥ ይህ ለሰው ሁሉ ዋናው አስፈላጊው ነገር ነው ብለዋል።» ያዕ. 1፥27። ሐዋርያው ጳውሎስ ከንቱ የሆነውን የሰው ሥርዐት እየነቀፈ ሲያስረዳን፥ «አሁን ግን በመብልና መጠጥ፥ በዓላትንና ሰንበታትን በመጠበቅ፥ መባቻን በመቍጠር ማንም አይፍረድባችሁ፤ ይህ ሁሉ የሰው ትምህርት፥ የሰውም ትእዛዝ ነውና፤ ሥጋ እንዲጠግብበት በፈቃድ ስለ ተደነገገ፥ የአምልኮ መልክ ያለው፥ የማይረባ፥ የማይጠቅም ወደ ጥፋት የሚወስድ ስለሆነ ግን፥ ወደ ሕይወት አያሻግርምና ስለዚህ የፈቀዳችሁትን (ያስፈለጋችሁን) ሁሉ ብትበሉ፥ ብትጠጡ፥ ሥራም ብትሠሩ ከቶ የሚፈርድባችሁ ሰው የለም።» ብሏል፤ ቈላ. 2፥16-23። «አሁን ግን ክርስቶስ ነጻ ባወጣን በሰው ልጅነት ጽኑ፤ ከእንግዲህ ለሰው ሕግና ለባርነት ቀምበር አትገዙ።» ገላ. 5፥12። ወንድሞቼ ሆይ! የሰው ባሮች፥ የአሮጌ ልማድ ደንቆሮች አይደላችሁም፤ የክርስቶስን እውነተኛ ቃሉንና ጣፋጩን ጣዕመ ወንጌሉን ከሐሰት ለይታችሁ አጽንታችሁ በልብ ከያዛችሁ፥ ቃሉ አርነት (ነጻነት) እንደሚያወጣችሁ ጥርጥር አይግባችሁ፤ ዮሐ. 8፥30-32፤ 15፥1-17፤ ሮሜ 14፥20፤ ቲቶ 1፥15። እውነትን ከሐሰት ለይቶ የሚይዝ አእምሮ ይስጠን። አሜን።

<u>ምዕራፍ 23</u>

<u>ሞትና ሐዘን</u>

ወንድሞቼ ሆይ! ዓለማውያን ወንድሞቻችን በሰው ዘንድ ሐዘንተኞች ተብለው እንዲመሰገኑ ሲሉ ለሟቹ ጥቁር ጨርቅ (ምልክት) ይለብሱለታል:: ክርስቶስ «በኔ የሚያምን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፥ ወደ ፍርድ አይሄድም፤ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝና በእኔ የሚያምን ሁሉ ቢሞትም ይድናል::» ዮሐ. 5፥24-29፤ 11፥23-27 የሚለውን ቃል ስለ አልተገነዘቡ፥ ዘመዳችን ሞተ፤ ጠፍቶ በስብሶ ቀረ፤ ሸሸ ተበላሸ እያሉ በስም ብቻ ክርስቲያኖች ተብለው እየተጠሩ፥ እንደ አሕዛብ ልማድ ፊታቸውን እየነጩ፥ ደረታቸውን እየመቱ፥ ራሳቸውን ይላጫሉ አለጫማም ይሄዳሉ፤ ዘሌ. 19፥26-31:: በዚሁ ምክንያት እየታመሙ ብዙዎች ይሞታሉ፤ ጥቂቶቹም ዐይናቸውን ይታወራሉ::

የተጠመቃችሁበትን ወንጌል ስላመናችሁና ክርስቶስንም ብቻ ስላመለካችሁ፥ በአውሮፓውያን ፕሮቴስታንት (እልሸኛና ተጋዳይ)፥ በኢትዮጵያችንም <u>«ማርያም ሕግ አፍራሽን ትጠላለች::» ስለምትሉ ፀረ ማርያሞች እየተባላችሁ የምትሰደቡና የምትጠሉ ወንድሞቼ ወንጌላውያን ሆይ፥</u> (ስለ ስሜ ክፉ ስም ያወጡባችኋል የሚለውን ቃል አትርሱ::) ዘመዶቻችሁ በሞት ቢለዩአችሁ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሰማይ እንገናኛለን ብላችሁ እየዘመራችሁ፥ ደስታ በተሞላው የትንሣኤ ተስፋ ሸኙዋቸው እንጂ ፍሬ በሌለው የአሕዛብ ልማድ ተገርኝታችሁ (ተይዛችሁ)፥ ከልክ ካለፈ ሐዘንና ልቅሶም ተሸራችሁ (ተጽናንታችሁ)፥ ነጭ ልብስም በመልበስ ወደ ክርስቶስ እቅፍ ስለሄዱ፥ በደሙ ታጥበው ስለነጹና በተስፋው ድነው ስላረፉት ወንድሞቻችሁ በቅዱስ ቃሉ እየተጽናናችሁ መልካም አርአያ በመሆን ተለዩ እንጂ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳላነበቡ ሰዎች ራስን በመላጨትና ጥቁር ጨርቅ በመልበስ፥ ራሳችሁን እያታለላችሁ በግብዝነት እንዳታዝኑና የትንሣኤ ተስፋ እንደሌላቸው አረማውያን (የሚሰድቧችሁን) እንዳትመስሉ በአምላካዊ ቃል አማጽናችኋለሁ፤ 2ቆሮ. 6፥13-18፤ 1ተሰ. 4፥13-18፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 178::

ይልቁንም የሃይማኖታችንን ዐላማውን ልንገራችሁ የሞዉትን ቤት እርዱ፤ ደግፉ:: የሞዉት ልጆችን አልብሱ፤ አጉርሱ:: ዋጋ አልባ ሆናችሁ እንዳትቀሩ ለእዩልኝ አትደግሱ፤ ተዝካር ዝክር ያጸድቃል መስሏችሁ ክቡር ገንዘባችሁን በአሸዋ ላይ አታፍስሱ፤ ድኾችን በመከራቸው ጊዜ ዕስቧቸው፤ በሰማይ

እንዳትከሰሱ ራሳችሁን አታታልሉ፤ በወንጌል የሰማችሁትን ቃል በምግባር ግለጡት (ስበኩት)፤ ቃልንም አድራጊዎች እንጂ ሰሚዎች ብቻ አትሁኑ፤ እንዳትወቀሡ በሕገ ወንጌል ተቀደሱ፤ የአሕዛብን ልማድ አትከተሉ፤ እንዳትረክሱ ለሞተ ማልቀስ አይገባምና መጽሐፍን አታፍርሱ ኤር.22÷10፤ ኧረ! እባካችሁ የአሕዛብ መሳቅያ እንዳንሆን የተፋችሁትን አትላሱ፤ 2ጴጥ. 2÷20-22፤ በሰማይ እንድትካሡ ስንቃችሁን በከርሠ ርኁባን ቋጥሩት፤ ታሪካችሁንም በሕይወታችሁ ሥሩ፤ አድሱም:: በመጽሐፈ ሕይወት እንድትታወሱ ዛሬ ልባችሁን ግዘሩ፤ በኃጢአታችሁም አልቅሱ፤ ኢዩ. 2÷11-14::

አባቶቼና እናቶቼ÷ ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ! የወንጌልን ጣዕም ላልቀመሱት ወንድሞቻችሁ አዘኑና ተቈርቈሩላቸው፤ በትጋትና በድፍረትም አቅምሱአቸው:: ትልቁ ኃጢአትም ሥጋን የሚገድሉትን መፍራት መሆኑን አትርሱ፤ እባካችሁ! ኧረ! እባካችሁ! ከክርስቶስ መንጋ የጠፉ ወንድሞቻችሁን ቅን ጸሎትና ንጹሕ ምግባር ታጥቃችሁ እየፈለጋችሁ መልሱ፤ «ቃሌን ባትነግረው ደሙን ከእጅህ እፈልገዋለሁ::» የሚለውን አምላካዊ ቃል ስንት ጊዜ ትረሱ? ሕዝ. 3÷16-21፤ 33÷1-8::

ይገርምዩ ኦ ቃሉ እተንብቡ ዘበልኩም ክንድዚ ዚኣክል ዕዳ ተሰኪምኩምዶ ትድቅሱ? ኣይትገብሩምን ደጊምሲ ተባራብ ሩሞ ጽሑፋት ዳህስሱ ኣየ. . . እንቱም መራሕትና ዓለም ቀትሪ ኸይኑስ ገና ትታኸሱ፤ ክላ ደጊም ዋዛ ይትረፍሞ ኣሕጺርኩም ዕጠቑ ጽዒርኩም ኲልሱ፤ ቅዱስ እትብሉዎ ቐምሽ ፈሪሳዊያንሲ ብወንጌል ረኺሱ፤ ተዝካርን ዝክርን ዘመናም ሓሊፉስ ውዕሉም ፈሪሱ፤ እኽለ ሕማም እዮም ደቅ ሰብ ዜርክሱ፤ ገድለ ተአምርስ ክንድዚ ይሕሱ፤ <u>ንዝክር መድኃኔ ዓለም ዚኾን ቅጫ እንተስንከት ትኩ ዝጨነም ኹሉ ይጸድሆ</u> ይብል፤ ኣንታ ደም ክርስቶስዶ ብኸንቱ ፈሲሱ ወይዙ ወድ አዳም ንነፍሱ ረሲዑስ ጥራሕ ነታ ኸርሡ፤ አረ በይዛኻትኩም ደቅ መን ምኳንኩም ውልደትኩም ሕሰሱ፤ ዘመን ተዓዚብኩም ምኽሩ ዘትዩ (አብ) ሚዛን ከይትንእሱ፤ ስቐልቲ ክርስቶስ ወትሩ ብዝተኸሱ፤ ይሉኻታ እኮ እዩ ንወድ ሰብ ፈውሱ፤ ቅንኣት ምቀኝነት አብ ካህናት ነጊሡ፤ ተግሣፅና ምክር ደጊምዶ ደቂሱ፤ ንሓሶት ግብዝና ዓጺዱ ኊልሲሱ፤ ሓዊ ኼእትወሉ ዓጢቑ ጨሪሱ፤ ይሉኻታ እንካብ ሞተስ ሕይወት ብዘይ ንሱ፤ ከቶ ኣይርከብን ብኸምኡ ኣይንሓሱ፤ ቅኔ ተጻሒፉስ ምኽሪ ተኸስኪሱ፤ ስምዑ ኸንብበልኩም እዝንኹም ምለሱ፤ ብመልአከ ብርሃናት ብርሃን (ዓድዋ ሥላሴ) ነገር ተጠሪሱ::

ትርጓሜ

ይገርማል እናንተ ቃል የምታነቡ ይህን ያህል ዕዳ ተሸክማችሁ ትተኛላችሁን? ተነሡ፤ ገሥግሡ፤ ከእንግዲህስ አታድርጉት፤ መጻሕፍትን ዳስሱ፤ አዬ! እናንተ መሪዎቻችን ለዓለም ቀትር ሆኖ ሲሯሯጥ እሱ በሱ፤ በሉ ዋዛ ይቅርና ባጭሩ ታጥቃችሁ ጥራችሁ ጉረሱ፤ ቅዱስ የምትሉት የፈሪሳውያን ቀሚስ በወንጌል በመርከሱ፤ ተዝካርና ዝክር ዘመናቸው አልፎ ውላቸው በመፍረሱ፤ እክለ ሕማም (የመከራ እንጀራ) ናቸውና የሰውን ልጅ የሚያረክሱ፤ ተኣምርና ገድል ይህን ያህል ያልሆነውን ነገር ደራርበው ሊያለብሱ፤ ለመድኀኔ ዓለም የሚሆን ቂጣ ሲጋግሩ የሸተታቸው ሁሉ ይጸድቃሉ ይላል፤ እንዲህማ ከሆነ የክርስቶስ ደሙ በከንቱ ነዋ መፍሰሱ፤ አወይ የሰው ልጅ ነፍሱን ረስቶ መሽቀዳደሙ ለከርሱ፤ ኧረ እባካችሁ! የማን ልጅ መሆናችሁ ነው? ልጅነታችሁን አስታውሱ፤ ዘመን ታዘባችሁ ምከሩ÷ ተወያዩ÷ በሚዛን እንዳታንሱ፤ የክርስቶስ ሰቃዮች ሁሌ እንደተከሰሱ፤ ይሉኝታ እኮ ነው ለሰው ልጅ ፈውሱ፤ ቅንኣት ምቀኝነት በካህናት በመንገሡ፤ ተኛ ተግሣጽና ምክር በነፍሱ፤ ውሸትንና ግብዝነትን ዐጭዶ ከምሮ ከነ ግብስብሱ፤ እሳት ሊለቅበት ታጥቆ ጨርሶ በመንፈሱ፤ ይሉኝታ ከሞተስ ሕይወት ያለእርሱ፤ ከቶ አይገኝም በከንቱ ቢያወስውሱ፤ ቅኔ ተጽፎ ምክር በመከስከሱ፤ ስሙ ላንብብላችሁ ጆሮአችሁን መልሱ፤ በመልአከ ብርሃናት ብርሃን (ዓድዋ ሥላሴ) ነገር ፍጻሜ ላይ መድረሱ።

መወድስ

በአልባሰ አይሁድ ቅንአት ወምቀኝነት
ዑጽፍታ ታንሶሱ ወታሰተርኢ ጉብርታ
ልበ ካህናት አይሁድ አንተ ይእቲ አውታታ
ወይነድድ ባቲ ቀኛዝማች የማኑ አማኑኤል ምታ
ልበ ካህናት ጋለሞታ
እስመ ታቀንእ ፈድፋደ ግራዝማች ዳብዬን አግብታ
ሞተሂ አለ ጊዜው በጸሊዐ ቢጽ በሽታ
መርዓዊ ሀብተ ክህነት ዘተፍሕረ ለደስታ
እምዝኒ ኵሉ ነገር ታሐዝነኒ ይሉኝታ
እስመ ቀተልዋ ካህናት ወተቀብረት ሳትፈታ።

ትርጓሜ: - «በአይሁድ አልባሳት ቅንዓትና ምቀኝነት፤
አሽብርቃለች ያችው ትታያለች በጉብታ፤
ልበ ካህናት አይሁድ ዘትርጓሜሃ አውታታ፤
ይናደዳል በርሷ ÷ቀኛዝማች የማኑ÷አማኑኤል ምታ (ባሏ)
ልበ ካህናት ጋለሞታ፤

ታስቀናዋለች እጅግ ግራ አዝማች ዳብዬን (ዲያብሎስን) አግብታ
ደግሞም ሞተ አለጊዜው ወንድምን በመጥላት በሽታ፤
ሙሽራው ሀብተ ክህነት የታጨው ለደስታ፤
ከዚህም ሁሉ ጋር ታሳዝናለች ይሉኝታ፤
ካህናትኮ ገደልዋት ተቀበረችም ሳትፈታ፡፡»

ተብሎ አስቀድሞ በሊቃውንት አፍ ተነግሮ ነበር፡፡ ወይዘሮ ይሉኝታን የገደሏትና ከጎሊናቸውም ውስጥ ከነሥሯ ነቅለው የጣሏት፥ የሀገሬ ካህናት ግን በሟቹ መቃብር ላይ የማያሸተውን ዕጣን እያጠኑ የሚጠቅመውን የወንጌልን ተስፋ በሕይወቱ ሳለ ሳያስረዱት፥ ከሞተ በኋላ እስከ 40 ቀን ድረስ የማይሰማውን ግንዘት ከራስጌው ተቀምጠው እየደገሙ ኃጢአቱን አስተስርየናል ብለው ስርየትን በዋጋ ይሸጣሉ፡፡ እንዳንረሳው እያሉም ከሞተበት ቀን ጀምረው 7፥ 12፥ 30፥ 40፥ 80 ቀን፥ መንፈቅና ዓመታትን እየቈጠሩ ሐዘንተኞችን በውድም፥ በግድም፥ በማታለልም <u>«ደግሱ፤ መታሰብያውን እንዳታስታጉሉ፡፡»</u> ብለው እያጭበረበሩና ጥብቅ የሆነ ትእዛዝ እየሰጡ፥ በአንድ ዋንጫ ጠላ ኃላፊውን ሥጋቸውን ለመጠገን ሲሉ ሕዝባቸውን ስካርና ጥፋት ወደ ተባለው ባሕር በመጎተት፥ ስንፍናን እያስተማሩና እያሳሳቱ በልማድ ረግረግ ይዘውት ሲዋኙ ይኖራሉ፤ ኢሳ. 56፥8-12፤ ሕዝ. 34፥1-8፡፡

<u>ፈቃድ (ሊቸንስ) የሌላቸው የሥጋ ነጋዴዎች «በእኛው ገዳም የተቀበረ ሰው ይጸድቃል፡፡» ብለው እያታለሉአቸው</u> የዋሆቹ ወንድሞቼ እውነት መስሏቸው ወንድማቸውን፥ ወይም እህትና ልጆቻቸውን ለማጽደቅ ሲሉ የሸተተ አስከሬን ተሸክመው፥ የሁለትና የሦስት ቀን መንገድ ተጉዘው ይቀብራሉ፡፡ ዮሴፍ ስትወጡ ዐጥንቶቼን አትርሱ ማለቱ ግን ለመውጣታቸው እርግጠኛ ተስፋ ሲያስጨብጣቸው ነው፤ ያውም ሬሳውን የማያሸትና የማያበሰብስ መድኃኒት 40 ቀን ተቀብቶ እስከ 2 እና 3 ሺህ ዓመት ሳይፈርስ የሚኖር ስለሆነ ነው እንጂ፥ በከነዓን የተቀበረ ዐጥንት ይጸድቃል ብሎ አይደለም፤ ዕብ. 11፥22፤ አብርሃም አበ ምእመናን በሕይወቱ ሳለ የሠራው በጎ ምግባር «አርከ እግዚእነ» (የጌታ ወዳጅ) አሰኘው እንጂ የተቀበረውስ በገንዘቡ ከገዛው የጓሮው ርስቱ ውስጥ ነው፤ ዘፍ. 25፥7-10፡፡

በተመረጠ መቃብር የሚጸደቅ ከሆነማ ጲላጦስና ይሁዳ፥ ሐናንያና ሰጲራም ጎረይክዋ በተባለችው ኢየሩሳሌም ተቀብረዋል፡፡ የነሱ ጽድቅ ግን ዐረቦነ ቤልሆር ሳይሆን አለመቅረቱ የታወቀ ነው፡፡ <u>«አንተ የተመረጠ መቃብር ያስቈፈርህ ሰው፥ እግዚአብሔር በኃይል</u>

ወረውሮ ይጥልሃል እንደ ኳስም ጠቅልሎ ያንከባልልሃል::» ተብሏል፤ ኢሳ. 22÷15-19::

ስለ ተዝካር ነገር ዐዋቂዎች በሚባሉት በአውሮፓዎች ዘንድ ደግሞ በእኛ ከሚደረገው ስሕተት የባሰ ጌጋይ ይደረጋል:: ማለት በእኛ የሚደረገው የምውቱን ገንዘብ ሕያዋኑ አመካኝተው ለመብላት ነው፤ በእነርሱ ዘንድ ግን ለበሰበሰው የአስከሬኑ ማስጌጫያ ተብሎ በብዙ ሺህ ገንዘብ ተገዝቶ የዕብነ በረድ ደንጊያ በመቃብሩ ላይ ያቆሙለታል:: ሌላው ቀርቶ ሟች አይቶ ለማይደሰትበትና ሰጭዎችም ለማይመሰገኑበት በየእሑዱ የ5 እና የ10 ብር አበባ ስጦታ ያደርጉለታል:: እንዳይጨልመው ብለውም በሥዕሉ አጠገብ የማይጠፉ መብራት ያስቀምጡለታል::

ለሰው ማስታወሻ (መታሰቢያ) የሚሆነው ግን ራሱ በሕይወቱ ሳለ የሠራውና የወለደው የሥራ ሐውልት፥ በመጽሐፈ ሕይወት ተጽፎ በታሪክ ዐምድ ታውቆ ስፍራ ይዞ ሲገኝለት ነው ሞያና ጌጡ፥ ክብረቱና ዕውቀቱ ሲነገርለት የሚኖረው:: ነገር ግን «እኔ በበላሁ አንቺ ተፈወስሽ፤» እንደተባለው ተረት ሕያዋኑ ለሙቱ ጸሎትና ጌጠኛ የልማድ ግብዝነት ዲቃላ ቢለስኑበት፥ ሊጠጋውና ሊጠቅመው እንደማይችል አስተዋይ ሕሊና ያለው ሰው ሳይገነዘበው አይቀርም፤ መክ.9÷10::

ወንድሞቼ ሆይ! እኔ ጡት ከተውኩኝ በኋላ እናቴ ከምትመገበው ምግብ አንድ ጠብታ ሊደርሰኝ እንደማይችል፥ እንደዚሁ ያ ባለጸጋ ራሱ በሕይወቱ ሳለ ያልቋጠረውን ጠብታ ውሃ ከአልዓዛር ጣት ሊያገኝ ከቶ አልቻለም፤ አይቻልምም፤ ሉቃ. 16÷19-31::

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ምእመናን ሆይ! ሰው የተፈጠረው የሞትን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዲደርስ ነው:: ይህ ኃላፊው ዓለም ለጥቂትና ለተወሰነ ጊዜ ማቄያ ስለሆነ፥ በኃላፊው ዓለም እንዲኖር የአምላክ ፈቃድ አይደለምና የሁላችን አገር በሰማይ መሆኑን አንርሳ:: «ስለዚህም ከኛ ሕይወቱ ለራሱ የሆነ የለም፤ ብንኖር ለእግዚአብሔር እንኖራለን፤ ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን::» ሮሜ 13÷7-9 እንደ ተባለው፥ መሞታችንና መኖራችን በእግዚአብሔር ፊት የሚገባና የተወደደ ሆኖ ሊገኝ ያስፈልጋል:: ለሞቱት ቤተ ሰዎቻችን አዝነን ከምናለቅስላቸውም፥ የማይሞተውንና በኃጢአት የተበላሸውን ሕይወታችንን በንስሓ ዕንባ ረጭተን እናነጻው ዘንድ፥ የያንዳንዳችን ዋና ጉዳይ መሆኑንም መርምረን ልንረዳው ይገባናል፤ መዝ. 51÷1-9::

አሁን ግን ብናዝን ወይም ብንደሰት÷ ብንጠግብ ወይም ብንራብ ሁሉም በቶሎ ኃላፊ ነውና÷ የማትቀረው የሞታችን ቀን እስክትመጣ ድረስ በእውነተኛው የወንጌል ሃይማኖት ተስፋ ማዝገም ከሁሉ የበለጠ ትልቅ ተግባራችን መሆኑን እንዘንጋ፤ 1ቆሮ. 7÷26-31:: በሥጋዊ ሞት አንዘን፤ የነፍስ ሞት እንዳያገኘን ይልቅ ዛሬ መድኃኒቱን ፈልገን እንያዝ፤ እርሱም ድካምና ዋጋ የማንከፍልበት ክቡሩ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው:: ከኃጢአት እንጠንቀቅ፤ እንፍራም:: የዕድሜአችን ፀሓይ ሳይጠልቅ ወደዚህ ዓለም ለምን ጉዳይ እንደመጣን እናስብ፤ እንረዳ:: በመጻሕፍት መስተዋትነት የልባችንን ጉድፍ እንጥረግ፤ በኀሊናችን በር ቆሞ መዝግያውን የሚያንኳኳ ክርስቶስ መሆኑን በድምፁ ለይተን ከፍተን እናስገባው፤ ከኛ ጋር አብሮን እንዲኖርም ዛሬ በሥጋችን ውስጥ የተመረጠ ንጹሕ ስፍራ እንስጠው (እናውርሰው)፤ እርሱም ነገ ዐይን ያላየውን÷ ጆሮም ያልሰማውን÷ ዓለም ሳይፈጠር ለወዳጆቹ ያዘጋጀውን ቤቱን እንደሚያወርሰን በማይታበል ቃሉ አረጋግጦልናል፤ 1ቆሮ. 3÷9፤ ራእ. 3÷19-22::

ወዳጆቼ ሆይ! እኔ በወንጌል ከማውቃቸው ሁለትና ሦስት ቃላት ጽፌ ማስተማሬና ማስረዳቴ በግድ ወድቆብኝ ነውና አልመካበትም:: ተምሬ ባላስተምር ግን ወዮልኝ! 1ቆሮ. 9÷16:: እውነት ነው፤ ከአምላኬ በተሰጠኝ ትንሽ ጸጋ ስለ ነፍሳችሁ ደኅንነት እንድታስቡ ብዬ ጥቂት ቃላትን በድፍረት ጽፌላችኋለሁ፤ ሮሜ 15÷15:: ስለዚህ ሃይማኖታችሁ በእግዚአብሔር ኃይልና መንፈስ ብቻ እንጂ የሰው ጥበብ ተዘንቆበት (ተጨምሮበት) እንዳይሆን ቃሉን በውል መርምሩት:: እውነትን የሚመስላት ነገር ከቶ አይገኝምና እውነትን ተግተን እንፈልጋት፤ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥም አግኝተን አጥብቀን እንያዛት:: <u>እውነት! እውነት! እውነት!</u> እያልን በልባችን ብናፈቅራትና ብንከተላትም ሕይወታችን ሁሉ ሕይወትነቱ የሚታወቀው የዚያን ጊዜ ብቻ ነው:: እውነት የሌለው ሕይወትስ ሕያው መስሎ ቢታይም ዱሮ የሞተ ነው:: «እኔ ግን ሕይወቴ ለኔ እውነተኛው ክርስቶስ ብቻ ነው፤ መሞትም ጥቅሜ ነው::» እንበል:: ሞትና ሐዘንንም በአግባብ እንያዛቸው በመንፈሳዊ ዕውቀትም እንኑርባቸው፤ ሉቃ. 9÷57-62፤ ፊልጵ. 1÷20-22፤ 1ጢሞ. 5÷1-6፤ 1ቆሮ. 2÷4-8::

እግዚአብሔር ብርሃኑን ይግለጽላችሁ፤ አሜን::

ምዕራፍ 24

ስለ ምጽዋት ጸሎትና ጾም

ኢሳ.58÷1-14፤ ማቴ.6÷1-21፤

ጾም ማለት ከምጽዋትና ጸሎት ጋራ የተሰናሰለ ሲሆን ሦስቱም የማይለያዩ አንድ ዐይነት ምስጢራዊ ነገር ናቸው:: ይኸውም ከአምላክህ ጋራ በኅቡእ የምትነጋገርበት÷ በተለይም መንፈሳዊ ዘር የምትዘራበት ጊዜ ማለት ነው፤ ገላ. 6÷4-10፤ እርሱም በ4 ክፍል ይከፈላል::

1ኛ. ማናቸውንም አገርና ሕዝብ በጠቅላላው ሁሉን የሚያጠፉ በሽታ÷ ረኀብ÷ አፈ ዐራዊት÷ ቸነፈር÷ ድርቅ÷ ዋግ÷ ቀጠና÷ የጠላት ሰይፍ ዋናው ስሙ መዓተ እግዚአብሔር በሰው ሁሉ ላይ በታዘዘ ጊዜ÷ በአንድነት በዐዋጅ መንግሥት እንደ ሰብአ ነነዌ የታዘዘውን የአምላክ ቁጣ አዝኖ አልቅሶ ወደ ምሕረት ለመመለስ የሚጾም ነው፤ ዮና. 3÷1-10፤ ኢዩ. 1÷1-20::

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፋሽስት በመምጣቱ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ 15 ቀን እንዲጾም ዐውጀውለት እንደነበረው ማለት ነው::

2ኛ. ሥጋ አሸንፎህ የአምላክን ሕግ አፍርሰህ በሠራኸው ኃጢአት ለሚመጣብህ ፈተና ሁሉ ሐዘን÷ በሽታ÷ ድኽነት÷ እስራት÷ ዕዳ÷ ማናቸውም ትልቅ ይሁን ወይም ትንሽ መከራ በደረሰብህ ቀን÷ እንደ ዳዊት ከቤርሳቤህ የወለደው ልጁ በታመመ ጊዜ÷ አምላክ ቢምርልኝ ብሎ በፈቃዱ ሰባት ቀን ልብሰ መንግሥቱን አውልቆ÷ ከመሬት ወድቆ÷ አዝኖ÷ ማቅ ለብሶ÷ አመድ ነስንሶ እንደ ጾመው የመሰለ ጾም ነው፤ 2ሳሙ. 12÷15-23::

እንዲሁም ሕዝቅያስ ንጉሥ መጀመርያ ከጠላት ከእደ ሰናክሬም ድኗል:: ሁለተኛም እግዚአብሔር በበደሉ ሊቀሥፈው ካዘዘ በኋላ÷ አዝኖ÷ አልቅሶ÷ ጸልዮ÷ ማቅ ለብሶ÷ (ጾም ጹሞ) ፈጣሪውን በእውነት ስለ ለመነ 15 ዓመት ዕድሜ ቀጥሎለታል ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 37 እና 38ን ተመልከት:: አክዓብም ጹሞ÷ አዝኖ መዓተ እግዚአብሔርን መልሷል፤ 1ነገ. 20÷17-29::

ያገሬ ሕዝብም «በጾምና ጸሎት ጽሙድ ነኝ::» ባይ ነው፤ በትምክሕቱም ለዓለም ሁሉ የሚተርፍ መስሎ ያታየዋል:: በጾሙና ጸሎቱ ታዲያ የትኛውን መዓት መልሶ ያውቅ ይሆን? አገራችን ግን ዘወትር ከበረዶና አንበጣ÷ ከዋግና ቃቄጣ÷ ከረኃብና ፌራ÷

ከችግርና መከራ ድኖ አያውቅም:: እደ ጸላኢም ዘወተር እንዳጠቃውና ደሙን እንዳፈሰሰው ይኖራል::

ባጭሩ በ1515 ዓ.ም የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነው እስላሙ መሐመድ ግራኝ÷ የአምላክን ሰይፍ ተቀብሎ አምላክ ያዘዛቸውን ትተዉ በሥርዐታቸው መቅደሱን ያረከሱትንና ትእዛዙን ያፈረሱትን ካህናት (ክርስቲያኖችን)÷ የጸዋሚዎችን መቅደስ ከነታቦቱ እያቃጠለ÷ መጻሕፍቶቻቸውንና ንዋየ ቅድሳታቸውንም እየቈነጻጸለ÷ ንጉሡን ከነመኳንንቱ ከኤረር እስከ ትግሬ እያሳደደ÷ ሕፃንና ሽማግሌም እያረደ 15 ዓመት ሙሉ ቅድስቲቱን ኢትዮጵያ በልጆችዋ ደም ለውሶ÷ የንጉሡን የአጼ ገላውዴዎስን ራስ ቈርጦ እንዳጠፋትና እንደደመሰሳት ታሪክ ይነግረናል ዋዜማ ገጽ 42፤ ሕዝ. 9÷1-7 ቀጥሎም ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ ከገጽ 35-51 መመልከት ነው::

በ1860 ዓ.ም ሠላሳ ስምንት ሺህ የእንግሊዝ ወታደር ኢትዮጵያን ቈራጡን ንጉሥዋን የክርስቶስ ባሪያ አጼ ቴዎድሮስንና ሕዝቧንም ጭምር ደምስሷል:: በ1866 ዓ.ም ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የሚሆኑ የወዳጃችን የግብጽ መንግሥት ወታደሮች ምንም ድሉ የኛ ቢሆን የኢትዮጵያውያንን ደም እንደ ጐርፍ አፍስሰውታል:: በ1881 ዓ.ም እደ ጸላኢ (ደርቡሽ እስላሙ) የኢትዮጵያውያን ፀሓይ አጼ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮንን ገድሎ ሕዝቡንም ሁሉ አጥፍቶታል:: እንዲሁም የኢጣሊያ ወታደር በ1888 ዓ.ም እና በ1928 ዓ.ም ሌላው ቀርቶ በመርዝ ጢስና ጭከና÷ እንደ ዕንጨትም በአካፋና ዶማ ሕፃንና ሽማግሌ÷ ወንድና ሴት ሳይለይ መዓትና እደ ጸላኢ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደምስሶአል:: ስለዚህ ጹመውና ጸልየው መዓትን ካልመለሱ÷ እንዳልጸሙና እንዳልጸለዩ ሰዎች መቈጠር ነው፤ አሞ. 5÷1-27፤ ሚክ. 3÷1-12፤ ዘካ. 7÷1-14:: አምላካችን «እነሆ ለክርክር ትጾማላችሁና ዛሬ እንደ ጾማችሁት ጾም ለኔ አትጹሙልኝ::» ኢሳ. 58÷4 እንዳይለን በጣም ያስፈራል::

3ኛ. ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሚነግረን እውነተኛው ጸዋሚ÷ ዘወትር ከዲያብሎስ ጋራ ለመታገል በዓለም ካለው የከንቱ ስሕተትና የጥፋት ወጥመድ ሌትና ቀን ነቅቶ ሉቃ. 12÷35-48፤ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መድኃኒቱን ለማግኘት ተግቶ ፊልጵ. 2÷12-18፤ በጸሎት በንጽሕና ሁል ጊዜ ተጠንቅቆ÷ መንፈሳዊ ቃል ለመመገብ (ለመስማት) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሙቆ÷ በውሃ አጠገብ እንደ ተተከለች ዛፍ በሕገ እግዚአብሔር እየለመለሙና በጎ ምግባርን እያፈሩ÷ ዕድሜ ልክ እውነተኛ ክርስቲያን ሆነው÷

ኃጢአትን እየጸሙ በክርስቶስ ጸጋ ጎልምሶ ለዘለዓለም ሕይወት መኖር ነው፤ 1ጴጥ. 5÷5-11፤ ሉቃ. 21÷34-36፤ 1ተሰ. 5÷1-24::

ይህን ሁሉ ማድረግ ማለት ግን በምትጾምበትና በምትጸልይበት ጊዜ ክፉ ከሆነው የዓለም ምግባር ሁሉ ተለይተህ÷ ኀሊናህን አንጽተህ÷ እግዚአብሔር በሚወደውና እርሱ ብቻ ባዘዘው አካሄድ መመላለስ ማለት ነው እንጂ÷ የሰው ሥርዐት በመጠበቅ ቅቤና ሥጋ (ጥሉላትን) ከመብላት ብቻ ተለይተህ በእህል ወጥ÷ ዘይትና ዓሣ እየበላህ አምላክ የከለከለውንና የሚያዝንበትን ክፉ ሥራ እየሠራህ ከሆነ ሐሰት ነው፤ ጾም አይባልም:: በምትጾምበት ጊዜ ግን ያንተውን ፈቃድ ትተህ የአምላክህን ፈቃድ ብቻ መሥራት ታዟል፤ ኢሳ. 58÷3::

ለዘለዓለም ፈጽሞ እንዳይነካና እንዳይበላ የተከለከለውም በአንድ ስም ተጠቅልሎ ኃጢአት የሚባለው ክፉ ሥራ ሁሉ ብቻ ነው «እኔ ግን ኃጢአት እንዳትሠራ ከለከልኩህ::» ዘፍ.20÷6:: ይህ አምላክ የከለከለው ኃጢአት ከዚህ ዓለም ተጠርተህ እስከምትሄድበት ቀን ድረስ ይጾማል:: ከአንድ ዓመት (ከዐሥራ ሁለት ወር) ሁለት ወይም ሦስት ወር ብቻ መጾም ግን የሰው ሕግ ስለሆነ «ሠለጡ ዕሤቶሙ::» እንዳለው በሰው ዘንድ ነው ዋጋ ያለው:: በክርስቶስ ዘንድ ግን ጾዋሚው የሚቀበለው ከንቱ ድካም የሆነ የፈሪሳዊው ዋጋ ብቻ ነው፤ ሉቃ. 18÷9-14::

ወንድሜ ሆይ! አምላካችን ያዘዘው የመጀመርያው ጾም ግን ለአዳም ያቀመለት ሕግ «ኢትብላዕ እምዛቲ ዕፅ» የሚለው ብቻ ነው:: ከዚህም በኋላ ደግሞ ለኛ ለልጆቹ በ2454 ዓመተ ዓለም «ኢታምልክ ባዕደ አምላከ፤ ኢትቅትል፤ ኢትዘሙ ኢትስርቅ . . .» «ሌላ አምላክ አታምልክ፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ . . .» የሚለውንና ሌላውንም የመሰለውን ሁሉ ዐሥር ቃላትን በጣቱ ጽፎ አትቅረቡዋቸው፤ አትንኳቸውም፤ ለዘለዓለም ጹሚቸው ብሎ በሙሴ አማካይነት አዞናል፤ ዘፀ. 20÷1-17::

አሁን ግን እነዚህን አምላክ ጠብቋቸው ብሎ ያዘዘንን ትተን÷ ሰዎች የከለከሉትን÷ የሠሩትንና የደነገጉትን 1ነገ. 21÷9-12፤ ዕዝ. 8÷21፤ አስ. 4÷16፤ ዮና. 3÷5 ቅቤና ሥጋ ብቻ እየጾምን ኃጣውእን ብንበላ÷ አምላካችን እንደዚህ ያለውን አጿጿም እኔ አልመረጥሁትም፤ አላዘዝሁትም፤ በኔ ዘንድ ዋጋ እናገኝበታለን ብላችሁ ለኔ አትጹሙልኝ እንደሚለን ጥርጥር የለውም፤ ኢሳ. 1÷10-20፤ 58÷4፤ አሞ. 5÷21-27::

4ኛ. ስለ ጾም ነገር ወንጌላውያን ጽፈው የተዉልን እውነተኛው በቂ ቃል እንደሚከተለው ነው:: እውነተኛው አማኝ

ዳግም ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ፥ ዐዲስ ፍጥረት ሆኖ፥ ከአሮጌው ሥራ ተወግዶ፥ ሕይወቱን በንጹሕ ልቡና ከክርስቶስ ጋር አዋሕዶ፥ በጫጉላ ቤት የሚኖር የሙሽራ ቤተ ሰብእን መስሎ፥ ክቡድ ዕዳውን ክርስቶስ ጎልጎታ ላይ በጸጋዊ ፍቅሩ እንደ ከፈለለት በመገንዘብ ሲያመሰግን፥ ዘለዓለማዊው መፍቀሬ ሰብእ በጸጋ ትሩፋቱ ከሠራለት ከማይናወጸው ሰማያዊ ገዳም ገብቶ፥ ዘወትር ልዝቡንና ቀላሉን ክርስቶሳዊ ቀምበር ተሸክሞ፥ በፊቱ ወዝ እየበላ ከኃጢአት ርቆ በመንፈሱ የሚሰማውን ደስታና ሰላም እየተመገበ ጸሎትንና ትሕትናን፥ ፍቅርንና ንጽሕናን ተጐናጽፎ፥ የጌታውን መምጣት በመጠበቅ ሁልጊዜ ነቅቶ በሕያው ተስፋ ይኖራል እንጂ፥ እንደ ፈሪሳውያንና የዮሐንስ ተማሪዎች በድባና መቍጠሪያ የሚደረግ ጸሎት፥ ሥራ ፈቶች የደነገጉት፥ ዋጋ የሌለው ቀኖችንና ሰዓታትን በመቍጠር የሚደረግ አፍአዊ ኃዘንና ጾም የሚሉትን ከባድ ቀምበር ሊሸከም ከቶ አይሆንለትም፤ ማር. 2፥14-22፤ ሉቃ. 5፥30-39፤ የሐዋ. ሥራ 15፥5-11፤ ቈላ. 2፥16-23።

«በእውነት ዋጋ ለማግኘት ብዬ ልጾም እችላለሁ፤ ጸዋሚ ነኝ፤» የሚል ሰው ቢኖር ግን፥ እርሱ ጾሙን ውሎ ያቺን ምሳውን ለተራበ ድኻ ወንድሙ ቢያበላው አምላኩ ተደስቶ «ርኅብኩ ወአብላዕከኒ» «ተርቤ አብልተኸኛል።» ብሎ ዋጋውን በግልጽ እንደሚሰጠው አምኖ ይጹም፤ ማቴ. 25፥31-40።

ስለዚህ በ፹ወ፩ መጻሕፍት ውስጥ ለይቶ <u>በዚህ ቀን በዚህ ወር ጹሙ፤ ቅቤና ሥጋም በሳምንት ሁለት ቀን አትብሉ፤ የሚል አምላካዊ ትእዛዝ በአንድ ጽሑፍ ከቶ የለም፤ ምንም አይገኝም። እግዚአብሔር የሚወደው እውነተኛው ጾም ማለት ግን፥ በሐዘን፥ በንስሓ፥ በልቅሶና በልብ ትሕትና</u>፥ ዋጋና ጥቅም አገኝበታለሁ ብለህ በፈቃድህ ባስፈለገህ ቀን የሚጾም ነው እንጂ፥ በዚህ ቀን <u>ጹሙ</u> ስለማይል የትእዛዝ አይደለም። «ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ መደልዋን፤ ኢትጸመሆዩ እስመ ያማስኑ ገጾሙ ከመ ያስተርእዩ ለሰብእ ከመ ጾሙ፤ አማን እብለክሙ ሠለጡ ዕሤቶሙ። ወአንተሰ ሶበ ትጸውም ቅባዕ ርእሰከ፤ ወገጸከ ተኀፀብ፤ ከመ ኢታስተርኢ ለሰብእ ከመ ጾምከ ዘእንበለ ለአቡከ ዘበኀቡእ፤ ወአቡከ ዘይሬኢ ዘበኀቡእ የዐስየከ ክሡተ።» «በምትጾሙበት ጊዜ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉና፤ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ራስህን ተቀባ፤ ፊትህንም ታጠብ፤ ለሰው ጾመኛ መስለህ እንዳትታይ ነገር ግን በምስጢር ለሚያይ አባትህ ጹም። በምስጢር የሚያይ አባትህም ዋጋህን በግልጽ ይሰጥሃል።» ይላል ማቴ.6፥16-18፤ አምላክ ያዘዘውና የመረጠውን እውነተኛውንም ጾም

ልታውቅ ከፈለግህ ግን ትንቢተ ኢሳይያስ 58ኛውን ምዕራፍ ማንበብና ማስተዋል ነው::

እውነተኛ ጾም ማለት እንደ ዳንኤል 10÷1-14፤ እንደ ዕዝራ 8÷21፤ እንደ ነህምያ 1÷1-11፤ እንደ አስቴር 4÷16፤ እንደ ሰብአ ነነዌ ዮና. 3÷1-10፤ 2ዜና. 20÷1-30 ያለው ነው:: እንደነዚህ አባቶቻችን በእውነተኛውና ባዘነ ኅሊና ብንጾም መዓቱን ወደ ምሕረት÷ ቍጣውን ወደ ትዕግሥት÷ ኃጢአቱን ወደ ጽድቅ ይለውጥልናል እንጂ በጅምላ በሃገራችን እንዳለው ለአዩልኝ የተሠራው ጾም ከንቱ ድካምና ዋጋ የሌለው ነው:: ጾምን ሊባልም አይቻልም፤ ማቴ. 23÷23-28::

አክሱማዊ የኢትዮጵያ ሊቅ አባታችን ያሬድ በጾመ ድጓ ስለጾም ሲናገር÷ መጾም ከኀጣውእ (ከኀጢአቶች) ጾዋሚውም ሪቂቁ ሕዋሳት መሆኑን ዐውቆ «ንጹም ጾመ ወናፍቅር ቢጸነ ወንትፋቀር በበይናቲነ:: ዐይን ይጹም እምርእየ ሕሱም፤ እዝን ይጹም እምሰሚዐ ሕሱም፤ ልሳንኒ ይጹም እምተናግሮ ሕሱም::» «ጾምን እንጹም፤ ባልንጀራችንንም እንውደድ፤ እርስ በርሳችንም እንፋቀር:: ዐይን ክፉውን ከማየት ይጹም፤ ጆሮም ክፉውን ከመስማት፤ አንደበትም ክፉውን ከመናገር ይጹም::» እያለ በብዙ ቃል አስረድቷል:: ዘወትር ጾዋሚዎች ሊሆኑ የሚገባቸውና እግዚአብሔር የሚጠላቸውን ክፉ ሥራዎች የሚሠሩ ረቂቅ ሕዋሳት ሰባት ናቸው፤ ምሳ. 6÷16-19::

ሊቁ ዘርዐ ያዕቆብ «ንብ ማርን የምታስገኘው ከብዙ አበቦች ቀስማ ነው፤ ሰውም እንዲሁ ብዙውን መጻሕፍትና ሕገ ተፈጥሮን ተግቶ ከመረመረ እውነተኛይቱን ሊቅነት (ዕውቀት) በቶሎ ያገኛታል::» ሲል ተናግሮአል፤ ገጽ 47 ክፍል 17 ተመልከት:: ከያሬድም አስከትሎ ስለ ጾም ነገር ጽፎአልና እውነትን ከሐሰት ለይቶ ለማወቅ በጎ ፈቃድ ካለን÷ ማናቸውንም ሳንንቅ ሁሉን አስቀድመን እንመርምርና ክፉና ሐሰትን እየተውን እውነትና መልካምን ብቻ እንያዝ ሮሜ 12÷9፤ እንስማማም:: «እስመ እግዚአብሔር ኢይኤዝዝ ነገረ ከንቱ፤ ወኢይብል ዘንተ ትበልዕ÷ ወዘንተ ኢትበልዕ፤ ዮም፤ ብላዕ÷ ወጌሠም ኢትብላዕ፤ ወሥጋሰ ኢብላዕ ዮም፤ ወጌሠመ ብላዕ፤ ወለእስላምሂ ኢይቤሎሙ እግዚአብሔር ብልዑ ሌሊተ ወመዓልተሰ ኢትብልዑ፤ እስመ ልቡናነ ይሜህረነ ይኩነነ ብዉሐ ንብላዕ ኵሎ ዘኢያማስን ጥዒናነ ወፍጥረተነ፤ ወንብላዕ በበዕለት ዘየአክለነ ለመፍቅደ ሕይወትነ:: እስመ ፩ ዕለተ በሊዕ ወ፩ ዕለተ ጸዊም ያማስን ጥዒና ወምግባረ፤ ወሕገ ጾምሰ ውጹእ ውእቱ እምሥርዐተ ፈጣሪ:: ወበእንተዝ አይሁድ÷ ክርስቲያን÷ ወእስላም ኢለበዉ ውስተ ግብረ

እግዚአብሔር ሶበ ሠርዑ ሕገ ጾም:: ወይሔስዉ እንዘ ይብሉ እግዚአብሔር ሠርዐ ለነ ጾመ ወከልአነ በሊዐ፤ ኦ ሰብእ ለባዊ ይክልኑ ይጻእ እምእግዚአብሔር ዝንቱ ዓመፃ፤ ወእግዚአብሔርሰ የዓቅብ ዓለመ በሥርዓቱ፤ ዘሰብእ ኢይክል አማስኖቶ:: እስመ ሥርዐተ እግዚአብሔር ይጸንዕ እምሥርዐተ ሰብእ፤ ወበእንተዝ እለ የአምኑ ከመ ምንኵስና ይኄይስ እምአውስቦ፤ እሙንቱ ይሰሐቡ እምጽንዑ ለሥርዐተ ፈጣሪ ኀበ አውስቦ፤ ወእለ የአምኑ ከመ ጾም ያጸድቅ ነፍስ እሙንቱኒ ይበልዑ አመ ይእኀዞሙ ረኀብ:: ወእምድኅረ ኀደግዎ ካዕበ ይትመየጥዎ በከመ ይገብሩ ብዙኀን እመነኮሳተ ብሔርነ:: ወከመዝ ኵሎሙ ሐሳውያን ይፈቅዱ ይንሥትዎ ለሥርዐተ ፍጥረት÷ ወባሕቱ ኢይክሉ እንበለ ያርእዩ ሐሰቶሙ ድኩመ:: ፈጣሪሰ ይሥሕቆሙ ወእግዚአ ፍጥረት ይሣለቅ ላዕሌሆሙ እስመ ውእቱ የአምር ገቢረ ፍትሕ ወበግብረ እደዊሁ ተሠግረ ኃጥእ::» «እግዚአብሔር ከንቱ የሆነን ነገር አያዝም፤ ይህን ትበላለህ፤ ይህን ግን አትበላም÷ ዛሬ ብላ÷ ነገ ግን አትብላ አላለም፤ ሥጋንም ዛሬ አትብላ፤ ነገ ግን ብላ:: እስላምንም ቢሆን በሌሊት ብሉ በቀን ግን አትብሉ አላላቸውም:: ጤናችንንና ባሕርያችንን የማያውከውን ሁሉ÷ በየዕለቱ የሚበቃንንና ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ያህል ለመብላት ሥልጣን እንዳለን ኅሊናችን ያስተምረናል:: አንድ ቀን መብላት÷ አንድ ቀን መጾም ጤናን ያውካል፤ እንዲህ ያለው የሕግና የምግባር ጾም ከፈጣሪ ሥርዐት ውጪ ነው:: ስለዚህም አይሁድ÷ ክርስቲያንና እስላም የጾምን ሥርዐት በሠሩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ አላስተዋሉም:: እንዲህ እያሉም ይዋሻሉ: - እግዚአብሔር ጾምን ሠራልን÷ መብላትንም ከለከለን:: አስተዋይ የሆንክ ሰው ሆይ! ይህ የዐመፃ ንግግር ከእግዚአብሔር ይወጣ ዘንድ ይችላልን? እግዚአብሔር ግን ሰው ሊያጠፋው በማይችለው ሥርዐቱ ዓለምን ይጠብቃል:: ከሰው ሥርዐት ይልቅ የእግዚአብሔር ሥርዐት እርሱ ይጸናል:: ስለዚህም ከማግባት ይልቅ ምንኵስና እንደሚሻል የሚያምኑ እነርሱ÷ ጽኑ ወደ ሆነው ሥርዐተ ፈጣሪ ወደ ጋብቻ ይሳባሉ:: ጾም በነፍስ እንደሚያጸድቅ የሚያምኑ እነርሱም÷ ረኃብ በያዛቸው ጊዜ ይበላሉ:: በሀገራችን ከሚገኙ መነኰሳት ብዙዎቹ እንደሚያደርጉት÷ አስቀድሞ ከተዉት በኋላ ዳግመኛ ወደ ተዉት ይመለሳሉ:: ሐሰተኞች ሁሉ የፍጥረትን ሥርዐት ያፈርሱ ዘንድ ይወዳሉ፤ ነገር ግን ደካማ የሆነ ሐሰታቸውን ለማሳየት ካልሆነ በቀር ይህን ማድረግ አይችሉም፤ ፈጣሪም ይስቅባቸዋል፤ የፍጥረት ጌታም በእነርሱ ላይ ይሳለቅባቸዋል፤ እርሱ ፍርድን ማድረግ ያውቃል፤ በእጆቹ ሥራም ኀጢአተኛ ይሰነካከላል::» ክፍል 5 እና 7 ተመልከት::

እናንት የኢትዮጵያ ሕዝብ በኅዳርና መጋቢት፥ በሠኔና ነሐሴ ወሮች በሥርዐታችሁ ሰባት አጽዋማት አቁማችሁ ዕድሜአችሁን ሙሉ ስትጾሙና ስትጸልዩ፥ በዐላት እየቈጠራችሁ ቤተ ክርስቲያን ስትሳለሙና ስታከብሩ፥ በውኑ ይህን ሥርዐት እኔን ደስ ለማሰኘት ብላችሁ የሠራችሁት ይመስላችኋልን? የመባእና ዘቢብ፥ የዕጣንና ጥዋፍ፥ የሻማና የመጋረጃ ስጦታ ይዛችሁልኝ ከኔ ፊት ቁማችሁ ይቅርታን ለመለመን ስትመጡ ይህንኑ ከእጃችሁ መቀበሉን የሚሻ ከቶ ማን ይሆን? ዘካ. 7፥1-14።

እናንተ የሰዶም አለቆችና የገሞራ ሕዝብ ሆይ! በጉባኤ መሰብሰባችሁንና የምትሰክሩበትን በዓላት ማክበራችሁን፥ የከንፈር ጸሎት ማብዛታችሁንና ምህላ ማርዘማችሁን፥ ነፍሴ ጠልታ ተጸይፋዋለችና ከቶ አልወደውም። እጃችሁ በዓመፅና በሰው ደም ተነክሯልና የምናምን ቍርባን ጨምራችሁ አታምጡብኝ፤ የግብዝነትን መሥዋዕትና እጅ መንሻም ብታቀርቡልኝ አልቀበልም። የስዕለታችሁን ሽታና ዕጣንም ዞሬ አላየውም፤ የከበሮና የጸናጽላችሁን ድምፅ፥ የዝማሜአችሁንና የቅኔአችሁንም ብዛት ከኔ አርቁት። በዓላቶቻችሁን ፈጽሜ ጠልቻለሁ፤ የመከማቻታችሁንም ሽታ ምንም አላሸተውም። ትዕቢት የእግዚአብሔር ጠላት ነውና አስቀድማችሁ ትሕትናን ተማሩ፤ ኢሳ. 58፥5፤ ያዕ. 4፥4-10፤ 1ጴጥ. 5፥5፤ ኢሳ. 1፥10-15፤ አሞ. 5፥1-27።

ይህ ሕዝብ በአፉ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከኔ በጣም የራቀ ነው። ትእዛዜን ትተው ግብዝ በሆነ በሰው ሥርዐት ተመርተው በከንቱ ያመልኩኛል፤ ማቴ. 15፥1-9።

እናንተ ግብዞች የአምላካችሁን ትእዛዝና ሕግ ስሙ፤ አድምጡም። በምትጾሙበትና በምትጸልዩበት ጊዜ የሥራችሁን ክፋት ሁሉ ከዓይኔ ፊት አስወግዱ ዮና. 3፥10። ክፉ ማድረግን ትታችሁ ድኻ አደጎችንና መበለቶችን እርዱ፤ በእውነት ፍረዱ። መልካም ትሠሩ ዘንድ ተማሩ። ሁላችሁም ከባልንጀሮቻችሁ ጋራ በእውነት ተነጋገሩ። ለተራበ አጕርሱ፤ ለታረዘም አልብሱ፤ ይቅርታና ግብረ ምሕረትን ዘወትር አትርሱ። አሕዛብ በሚሠሩት ክፉ ልማድ አትርከሱ፤ በብርሃነ ወንጌል ተቀድሳችሁ ክርስቶሳዊ ትሕትናን ልበሱ፤ በምትጾሙበት ቀን በድኾች ወንድሞቻችሁ ላይ ያለውን የብረት ቀምበር አፍርሱ (ስበሩ)፤ ዳን. 4፥27። ፍርድን እንደ ውኃ አፍስሱ፤ በኃጢአታችሁ እየተጸጸታችሁ ልባችሁን ቅደዱና አዝናችሁ አልቅሱ፤ ኢዩ. 2፥11-18፤ ዘካ. 7፥8-14፤ ኢሳ. 58፥5-14፤ ኤር. 7፥1-11።

አሁን ግን ይህን ትእዛዜን ፈጽማችሁ ብትጾሙና ብትጸልዩ÷ የሰማይ መዝገብ እሰጣችኋለሁ፤ ከአሕዛብም ሁሉ በላይ ሆናችሁ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እናንተ ኃጢአትን በምትጠሉበት ጊዜ መሥዋዕታችሁን እቀበላለሁ፤ እርሱም የከንፈሮች ፍሬና የተደቈሰ ልብ ነው፤ መዝ. 51÷10-17፤ ዕብ. 10÷1-22፤ 13÷11-16:: እኔም ከሰል የሚመስለውን ኃጢአታችሁን በረዶ አስመስዬ አንጽቼ÷ ሙሉ ይቅርታንና ስርየትን ሰጥቼ÷ የጾማችሁ ዋጋ እንዲሆን አምላካዊ የንጽሕና ልብስ አልብሼ÷ ስለ ክርስቶስ ብዬ በብርሃን ዙፋኔ ቀኝ እንድትቆሙና ዘለዓለማዊ መንግሥቴንም እንድትወርሱ አደርጋለሁ፤ ዘካ. 8÷14-23::

እምቢ ብላችሁ በትእዛዜና በሕጌ ላይ ብታምፁ ግን የእግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና ሰይፍና መከራ እንደሚበላችሁ አስቀድማችሁ ዕወቁ፤ ኢሳ. 1÷16-20፤ ኢዮ. 36÷5-13፤ ኤር. 7÷21-34 ብሏል::

የእግዚአብሔር ቃል (ቅዱስ መጽሐፍ) «አምላክህንና ወንድምህን አፍቅር» በሚለው ፍጻሜ ሁሉ ነገር ይጠቀለላል፤ ማቴ. 22÷35-40:: ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ትሰውራለችና ከሁሉ በፊት በመካከላችሁ እንደ እሳት የምትቃጠል ፍቅር ልትኖር ይገባል፤ 1ጴጥ. 4÷8:: እንዲህ ካልሆነ ግን ያለ ፍቅር ቢጾሙ በረከት የማይገኝበት የዔሳውን ጻማ (ድካም) መምሰል ነው:: ስለዚህ ያዕቆባዊውን በረከት ለማግኘት የሚፈልግ ጾመኛ የሰውን ሕግ ትቶ እውነተኛይቱንና ከአምላክ የታዘዘችውን ጾም መጾም አለበት (ይገባዋል)፤ ዘፍጥ.27:: እርስዋም ነፍስና ሥጋን የምታረክስ÷ አምላክ የከለከላት የኃጢአት ፍትወት ናት እንጂ መብል አይደለችም፤ ዘፍ. 6÷1-13::

አምላካችን በሰው የአጿጿም ሥርዐት ለኔ አትጹሙልኝ እያለን እኛ ግን እምቢ ማለታችን÷ በምሕረቱ ፈንታ መዓቱን በገዛ እጃችን ማምጣታችን መሆኑን እንወቀው:: «እፎ እንከ ትቄስሉ እንዘ ትዌስኩ ኃጢአተ በዲበ ኃጢአት::» «ደግሞስ ዐመፃን እየጨመራሁ ለምን ትቀሠፋላችሁ?» እንዳለ ነቢይ፤ ኢሳ. 1÷5-15::

ወንድሜ ሆይ! የአምላክና የሰው ሥርዐት የሆነውን ጾም ለይተህ÷ ዋጋ የምታገኝበትን አምላክ የከለከለውንና ኃጢአውእን ብትጾም÷ ለጊዜው በዋሾዋ ዓለም ዘንድ ብትሰደብና ብትነቀፍ÷ እርሱ እንዳዘዘህም በኀቡእ ብትጾም ዋጋህን በግልጥ እንደሚሰጥህ በቃሉ አረጋግጦልሃል::

ይህንን እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ሥራ (ጾም) በተመለከተ «ተፋቀሩ ዘእንበለ ኑፋቄ፤ ተገሐሡ እምእኩይ፤ ወትልዉ ሠናየ፤ ወአድልዉ ለጽድቅ፤ ኅልዩ በዘታነጽሑ ርእሰክሙ እምዝሙት:: ሥጋችሁን ንጹሕ መሥዋዕት አድርጋቸው ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ ጠባያችሁን ለውጡ እንጂ የዚችን ዓለም ሰዎች አትምሰልዋቸው::» ሮሜ 12÷1-21 የሚለውን የሐዋርያትን ቃልና ትእዛዝ መርምሮ አስተውሎ መቀበል ያስፈልግዛል እንጂ÷ መብላችሁን ለውጡ ከሚለው የሰው ሥርዐት የሆነው ጾም ምንም ጥቅም አታገኙበትም፤ ዘካ. 7÷4-14::

የሀገራችን ጾም ሲመሠረት በሰው ሥርዐት የቆመ መሆኑን የሚያስረዳን ደግሞ÷ ብዙ ሰዎች በመብል ምክንያት አምላክ እንደማይኰንናቸው በመረዳት÷ ጾም በተባሉት ቀኖችና ወሮች ሰዎችን ስለሚፈሩ ከሰዎች ተሰውረው ጥሉላትን (ሥጋ÷ ቅቤ÷ ዕንቍላል÷ ወተትን) መብላታቸው ነው፤ ቈላ. 2÷16-23::

እኔም ብሆን ላልተረዱ ሰዎች ዕንቅፋት ሆኜ እንዳልገኝ÷ ወይም እንጸድቃለን የሚሉ ጸዋሚዎች እንዳይገድሉኝ ስል የቀን ጸዋሚ የማታ ገዳፊ ነኝ:: ይህ የግል ጉዳዬ ተሰውሮልኝ የሚኖረውም የወፍ ቤት በማያህለው ትንሹ ጎጆዬ ውስጥ ብቻ ነው፤ 1ቆሮ. 10÷23-33፤ 11÷22::

አጼ ዮሐንስ የዓድዋ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ሲሉ÷ የአንዲትን መበለት ቤት (እድሞ) አፍርሰውባቸው ኖሮ÷ «እንዳይከመይ አግኜኺ ቤተይ ሐመድ ልብሱ ዓርበ ረቡዕ ደሪሱ አይደረሱ በላዕኹም ሰቴኹም ኢላ ዘይትሕሱ» «ቤቴ እንዴት አገኘሁህ! ቤቴ ዐፈር ልብሱ፤ ዐርብ ረቡዕ ደረሱ አልደረሱ÷ በላችሁ ጠጣችሁ ብሎ አይናገር እሱ::» ብለው የሐዘን እንጕርጕሯቸውን ገጠሙ ይባላል::

በውል ቢመለከቱ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰውራችሁ ጹሙ ብሏል፤ የሰው ሥርዐት ግን በግልጽ ጹሙ፤ በስውር ብሉ ሲል ይገኛል፤ ኤር. 14÷14-16፤ ማቴ. 15÷1-9:: ታድያ ዋጋ ያለውን የአምላክ ሥርዐት ወይስ ዋጋ የሌለውን የሰው ሥርዐት መጠበቅ ይገባናል? ይህን መምረጡና መርጦ ማድረጉ ግን የኛ ሥልጣን ነው፤ የሐዋ. ሥራ 4÷12-22፤ 5÷25-33::

በሀገራችን ሰዎች ነፍስ ወደ መግደል እየሄዱ ጾመኛ ነን ብለው የሽምብራ ስንቅ ይቋጥራሉ ተብሎ ይተረካል:: ሕዝባችን የሚበላውንና የሚታረመውን (የማይበላውን) ለይቶ የሚነግረው እውነተኛ መሪ በማጣቱ÷ እውነትም ይህ ምሳሌ የተደረገ ሳይሆን የሚቀር አይመስለኝም:: ከትንኝ ብልት ማውጣትና ግመልንም እንዲሁ መዋጥ ማለት ይህ ነው፤ ማቴ. 23÷23-28:: የእናንተን

ሥርዐት ለማጽናት ብላችሁ የአምላክን ትእዛዝ በጣም አላላችሁ (አፈረሳችሁ)፤ ማር. 7÷1-15:: የሰው ሥርዐት ጾም ግን በዘይት÷ በእልበት÷ የዓሣ ሥጋ እየተመገቡ÷ ጠላ÷ ጠጅና አረቄ እየጠጡ÷ «እጾማለሁ፤ ጾዋሚ ነኝ» ቢሉ በኃላፊው ዓለም ነው እንጂ በሚመጣው ዓለም ሳንቲምን የሚያህል ዋጋ አይገኝበትም፤ ማቴ. 25÷24-30:: ዳንኤል ሲጾም ግን እንኳን በዘይት እየበላ መጠጥ ሊጠጣ÷ «ኢበላዕኩ እክለ ፍትወት፤ ወኢቦአ ውስተ አፉየ ሥጋ ወወይን÷ ወቅብዐ ኢተቀባዕኩ::» «ማለፊያ እንጀራ አልበላሁም፤ ሥጋም ጠጅም በአፌ አልገባም፤ ሦስቱም ሳምንት እስከሚፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም::» በማለቱ ጾም የኀዘን እንጂ የደስታ ጊዜ አለመሆኑን አስተውል፤ ዳን. 10÷3::

እንዲሁም ቅዱስ ዳዊት «ወአሕመምክዋ በጾም ለነፍስየ» «ነፍሴንም በጾም አደከምኋት::» 35÷13 «መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር መንፈስ የዋህ::» «የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው::» 50÷1-23:: «ሡዕ ለእግዚአብሔር መሥዋዕተ ስብሐት::» «ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ሠዋ::» መዝ. 50÷14:: «ምስጋናን የሚሠዋ ያከብረኛል::» 50÷23 ማለቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ወይም አራት ወር ብቻ ማለቱ ነውን? አይደለም፤ አምላካችን የመረጠውና የሚደሰትበት <u>እውነተኛ ጾም</u> ማለት ግን÷ እርሱን ብቻ እያመሰገኑና እየፈሩ÷ ቃለ ወንጌሉንም እያዘወተሩ÷ ትሑት በሆነ ልብ ወንድምን እያፈቀሩ÷ የከንፈሮችን ፍሬ ለስሙ ብቻ እየመሰከሩ መኖር ነው፤ ዕብ. 13÷13-16፤ በጥቅሉ ኀጢአትን እስከ ዘለዓለም እየጾሙ መኖር ነው::

«ሕግህንም ሁልግዜ ዘወትር ለዘለዓለም እጠብቀዋለሁ፤ ትእዛዛትህንም ለዘለዓለምና ለፍጻሜው እጠብቀው ዘንድ ልቤን አዘነበልሁ::» መዝ. 119÷44-112:: «በጸሎትና በልመናም ሁልግዜ ተግታችሁ አዘውትራችሁ በመንፈስ ጸልዩ::» ኤፌ 7÷14-18:: «የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ ደጅ ለሚመታም ይከፈትለታል::» ሉቃ. 11÷1-13 ይላል::

አሁን ግን አንተ ሰው በአምላክህ ዘንድ ዋጋ አገኛለሁ ብለህ ልትጾም ብትፈልግ÷ ጾምህ÷ ጸሎትህና ምጽዋትህ ሦስቱ ነገሮች ስለሚያስጡህ ዋጋ ፍጡር ሳያውቅብህ ዘወትር ለርሱ ብለህ በኅቡእ ብትሠራቸው÷ እርሱም ዋጋህን በግልጽ እንደሚሰጥህ አምነህ ሳትታክት ጉዞህን በእርሱና ወደርሱ ብቻ ቀጥል፤ ዕብ. 10÷35-39:: በዓለም ካለው ሥጋዊ እንቅፋት እርሱ ይጠብቅህ አሜን፤ ፊልጵ. 1÷10፤ ይሁ. 20-25::

ምዕራፍ 25

የሐሰት ወሬ አትቀበል ዘፀ. 23፥1

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! ያገሬ ካህናት የሥጋ ባሮችና የሆዳቸው አገልጋዮች ስለሆኑ፥ «አድርግና አታድርግ» የሚለውን የአምላክ ቃል አምዘግዝገው ጥለው፥ ዐውቀው እንዳላወቁና እንዳልሰሙ መስለው፥ ብቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ «ወነበረ 1 ሠራቂ፥ ዘማዊ፥ ሐሳዊ፥ ቀታሌ ነፍስ፥ ወያፈቅራ ለእግዝእትነ ማርያም፤ ወአብአቶ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት።» «አንድ ሌባ፥ አመንዝራ፥ ሐሰተኛና ነፍሰ ገዳይ ሰው ነበረ። እመቤታችን ማርያምን ይወዳት ነበር። እርሷም ይህን ሰው ወደ ደስታ ገነት አስገባችው።» እያሉ ለሕዝብ ማስተማራቸውን ስለ ሰማሁ፥ ኀሊናዬ በሐዘን እያረረ የምሠራው ጨንቆኝ ዝም ብዬ እደነቃለሁ። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው በ2ኛው መልእክቱ ምዕራፍ 2 ቁጥር 10-11 «ይድኑበት ዘንድ የሚገባቸውን እውነተኛውን የአምላክ ፍቅር የተገለጸበትን «አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ» የሚለውን ሕይወት የሚሰጥ ቃለ ወንጌሉን ስላልተቀበሉና የሐሰት ወዳጆች ስለሆኑ፥ የሚወዱትን ሐሰት እንዲጠግቡትና እንዲያምኑት ብሎ እግዚአብሔር የስሕተት መንፈስ ይሰድባቸዋል።» የሚለውን ትንቢቱን የዛሬው ዘመናችን ደርሶ ተርጕሞታል።

እግዝእትነ ማርያም ድንግል፥ ወላዲተ ቃል፥ በሥጋ ንጽሕት ስትሆን እንደምን የሕግ አፍራሾችና የዓመፀኞች ዋሻ ትሆናለች? ብለው ሳይፈሩ፥ አምላክ በመረጠው የሥጋዋና የኀሊናዋ ንጽሕና ላይ እንዲህ ያለውን የማይገባ ነገር ለመናገር ደፈሩ? እውነትም የስሕተት መንፈስ ቢወድቅባቸው ነው እንጂ «መኑ ዘያስተዔርያ ለጽድቅ ምስለ ኃጢአት፥ ወመኑ ዘይዴምሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት፡» «ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» 2ቆሮ. 6፥14-18፤ የሚለውን ቃል ምንም እንኳ ባያነቡት፥ እህልን በጨው ለሚበላ ሰው እውነትንና ሐሰትን መለየት አይጠፋውም።

አንባቢና ሰሚ ሆይ! ተኣምረ ማርያም በሚሉት መጽሐፍ ም.12 ቁ. 1-67 ገጽ 66 እና 75 ላይ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ፥ እንኳንና በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ በጫጉላ መዘባበቻ ቦታ ላይም ሊነገር የማይቻል ሐሰት እንዳለ ስነግርህ፥ ያገሬ ሕዝብ ይህን ሐሰትና ማታለል አምኖ በካህናተ ሐሰት በመመራት የዲያብሎስ ከተማ ወደሆነው ሲኦል እየተጓዘ መሆኑን ስመለከት ሐዘኔ ወሰን የለውም። አንተም ኢትዮጵያዊ ወንድምህን

ወደ እውነትና የሕይወት መንገድ መጥቶና ቃለ ወንጌልን ሰምቶ ሕገ እግዚአብሔርን የሚጠብቅበትን ዘዴ ለመፈለግ ጥረት (ሐበ ኒሕ) እንደሚኖርህ ስለምተማመን ስማኝ፤ ተአምር እንዲህ እያለ ሐሰቱን እንደ አቧራ ያበነዋል:: «አ! አንውየ ኃጥአን እለ ከማየ እምይእዜሰ ኢንኅሥሥ ከዊነ አግብርተ እግዚአብሔር፤ ወኢዐቂበ ፲ወ፮ ትእዛዛቲሁ ዘእንበለ ስማ ለድንግል፤ ወስማሰ ለቅድስት ድንግል ጽሑፍ ውእቱ በቀለመ ወርቅ ውስተ ፍጽሞሙ ለኃጥአን፤ ወእንዘ ይቀውም እግዚእነ ውስተ ዐውደ ፍትሕ ሶበ ይሬኢ ስማ ለድንግል ውስተ ፍጽመ ኃጥአን፥ ይነሥት ዐውዶ ወይገብእ ይኅሬሁ ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን፤ ወኵሎሙ ኃጥአን ይገብኡ ምስሌሁ፥ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ዘእንበለ ሐተታ::»

ትርጓሜ: - «እኔን የመሳሰላችሁ ወንድሞቼ ኃጥአን ሆይ! ከእንግዲህስ ወዲህ የእግዚአብሔር ባሮች መሆን፥ ዐሠርቱን ቃላተ ኦሪትና ስድስቱን ቃላተ ወንጌሉንም መጠበቅ አያስፈልገንም (አይገባንም):: እንደምን ብትሉኝ ግን፥ የድንግል ማርያምን ስሟን ብቻ ማውሳት (መጥራት) ይበቃናል:: የድንግል ስሟን ካወሱ፥ ስሟ በወርቅ ቀለም በኃጥአን ግምባር ላይ ይጻፋልና፥ ልጅዋ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማ መለኮቱ ለፍርድ መጥቶ በተቀመጠ ጊዜ፥ የድንግልን ስም በኃጥአን ግምባር ተጽፎ ሲያይ፥ ደንግጦ የፍርዱን ጉዳይ ይተውና በማንም ላይ ሳይፈርድ ወደቤቱ ተመልሶ ይገባል፤ ኃጥአንም ሁሉ ለበደሉት በደልና ዓመፅ ሳይጠየቁበት አብረውት ይገባሉ::» ይልልሃላ!

እውነትና ሐሰትን እስከ መሠረታቸው ለመመርመር የተነሣኸው ወንድሜ ሆይ! እንዲህ ያለውን ቃል በአምላክ መንግሥትና በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚያፌዙ፥ ጭብጥ ቆሎና አንድ ዋንጫ ጠላ ለማግኘት ብለው ብርሃነ አእምሮአቸውን አውቀው ያደነዘዙ፥ የብርሃኑን መንግሥት ጥለው በፈቃዳቸው ለጨለማው ንጉሥ ለዲያብሎስ የተገዙ፥ ደፋሮችና ከሐዲዎች የሆኑ መምህራነ ሐሰት፥ እየሳቱ የሚያስቱ ግብዞች እንደጻፉት የተረዳህ ሁን፤ ሕዝ. 13፥17-23፤ 1ጢሞ.4፥1-8፤ 2ጢሞ. 3፥1-13::

አንባቢና ሰሚ ሆይ! ይህ ለመስማት የሚያስቸግርና የሚያስደንቅ ቃል፥ በካህናት እጅ ብቻ ተይዞ ሰው ሲታለልበት የኖረው፥ ቃሉ በግዕዝ ቋንቋ ስለ ተሸፈነ፥ ሕዝባችንም የሚበዛው ያልተማረ ስለሆነና ካህናትም የሚዋሹ ስላልመሰለው ነው:: በመሆኑም እስከ ዛሬ ድረስ የጽድቅ ሕግ ብሎ ይዞት ቈይቷል:: ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ ግን በጨለማ ሥልጣን የተሰወረውንና በጥልቅ ጥበባት የተሠራውን ሥራ ሁሉ ወደ ብርሃን አምጥቶ

የሚገልጽ፥ ጠቢባን ነን የሚሉትንም ከንቱ አድርጎ የሚያሳፍራቸው አምላክ ምስጋና ይድረሰው፤ 1ቆሮ. 1፥18-31፤ ዕብ. 4፥13::

ይኸው አዋልድ የተባለው መጻሕፍተ ሐሰት ግን ከነአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ አጼ ልብነ ድንግል ድረስ፥ ደብተሮች እየጻፉ በቀናተኛው አምላክ ላይ ሲያፌዙበት ቆዩ:: እንዲያውም አጼ ልብነ ድንግል ጣዖት እያመለኩና ትምባሆ እየጠጡ በፈረሶቻቸው ግንባር ላይ የቦረንትቻ ደም እየቀቡ በአምልኮ ባዕድ ተነክተው ነበረ ይባላል:: ከልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ ምዕራፍ 7ን ተመልከት:: ተበቃዩ አምላክ ግን ቅንአቱ ስለማያስችለው በ1518 ዓ.ም የበቀሉን ሰይፍ በማስያዝ ግራኝ መሐመድን ልኮ፥ 15 ዓመት ሙሉ ንጉሡን በስደት፥ ካህናቶቹን በሰይፍ የሚመኩባቸውንና የሚያታልሉባቸውን አብያተ ክርስቲያናትንም በእሳት እንዳቃጠለው በታሪክ ላይ ተጽፎ ይገኛል፤ ሕዝ. 9፥1-11፤ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ ገጽ 35-51 ተመልከት::

እንደ ጠፉ ይቅሩ ያላለን ቸሩ አምላክ በመንፈሱ አነሣሥቶ በግዕዝ ቋንቋ ተሸፍኖ ብዙ ዘመን የቈየውን ተአምረ ማርያም፥ በአማርኛ በማስተርጐም ለሕዝባቸው ቸሮታ ያደረጉለትን ሰዎች እያመሰገንሁ፥ ዋጋቸውን ዘለዓለማዊ የብርሃን መንግሥት እንዲሰጣቸው እመኝላቸዋለሁ፤ ማቴ. 10፥26-27::

ድርሳነ መድኃኔ ዓለም የተባለው ማታለያ ሲዋሽ ደግሞ ለዚሁ ዝክር ተብሎ ከተደገሰው ጠበል የቀመሰ፥ እንኳንና ጠበሉን ገና ለድግሱ የሚሆነው እንኩሮ (ቂጣ) ሲሰናዳ፥ የቡኮው ዕቃ ሲታጠን ጢሱ የሸተተው ሰው ሁሉ፥ ምንም ዓይነት ኀጢአት ቢሠራ በጢሱ ሽታ ምክንያት ሳይጠየቅ ወደ ገነት ይገባል ይላል::

የሀገሬ የዓድዋ ጻድቅ የአቡነ ገሪማ ገድል ደግሞ፥ «ጥዋት ስንዴና ወይን ለመሥዋዕት፥ ወይራ ለፍሕም ዘሩ:: በእኩለ ቀንም ስንዴውን ዐጭደው፥ ከዛፍ ላይ ቈልለው ወደ ዛፉ በሬዎችን ሰቅለው ቢያኼዱት፥ ገለባው ወደ መሬት ተበተነ:: ስንዴውን ግን በዛፉ ላይ አምርተው፥ ሦስቱንም ነገሮች ከመ ቅጽበት በየሥራቸው አድርሰው፥ ይህን ሁሉ ሥራ በተአምራታቸው በአንድ ቀን አጠቃልለው መሥዋዕተ ሠርክ አቅርበው ቀደሱ::» ይላል::

ወዳጆቼ ሆይ! እውነተኛው አምላክ ሥራው ሁሉ የማይቃወስ ሕጋዊ ስለሆነ፥ አዝርዕት የሆኑ ሁላችሁ ተዘርተው ከ7 ቀን በፊት ሠርፅና ብቅል ሊያሳዩ እንደማይችሉ ማንም ሰው ያውቀዋል:: እንደ ገድሉ ቃል ግን አባ ገሪማ ቅጽበት

በመፍጠራቸው ከአምላክ መብለጣቸው ነዋ! እበላ ባይ ይሉኝታን የማያውቅ ደፋር ጸሐፊ በከንቱ ይወሸክታል እንጂ÷ ይህ ቃል እንኳንና በሰው ሐሳብ የዶሮ ጭንቅላት በሚያህል አንጐልም እውነት ነው ተብሎ ሊታመን የማይቻል ነገር ነው:: እኔ ግን ሐሰትን በማታለል እየሸጡ ሲመገቡ የነበሩና ያሉ ሰዎች ይብላኝላቸው እንጂ÷ የሃገሬ ወጣት ከዛሬ በኋላ ሊቁ የማነ ብርሃን አበራ «የሀገሬ ሰው እንደ ዋዛ፤ ገበያ ወጥተህ ጥበብ ግዛ::» ብለው እንደ ተነበዩለት÷ ዕድሜ ለኃይለ ሥላሴ በየተማሪ ቤቱ እየሔደ ማንበብና ጥበብ÷ ምርምርና ማስተዋል የተባሉትን 4 ነገሮች ተምሮ÷ በአራቱ ማእዘን ብቻ ሳይሆን እስከ 8ቱ መአዝነ ዓለም ድረስ ሐሳቡን ዘርግቶ ሁሉንም ለመመርመር ጊዜ አጋጥሞታል:: ስለዚህ ሐሰቱን አምዘግዝጎ ጥሎ÷ ሥጋውና ነፍሱ የሚጠቀሙበትን እውነተኛውን ነገር ፈልጎ አግኝቶ ሠርቶ ይጸድቅበታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁኝ እንጂ በሐሰተኞች እየተታለለ በንዝህላልነት ይኖራል ብዬ አልጠራጠረም፤ ምሳ. 1÷20-33፤ 8÷1-36::

ከዚሁ የባሰ ውሸት ደግሞ «አባ ገሪማ ይህንኑ ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ÷ ጨርቆስ የተባለ አህያ ነበራቸውና ከኢየሩሳሌም ዓድዋ ድረስ በ1 ቀን 7 ጊዜ ደንጊያ ተጭኖ እየተመላለሰ ከኢየሩሳሌም በመጣ ድንጋይ ይህ ቤተ ክርስቲያን ተሠራ::» ይላል::

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! እውነትና ሐሰትን ሊመረምር የሚፈቅድ ቅንና ንጹሕ ኅሊና ካለህ ግን÷ ከመጻሕፍተ ሐሰት ሁሉ የባሰ ሐሰትንና የሚያስጸይፍ ነውርም÷ ከቶ በሰው አንደበት ሊነገርና ሊደፈር የማይቻል የጉድ ጉድ÷ ተአምረ ማርያም በተባለው በሀገሬ መጽሐፈ ኢትዮጵያ በ19ኛ ምዕራፍ ተጽፎልሃልና÷ ይህንኑ ጉደኛ ቃል ሳታነብልኝ እንዳትቀር በእውነት አምላክ አማጽኜሃለሁ::

ይህንኑ በተኣምረ ማርያም የተጻፈው የመሐመድንና የሚስቱ ናቃት (ግመል) ታሪክም÷ ቃሉ በሙሉ በጉልህ ተሥሎ ከቤተ ክርስቲያን እኔው ከነነውሩ በዐይኔ አይቼዋለሁና ስንገናኝ እንድትጠይቀኝ ዐደራ ዐደራ፤ 2ተሰ. 2÷12::

ቀጥሎ ተኣምረ ማርያም የወንድ ወይም የሴት ልጁን ስም በማርያም ስም ያወጣ÷ ገብረ ማርያምና ወለተ ማርያም ተብለው የተሠየሙት ሁሉ ገነት ይገባሉ ይላል (ተኣ.ማር. 12÷41):: አስከትሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ በሞላው ማርያም ዐሥራት ስለ ተቀበለችው ሁሉም የማርያም ልጅ ሆኖ ገነት ይገባል ይላል

(ምዕራፍ 111 እይ)። ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከጐጃም በቀር ኢትዮጵያን በሙሉ አቡዬ ዐሥራት ተቀብለውታል ብሎ፥ ዐባይ ባሕር ገብተው 100 ዓመት ቢጸልዩ ግን ጐጃምንም ከነ ስራዩ አስምረውታል ይላል።

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! ተኣምርና ገድላት የሚሉዋቸው መጻሕፍት በሙሉ፥ ያ ዱሮ እናታችን ሔዋንን በከርሠ አርዌ ተሠውሮ፥ ለሥጋዊ ምኞት ደስ የሚያሰኝ ማታለል ተናግሮ፥ እናት አባታችንን በተንኰል አሳስቶ፥ ከገነት ያስወጣቸው ከይሲ፥ ዛሬም መልኩን ለውጦና መልአከ ብርሃን መስሎ የክርስቶስን በጎች ለመዝረፍ «አይዞአችሁ ሕግ ብታፈርሱ የማድናችሁ (የምክስላችሁ) እኔ አለሁ።» እያለ በመንፈሰ ማታለል ያስጻፈው ሳይሆን አይቀርም፤ 1ነገ. 22፥20-23።

«እስመ ሀለዉ ሐሳውያን ገበርተ ዓመፃ እለ ይትሜየኑ ወይትሜሰሉ ሐዋርያተ ክርስቶስ፤ ወዝኒ አኮ ለአንክሮ እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን።» «እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያ እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና፤ ይህም ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።» 2ቆሮ. 11፥1-15።

መጻሕፍተ ሐዲሳትን የምታነቡ ወንድሞቼ ሆይ! መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 24፥23-26 ብዙዎች ነቢያተ ሐሰት እንደሚመጡና ቢሆንላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እንደሚያስቱ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ከቤተ ክህነት ሌላ ማነው የተመረጠው? ይህ ሁሉ ለሰሚው ግራ የሆነ ስሕተታዊ ቃል፥ በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ሲነገር፥ ሲነበብና እውነት ተብሎም በምእመናን ጆሮ ሲደመጥ እናንተስ ዝም ብላችሁ ታዩና ትሰሙ ይሆን?

ወዳጆቼ ሆይ! እባካችሁ ለባዕዶች መሳቂያና መሳለቂያ እንዳንሆን አብረን እየተመካከርን፥ ከዓለማውያን የምንቀበለውን ግብዝነት የተሞላ ምስጋና አምዘግዝገን ጥለን፥ በቃሉና በመክሊቱ ሳናፍር ሰማያዊ ዋጋ እንድንቀበል እውነቱን ለመመስከር እንትጋ፤ ማቴ. 10፥26-38።

ወንጌል «ባርኩ ወኢትርግሙ እስመ ለበረከት ተጽዋዕክሙ» «ባርኩ እንጂ አትርገሙ፤ በረከትን ልትወርሱ ተጠርታችኋልና።» ሲል፥ መቅድም ተብሎ የሚነበበው ተአምረ ማርያም ደግሞ ክርስቶስ «አባ ስረይ ሎሙ» ብሎ የጸለየላቸው አይሁድን፥ ወደ ሲኦል መሠረት ወርደው በእሳት ሰንሰለት ታስረው

ላይወጡ ለዘለዓለም ይኑሩ፤ በሰይፈ ሚካኤል ይትመተሩ፤ (ይቈረጡ) ወይትገዘሙ (ይጨፍጨፉ) ይትዓጸዱ (ይታጨዱ) ወይጽደፉ (ወደታች ይውረዱ) እያለ ሲፈርድና ሲራገም፥ የመንግሥተ ዲያብሎስ ሕግ አስከባሪ፥ አቀንቃኝና ነገረ ፈጅ የጻፈው ሳይሆን አይቀርም እንላለን:: ስንሰማውም በኀሊናችን ውስጥ ረመጥን በጭከናው ሲያፈስብን «ተገሐሰ እምእኩይ» «ከክፉው ሽሽ» ተብሏልና ከሐሰባችን አውጥተን ጥለን ሸሽተነው እንኖራለን::

ወጣት ሆይ! ለሀገርህ የሚጠቅመውንና ሐሰት ያልተደባለቀበትን የነፍስ መድኃኒት የሆነውን የወንጌልን ወተት፥ የሀገራችን ሕፃናት እንዲመገቡትና ጤናሞች ዘሮችም ሆነው እንዲወጡልን ሆነ ብለህ ለሕዝብህ አስብለት፤ 1ጴጥ. 2፥1-9::

ሽማግሌው ሐዋርያ ጴጥሮስ ለቀሳውስት ሲመሰክር «ከናንተ ጋራ ያሉትን የክርስቶስን መንጋዎች ስትጠብቋቸው፥ በሰማይ የሚቈያችሁን የክብር አክሊል እንድትቀበሉ እውነትን እያስተማራችሁ በልብ ፈቃድ ጠብቋቸው እንጂ፥ የማይጠቅም ሥጋዊ ነገርን (ዋንጫ ጠላና ጭብጥ ቆሎ) ለማግኘት ስትሉ በማይጠቅም ተስፋ እያታለላችሁና ሐሰት እያስተማራችሁ በግድ አትግዟቸው::» ብሎ ጽፎ ነበር:: ዐደራህን! «ብዙ ከሰጡት ብዙ ይሹበታል::» ተብሏልና ቀባሪ መክሊቱ እንዳትሆን በጊዜውም አለጊዜውም ለሁሉም ንገር፤ መስክር:: እግዚአብሔር አምላካችን የኃይልና የፍቅር፥ የጥበብና የድፍረት መንፈስ እንጂ የፍርሃትና የኀፍረት መንፈስ አልሰጠንም:: ስለ ክርስቶስ ቃል መከራም ልንቀበል ይገባናል እንጂ በስመ ማመን ብቻ ጻድቃን እንደማንሰኝ የተረዳህ ሁን፤ 1ጴጥ. 5፥1-11፤ 2ጢሞ. 1፥7፤ ፊልጵ. 1፥27-30::

ወዳጄ ሆይ! ፍትሐ ነገሥት በሁለተኛው አንቀጽ ስለ መጻሕፍት ቊጥር የአምላክ መጻሕፍት ሰማንያ አንድ ብቻ መሆናቸውን ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእየ ዮሐንስ ዘርዝሮ ቈጥሮ ሲያበቃ፥ «በእንተ መጻሕፍት አምላካውያት ዘእዙዝ ተወክፎቶን ኀበ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ዘኊልቆሙ ፹ወ፩፤ እሎንኬ ሕገጋት እንተ አዘዝናክሙ ባቲ እመቦ ብእሲ ዘነሥአ እመጻሕፍተ ሐሰት እንተ አንበርዋ ከሐድያን ወአባእ ውስተ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ቅዱስ ከመ ይእቲ መጽሐፈ እግዚአብሔር ንጽሕት በእንተ ሙስና ሕዝብ ይሰደድ::» «ስለ አምላካውያት መጻሕፍት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያላቸው የታዘዙት መጻሕፍት ቊጥር ሰማንያ አንድ ነው፤ እናንተን ያዘዝንባቸው ሕግጋት እነዚህ ናቸው:: ከሓዲዎች ጽፈው ካስቀመጧት ከመጻሕፍተ ሐሰት

ምእመናንን ለማሳት ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ያስገባ ማንም ቢኖር ከቤተ ክርስቲያን ይለይ።» ይላል።

ተኣምረ ማርያምን እኛ ከእስክንድርያ መጣ ስንል እነርሱ ግን «ከቶ የኛ አይደለም በሃገራችንም የለም።» ብለውናልና፥ መድን ካጣንበት ለመስሐቲ የሚገባው በድንጋይ አስሮ ከባሕር ውስጥ አምዝግዝጎ መጣል ብቻ ነው፤ ማቴ. 18፥1-3፤ ዮሐ. 19፥19።

አወይ እኔ ምን ልበል! ከላይ የሰማነውን የተኣምረ ማርያም ታሪክ ከሓዲ ጽፎና የአምላክ መጽሐፍ አስመስሎ እንዳገባው ተረድተን፥ ጸሐፊውን ከነመጽሐፉ ሐሰቱ ከቤተ ክርስቲያን እንድናባርረው ታዘናል። ኦሪትም «ሌላ እናምልክ የሚል ሰው ቢገኝ ግደለው።» ትላለችና መርጦ መያዝና መሥራት ገንዘባችን መሆኑን እንርሳ፤ ዘዳ. 13፥1-11፤ 30፥1-20።

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! መጠርጠር ባይኖር ማመን ሊገኝ አይችልምና፥ ቶማሳዊ መጠርጠርህም ሳይቀር አጥልቀህ ጠርጥረው። በዓለም ውስጥ ያለውን ባሕርያዊ ግቡር ሁሉ ኅሊናህን ጣልበት እንጂ ችላ ባይ አትሁን። ጠርጥረህ ያላመንኸው እምነት ግን ግዙፍና ሽፍን የጅምላ አምልኮ ስለሆነ በሰማይ አይጠቅምህም። እውነትን ከሐሰት ለይቼ አውቄ አምኜ ይዣታለሁ ለማለትም አያስደፍርህምና አስቀድመህ ጠርጥር፤ መርምረህም እመን።

ጠርጥር ብዬ ስመክርህም አምላክን ከነሥራው ሰው መርምሮ አያገኘውምና፤ መክ. 3፥10-11፤ 8፥17፤ ሁሉንም መመልከትና መታዘብን ሳትተው፥ ሃይማኖትና አምልኮ የተባሉትን 2 ነገሮች አምላካዊ ስም ለብሰው የሰው ሐሳቦችና የሥጋዊ መናገጃ ጥቅሞች ተዘንቀውባቸው ታገኛቸዋለህ። አስቀድመህ አንብበህ ስታበቃ የሐሰት እንክርዳዶችን ነቅለህ እየጣልህ (እየተውህ) እውነተኛውንና ንጹሑን የወንጌልን ስንዴ በልቡና ጎተራ ከተህ ያዝ እንጂ፤ ምንም እንኳ ቅጠላቸው አንድ ሆኖ ለምልሞ ሁሉንም ስንዴዎች (ክርስቲያኖች እስላም አረሚ) መስለው ቢታዩህም ዋናው አስተማሪህ ፍሬአቸውና ግብራቸው መሆኑን አትርሳ፤ የሐሰትም ወሬ ተቀባይ አትሁን። እውነተኛይቱ ጥርጣሬ ግን ቶማስን መርታ ከጌታውና ከአምላኩ ጋራ አገናኝታ ሕይወት ሰጥታ የልብ ዕረፍት እንደአስገኘችለት መጽሐፍ ይነግረናልና፥ መጠርጠር የእምነት መንገን (ማግኔት) መሆኗን አንርሳ፤ ዮሐ. 20፥24-29። ቶማስን ብቻውን ሳይሆን ሐዋርያትንም ሁሉ ጥርጣሬ ወደ እምነት መራቻው እንጂ በሴቶቹ መረዳት ትንሣኤውን ሊያምኑ ይቅርና፥ ሦስት ጊዜ ተገልጦ ሲታያቸውና ሲናገራቸውም ጌታቸውንም ሳይቀር ጠረጠሩት እንጂ ሊያምኑት አልቻሉም። ጠርጥረንም ስናበቃ የእምነትና የእውነት ደጋፊዎች ለመሆን በኃይሉና በቃሉ ይርዳን፥ አሜን፤ ማቴ. 23፤ ማር. 16፤ ሉቃ. 24።

ሕዝቤ ሆይ!
ብዙ የሰጡትን ብዙ ይሹበታል
ዐቅሜ በማነሱ ሆዴ ይሸብታል
መንፈስ ከጨከነ ከቶ ምን ያቅታል
ተራራ ይፈርሳል ዋርካም ይነቀላል
መምሬም ያውቁታል
አልሰማሁም ቢሉ ይጠየቁበታል
ሐሰተኛ መንግሥት አይቆምም ይረታል፡፡
እየገነፈለ እምቢ አለኝ ስሜቴ
በወንጌልህ ፍቅር ተቃጥሏል አንጀቴ
ያነሣል ይጥላል ይኸው አንደበቴ
ምስጢርህን ለመግለጽ ቢፍጨረጨር ጣቴ
ሐሰት ያሰረውን በእውነት በመፍታቴ
ወይዘሮ ዓለሚቱ ብትሆንም ጠላቴ
እኔ ግን አልፈራም ጥቅሜ ነው መሞቴ
በፈቃድህ አውለኝ የሱስ ሆይ ሕይወቴ
ማቴ. 17÷20፤ 21÷21፤ 25÷12-30፡፡

የሀገሬ ወጣት ሆይ! ባዕዳን የሃይማኖት መሪዎቻችን በሥጋዊ ጦርነት ኮሎኒ መያዝ ሳይሆንላቸው ቢቀር÷ ሕዝብ እንዳይበለጽግና ኃይልም እንዳያገኝ ሲሉ (በሀገራቸው የሌለውን) በዓላትና አጽዋማትን÷ ዝክረ ፍጡራንና አማላጅነት የሚባል ሥራ ፈትነትን አስተምረው ቅድስቲቱን ኢትዮጵያችንን አበላሿት፤ ዘፀ. 17÷14-20፡፡

አሁን ይህ የባዕዳን ተንኰልና ልማድ የሚወገደው ግን የሐዲሱ ዘመን መሪዎቻችን÷ <u>«ዛሬ በዓል ነውና ውጉዝ እንዳትሠሩ፤ የሚያስክር መርዝ እየጠጣችሁ ፍጡራንን አክብሩ፡፡»</u> እያሉ በተናገሩበት ልሳናቸው የጠላትን ምክር በመስማት ተሳስተን ኑረናልና÷ መጻሕፍትን አንብበን ከተረዳን ወዲህ ግን÷ «ስድስት ቀን ሥሩ፤ ሰባተኛውን ቀን ብቻ አክብሩ፡፡» ብለው÷ በዐዋጅ ካላስተማሩት ሕዝባችን በሥጋዊና መንፈሳዊ ነገሮች ጥቅም ያገኛል ብዬ ከቶ አልጠራጠርም፤ ሕዝ. 44÷15-28፡፡

መድኃኒታችን «መንፈስ ቅዱስን እሰድላችኋለሁ፤ ከሐሰት አውጥቶ አስተምሮም ወደ እውነተኛው የወንጌል አምልኮ ይመራችኋልና ቃሌንም ያሳስባችኋል፡፡» ዮሐ. 14÷23-27፤ ያለውን ቃሉን ዛሬ በኢትዮጵያችን እንዲፈጽምልን÷ ልባችሁን ወደ ሰማይ አንሡና ተግሣጽና ምክርን ቅመሱ፤ ከክርስቶስም ጋር እንድትነግሡ፤ እርሱም የብርሃን መንፈሱን አብዝቶ እንዲሰጣችሁ በመሉ ልቤ እመኝላችኋሁ፤ በኃይሉ ይርዳን፤ አሜን፡፡

ምዕራፍ 26

ስለሚያሰክር መጠጥ

አንባቢ ሆይ! መጠጥ ማለት ለኃጢአት ሁሉ ምንጩ መፍለቂያው የበሩ መክፈቻ መግቢያው ማለት ነው:: ስለዚህ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ሁሉ አስቀድሞ መጠጥ (ስካርን) ሊጾም ይገባዋል:: ስለምን ብትለኝ ግን ስካርን ተከትሎ የሚመጣው ፍሬው ጥፋት÷ አሴ÷ ወዮ÷ ወዮታ ብቻ ነው:: «አሌ ሎሙ ለእለ ይገይሡ በጽባሕ ቤተ መያሲ÷ ወይወዕሉ ውስተ ስታይ÷ ወያነድዶሙ ወይን:: አሌ ሎሙ ለጽኑዓን እለ ይስትይዎ ለወይን÷ ወለኀያላን እለ ይቶስሕዎ ለሜስ::» «ስካርን ለመከተል በጥዋት ለሚማልዱ÷ የወይን ጠጅም እስኪያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወዮላቸው:: የወይን ጠጅ ለመጠጣት ኀያላን÷ የሚያሰክረውንም ለማደባለቅ ጨካኞች ለሆኑ ወዮላቸው::» ኢሳ. 5÷11-22::

«ወዮታ ለማን ነው? ሐዘን ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ጠጅ ሲጠጡ ለሚውሉ አይደለምን? ወደ ጠጅ አትመልከት፤ የመልኩ ቅላት በብርሌ ሆኖ ባንጸባረቀ ጊዜ ጣዕሙ እየጣፈጠ ይገባልና÷ ከጠጡት በኋላ ግን እንደ እባብ ይነድፋል፤ መርዙንም እንደ እፉኝት በሰው ሕይወት ያፈሳል ወደ ሞትም ያደርሳል::» ምሳ.23÷29-32:: «ወኢትስክሩ በወይን እስመ ምርዓት (ኃጢአት) ውእቱ::» «በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ማባከን ነውና::» ኤፌ.5÷18:: «ዑቁ ርእሰክሙ ኢታክብዱ ልበክሙ በስታይ ወበፈጊዕ::» «ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር . . . እንዳይከብድ . . . ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::» ሉቃ. 21÷34-36:: «ወይእዜኒ ኢትስተዪ ወይነ ወሜሰ::» «አሁን የወይን ጠጅ÷ የሚያስክርም ነገር አትጠጪ::» መሳ. 13÷7:: «እስመ ዐቢየ ይከውን ውእቱ በቅድመ እግዚአብሔር፤ ወኢይሰቲ ወይነ ወሜሰ::» «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፤ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም::» ሉቃ. 1÷15:: <u>«ይሠየም ጳጳስ ዘኢያበዝኅ ሰቲየ ወይን::» 1ጢሞ. 3÷1-16፤ ቲቶ 1÷5-9፤ «ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ÷ . . . የማይሰክር . . . ሊሆን ይገባዋል::»</u> «እስመ እሉ ሰክሩ በወይን፤ ወአስሐቶሙ ወይን፤ ወአደንገጾሙ ሜስ ለካህን ወለነቢይ፤ ወአስጠሞሙ ወይን፤ ወጌገዩ በሰኪር ወዝኒ መትሕተ ዐይን ውእቱ::» «እነዚህም ደግሞ ከወይን ጠጅ የተነሣ÷ ከሚያስክር መጠጥ የተነሣ ይፋንናሉ፤ ካህኑና ነቢዩ ከሚያሰክር መጠጥ የተነሣ ይስታሉ፤ በወይን ጠጅም ይዋጣሉ:: . . . በራእይ ይስታሉ፤ በፍርድም ይሰናከላሉ::» ኢሳ. 28÷7::

ወዳጄና ወንድሜ ሆይ! ሰማህን? አየህን? የሚያሰክር መጠጥን (ሐሊበ አዝርእት) ቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ቦታ ደጋግመው ይነቅፉታል:: ሐሊበ እንስሳት (የእንስሳት ወተት) ግን ቢጠጡት ኃጢአት አይሆንም፤ የሰው አእምሮ የማያዛባና የማይበጠብጥ ስለሆነ መጻሕፍት አምላካውያት አይከለክሉትም፤ ያስጸይፋል ብለውም አይነቅፉትም:: ከቶውንም ብዙዎችን ልበ በሽተኞች ከሞት ስለሚያድናቸው፥ የደረቀ ሕይወትን የሚያለመልም፥ ውስጣዊ በሽታ እንደ እሳት ሲያቃጥል ጠለ ሕይወት ሰጥቶ የሚፈውስ፥ አምላካችን በምስጢሩ አሰናድቶ የሰጠን እውነተኛ መድኃኒተ ሥጋ ስለሆነ ሊጾምና ሊታረም አይገባም:: አውስቦና (ጋብቻና) መብልዕ (መብል) ሊታረም ይገባል እያሉ የሚያስተምሩትን መምህራነ ሐሰት ግን ቅዱስ ጳውሎስ «ነባብያነ ሐሰት . . . እለ የሐርሙ አውስቦ፥ ወይከልኡ መባልዕተ ዘእግዚአብሔር ፈጠረ ለምእመናን ከመ ይሴሰዩ ወያእኵቱ እለ የአምርዋ ለጽድቅ::» «እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፤ አምነው እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ::» እያለ ይዘልፋቸዋል፤ 1ጢሞ. 4፥1-5፤ ሮሜ 14፥14-23::

ጻድቁ አምላካችን ግን በአምሳሉ የፈጠረው የአዳም ልጅ ሁሉ በመጠን እንዲበላና እንዲጠጣ፥ እንዲለመልምም፥ በልቶና ጠጥቶም ሰጪውን እንዲያመሰግን፥ «ብልዑ ወስግዱ ኵልክሙ ጥሉላነ ምድር::» «የምድር ደንዳኖች ሁሉ ይበላሉ ይሰግዳሉ::» መዝ. 22፥29 ብሎ ፈጠረው እንጂ፥ የእግዚአብሔር መቅደስ እንዲሆን የተመደበውን ሕይወቱን በረሃብ በሽታ እንዲያመነምነውና እንዲያበላሸው አላዘዘም:: «ኢተአምሩኑ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ፤ ወመንፈስ እግዚአብሔር ሳዕሌክሙ:: ወዘሰ አማሰነ ቤተ እግዚአብሔር ሎቱኒ ያማስኖ እግዚአብሔር::» «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል::» እንዳለ ጳውሎስ፤ 1ቆሮ. 3፥16-23::

አሁን ግን ሰው «በሐፈ ገጽከ ብላዕ» ተብሎ ታዟልና ካልሠራ አይበላም፤ ካልበላና ካልጠጣ ደግሞ ሊሠራ አይችልም:: የማይሠራ ግን እንዳይበላና እንዳይጠጣ መጽሐፍ ከልክሎታል 2ተሰ.3፥9-10:: መሥራት፥ መብላት፥ መጠጣትና የመሰለውም ሁሉ በመጠን ሊደረግ ይገባል:: ከልክ ያለፈ ሁሉ ግን ኃጢአትና ርኵሰት ይባላል፤ ምሳ. 25፥16::

መጠጥ (ሐሊበ አዝርእት ወአትክልት) የኃጢአት ምንጭ ነው:: ብዙ ብዙ ሕይወቶችን ያሳሳተ÷ ያሰናከለና ያጠፋ ስለሆነ ይበልጥ መጠጥ ከነስካሩ እርም ተብሎ ዘወትር ሊጾም ተገቢ ነገር ነው:: ኖኅ ትልቁ አባታችን በመጠጥ ምክንያት ኀፍረቱ ተገልጦ÷ አንጎሉ ተበጥብጦ÷ ልቡናው ጠፍቶ እስኪወድቅ ድረስ ሰክሮ ነበር:: በዚህም ለልጁ ለካም ዕንቅፋት ሆነና ከመራገም ደረሰ፤ ዘፍ. 9÷20-27:: እንዲሁም ሎጥ በመጠጥ ሰክሮ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር የማይገባ ነውር ሠርቷል (ወልዷል)፤ ዘፍ. 20÷30-38::

ሊጾም ይገባዋል ከምንለው መጠጥ የእስራኤል ንጉሥ የባኦስ ልጅ ኤላ÷ በመጠጥ ሰክሮ መንግሥቱንና ሕይወቱን ቤተሰዎቹንም ጭምር አጥፍቶ ጠፍቷል:: ከወገኖቹም ሁሉ አንድም ሳይቀር በእደ ጸላኢ በክፉ ሞት ተደምስሰዋል፤ 1ነገ. 16÷8-14:: እንዲሁም ብልጣሶር የባቢሎን ንጉሥ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ መንግሥቱንና ሕይወቱን በአንድ ሌሊት አጥፍቷል ዳን.5÷1-30::

በመጻሕፍት የተገለጸው የፈቃድ ጾም ግን (ማናቸውም ሰው በፈቃዱ ስዕለት ቢሳል÷ የጾም ቀን ቢለይ) እግዚአብሔርን የሚያገለግልበት ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ ከጠጅ ይከልከል የሚያሰክርም ነገር ሁሉ ፈጽሞ አይቅመስ፤ ዘኍ. 6÷1-21፤ የሐዋ. ሥራ 18÷18፤ 22÷24-26:: «<u>መከራቸውን እንዲረሱት ለሐዘንተኞች ወይን÷ ወደ ሞት ለቀረቡት ጠጅ ስጡ:: ነገሥታትና መኳንንት ግን ጠጅ ይጠጡ ዘንድ አይገባም:: የሚያሰክር የጠጡ እንደ ሆነ ሕገ እምላክን ይረሳሉና፤ እውነተኛውንም ፍርድ ይለውጣሉ::</u>» ምሳ. 31÷1-9::

ሕፃን ተወልዶ የእንግዴ ልጅ ሊቀር እንደማይችል÷ እንዲሁም ሰው በስካር በሽታ ከተለከፈ በኋላ ዝሙትና ቀቲል÷ ሐሰትና ሰረቅ የመሳሰሉትን ሕግጋት ሁሉ ከማፍረስ እንደማይቀር ዐውቆ÷ ፍትሐ ነገሥት በ10ኛው አንቀጸ ጾም ይልቁንም <u>ካህን ቢሰክር ከክህነቱ ይመተር (ይሻር)</u> ብሎ አዝዟል:: ለፍልፎ ይቀራል እንጂ ማን ቢሰማው! ባለሥልጣኖቹም እንኳንና እንዲህ ይላል ብለው ሕዝብን ሊያስተምሩበት ቀርቶ÷ ለተጣሉ ምስክርነት ሲጠሩም 12 ብር ካልጨበጡ አይሆንም፤ ሚክ. 3÷9-12 ተመልከት::

መጽሐፈ መነኰሳት እንዲያውም ሕዝብ እንዳያየውና እንዳያውቀው ተብሎ በስውር ተይዞ በጥንቃቄ ሲጠበቅ ይኖራል:: «የተሸሸገ ሳይታወቅ÷ የተሰወረውም በብርሃን ሳይገለጥ የሚቀር ከቶ የለም::» ሉቃ. 8÷17 እንደተባለው ግን÷ ማኅተም (መጻሕፍት

ማተሚያ ቤት) ስለ ተገኘልን ሁሉም ሳይገለጥ አልቀረምና የሚመነኲሱ ሰዎች አስቀድመው ቢያዩት ኑሮ፥ እንደ ሕጉ እናደርጋለን ብለው ጨክነው ባልገቡበትና የሕዝባችንም ዘር ባልተቀነሰም ነበር:: አብዛኛዎቹ ግን ቢያውቁትም ቅሉ ሥጋዊ ክብረትና አባ አባ መባልን፥ ጉልታችን ሪማችን እያሉም ገበሬ ማዘዝን፥ (እንዲያውም በአገሬ አባ ገሪማዎች ሲመነኲሱ «ግራት ቆብዕ» ብለው አምስት ማሳ መሬት ይቀበላሉ::) አንድ ደቂቃ እንኳ ያልደከሙበት የተመረጠ ምርት ከአውድማ ሄዶላቸው እንደሚካፈሉ ስለ ተረዱ ግን፥ እሾኽ እየተወጉ በፀሓይና ብርድ መከራ ከመብላት፥ ጥላ ውስጥ ተኝተው እየዋሉ ሳያስቡ መመገብ የሚቻልበት ኑሮ ነውና ሆነ ብለው በጠቃሚነቱ መርጠው ይገቡበታል::

የመነኲሴዎቹ አለቆች ደግሞ ጮማ እየቈረጡና ጠጅ እየጠጡ፥ እንደ ፀሓይ የሚያበራ የወርቅ ካባ ለብሰው፥ በፈርጥና ዕንቍ የተጌጠ የራስ ወርቅ ጭነው፥ በጥሩ ወርቅ የተሠራ መስቀልና ማርዳ አስረው፥ ገሣነም አለ ብላ ሰምታ እንዳታዝን እናታቸውን ወይዘሮ ዓለሚቱን እንደ አሻንጉሊት ተጊጠውላት በየጊዜው ሲናዝዟትና (ሲያጽናኗትና) እየተቀናጡ ሲያስደስቷት ይኖራሉ:: በእውነት መጠጥን እየጾሙ ሀገራቸውን ከጨለማ ወደ ብርሃን የመሩ ሊቃውንት፥ የእነ ማኅትማ ጋንዲ ልብሶችና በሐሳብ የሰለቸ ደም ግባት መልካቸውን ትኩር ብሎ በየፎቶ ግራፉ ላይ ለተመለከተው ሰው ግን ትልቅ ትምህርት ሳይሰጥ አለመቅረቱ የታወቀ ነው፤ 2ነገ. 1፥8::

መድኃኒታችን በዚህ ዓለም አርአያ ሊሆነን መጥቶ ሳለ ግን፥ የርሱ የነበረው ጌጥ ብዙ ሥቃይና እሾኽ፥ ከበደኖ መቈዕ የተሠራ የመከራ ዘውድ መሆኑን አንርሳ፤ ማቴ. 27፥27-35:: የጌታ መጥምቅ ጾመኛው ዮሐንስም ልብሱ እንደ እሾህ የሚዋጋና ከግመል ጠጕር የተሠራ ዝተት (ማቅ)፥ ምግቡም ጣዝማና አንበጣ ብቻ እንደ ነበረ ይነገረናል ማቴ. 3፥1-4:: የሚበሉትን መንቀፍ ትተን አንበጣ የድኾች አዝመራ መሆኑንና በሕገ ሙሴም ንጹሕ ሆኖ እንዲበላ መፈቀዱን ከመጽሐፍ መመልከት ይገባናል፤ ዘሌ. 11፥20-22::

አሁን ግን ወደ ጥንተ ነገራችን እንመለስ፤ የሚያሰክር መጠጥ (ሐሊበ አዝርእት ወአትክልት) በመጻሕፍት የሚያስጸይፍ ነውርና ርኩሰት ተደርጎ መቈጠሩ፥ ብዙዎችን ሰዎች ነገሥታትና መኳንንትን መንገዳቸውን አሳስቶ፥ ሕይወታቸውን እያበላሸና እያዋረደ፥ እያስገደለና እያጠፋ ስለሚኖር ነው:: ስለዚህ ጾም ማለት

ፍሬ ነገሩ ሐዘን ማለት ነው። እጾማለሁ የሚል ሰው ግን ከሁሉ ይልቅ መጠጥን ቢጾም ዋጋውን ባላጣ ነበር። ዘይትና ዓሣ እየበሉ፥ ጉሽና ጥሩ ጠጅ አረቄም እየጠጡ እጾማለሁ ማለት ግን ስሕተት ነው። «ወይን ያስተፌሥሕ ልበ ሰብእ፤ ወቅብዕ ለአብርሆ ገጽ።» «ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፤ ዘይትም ፊትን ያበራል።» መዝ. 104፥15፤ ተብሎ እንደ ተጻፈው እነዚህ ሁለቱ ቅብዕና ወይንም የደስታ ቀን እንጂ የሐዘን ምግቦች እንዳልሆኑ አስተውል። ሐዋርያው ያዕቆብም ሲመሰክር: - «እናንተ ኃጥአን ጽድቅን ብትፈልጉ፥ ከእግዚአብሔር ፊት በእውነት ዝቅ ብላችሁ ሳቃችሁን ወደ ልቅሶ፥ ደስታችሁንም ወደ ሐዘን ለውጡት።» ይላል፤ ያዕ. 4፥8-10። ፍትሐ ነገሥትም በ15ኛው አንቀጽ ጾም በ114ኛው ገጽ ሲያዝ «ወኢይደሉ ይስተይ መኑሂ እምካህናት ወይነ በጾመ 40 ወኢበጾመ ረቡዕ ወዓርብ ወኢይጸውዑ ሰብአ ኀበ መካነ ስቴ ለስትይ።» «ከካህናት ወገን ማንም በጾመ አርብዓም ሆነ በረቡዕና በዓርብ ጾም ወይን ይጠጣ ዘንድ አይገባውም። ለመጠጣትም ሰውን ወደ መጠጥ ቤት አይጥሩ።» ብሏል። በሐዘን ቀን ደስታ ማድረግ ግን ላዘነ ልብ የደስታን መዝሙር ማሰማት ማለት ነው፤ ምሳ. 25፥20።

ሐሊበ እንስሳት ግን እንኳን ሰዎችን ሊያስገድሉ ቀርቶ ለሞት የቀረቡትንም ሕይወት ሰጥተው ብዙ ፍጥረቶችን እያዳኑና ቊስለ ሥጋን እየፈወሱ ይኖራሉ። «እንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ።» «ያለሥጋ ነፍስ አትቆምም» እንደሚባለው እንደዚሁም ሥጋ ያለ ሥጋ ሊቆም አይችልም። ለዚህ አስረጂው እግዚአብሔር ኤልያስን 3 ዓመት ሙሉ ጥዋትና ማታ እንጀራና ሥጋ መግቦታል፤ 1ነገ. 17፥1-6። ለእስራኤል 40 ዓመት ሥጋና የሰማይ እንጀራ መግቧቸዋል፤ መዝ.78፥19-29። ቸሩ አምላካችን ሕይወት በሕይወት ካልሆነ በሌላ ነገር ሊኖርና ሊቆም እንደማይችል ስላወቀ፥ መጀመሪያ ለአዳምና ሔዋን እንስሳትና ሐመልማላትን በምድርና በባሕር ያሉትን ሕይወት ያላቸውን ፍጥረቶቹን ሁሉ ባስፈለጋችሁ ጊዜ መብል ይሁኗችሁ ብሎ ፈቅዶ አዞላቸዋል፤ ዘፍ. 1፥27-31፤ 9፥2-3፤ ዘዳ. 12፥20-21።

የጥሉላት መብል ኃጢአት ስላልሆነ ግን ራሳቸው ሥላሴም ከአብርሃም ቤት በገቡ ጊዜ ሥጋና ወተት በሉ፥ ኮመኮሙት እንጂ፥ «እኛ ጾመኞች ነን ሥጋም ኃጢአት ነውና ትንሽ እንጀራ በጨው ብቻ ስጡን።» ብለው ደረቁን አልበሉም፤ ዘፍ.18፥1-8፤ መሳ. 13፥15-20።

ወንድሜ ሆይ! በኦሪቱ ሕግ ዘሌዋውያን 11ኛ ምዕራፍ እንደምታውቀው፥ «ይህ ቅዱስ ነው ብሉት፤ ይህን ርኩስ ነው

አትንኩት::» ማለቱ ግን ሕግ ከቆመላቸው በኋላ ከአሕዛብ ጋራ ከመብላትና ከመጋባት በብዙ ነገር እንዲለዩ ነው እንጂ ኃጢአት ወይም ርኩስ ሆኖ አይደለም፤ ዘፀ. 34÷11-17፤ 1ነገ. 11÷1-9::

ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ 2400 ዘመን ያህል የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ሲመገቡት ምንም አላረከሳቸውም:: አምላካችን የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ አይቶ ሲያበቃ «እጅግ መልካም» ብሎ አደነቀው እንጂ ይህ ርኩስ ነው የሚባል አንድ ነገር አላገኘበትም:: ስለዚህ ኦሪት ኃጢአትን የምታሳይ መስተዋት ስለሆነች ሮሜ. 3÷18-24፤ «አትንካ፤ አትቅመስ፤ አትያዝ» እያለች የምታስፈራራ ትምህርተ ሕፃናት 1ቆሮ. 13÷10-13፤ ገላ. 4÷1-5፤ ቈላ. 2÷16-23 ናትና÷ ወደ (እስከ) ክርስቶስ ልታደርሰን (ልትጠብቀን) ገላ. 23÷27 ተላከች እንጂ በክርስቶስ ግዛት ውስጥ ከቶ ሥልጣን የላትም::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ አሕዛብን እያስተማራችሁ አጥምቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው::» ብሎ ሲልካቸው ማቴ. 28÷18-20፤ «ኵሉ ዘአቅረቡ ለክሙ ብልዑ::» «ያቀረቡላችሁን ሁሉ ብሉ::» ብሏቸዋል:: በዚህም አሕዛብ የሚበሉትንና ዛሬ እኛ ርኩስ ነው እያልን የምንጸየፈውን ሁሉ በጸሎታቸው እንዲቀድሱት ሥልጣን ሰጥቶ «በገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ሳትመረምሩ ገዝታችሁ ብሉ::» ብሎ እንዳዘዛቸው (እንዳዘዘን) እንረዳለን፤ ሉቃ. 10÷1-8፤ 1ቆሮ. 10÷25::

ዛሬ ግን አይሁዳዊና አረማዊ÷ ግዙርና (የተገረዘና) ቈላፍ ብሎ በማያለያይ በዐዲሱ በክርስቶስ ሕግ÷ ረቂቁ ክፉ ሥራ ነው ርኩስ እንጂ÷ በ6ቱ ቀን የተፈጠረ ሥራው ሁሉስ እጅግ ንጹሕ ነው ዘፍ1÷31፤ ገላ.3÷26-29:: ሐዋርያው ጳውሎስ «እኔ በጌታ በኢየሱስ ዘንድ ርኩስ ፍጥረት እንደ ሌለ አምኜ አውቃለሁ:: ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው፤ በኢየሱስ ለማያምኑ ርኩሳን ግን ኅሊናቸው ርኩስ ስለሆነ ከቶ ንጹሕ የለባቸውም::» ሮሜ 14÷14፤ ቲቶ 1÷15:: «እስመ ኵሉ ተግባረ እግዚአብሔር ሠናይ÷ ወአልቦ ግዱፍ ወኢምንትኒ ለእመ ተወክፍዎ እንዘ የአኵቱ÷ እስመ ኵሉ ይትቄደስ በቃለ እግዚአብሔር ወበጸሎት::» «እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና÷ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለውም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና::» እንዳለ፤ 1ጢሞ. 4÷1-5፤ አመክንዮ ዘሐዋርያት «እኛ ግን አምላካችን የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ (አውስቦና መብልዕ) ንጹሕ

እንደሆነ እንመሰክራለን እንጂ ርኵስ ነው አንልም።» ብለዋል የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ተራ ቁ. 94 ገጽ 47 ተመልከት።

አክሱማዊው ሊቁ ዘርዐ ያዕቆብም «እስመ እግዚአብሔር ኢያረኵስ ግብረ እደዊሁ።» «እግዚአብሔር የእጆቹን ሥራ አያረክስም።» ብሏል። ክፍል 5 ቊጥር 30 ተመልከት።

ወዳጄ አንባቢ ሆይ! መብል (ቅቤና ሥጋ) ኃጢአት የሚሆን ከሆነ ግን አምላካችን እንደ ዕፀ በለስ «ኢትብልዕምሙ» «አትብላቸው» ብሎ በመጻሕፍቱ ውስጥ ሕግ አለማቆሙ ከቶ እነመምሬ ማንደፍሮን ፈርቶ ይመስልሃልን? እርሱ የሚጠላውንና የሚያስቆጣውን የከለከለውንም ነገርስ ልንገርህ። ለያዕቆብ «በልዐ ያዕቆብ ሰብሐ ወገዝፈ ወርሕበ ወኀደጎ ለእግዚአብሔር ፈጣሪሁ፣ ወርኀቀ እምእግዚአብሔር ሕይወቱ።» «ይሹሩን ወፈረ፥ ረገጠ፣ ወፈረ ደነደነ፥ ሰባ፤ የፈጠረውንም እግዚአብሔርንም ተወ።» እንደተባለው፥ እንዳናደርግ ብቻ ነው፤ ዘዳ. 32፥12-21። አሁን ግን በመጠን በልተን፥ ጠጥተን፥ ከስካር ተለይተን፥ ከእጁ መቀበላችንን እንዳንረሳ ሲያስጠነቅቀን ፥ ሁል ጊዜ በልታችሁና ጠጥታችሁ፥ ጠግባችሁ ስታበቁ እኔን አትርሱኝ፥ ስገዱልኝ፥ አምልኩኝ፥ አመስግኑኝ «ብልዑ ወስግዱ ሊተ ኵልክሙ ጥሉላነ ምድር።» መዝ.22፥29 አለን እንጂ፥ ጽድቅ በምትሠሩበትና በምትጾሙበት ቀን ጥሉላትን (የፍስክ ምግብ የሚባሉትን) አትብሉ ብሎ ከቶ አላዘዘም፤ ዘዳ. 12፥14-22።

ስለዚህ ፈረስን ያለ ልጓም ቢሰቀሉት (ቢቀመጡበት) ገደል አግብቶ እንደሚገድል፥ እንደዚሁ ከመጠን (ከልክ) ያለፈ መብልና መጠጥ፥ የበዛም ጥጋብ ወደ ሲኦል የሚያስገባ ስለሆነ ሁል ጊዜ ዕጉሣችና (ትዕግሥተኞችና) መጣኞች ልንሆን ይገባናል እንጂ፥ ለኛ ብሎ የፈጠረውን በረከቱን እርም ነው ወይም ርኵስ ነው ልንል አይገባንም። አምላካችን ንጹሕ ቅዱስ ስለሆነ ርኵስና የሚታረም ነገር አይፈጥርም፤ አልፈጠረምም፤ ሮሜ 14፥1-14።

መጠጥ የኃጢአት ምንጭ ነውና ለዘለዓለም ሊጾም በተሻለ ማለታችን ግን «ዘኢይክል ጸዊሮቶ» «መሸከሙን የማይችለው» ባይጠጣው ቢጾመው የበለጠ ያማረ ነበር ስንል ነው እንጂ መጠጥ በራሱ ርኵስ ነው ማለታችን አይደለም። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ከመ አኮ ዘይበውእ ውስተ አፍ ዘያረኵሶ ለሰብእ፥ አላ ዘይወጽእ እምውስተ አፍ ውእቱ ያረኵሶ ለሰብእ።» «ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣ ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው።» ማቴ. 15፥1-12፤ ማለቱ ለኃጢአት መምጫውና መገለጫው ስካር ስለሆነ፥ «ሰካርያን

ኢይወርስዋ ለመንግሥተ እግዚአብሔር » «ሰካሮች . . . የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም::» ይላልና ስካር ከሁሉ የባሰ የከፋ ትልቅ ዕዳ÷ ወደ ሞተ ነፍስ የሚያደርስ ኃጢአት ነው ማለታችን ነው፤ 1ቆሮ. 6÷9-11::

ስለዚህ ዋጋን የሚያሰጥ የነቢያትንና የሐዋርያትን አጿጿም ሊጾም የሚፈልግና የሚችል ሰው እንዳለ (ቢኖር)÷ በ2ኛቆሮ.6ኛ እና 11ኛ ምዕራፍ÷ በዕብራውያን 11ኛ ምዕራፍ ያለውን (የተጻፈውን) የአበውን ገድላቸውንና ሥራቸውን አይቶና (አንብቦና) እውነተኛ ውንም ቃል ተረድቶ÷ ጾዋሚዎቹ እነርሱ በሄዱበት ጎዳና አሰራቸውን ይዞ መከተል ይገባዋል:: ጻድቃን በሄዱበት በጠባብ አንቀጽ ሳይሄዱ÷ ለሥጋዊ ሐሳብ የተስማማ አፍአዊ የሰው ሥርዐት ጾም ይዘው እንጸድቃለን ለሚሉት ግን «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደኔ ይቀርባል፤ በከንፈሩም ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከኔ በጣም አስረዝሞ ይርቃል:: የሰውን ሥርዐትና ትምህርት እያስተማሩም በከንቱ ያመልኩኛል::» የሚለው አምላካዊ ቃል በራሱ እንደሚፈጸምባቸው ያስተውሉ፤ ማቴ. 15÷1-11::

አሁን ግን መጠጥን (ከነስካሩ) የኃጢአት መክፈቻ የተጠላ እንደ ዝሙት ቀቲል የሚቈጠር ነውና÷ ከስካር የተለዩ÷ ጥንቁቅ÷ ዘወትር ጸዋሚ ስካር (ስካርን የሚጾም) መሆን ክርስቲያናዊ ዋጋ እንደሚያሰጥ እርግጥ ነው፤ ኤፌ. 5÷18፤ 1ቆሮ. 3÷9-11፤ ገላ. 5÷19-21::

ሕዝቤ ሆይ! የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ «ካህናቴ ሆይ! ሕዝቤን እንድታስተምሩና በንጹሕና ርኩስ መካከል ያለውን መለየት እንድትችሉ÷ ከቶም ፈጽማችሁ ጠጅና ጠላ÷ አረቄና ማናቸውንም የሚያሰክር መጠጥ እናንተና ልጆቻችሁ እስከ ዘለዓለም ምንም አትቅመሱ::» እንዳላቸው ጥቅሶቹን ተመልከት፤ ዘሌ. 10÷8-11፤ ኤር. 35÷1-19፤ ሕዝ. 44÷15-28::

ኢትዮጵያ ሀገሬ ሆይ! በቅዱሳት መጻሕፍት ተቃኝተው÷ የሰማዩን ዋጋ ተገንዝበው÷ ሥጋዊ ጥቅምን የናቁ÷ ጠበል (ማለት አባራ ትቢያ ነውና) አቅምሱን ሳይሉ÷ መርዙንም ጽዋዐ መድኃኒት ያድርግልን እያሉ በመባረክ ፈንታ÷ ጥፋት አለበትና የአልኮልና የጌሾ÷ የትምባሆ የጸዶ÷ የዕፀ ፋርስና የአብሾ÷ የጫትም ባሮች አትሁኑ፤ በነፍሳችሁም ጉዳይ ተጠንቀቃችሁ በንቃትና ጸሎት ቁሙ፤ የሚያሰክረውን ነገር ሁሉ ዘወትር አጥበቃችሁ ጹሙ፤ ዐሥሩ ስድስቱን ትእዛዛት በሙሉ ፈጽሙ፤ እያሉ በቀጤማ ሕዝብን ማታለል ትተው የወንጌልን ወተት በእውነተኛው ቅንአት ሕዝባቸውን መግበው የሚያሳድጉ ሊቃውንት መምህራንን÷ ዛሬ

በዐዲስ ዘመን እንዲልክልህ ፈጣሪዬን እየለመንሁ በሙሉ ልቤ እመኝልሃለሁ፤ ኤር. 3÷14-16፤ ሉቃ. 21÷34-36፤ ኤፌ. 5÷18።

ዕንጨት ምንም መልካም ቢሆን መጥረቢያና መላግያው በውል ስለታም ካልሆነ÷ የዕንጨት ዕቃና መሣሪያ ሊገኝ እንደማይቻል÷ እንዲሁም ምክርና ኮሶ ካልመረሩ ሊያሽሩና ሊያድኑ አለመቻላቸው የታወቀ ነው ሕዝ.3÷1-4፤ ራእ.10÷8-11።

የእግዚአብሔርን ቃል በሥጋ ለተመለከተው ከዕሬትና ኮሶ ይልቅ መራራ÷ በመንፈስ ፈርዶ ላስተዋልው ግን ከማርና ስኳር እልፍ ጊዜ ጣዕም ያለውና ጣፋጭ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ መስክሮለታል። ተግሣጽና ምክርን መጥላትና ማማረር ግን ሰው የሰው ልጅነቱን መርሳትና ከተፈጥሮ ውጭ መሆን ማለት ነው፤ መዝ. 19÷7-11፤ 119÷103።

«ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል፤ ምክር የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው።» ምሳ. 12÷1።

አንባቢ ሆይ! ጠጅ እየጠጡ ነፍስና ሥጋቸውን ከሚያጠፉ ጋር አትቀመጥ፤ ምሳ. 23÷15-35።

ስካርን ጾሞ የሚያሸንፍ ኃይል ይስጠን፤ አሜን።

ምዕራፍ 27

ስለ መብልና ፈቃድ

የተወደድህ ወንድሜ ሆይ! ጾም በኀቡእ ያውም የፈቃድና የውዴታ ነው ብዬሃለሁ:: እንደዚሁ መብላትና መጠጣትም በአስፈለገህ ጊዜ የፈቃድህ ነው እንጂ በግድ የትእዛዝ እንዳልሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳን «ወባሕቱ ለኵሉ በከመ አዘዞ ልቡ::» «እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ::» ይላል፤ ሮሜ 14÷1-5:: ምጽዋትና ጸሎት÷ ጾምና ንጽሕና ምግበ ነፍስ ስለሆኑ አምልኮ አለኝ የሚል ሰው ሁሉ የእሊህ የአራቱ ነገሮች ረኃብ እንዲገኝበትና እንዲኖረው ሕሊናው ያስገድደዋል፤ አስፈላጊውም ነው:: ይልቁንም የዕንባ ጸሎት ሰማያዊ ስጦታን ጐትታ አምጥታ የምታስገኝ መንገን (ማግኘት መቃጥን) ስለሆነች÷ ለእውነተኛው ክርስቲያን ዓለምና ዲያብሎስን የሚያሸንፍባት ዋና መሣሪያው ገንዘቡና ሕይወታዊ (የመንፈስ) ምግቡ ልትሆን ይገባዋል፤ ዘፍ. 32÷24-30፤ ሉቃ. 11÷5-13፤ 18÷1-8::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያዝዘን ግን÷ «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ሌላው ሁሉም ይጨመርላችኋል::» ይለናል፤ ማቴ. 6÷44:: <u>የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ÷ ጽድቅን÷ ደስታንና ሰላምን እየሠሩ÷ ክፉ ጠባይን ወደ በጎ ለውጠው ከሰው ጋር በፍቅር ካልኖሩ መብል ብቻ ቢውጡ ከቶ ጽድቅ አይገኝም፤</u> ሮሜ 14÷17:: መብልና መጠጥ ግን ለሥጋዊ ሕይወት ብቻ መቆሚያው ስለሆነ ለነፍስ ምንም አይደለምና÷ በጽድቅ ወይም በፍርድ ቦታ ላይ ብንበላ አንጨምርም፤ ባንበላ አንጎድልም፤ 1ቆሮ. 8÷8::

ወዳጄ ሆይ! ጳውሎስ ሐዋርያ ስለ መብል ሲናገር «ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ነገር ግን ሁሉ አይረባኝም:: መብል ለሆድ÷ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሆድና መብልን ያጠፋቸዋል::» ይላል፤ 1ቆሮ. 6÷12-20:: አሁን ግን ሥጋችን ከዐፈር ነውና ወደ ዐፈርም ይመለሳል:: ከዚህም ዓለም ያለው ሁሉ ሰማይና ምድርም ቢሆን ኃላፊ ነው:: የማያልፈውን መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት ብትፈልግ ግን በሩ÷ መክፈቻውና መግቢያው ኢየሱስ ብቻ መሆኑን አስቀድመህ ማመን ያስፈልግሃል:: መልካሙ የጽድቅ ምግባርህ ግን በገዛ እጁ ከእምነትህ በኋላ ይመጣል (ይጨበጭባል):: መልካም ምግባር ማለትም ሃይማኖት አለኝ የሚል ሰው ሁሉ (አይሁድ÷ አረሚ÷ እስላም÷ ክርስቲያን) የታዘዘውና ሊፈጽማቸው የሚገባው

ዐሠርቱ ቃላተ ኦሪትና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ብቻ ነው:: ሌላው ሁሉ የሚሠራው ከዚህ በኋላ ነው:: የብሉይና የሐዲስ ፍጻሜና ሕይወታዊ ትእዛዝ ማለትም፥ እነዚህ ዐሥራ ስድስቱ ቃላት ብቻ መሆናቸውን አስተውል፤ ማቴ. 22፥35-40፤ ሮሜ 13፥8-10::

ወንድሜ ሆይ! የታዘዘውና ያልታዘዘው፥ የሚበላውና የማይበላው፥ የሚሠራውና የማይሠራው የትኛው መሆኑን ለይተህ ለማወቅ ቅዱስ መጽሐፍን አዘውትረህ አንብብ:: እውነተኛውን የአምላክ ትእዛዝ ያለ ኀፍረት ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ብታደርገው፥ «የከበረውን ከተዋረደው (እውነቱን ከሐሰት) ለይተህ ብትይዝ፥ የእግዚአብሔር አፍና ልጅ ለመባል የበቃህ ትሆናለህ::» ኤር. 15፥19::

የእውነትና የሐሰትን፥ የብርሃንና የጨለማን፥ የጨውና የአልጫን ጣዕሙን ለይተህ ሳታውቀው፥ በምግባርህ ሳይሆን በአፍህ ብቻ ሃይማኖት አለኝ በማለትህ ግን፥ ለባዕድ መሳቂያ ለዘመድም መሰቀቂያ መሆንህ እጅግ ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም:: አሁን ግን በዚህ ሁኔታ ላለ ሰው የሚጠቅመው ኀፍረትና ይሉኝታ ነውና ለጉድለትህ እፈርበት እንጂ አትፎክርበት፤ ኤር. 8፥10-12፤ ራእ. 3፥14-18::

አንባቢ ሆይ! ከኃጢአት ጽድቅን፥ ከክፉው መልካሙን የተሻለውን መርምረህ፥ መርጠህ፥ ለይተህ እውነተኛውን አምልኮ፥ የወንጌል ብርሃን አምነህ ያዝ እንጂ፥ ዋጋ የሌለው ልማድ ወይም ያባቶቻችን የሚባል የሰው ሥርዓትና የድንቊርና ጨለማ እስሮ ሲኦል እንዳያስገባህ ተጠንቀቅ:: «እስመ ብርሃን መጽአ ውስተ ዓለም፤ ወአብደረ ሰብእ ጽልመተ እምብርሃን» «ብርሃን ወደ ዓለም ስለመጣ፥ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው::» ዮሐ. 3፥16-21 የተባለው ቃል በአንተ እንዳይፈጸምብህም አስተውል:: ዛሬም የወንጌሉን ፋና በልብህ ውስጥ አግብተህ አብራ::

አሁን ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተከትለው ከዚህ ክፉ ዓለም (አረሚነት) እንደ ተለዩት እንደ አባቶችህ እንደ እነኖኅ፥ ሎጥ፥ አብርሃም፥ ነቢያትና ሐዋርያት መስለህ እውነትን ከሐሰት ለይተህ ያዝና ተለይ፤ ዘፍ. 12፥1-9:: «ፃኡ እምነ ማእከላ ወተፈለጡ::» «ከመካከሏ ውጡ ንጹሐን ሁኑ::» ኢሳ. 52፥11:: «ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ እለ ኢየአምኑ:» «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ::» 2ቆሮ. 6፥14-18:: መጻሕፍት በብዙ ክፍልና ስፍራ እየደጋገሙ በዓለም ላይ ካለው ከሚደረገው የከንቱነትና የሐሰት ርኵሰት ተለዩ ይላሉ:: አበ ምእመናን የተባለ አብርሃም ከአገሩና ቤተሰዎቹ ስለ ተለየ የእግዚአብሔር ወዳጅ

ተባለ፤ ኢሳ. 41÷8:: አምላካችን ወዳጆቹን ሲመክርም «ወዳጄ፤ ከብዙዎች ጋር ተንኰሏን እየሸረበች፤ በቤቴ ውስጥ ምን ጉዳይ አላት?» ኤር. 11÷15 ዐ.መ.ት፤ «ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አንድነት አለው::» ኤር. 23÷18 «ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል፤ እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት::» ማቴ. 21÷13:: «ነቢዩና ካህኑ ግብዞች ናቸውና÷ ክፋታቸውን በቤቴ ውስጥ አገኘሁት::» ይላል፤ ኤር. 23÷9-16::

የአምላካችን ትእዛዝና ምክር ግን አንተን ኃጥኡን እንድትጸድቅለት ብሎ ከዓለማዊው የሰው ሥርዐትና ልማድ ተለይ ይልሃል:: ተለይ ማለቱም በአእምሮህ መታደስ ከመንፈስ ሁለተኛ እንድትወለድና በዓለም ጨለማ የሚኖሩ ወንድሞችህንም÷ የወንጌሉን ብርሃን እያበራህላቸው በመከራቸው ሁሉ ተካፋይ ሁነህ እንድትረዳቸው ማለት ነው እንጂ÷ <u>እንደ ሀገሬ መነኩሴዎች ከዓለም ተለይተናል ብለው÷ ማር በሚገኝበት ዱር (ጫካ) ተቀምጠው÷ ሥራ ጠልተው÷ ተዘግተው÷ ሰውን ሳይረዱና በሕግ (በጋብቻ) ሕፃናት ሳይወልዱ የሥጋቸውን ምኞት ይዘው÷ መክሊታቸውን ቀብረውና በዓለም ዘንድ ከብረው እንደሚኖሩት አይምሰልህ::</u> ለሐዋርያት የነገራቸው ቃሉ ግን «ናሁ አነ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማእከለ ተኩላት::» «እነሆ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ::» ማለቱ የሰው ተኩላ የሆነ ኃጥእን እያስተማሩ ወደ ንስሓ እንዲመልሱ ነው እንጂ÷ እንደ ንባቡ የዱር አራዊት ጠብቁ÷ አሰማሩ÷ በጫካና በጎርጎሮ (በጕራንጕሩ) ስፈሩ÷ ለኃጥእ ነፍስም የወንጌልን ምሥራች እንዳትነግሩ ተሸሸጋችሁ ኑሩ ያላቸው አይምሰልህ፤ ማቴ. 10÷16-42:: የክርስቶስ ጸሎትና ትእዛዝ ግን «ቅዱስ አባቴ ሆይ! ከክፋ ትጠብቃቸው ዘንድ እንጂ÷ ከዓለም ታወጣቸው ዘንድ አለምንህም:: አንተ ወደ ዓለም እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ ወደ ዓለም ላክኋቸው::» ዮሐ. 17÷1-26:: «ወይቤሎሙ ሑሩ ውስተ ኵሉ ዓለም÷ ወስብኩ ወንጌለ ለኵሉ ፍጥረት::» «እንዲህም አላቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ::» ይህ ብቻ ነው ትእዛዙ ማር. 16÷15-20:: የጋን መብራት ለማንም አይጠቅምም:: ጨውም አልጫ ከሆነ በድንጋይ ወይም በካብ ሥራ ስለማይጠቅም ስሙ ከንቱ ይባላል፤ ማቴ. 5÷13-16፤ ሉቃ. 14÷35::

አሁን ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ብትፈልግ÷ መግቢያው ምክሩን ሰምተህ ትእዛዙንና ሕጉን ፈጽመህ ስታበቃ÷ «የክርስቶስ ወዳጅና ተከታይ ነኝ፤ ከዓለምና ከሰው ሥርዐት÷ ከአሮጌ ልማድም ጋራ ምን አንድነት አለኝ፤» ብለህ ክርስቶስን ለመከተል በቁርጠኛው ኅሊናህ ቃል ወንጌሉን ሰምተህ ለማድረግ

ብትለይ፥ ለርሱ ብቻ ብትታዘዝ፥ ለክርስቶስ እንደ እናቱ ወንድሙና እህቱ ለመሆን የበቃህ ትሆናለህ፤ ማቴ. 12፥47-50::

ክርስቶስን ለመከተል ብትፈልግ ግን አስቀድመህ እርሱ የሄደበትን ፍኖተ መስቀል (የመከራ ጎዳና) መገንዘብ አለብህ:: «በዓለም ውስጥ መከራ ያገኛችኋል፤ ያስሯችኋል፤ ይገርፏችኋል፤ ያሳድዷችኋል፤ ይገድሏችኋል ከመስጊዳቸውም (ከምኩራባቸውም) ያወጡአችኋል::» ማቴ. 10፥1-39፤ ዮሐ. 16፥1-33፤ «በክርስቶስ ማመን ብቻ አይበቃችሁም፤ በስሙ ምክንያት ደግሞ መከራ ልትቀበሉ ይገባችኋል::» ፊልጵ. 1፥27-30 «እኔ በክርስቶስ ሃይማኖት እኖራለሁ የሚል ሰው እንዳለ ክርስቶስ በሄደበት አሰር (ኮቴ ዱካ) ሊከተለው ይገባዋል::» 1ዮሐ. 2፥1-6:: ይህንን ቃሉን ስንቅና መሣሪያ አድርገህ፥ የሚያገኝህን ፈተና በትዕግሥትና በጸሎት ድል ነሥተህ ብትከተለው ግን፥ እርሱ በሚኖርበት በየማነ አብ (በአብ ቀኝ) ለዘለዓለም በደስታና ክብር ትኖራለህ፤ ዮሐ. 17፥20-26፤ ራእ. 3፥1-22::

ወንድሜ ሆይ! ዛሬ በኃላፊው ዓለም ሳለህ የርሱን ትእዛዝ ብቻ ለመፈጸም የክርስቶስ ተከታይ (ወገኑ) ለመሆን፥ በአካሄድህና በኑሮህ ካልታየህ፥ በሚመጣው ዓለም ምን በመሰለ ዘዴ ከጻድቃን ጋራ ትተባበራለህ? ዛሬ እርሱ ባዘዘው መንገድ ስትመላለስ ካላየህ ነገ ወደ ቤቱ አስገባኝ ብትለው፥ አንተ ዓመፀኛ ከቶ አላውቅህም ባይ መሆኑን ለማወቅ ብትሻ ማቴዎስን ጠይቀው 7፥21-23:: እርሱ በአምሳሉ ፈጥሮ የኔ ነህ ብሎ ሠይሞ ኢሳ. 43፥1፤ በኪነ ጥበቡ እየመገበ እርሱን ብቻ እንድታመልክ አዝዞ፥ የኔ ልጅ የኔ ገንዘብ እያለህ፥ አንተ ግን እርሱን ትተህ ጌቶች ያልሆኑ ፍጡራንን፥ አንድ ጠብታ ውሃ ማዝነብ የማይችሉትን ኤር. 14፥22፤ ያድኑኛል፥ ይረዱኛል፥ ያማልዱኛል ብለህ ውሸትን አምነህ መኖርህ፥ ጣዖት ማምለክ ማለት እርሱ መሆኑን አስተውል:: ስለዚህ ከዛሬ ጀምረህ እዝነ ልቦናህን ለርሱ ሰጥተህ፥ የታዘዘውንና ያልታዘዘውን፥ የሚበላውንና የማይበላውን፥ የሚመለከውንና የማይመለከውን፥ እውነቱን ከሐሰት ፈጣሪን ከፍጡር በቅዱሳት መጻሕፍት ለይተህ ያዝ:: ከርሱ ጋር ብቻ ተጣበቅ፤ በስሙም ብቻ ማል፤ አማልከት ያልሆኑ ፍጡራንንና ልማድን አትመን፤ በስማቸውም ከቶ አትማል፤ ዘዳ. 12፥1-25፤ ኤር. 5፥7-14፤ ዘፀ. 23፥13::

ምዕራፍ 28

ስለ ልማድ

ወንድሜ አንባቢ ሆይ! የሀገራችንና የአባቶቻችን ሥርዐት (ሕግ) ቅዱስ ለሆነው ለአምላክ ትእዛዝ ተቃዋሚውና ተጻራሪው መሆኑን ልገልጽልህ እወዳለሁ:: ለምሳሌ እግዚአብሔር «በሐፈ ገጽከ ብላዕ» ብሎ ያዘዘውን የሀገሬ መሪዎች እነ መምሬ ልማድ ግን÷ «ዛሬ በዓል ነው አትሥሩ፤ ነገም ጾም ነው አትብሉ::» እያሉ ሕዝባችን እንደ አምላኩ ትእዛዝ ሠርቶ እንዳይበላ÷ እነ ቄስ ዓለማየሁ እና እነ መምሬ አታለለ÷ እነ የኔታ አሸብርና እነ አለቃ ጨቀኑን ተሰብስበው÷ ውግዘት በሚሉት የሽሪሪት ዘሃ አጥብቀው አስረው ይዘው÷ ወደ ፈለጉት ሲነዱትና ሲያዞሩት ይኖራሉ:: ዋናዎቹ ሥራ አስኪያጆችም አባ ልዋጥህና ግራ ጌታ ጣሰው ይባላሉ፤ ኢሳ. 59÷1-14፤ ኤር. 23÷9-32፤ ሕዝ. 13÷17-23፤ ሚክ. 3÷1-12፤ ማቴ. 23÷13-15፤ ፊልጵ. 3÷19::

ይህን በከንቱ ሐሰት የተደነገገብንን የሰው ሥርዐት ግዝት÷ ሊቁ የማነ ብርሃን ኣብራ ዓድዋ «አባ ልማድ ተዉ ፍቱ፤ በሥራ ላይ አትገዝቱ::» እያሉ ብዙ ጊዜ እየወቀሡ ሲጮኹበት ነበረ::

ወዳጄ አንባቢ ሆይ! ይህን የሰው ሥርዐት ግዝት እጠብቃለሁ ስትል ግን÷ ትልቅ ዋጋ ያለውን የአምላክህን ትእዛዝ አፍራሽ ሆነህ እንዳትገኝ ተጠንቅቀህ ማሰብ ያስፈልጋሃል፤ ማቴ. 15÷1-9:: ሐዋርያትን በዘመናቸው የነበሩት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን (ካህናተ ኦሪት) የክርስቶስን ትእዛዝ ትታችሁ÷ እኛ ያዘዝነውንና የደነገግነውን÷ ያወገዝነውንና ያቆምነውን የኛን ልማድ ጠብቁ ስላሉአቸው÷ «ወተሰጥዎሙ ጴጥሮስ ምስለ ሐዋርያት ወይቤሎሙ ይኄይስነ ናድሉ ለእግዚአብሔር እምነ አድልዎ ለሰብእ::» «ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ፤ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል::» የሐዋ. ሥራ 4÷19-21፤ 5÷20-29::

እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን ልንሰማ የሚገባ እንደሆነ እስኪ እናንተ ፍረዱ! እኛስ አይሆንልንም የእምላካችንን ትእዛዝ ብቻ ካልሆነ የሰውን ሕግና አርጌ ልማድ ከቶ ምንም ቢሆን አንጠብቅም ስላሉ÷ በዋሾው ዓለም ዘንድ እየተጠሉ÷ በምጣድ መከራ እየተቈሉ÷ እየታሰሩ÷ እየተገረፉ÷ በእደ አሕዛብ እየተሰየፉ÷ በአፈ አራዊት እየተበሉ÷ የዓለም ጉድፍና መሳቂያ÷ የአማረውያን መዘበቻና መሳለቂያ ሆነው ስለ ስሙና ትእዛዙ እየተዋረዱ÷ በአፈ

አንበሳ ወተኩላት እየታረዱ፥ ሕይወታቸውን መንነው (ንቀው) ሰጥተው፥ ዋሾውን ድል ስለነሡት፥ በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው የሕይወት ዛፍ እየተመገቡ ዐዲስ ስም የተጻፈበት ነጭ ደንጊያ ሉል ተቀብለው በእጃቸው ጨብጠው ይዘው ለዘለዓለም ነግሠው በደስታ ይኖራሉ፤ ዳን. 6፥10-17፤ 12፥3፤ ዕብ. 11፥1-40፤ 1ጴጥ. 5፥4፤ 2ጢሞ. 4፥8፤ ራእ. 2፥7-17።

ወዳጄ ሆይ! እነዚህ ደጋጎች ሰዎች ጸድቀው ያጸድቁኛል እኔ ሳልሠራ ሳልደክም የታዘዝሁትን ሳልፈጽም ፲ ቃላተ ኦሪትንና ፮ ቃላተ ወንጌልን ሳልጠብቅ፥ በእነርሱ ድካም ገነትን የአንድን ጻድቅ ስም አንሥቼ፥ ጓደኞቼንና አበ ንስሓዬን ጠርቼ፥ ጠላ ከጠጣሁ እነርሱ ካሉበት እገባለሁ ማለትህ የልማድና የንቀት ቀልድ ነው፤ ኤር. 3፥20።

በዚያው ሀገርስ አንተ ያልቋጠርኸውን ስንቅ ዘርፎ ነጥቆ እንደ መብላት መሰለህን? ኋላ ጸጸት፥ ሥቃይና ረኃብ እንዳትመገብ «ኢትዝግቡ ለክሙ መዛግብተ ውስተ ምድር፤ ዝግቡ ለክሙ መዛግብተ ውስተ ሰማያት ኀበ ኢያማስኖ ፀፄ ወኢቍንቍኔ፤ ኀበ ሀሎ መዝገብከ ህየ ይሄሉ ልብከኒ።» «ብልና ዝገት በሚያጠፉት፥ ሌቦች ቈፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ። ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት፥ ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ። መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።» ማቴ.6፥19-21 የሚለውን እውነተኛውን ቃል ሰምተህ፥ እነማንን ጠርቶ ማብላትና ማጠጣት እንደሚገባ ሉቃስን በወንጌሉ ጠይቀው፤ 14፥12።

ዛሬም የሚገባህን የነፍስህን ስንቅ አንተው ራስህ ቋጥረህ መያዝ ያስፈልግሀል (ይገባሃል) እንጂ፥ በውሸትና ልማድ እነ አባ ሆይ እገሌ ፥ እነ እማ ሆይ እገሊት ከጽድቃቸው ይተርፉኛል ወይም ያበድሩኛል ብለህ፥ እነርሱን <u>«ሀባነ እምቅብእክን» «ከዘይታችሁ ስጡን» ብትላቸው፥ «ኢያአክለነ ለነ፥ ወለክን» «ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ»</u> የሚሉ መሆናቸውን አስተውል፤ ማቴ. 25፥1-13።

ከክርስቶስ አዳራሽ ውስጥ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሕግ አፍራሽ ሰው ስለተገኘ፥ ባለቤቱ ክርስቶስ ለይቶ ከማዕድ ጎትቶ አውጥቶ ወደ ዘለዓለማዊ ጨለማ ሲጥለው፥ ከዚያ ሁሉ ጻድቅ አንድ ባለሚል አማልዶ ከእስራትና ሥቃይ ሊያድነው የቻለና የሚችል ከቶ አልተገኘም፤ ማቴ. 22፥1-14። የገነት በር ከተዘጋብህ በኋላ «እግዚኦ አርኅወነ» «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ክፈትልን» እያልክ ብትለፈልፍ፥ ከቶ የሚሰማህና የሚረዳህ ከጻድቃኖቹም አማልዶ በር

የሚያስከፍትልህ አንድ ፍጡር አይገኝም። ስለዚህ ምግብህ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ብቻ እንዳይሆን፥ ዛሬ አሮጌውን ልማድ ትተህ ዐዲሱን የአምላክ ትእዛዝ ቃለ ወንጌሉን ብቻ ሰምተህ፥ የሚገባህን ካልሠራህ ሌላ የስርቆሽ መግቢያ በር ምንም አታገኝም። በሩን ትቶ በሌላ የሚገባ ሌባና ወንበዴ ነው፤ ዮሐ. 10፥1-9።

ፍጡራን ጽድቅ ሊያካፍሉህ ይቅርና በሲኦል ገብተህ ስትቃጠል እያዩህ እንኳን፥ የጉሮሮ ማቀዝቀዣ የሚሆን አንድ ጠብታ ውሃም ሊሰጡህ አይቻላቸውም፤ ሉቃ. 16፥23-31። እውነተኛ ፈራጅና ጻድቅ፥ ጽድቃችንም የሆነው ጌታ ክርስቶስ ኤር. 33፥16፤ ባዘዘው የጽድቅ ሕግ ልትሔድ ብትፈልግ ግን፥ ጻድቃን በሄዱበት በጠባቡ መንገድ በፍኖተ መስቀል እነርሱን መስለህ ብትከተላቸው፥ ለነርሱ የተሰጣቸው ጸጋና ክብር ላንተም እንደነርሱ ልክ ይሰጥሃል። ቀኝና ግራ ሳትል ጉዞህን ቀጥል እንጂ ሳታገለግል ደመወዝ ብትመኝ በከንቱ ነፋስ እንደ መጨበጥ ማለት ነው፤ ዘዳ. 5፥32፤ መክ. 11፥6-10፤ ሉቃ. 9፥23- 27፤ ዕብ. 13፥7-16፤ ራእ. 7፥13-17።

ወዳጄ ሆይ! እንኳን ለኗሪው ለነፍስ የሚሆን ትልቁን ነገር ልታገኝ ቀርቶ፥ ለዚህ ለሚበሰብሰውና ለሚፈርሰው ኃላፊው የሥጋህ መኖሪያስ ቢሆን፥ አንድ ቀንና ሰዓት ሳትደክምበትና ሳታስብበት በከንቱ በሰው ድካም ኩርማን እንጀራና ጽዋ ውሃ ቀምሰህ ታውቅ ይሆን? ምንም ቢነግሡና ቢጸጽሱ ለአንዲት የጤፍ ፍሬም ብትሆን፥ ያለ ሐሳብና ድካም ሊያገኛት የሚችል አንድ ፍጡር ከቶ አይገኝም። ስለዚህ ሰው ለድካም ተወልዷልና የአምላክህን ትእዛዝ ለመፈጸምና ገነት ለመግባት ብትፈልግ አንተው መሥራትና መድከም ይገባሃል፤ ኢዮ. 5፥6-27፤ መክ. 1፥13።

አንተ በምትሄድበት ሀገር በሲኦል ሥራ አይገኝምና እጅህ ታገኘው ዘንድ የምትችለውን የጽድቅ ሥራ ሁሉ ተግተህ ዛሬ ሥራው፤ መክ. 9፥10።

አሁን ግን የጽድቅ ፍሬ በሙሉ እንኳ ባትሠራ ያቅምህን ያህል ግን የግድ መሥራት አለብህ። ሌላው ሁሉ ቀርቶ አንተ ነጋ መሸም በፈጣሪዬ ፊት ምን ይዤ እቆማለሁ? ከቶ ምን ይፈረድብኝ ይሆን? ኀጢአቴ እጅግ ብዙ ነው፥ ምን ባደርግ፥ ምን ብሠራ ስርየት አገኝ ይሆን? እያልክ መድኃኒትህን ለማግኘት፥ በክፉው ሥራህ እየተጸጸትህ ብትጨነቅ፥ «እመን ልጄ ሆይ ኃጢአትህ ቀረችልህ። በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እመን በኢየሱስ ክርስቶስ ወተሐዩ አንተ ወኵሉ ቤትከ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ።» ማቴ. 9፥1-8፤

የሐዋ. ሥራ 16፥26-31 የሚል የምሥራች አምላካዊ ድምፅ በእዝነ ልቡናህ ትሰማለህ። በኋላ ግን ሁል ጊዜ በኃጢአትህ መጸጸት፥ ማዘን፥ መፍራት፥ መጸለይ ይገባሃል። ጽድቅን ያህል ታላቅ ነገር በኢየሱስ ቊስል ካልሆነ በቀር፥ እንኳን በሰዎች ድካም ዓለምን በሞላዋ ሰጥተህም ቢሆን አንዲት ነፍስ ለማዳን ከቶ አይቻልም፤ ሉቃ. 9፥23-27፤ ኢሳ. 53፥1-12፤ 1ጴጥ. 2፥21-25።

ወንድሜ ሆይ! በጠባቡ በጽድቅ ጎዳና አባቶችህ ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት በሄዱበት መንገድ አሰራቸውን ይዘህ ልትከተላቸው ብትፈልግ፥ ጌታ ከእነርሱ ጋር የተዋዋላቸውን የመከራ ሹመትና ውል መገንዘብ ይገባሃል። «ናሁ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማእከለ ተኲላት፤ ወያወጽኡ ለክሙ ስመ እኩየ፤ ወትከውኑ ጽሉኣነ በእንተ ስምየ፤ አነሰ ወሀብክሞሙ ቃልየ ወዓለምሰ ጸልኦሙ፤ ዘለባዕለ ቤት በብዔል ዜቡል ይቤልዎ እፎ እንከ ፈድፋደ ለሰብአ ቤቱ፤ ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ ሰላመ እደይ ውስተ ምድር አላ መጥባሕተ ወፀሩ ለሰብእ ሰብአ ቤቱ።» «እነሆ እኔ እንደ በጎች በተኲላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ክፉ ስም ያወጡላችኋል፤ በሁሉ ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው። ባለቤቱን 'አጋንንትን የሚያወጣው በብዔል ዜቡል ነው' ካሉት፥ ቤተሰዎቹንማ ከዚህ የበለጠ እንዴት አይሏቸው? በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፥ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም፤ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል።» የሚለውን የመሳሰለውንም ሁሉ ነውና አክሊለ ጽድቅ የሚያሰጡ ቃላት መሆናቸውን አስቀድመህ መገንዘብ አለብህ፤ ማቴ. 10፥1-42፤ ሉቃ. 10፥1-24፤ 12፥1-12።

«ኢትኩኑ ድንዙዛነ ወተመሰልዎሙ ለእለ በአሚን ወበትዕግሥት ወረሱ ተስፋሆሙ። ወንትልዎ ለፍጹም መልአክነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ዘተዐገሠ ኀፍረተ መስቀል አናኀሲዮ በእንተ ፍሥሐሁ ዘጽኑሕ ሎቱ።» «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፤ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን፥ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል የታገሠውን ኢየሱስን እንከተለው።» የሚሉትን ቃላት፥ ዘወትር እያሰብህ እነርሱን ብትመስል እነርሱ ካሉበት ትደርሳለህ፤ ዮሐ. 17፥21-26፤ ዕብ. 6፥12፤ 12፥1-29። አማላጄ፥ አዳኜ፥ ጌታዬ፥ ዋሴ፥ ጠበቃዬ ኢየሱስ ብቻ ነው እያልክ በልብህ አምነህ በአፍህ ብታስታውቅ (ብትመሰክር) ሮሜ 10፥9-13፥ የእነ መምሬ ልማድ ተማሪ ዋሾው ዓለም፥ ይህ ሰው አብዷል፥ ጋኔን

ይዞታል፥ ሃይማኖት ለውጧል እያለ መዘባበቻና መሳለቂያ እንደሚያደርግህ ጥርጥር አይግባህ:: ይልቁንስ ዓለም መልካም ቢናገርልህ ወዮልህ! ሉቃ. 6÷26፤ ዮሐ. 8÷48-52፤ 1ቆሮ. 4÷10-13፤ ሉቃ. 6÷8-38::

ስለዚህ እንደዚህ የመሰለው ክፉ ስምና የስድብ ቃላት ሁሉ የክርስቲያን ጌጥና ሽልማት፥ ዕድልና ፈንታ መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ መስተዋትና መነጽር አስተውለህ አይተህ፥ አሮጌውን ልማድ በዐዲስ ሕይወት፥ የማይጠቅምህንም ሐሰት በእውነተኛው ቃለ ወንጌሉ ለውጠህ (ለይተህ)፥ ለኔ ነው የተጻፈው ብለህ፥ ከዚህ ክፉ ዓለም በሰይፈ ቃሉ ሐሳብህን ቈርጠህ (ወስነህ) ክርስቶስን ለመከተል ካልተለየህ፥ እግዚአብሔርን የካደ፥ መናፍቅ፥ የማርያምና የጻድቃን ጠላት ተብለህ ካልተሰደብህ፥ እንደ ጌታ በዓለም ዘንድ ፈጽመህ ካልተጠላህ 1ዮሐ. 2÷6፤ ቅዱሳን፥ ጻድቃን ሰማዕታትን መስለህ እውነተኛውን የክርስቲያን ገድል ካልተጋደልህ፥ መንግሥተ ሰማያት በዋዛ፥ በዋንጫ ጠላና አጭበርባሪነት፥ በተዝካርና ፍትሐት፥ በልማድና በሰው ሥርዐት ምንም ቢሆን አትገኝም፤ ማቴ. 7÷13-23::

አስቀድመህ ግን «ወእመኒ መስተጋድል ኢይከውኖ ምዝጋና እምዘበሕጉ ኢተጋደለ::» 2ጢሞ. 2÷5፤ «ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም::» «ወእምከመሰ ዐሪይን ሕማመ፥ ንዔሪ ክብረ ምስሌሁ::» «አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል፥ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን::» ሮሜ 8÷17 «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ይገባናል::» የሐዋ. ሥራ 14÷22፤ «በዓለም መከራ ያገኛችኋል፤ ነገር ግን ጽኑ! እኔ ዓለምን እንደአሸንፍኋት እናንተም ዲያብሎስን ተዋግታችሁ ድል ካደረጋችሁት፥ ከታላቅ መከራ የመጡ ናቸው ተብላችሁ ከኔ ጋራ ለዘለዓለም በሰማይ ትነግሣላችሁ::» የሚሉትን ቃላት መገንዘብ ይገባሃል፤ ዮሐ. 16÷33፤ ራእ. 7÷13-17::

ወዳጄ ሆይ! በእውነት ሊድን የሚፈልግ የጽድቅ ረኃብ ማቴ5÷6 በሕሊናህ ውስጥና በልብህ ጽላት ተቀርጾ ካለ የሁሉንም ትተህ «ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ::» «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» ዮሐ.2÷5 የሚለውን ቍርጠኛ የማርያም ድንግልን ምክር አጽንተህ ያዝ:: ትእዛዙን ካልፈጸምህ ግን፥ ገነትን ታላቁን ነገር በበሩ በየሉስ ስም ነው እንጂ፥ በአማላጅና በሰው ሥርዐት፥ በልማድና በስርቆሽ በር ከቶና አካቶ ሊገቡበት የማይቻል የነፋስ ዘገን ሐሳብ ነው፤

ማቴ. 7÷21፤ ሉቃ. 3÷7-9፤ ዮሐ. 10÷1-10፤ ገላ. 5÷13-26፤ 1ዮሐ. 2÷1-12::

ነፍስ ያለ ሥጋ ዓሣም ያለ ውሃ ቁመው ሊኖሩ እንደማይችሉ÷ እንደዚሁም ሃይማኖት ያለ ምግባር ምግባርም ያለ ሃይማኖት የሞተ ነው እንጂ ሕያው ወይም ህልው ተብሎ ሊነገር አይቻልም:: ስለዚህ ልማድ በሚባል የሐሰት ጽድቅ ራስህን እያታለልህ ከመኖር÷ «ግበሩ እንከ ፍሬ ዘይደልወክሙ ለንስሐ ወኲሉ ዕፀ ዘይፈሪ ሠናየ ፍሬ ይገዝምዎ ወውስተ እሳት ይወድይዎ::» «እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ . . . መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል::» ሉቃ. 3÷3-9 የሚለውን የመጥምቁ ዮሐንስን ምክር በሳጥን ልብህ ውስጥ አጥብቀህ ያዘው:: መጻሕፍት ግበሩ÷ ግበሩ÷ ግበሩ (አድርጉ÷ አድርጉ÷ አድርጉ) «እስመ አንተ ትፈድዮ ለኲሉ በከመ ምግባሩ» «አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳን ትሰጣለህና::» ይላሉ እንጂ÷ «በከመ ተዝካሩ» (እንደ መታሰቢያው) ወይም «በከመ ገብሩ ሎቱ» (እንዳደረጉለት) አይሉም፤ መዝ. 62÷12:: ለነፍስህ አንተ ካልሠራህላት አትጸድቅም፤ ራስህ ካልበላህ በስተቀር ሌላው በበላው አትጠግብም:: እምነትህና ጽድቅህ በኢየሱስ ምግባር ካልሆነ ከቶ በሌላ አይገኝም፤ አይጸደቅም:: በሰው ምግባር እንደማትጸድቅ የተረዳህ ሁን:: አንተው ዛሬ ለነፍስህ ማጽደቂያ የሚሆንህን መልካሙን የጽድቅ ፍሬ ዝራ፤ ሰው የዘራውን ብቻ እንደሚያጭድም አስተውል፤ ገላ. 6÷7-9::

«ይጠቅመኛል÷ ይረባኛል ብዬ ይዤው የነበረውን የአባቶቼን ሥርዐትና ልማድ ሁሉንም ፍሬ (ጥቅም) አጣሁበትና ስለ ክርስቶስ ብዬ እንደ ጉድፍ ጠራርጌ ጣልሁት::» የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ማድመጥና መከተል ይገባናል፤ ፊልጵ. 3÷3-11:: ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ «ኢይትከሃሎ ለሰብእ ይኩን ተአማኔ÷ እመ ኢያግሐሰ ርእሶ እምልማድ÷ ሐዲገ ልማድሰ ጽኑዕ ውእቱ::» «ሰው በልማድ መኖርን ካልተወ በቀር÷ ታማኝ ይሆን ዘንድ አይቻለውም፤ ልማድን መተውም አስቸጋሪ ነው::» ብሏል:: ልማድን ብተው አበ ነፍሴ ይጠሉኛል እንዳትል ግን÷ አባቶችህ÷ ለነፍስ÷ አባቷ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ስለተረዱ «ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አበ ነፍስየ አንተ::» «ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ÷ የነፍስ አባቴ አንተ ነህ እኮ!» ብለውታልና የልማድ ምርኮኛ እንዳትሆን ተጠንቀቅ:: መል. ኢየሱስ ለመላትሒክ ተመልከት:: መድኃኒታችን አባትና እናቱን ያልተወና ያልጠላ ሲል ልማዳቸውን ነው እንጂ ሀገራቸውን አይደለም፤ ሉቃ. 14÷25-27::

አስተውል አስተዋይ ልቦና ይስጥህ አሜን::

ምዕራፍ 29

ስለ ስግደት

ስግደት ወይም ሰጊድ ማለት የፈጣሪና ፍጡር÷ የጌታና ሎሌ÷ የገዢና ተገዢ÷ የሚያመልክና ተመላኪ ልዩነታቸውና አኗኗራቸው የሚታወቅበት ሥልጣን÷ ሕግ ወይም ትእዛዝ ነው፤ ዘፍ. 2÷15-16:: ይህ ስግደት ግን ለአምላክ የብቻው የባሕርይ ገንዘቡ ስለሆነ ከቶ ለሌላ አይሰጥም፤ ዘፀ. 20÷1-17፤ ማቴ. 4÷10::

አምላካችን ይህን አምልኮና ስግደት ለሌላ ለሥዕልና ምስል÷ ወይም ለማናቸውም ፍጡርም ቢሆን እንደማይገባና እንዳንሰግድም በጣቱ ጽፎ አስጠንቅቆ ሲያዝዘን (ሲከለክለን)÷ «ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ÷ ወኢትግበር ለከ ሥዕለ ወአምሳለ÷ ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ እስመ አነ ወእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ቀናኢ ወእሳት በላዒ::» «ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ፤ የማናቸውንም ምሳሌ÷ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፤. . . እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና አትስገድላቸው÷ አታምልካቸውም::» እያለ ከፍ ባለና ግርማ ባለው በሚያንቀጠቅጥ ድምፀ ቃሉ ዐውጆልናል፤ ዘዳ. 4÷15-21፤ 5÷6-9::

ወንድሜ ሆይ! ሰውን ያህል በአምላክ አርአያና አምሳል የተፈጠረው ትልቁ የፍጡራን ንጉሥ÷ በእጁ ዕንጨት ጠርቦና ደንጊያ አለዝቦ÷ ቀለም በጥብጦ ለሐሳቡ የሚስማማውን ሥዕል ሥሎ÷ ለማይሰማውና ለማይጠቅመው በከንቱ መስገዱ ጣዖትን ማምለኩ አይደለምን? ከሁሉ የከፋ ከንቱ የሆነ አሮጌው የጣዖት ልማድ ደግሞ÷ በሚጸለይበት ቦታ የማያድን «ሥዕለ አድኅኖ» እየተባለ÷ የማያሸተውን ዕጣን እያጠነለት ሕዝብ ተሰብስቦ የጸሎት ሐሳቡን በምድር ባለውና ራሱ በፈጠረው ሥዕልና ምስል ተስፋ አድርጎ መወሰኑ ነው:: «ሰብእሰ እንዘ ንጉሥ ወእቱ ኢያእመረ÷ አሕሰረ ርእሶ÷ ወአንደየ ነፍሶ በፈቃዱ÷ ወመለክም እለ ኢኮኑ አጋዕዝተ::» «ሰው ግን ንጉሥ ሲሆን አላወቀም፤ ራሱን አዋረደ፤ ነፍሱንም በፈቃዱ ድኻ አደረገ፤ ጌቶች ያልሆኑትም ገዙት::» ይላል ቅዳሴ አትናቴዎስ 1÷20-29::

«ኀሱራንኬ እሙንቱ ወበውስተ ምግባርኒ ምዉታን ተስፋሆሙ እለ ጸውዑ ግብረ እደ ሰብእ አማልክተ ዘእምወርቅ ወብሩር ገብርዎሙ በተኬንዎ ዘኢይበቍዕ ግብረ እድ ዘትካት ወእመኒ ቦ ጸራቢ ዘይጸርብ ዕፀ ዘሠናየ ሠረፀ ወፀረበ በሥነ ኪኑ ኵሉ ቅርፍቶ ወገብሮ ዘይበቍዕ ንዋየ ለመልእክተ ሕይወት::

ወገብረ ሎቱ ዘይደሉ ቤተ ዘውቅሮ፡፡ ወውስተ አረፍት አጥበቆ ወአጽንዖ በኀጺን ወአስተሐመመ ቦቱ ከመ ኢይደቅ እእሚሮ ከመ ኢይክል ረዲአ ርእሶ ወያስተበቍዕ ኀቤሁ በእንተ ጥሪቱ ወብእሲቱ ወውሉዱ ወኢየኀፍር እንዘ ይትናገር ምስለ ዘአልቦቱ ነፍስ፡፡ ወበእንተ ሕይወቱኒ ምውተ ይስእል ወያስተበቍዕ ኀበ ዘአልቦቱ አእምሮ፡፡» «እነርሳቸውስ ጐስቋሎች ናቸው፤ የሰውን እጅ ሥራ፥ በሥራ መራቀቅ ከብርና ከወርቅ የሠሯቸውን አማልክት ብለው ያመሰገኑ የእነዚህ በሥራም አለኝታቸው አላፊ ነው፡፡ . . . የቆመውን የተጋደመውን ዕንጨት የሚጠርብ ጠራቢ ቢኖር፥ በጎ ሆኖ የበቀለውን ዕንጨት ቈርጦ ቅርፊቱን ሁሉ ጠርቦታልና፡፡ በጎ አድርጎ ተራቆበታልና ለኑሮ አገልጋይ ሲሆን የሚረባ ዕቃን አድርጎ ሠርቶታልና፤. . . ለእሱ የሚገባው ተመትቶ የተሠራ ቤት ሠራ፤ በሠራለት ቦታ አኖረው፤ ከኖራው አስጠግቶ በብረት ቸነከረው፤ ምስል ነውና የሚረዳው ይፈልጋልና፥ ራሱን መርዳት እንዳይችል ዐውቆ እንዳይወድቅበት አስተነተነ፡፡ እንደዚህ አድርጎ ሠርቶ በእርሱ ዘንድ ስለ ገንዘቡ፥ ስለ ሚስቱ፥ ስለ ከልጆቹ ይለምናል፤ ነፍስ ከሌለው ከጣኦቱ ጋር ሲነጋገር አያፍርም፡፡ . . . ስለ ሕይወትም ምዉት ጣኦትን ይለምናል፤ አእምሮ ከሌለው ከጣኦቱ ዘንድ የንብረትን ነገር ይማልዳል፤ ይለምናል፡፡» ጥበብ 13፥10-19፡፡ ወንድሜ ሆይ! ይኸውልህ አስተውል፤ ልብ በል፤ መርምር፡፡

እግዚአብሔር በሐሳብ ፈጥራችሁ ለግብረ እድ ከቶ እንዳትሰግዱ ቢለንም፥ ያገራችን እልኸና ባህል ግን ለማናቸውም ይሁን፥ ደብተራ በጥበቡ ሥሎ ስም ሠይሞ ለሰጠንና በሰው እጅ ለሚሠራው ሁሉ፥ በጸጋ መስገድ ይገባል የሚሉት ነገር አለ፡፡ አምላካችን ግን ይህን አምልኮ ጣዖት፥ <u>«ኢትግበር ለከ ሥዕለ ወአምሳለ፥ ኢበአምሳለ ብእሲ፥ ወኢበአምሳለ ብእሲት ኢትስግድ ሎሙ፥ ወኢታምልኮሙ፤ ወኢትስግድ ለአምላክ ነኪር፤ እቀንእኒ በዘኢኮነ አምላከ ወአምዕዑኒ በአማልክቲሆሙ፡፡» «የተቀረጸውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ በወንድ ወይም በሴት መልክ የተሠራውን . . . ለግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትስት ተጠንቀቅ፤ . . . ለባዕድ አምላክም አትስገድ፤. . . አምላክ ባልሆነው አስቀኑኝ፤ በምናምንቴዎቻቸውም አስቈጡኝ፡፡»</u> ዘዳ. 4፥15-23፤ 32፥21 እያለ በምርና በቍርጥ ከልክሎአል፤ በቅንአትም ያስቈጣዋል፤ ተቈጥቶም ዝም ብሎ ለጊዜው ቢታገሥ፥ ዛሬ ቃሉን ሰምተህ በንስሓ ወደ እርሱ ካልተመለስህ የእምቢተኞች ዋጋ ምን መሆኑን ሮሜ 2፥10-16፤ 2ጴጥ. ምዕራፍ 2ን አንብበህ ተረዳ፡፡

ወዳጄ አንባቢ ሆይ! ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ታላቁ ነገር ስጊድ የአምላክ የባሕርይ ገንዘቡ ስለሆነ፥ እንኳን ፍጡር ለፈጠረው

ለአላፊው ምናምን ይቅርና፥ ለሕያዋኑ ረቂቃን መላእክትም ቢሆን ባሮቹ ስለሆኑ፥ ሰጊድ እንደማይገባቸውና ቢሰግዱላቸውም እንደሚያስቈጣቸው ራእየ ዮሐንስ 19፥5-10 እና 22፥7-9 ብታነብ እንደኔ ትረታለህ፤ አምላካችን በቃሉ «ኢይሁብ ክብርየ ለባዕድ፥ ወስብሐትየ ለግልፎ።» «ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።» ብሏል፤ ኢሳ. 42፥8።

ለታቦት ወይም ለንዋየ ቅድሳት በጸጋ መስገድ ይገባል ማለት ግን በፍጹም ሐሰትና ስሕተት ነው። «ጸገወ» «ሰጠ» ብሎ «ጸጋ» ሲል «ስጦታ» ማለት ነው። ስለዚህ ጸጋዊ (ሰጭ) ሰው ሲሆን፥ ስጊድን ተጸጋዊ (ተቀባይ) ያው በሰው እጅ በመጋዝና ምሳር ሲቈረጥና ሲጠረብ አመመኝ የማይል፥ ሕይወት የሌለው ምዉት ነገር ስለሆነ፥ ትልቁን የአምላክ ገንዘብ ስጊድን ቢሰጡት አያመሰግንም፥ ቢነሡትም (ቢከለክሉትም) አይቈጣምና የልማድ ስሕተት ወይም አእምሮ ማጣት አለማፈር ያልነው ስለዚህ ነው፤ ኤር. 2፥27-28፤ 6፥15፤

ከማይነቅዝ ዕንጨት ተመርጦ፥ ከዱር ከጫካ ተቈርጦ በሰው እጅ የተጠረበው ታቦት (ሣጥን) እንኳንና ሰውን ሊያድን በአምላክ እጅ ተጽፎ ሙሴ የተቀበለው ጽላትም ቢሆን፥ ሕዝበ እስራኤል ሕጉን ስለአፈረሱበት አምላክ ተቈጥቶ ሠላሳ ሺህ የሚሆኑ ወታደሮችን ለጠላት ሰይፍ አሳልፎ ሰጣቸው፤ የሚመኩበትም ታቦት ጭምር በፍልስጥኤማውያን እጅ ተማርኮ ሄደ እንጂ ከቶ ሊያድናቸው አልተቻለውም፤ 1ሳሙ. 4፥1-11።

በሕገ ኦሪትም ታቦትን እግዚአብሔር ትእዛዙን በደንጊያ (ጽላት) ላይ ጽፎ ከሕዝቡ ጋራ የተዋዋለበት ዘፀ. 31፥18፤ ዘዳ. 31፥26 (ውል ፊርማ)፥ ክቡር ቃሉ የሚኖርበት ሳጥን ማኅደር ስለሆነና እግዚአብሔርም ወደ እርሱ መጥቶ በላዩ ተቀምጦ የሚናገራቸው ስለ ነበረ አከበሩት እንጂ ሕይወት አለው ይሰማናል ብለው ከቶ አልሰገዱለትም፤ ዘፀ. 20፥24-25፤ 16-22። ለምሳሌ አንድ ሰው ፈረስ በቅሎ ወይም መኪና ላይ ተቀምጦ ሳለ እጅ ቢነሡለት ወይም ቢሰግዱለት ስግደቱ ለዐዋቂው ለሰውየው ነው እንጂ ለበሃማኑ (ለዲዳዎቹ) እንስሶችና ለብረቱ እንዳይደለ ማስተዋልና መለየት ይገባናል፤ ኤር. 15፥19።

ሰው ሆይ! እኛ በአምላክ መልክ ተፈጥረን፥ በአምላካዊ ሕይወት እየተንቀሳቀስን የምንኖር የሐዋርያት ልጆች ስንሆን፥ በሰው ብልሃት የተሠራው ወርቅና ብር፥ ዕንጨትና ድንጋይ ማናቸውም ይሁን ሕይወት የሌለውን ሰው ሠራሽ ሁሉ፥ እኛ ሕያዋን ልናከብረውና ልንሰግድለት፥ ልንጠጋበትና ልንታመንበት

ከቶ እንደማይገባን ሊያውቅ የሚፈልግ ሰው እንዳለ፥ ያባቶቹን የሐዋርያትን መጽሐፍ ተመልከቶ አሰራቸውን ይከተል ዘንድ ይገባዋል፤ የሐዋ. ሥራ 17፥22-31።

ግዙፋን መመኪያ ግን ጌዴዎን የኢዮአስ ልጅ ሰብሮት በተከሰሰበት ጊዜ ለሙግቱ «ራሱ መልስ ይስጥበት።» ተብሎ ተፈረደና በእጅ ከተሠራው ነገር አንድም መልስ ስላልተገኘ፥ ከሳሾቹም አፍረው እንደተበተኑ መጽሐፍ ይናገራልና መመልከት ነው፤ መሳ. 6፥25-33። ታቦት ግን እንኳን ሰውን ሊጠቅምና ሊያድን፥ ሙሴ ተቈጥቶ በጣዖት (የወርቅ ጥጃ) ላይ ሲጥለው ሁለቱም ግብረ እድ ስለሆኑ ተያይዘው ዶቄት ሆነው ጠፉ እንጂ ራሳቸውን ሊያድኑ አልቻሉም። በኋላም እስራኤል ለግብረ እደ ሰብእ (ለሰው እጅ ሥራ) ስለ ሰገዱ ቀናተኛው አምላክ ተቈጥቶ በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች በወንድሞቻቸው ሰይፍ ታረዱ፤ ዘፀ. 32፥1-35።

ሆኖም ዛሬ በዘመነ ሐዲስ ታቦት እንደማያስፈልግና እንደማይደረግም ነቢያት አስቀድመው ተናግረውለታል። «ናሁ ይመጽእ መዋዕል ይቤ እግዚአብሔር፤ እወዲ ሕግየ ውስተ ልቦሙ ወእጽሕፎ ውስተ ኅሊናሆሙ።» ሕዝ. 11፥19። «በዚያ ዘመን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት አይሉም፤ በልባቸውም የለም፤ አያስቡትም፤ አይሹትም፤ ደግሞም አይደረግም።» ኤር. 3፥11-17። «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ።» ምሳ.23፥26፤ «ቃሌንም በልብህ እሰራት።» ምሳ. 6፥20-23፤ «አባብላታለሁ፤ ወደ ልብዋም እናገራለሁ።» ሆሴ. 2፥16፤ ድኅነተ ነፍስን ለሚፈልጉ ግን ቃሉን በልብ ካልጠበቁ በአፍ ከቶ ሊገኝ አይቻልም፤ ማቴ. 19፥16-22፤ ዘሌ. 18፥5።

ወንድሜ ሆይ! በዘመነ ሐዲስ ግን ሰው ፈጽሞ የእግዚአብሔር መቅደስና ታቦት ሆኖ እንዲኖር፥ ቃለ እግዚአብሔር በደንጊያ ተጽፎ በአፍአ ሳይሆን በሰው ኅሊናና ልብ ሊያድር እንደሚገባ፥ «ኢተአምሩኑ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ፥ ወመንፈስ እግዚአብሔር ሳዕሌክሙ።» «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?» 1ቆር. 3፥16። «ኢታአምሩኑ ከመ ማኅደሩ ለመንፈስ ቅዱስ አንትሙ።» «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት፥ በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?» 6፥19 «እስመ አንተ ውስጡ ለሰብእ የኀድር ክርስቶስ በሃይማኖት ውስተ ልብክሙ በተፋቅሮ።» «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ፥

ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር::» ኤፌ. 3÷17:: እያለ ሐዋርያው ጳውሎስ አስረድቷል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም÷ «አንድ የሚወደኝ ሰው ቢኖር ቃሌን ይጠብቃልና÷ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን::» ዮሐ. 14÷23 ብሏል:: እግዚአብሔር ግን ራሱ በሠራው በሰው ልብ ይኖራል÷ ያድራል እንጂ ሰው በሠራው በታቦትና በሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እንደማያድር «በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋራ በምድር ላይ ይቀመጣልን? እነሆ ሰማይ የሰማያትም ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም::» 2ዜና. 6÷18፤ «ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ እናንተ የምትሠሩልኝ÷ እኔ የማርፍበትስ ቤት እንዴት የሚሰፋና ምን የመሰለ ነው?» ኢሳ.66÷1:: «እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና÷ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ ከቶ አይኖርም:: የሰው እጅም አያገለግለውም::» የሐዋ. ሥራ 7÷46-50፤ 17÷14-30:: እናንተ የሐዲስ ኪዳን ልጆች በሕያው አምላክ መንፈስ እንጂ በቀለም ያልተጻፈች÷ በልብ ሥጋ ነው እንጂ በዕንጨት ወይም በደንጊያ ጽላት ያልሆነች÷ የክርስቶስ ደብዳቤ መሆናችሁ በሁሉም ዘንድ የተገለጸ ነው ተብሏል፤ 2ቆሮ. 3÷1-11::

ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ሥዕልና ምስልን÷ ዕንጨትና ደንጊያን÷ በወርቅና ብር ወይም በማናቸውም ቢሆን በግብረ እደ ሰብእ (በሰው እጅ) ተሠርቶ ፍጡር ለፈጠረው ሁሉ እንኳን ሊሰግዱለት÷ የከንቱ ከንቱ ሕይወት የሌለው ምዉት መሆኑን በብዙ ስፍራ እንደዚህ እያሉ እየነቀፉት ያስረዳሉ:: «እያእመሩ መላእክት እለ ይገልፍዎ ለዕፅ÷ ወይጼልዩ ኀቤሁ ከመ ኀበ አማልክት እለ ኢያድኅኑ::» «የተቀረጸውን የምስላቸውን ዕንጨት የሚሸከሙና ያድን ዘንድ ወደማይችል አምላክ የሚጸልዩ ዕውቀት የላቸውም::» ኢሳ. 45÷18-25:: <u>«የአሕዛብ ሕግ ከንቱ ነው÷ ሰነፎች ሆኑ፤ ሁሉም ደናቁርት፤ ከንቱ የመሆናቸው ትምህርትም አምልኳቸው ከዱር (ደን) ተቆርጦ በተጠረበ ዕንጨት መሆኑ ነው::»</u> ኤር. 10÷1-15:: «ይትኃፈሩ ኵሎሙ እለ ይገብሩ አማልክተ ወይገልፉ ዘኢይበቍዖሙ በኀበ ተገብሩ ይየብሱ::» «የተቀረጸውን ምስል የሚሠሩ ሁሉ ከንቱዎች ናቸው፤ የወደዱትም ነገር አይረባቸውም፤ ምስክሮቻቸውም አያዩም÷ አያውቁም፤ ስለዚህ ያፍራሉ::» ኢሳ. 44÷8-20፤ <u>«ወይሰክምዎ ዲበ መትከፍቶሙ÷ ወየሐውሩ፤ ወእመኒ አውየዉ ኀቤሁ ኢይሰምዕ÷ ወኢያድኅን ርእሶ እምእኩይ::» «በጫንቃቸው ላይ አንሥተው ይሸከሙታል፤ በስፍራም ያደርጉታል፤ በዚያም ይቆማል፤ ከስፍራውም ፈቀቅ አይልም፤ ሰውም ወደ እርሱ ቢጮህ አይሰማውም፤ ከመከራውም</u>

አያድነውም፡፡» ኢሳ. 46፥1-9፤ «ወከንቶ ኮነ ዝሙታ፥ ወዘመወት በዕፀው ወበአእባን፤. . . ኢትትመሀሩ ፍኖተ አረማውያን፥ እስመ ከንቱ ውእቱ ሕገ አሕዛብ እስመ ዕፀ ዘገዘሙ እምገዳም፥ ግብረ እደ ጸራቢ በምሳር፡፡» «ከዳተኛይቱ እስራኤል ያደረገችውን አየህን? ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ፥ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች፤ በዚያም ገለሞተች፡፡ . . . የአሕዛብን መንገድ አትማሩ፤ ከሰማይ ምልክትም አትፍሩ፤ አሕዛብ ይፈሩታልና፥ የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፥ ዛፍ ከዱር ይቈረጣል፤ በሠራተኛም እጅ በመጥረቢያ ይሠራል፡፡» ኤር. 3፥6፤ ኤር. 10፥1-15፡፡

«ከመ ኀፍረተ ሠራቂ ሶበ ይእኀዝዎ ከማሁ የኀፍሩ ደቂቀ እስራኤል፥ እሙንቱኒ ወነገሥቶሙ፥ ወመላእክቲሆሙኒ ወካህናቲሆሙ፥ ወነቢያቲሆሙኒ፤ እስመ ይቤልዎ ለዕፅ አቡነ አንተ፥ ወለእብንኒ አንተ ወለድከነ፥ ወሜጡ ዘባኖሙ ኀቤየ፥ ወአኮ ገጾሙ፡፡» «ሌባ በተያዘ ጊዜ እንደሚያፍር እንዲሁ የእስራኤል ቤት እነርሱና ንጉሦቻቸውም፥ አለቆቻቸውም ካህናቶቻቸውም፥ ነቢያቶቻቸውም ያፍራሉ፤ ግንዱን አንተ አባቴ ነህ፥ ድንጋዩንም አንተ ወለድኸኝ ይላሉ፡፡ ፊታቸውንም ሳይሆን ጀርባቸውን ሰጡኝ፡፡» ኤር. 2፥5-28፡፡ «ምንተ ይበቍዕ ግልፎ ዘገለፉ፥ ወሰበኩ ወገብሩ ሐሰተ ምትሐተ ዐይን ወይትአመኖ ገባሪሁ፥ በዘለሊሁ ገብረ ከመ ይግበር ጣዖተ በሃመ፥ አሌ ሎ ለዘይቤሎ ለዕፅ ንቃሕ ወተንሥእ ወይቤሎ ለእብን ተለዓል፥ ወውእቱሂ ሐሰት ወይገብርዎ በወርቅ ወበብሩር፥ ወአልቦ ነፍስ፡፡» «የተቀረጸውን ምስል ሠሪው የቀረጸው ለምን ጥቅም ነው? ዲዳንም ጣዖት ይሠራ ዘንድ ሠሪው የታመነበቱ፥ ሐሰትን የሚያስተምር ቀልጦ የተሠራ ምን ይጠቅማል? ዕንጨቱን ንቃ፥ ዲዳንም ድንጋይ ተነሣ ለሚለው ወዮለት! በውኑ ይህ ያስተምራልን? እነሆ በወርቅና በብር ተለብጧል፥ ምንም እስትንፋስ የለበትም፡፡» ዕንባ. 2፥18-20፤ «ይትኀፈሩ ኵሎሙ እለ ይሰግዱ ለግልፎ፥ ወእለ ይትሜክሑ በአማልክቲሆሙ፡፡» «ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ሁሉ፥ በጣዖቶቻቸውም የሚመኩ ይፈሩ፡፡» መዝ. 97፥7፤ «ወመልአት ምድሮሙ ጣዖቶሙ ዘገብሩ በእደዊሆሙ፥ ወሰገዱ ለዘገብሩ በአጻብዒሆሙ፡፡» «ምድራቸው ደግሞ በጣዖታት ተሞልታለች፤ ጣቶቻቸውም ላደረጉት ለእጃቸው ሥራ ይሰግዳሉ፡፡» ኢሳ. 2፥8 «ተመይጡ ውስተ ኃጢአተ አበዊሆሙ ዘቀዲሙ እለ አበዩ ሰሚዐ ቃልየ፥ ወናሁ እሙንቱ የሐውሩ ወይተልዉ አማልክተ ነኪር ከመ ይትቀነዩ ሎሙ፤ ወይጸርሑ ኀበ አማልክቲሆሙ እለ የዐጥኑ ሎሙ፥ ወኢያድኅንዎሙ አመ ምንዳቤሆሙ፡፡» «ቃሌንም ይሰሙ ዘንድ እንቢ ወዳሉ ወደ አባቶቻቸው ኃጢአት ተመለሱ፤

ያመልኳቸውም ዘንድ እንግዶችን አማልክት ተከተሉ፤ .... ወደሚያጥኑላቸው አማልክት ይጮሃሉ፤ ነገር ግን በመከራቸው ጊዜ ከቶ አያድኑአቸውም።» ኤር. 11÷10-12።

የተወደድህ ወንድሜ ሆይ! ስግድ የሚገባው አምላካችን ምሉእ በኵለሄ÷ ረቂቅ÷ የሚታመን መንፈስ እንጂ ግዙፍ÷ የሚታይና የሚጨበጥ አይደለም፤ የሚሰገድለትም በእውነትና በመንፈስ እንዲሆን ስላዘዘ÷ እርሱም እንደዚህ ያሉትን ሰጋድያን ይወዳል፤ ዮሐ. 4÷19-25። አሁን ግን አንተ በግምባርህና በጉልበትህ ለሠሪህ ለፈጣሪህ ብቻ በኢየሱስ ስም ካልሆነ÷ ከቶ ለፍጡርና ፍጡር ለፈጠረው ለከንቱ ጣዖት ስግድን ብትሰጥ ፈንታህ የዘለዓለም ፍርድ (ገሃነም) መሆኑን አስተውል። «የዚያን ጊዜ ኢየሱስ አለው፡ - አንተ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና ከኔ ራቅ አለው።» ዘዳ. 5÷6-9፤ ማቴ. 4÷10፤ አምልኮ ስግድ ለሌላ ይገባል የሚሉህን ግን አትስማቸው አትስገድላቸውም ዘዳ. 13÷1-18።

ሥዕልን በቀለም ጨርቅ ወይም ወረቀትና ብራና ላይ ሥሎ÷ ምስልንም ዕንጨት ጠርቦና ደንጋይ አለዝቦ ጠቢብ ሰው የሠራውን÷ ምዉቱንና ሕይወት የሌለውን ነገር÷ ሕይወት ያለው ክቡሩ ሰው በከንቱ ማክበሩና ለእርሱም መስገዱ ዐይኑ እያየ በፈቃዱ ወደ ሲኦል መውረዱ መሆኑን ትንቢተ ሕዝቅኤል 8ኛ÷ 9ኛ እና 16ኛ ምዕራፍ ተመልከት።

ሕያው አምላካችን ሲያዝን ግን «እንዳትስቱ የተወቀረ የተጠረበም ጣዖት÷ ሥዕልና ምሳሌ÷ የወንድ ወይም የሴት መልክ አድርጋችሁ ከቶ እንዳትሰግዱና እንዳታመልኩ።» ይላል፤ ዘዳ. 4÷12-29፤ 5÷1-9።

«ማናቸውንም ነገር በእጅህ ሠርተህ÷ የሰው÷ የእንስሳ መልክና ምሳሌ አቁመህ ከቶ እንዳትሰግድለትና እንዳታመልከው።» ብሎ አዝዟል። የፊተኞቹ አባቶቻችን ይህንኑ ቃል ተገንዝበው «ኢርኢነ÷ ወኢሰማዕነ÷ ወኢነገሩነ አበዊነ ከመ ቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌከ፤ ይትኀፈሩ ወይኅሠሩ ኵሎሙ እለ ይሰግዱ ለግልፎ÷ ወእለ ይትሜክሑ በአማልክቲሆሙ፤ ነፍስነሰ ትሴፎ በእግዚአብሔር አምላክነ፤ አምላክነሰ ኃይልነ ወጸወንነ÷ አምላከ አሕዛብ ዕብነ ወዕፀ ኪነት ኢኮነ።» «በዐይኖቻችን አላየንም÷ በጆሮቻችንም አልሰማንም÷ አባቶቻችንም ከአንተ በቀር ሌላ ባዕድ አምላክ እንዳለ አልነገሩንም÷ ለጣዖት የሚሰግዱ ሁሉ÷ በአማልክቶቻቸውም የሚመኩ ይፈሩ÷ ይጐስቍሉም፤ ነፍሳችን ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ትታመናለች፤ አምላካችን ኀይላችንና

መጠጊያችን ነው፤ እንደ አሕዛብ አምላክ ድንጋይና በእጅ ጥበብ የተሠራ ዕንጨት አይደለም::» እያሉ አቄዩን:: የኂለኞቹ ደግሞ አምላካዊውን ቃል አፍራሽና ተቃዋሚ የሚሆነውን÷ «አምላክ ስለ አከበራቸው ለሁለቱ ፍጡራን (ማርያምና መስቀልን) ሰጊድ ይገባቸዋል::» ብለው አንጻርና ተቃራኒ የሆነ የድፍረት ቃል ጽፈዋል፤ ተአ. ማርያም ምዕ. 24:: ይገርማል! ማርያምንና መስቀልን ሰጋጁ እንደመረጠውና እንደመሰለው ንድፍ÷ በየአንጥረኛ ው ቤት አሠርቶ÷ መስሎ÷ አቁሞ መሳምና መስገድ ይገባል ማለት በውል ለተመለከተው ትልቅ ሐሰትና ስሕተት ነው:: እንኳን ለመስቀሉ ለተሰቀለው የክርስቶስ ሥዕልም ቢሆን አስመስለውና ፈጥረው በእጅ የሠሩት ስለሆነ መስገድ÷ መታመንና መጠጋት ግን እንደ ጣዖት የሚገመት ግዙፍ መመኪያ መስሎ እንዳይቈጠርብን መጠንቀቅና ማሰብ÷ መጻሕፍትንም ትክ አድርጎ መመልከትና ማስተንተን ይገባናል፤ ዘሌ. 19÷1-4፤ ዘዳ. 4÷1-28፤ 5÷6-9::

ረቂቁ አምላክ ግን በመንፈሳዊ ዐይን ካልሆነ በግዙፉ በሥጋዊ ዐይን ከቶ የማይወሰን መንፈስ ሲሆን÷ ሰጋጆቹም መንፈሳውያን ሊሆኑና ስግደታቸውም በእውነትና በመንፈስም ሊሆንና ሊደረግ ይገባል:: የመስቀሉ ምሳሌ ለኛ ጠቃሚ ከሆነማ የጦሩና የችንካሮቹ ምሳሌስ ስለምን ተረሳ? እስቲ በውል እናስብበትና አስፈላጊና ጠቃሚ ከሆነ ችንካሮቹንና ጦሩን÷ ዘንጉንና ገመዱን÷ ጅራፉንና የእሾህ ዘውዱን ሁሉንም ሥራ እንድናስይዛቸው ማኅበርተኞቹን ሳላሳስባቸው አላልፍም:: «አገሬ ኢትየጵያ ሆይ ለአንተ የሠራሃቸው አምላኮችህ ወዴት ናቸው? እስቲ ይነሡና በመከራህ ጊዜ ይርዱህ፤ ወገኔ ግን በማይረቡት ነገሮች ክብሩን ለወጠ::» ኤር. 2÷1-28፤ «ሕዝቤ የምንዝርና መንፈስ አስቶታልና በትሩን ጠየቀ፤ እስቲ ዕንጨቱ መልስ ይስጠው::» ሆሴ. 4÷6-14:: «ወገኔ ክፉ ለመሥራት ብልሃተኞች መልካም ለመሥራት ግን ሰነፎች ናቸው::» ኤር. 4÷24::

በእጅ የሠሩት ነገር ታማኝና ጠቃሚ ከሆነማ÷ ፍልስጥዔማውያን ይረዳናል ወይም ያድነናል ብለው የሚመኩበት÷ የፈጠሩት አምላካቸው እንኳን የሚያመልኩትን ሊያድን ይቅርና÷ ራሱንም ሊጠብቅና ሊያድን ስለአልቻለ÷ በአሸዋ ላይ ለተመሠረተው ግዛቱ በአምላክ እጅ የተጻፈው የእውነት ቃል አስደንግጦት እጅና እግሩ ተለያይቶ÷ ቁልቁል አፉ በግምባሩ ተደፍቶ÷ ተሰብሮ÷ ወድቆ ተገኘ እንጂ÷ እውነተኛውን የሕይወት ቃል ተቃውሞ ሐሰታዊ መንግሥቱን ሊያቆም ከቶ አልተቻለውም፤ 1ሳሙ. 5÷1-12፤ ኤር. 10÷1-16::

ወንድሞቼ ሆይ! ይህ እኛ የሐዲስ ኪዳን ልጆች የምንኖርበት የሕይወት ቃል ደግሞ፥ ጠቃሚነቱ በሰው ሕይወትና ኅሊና ቢጻፍ እንጂ እኛ በፈጠርነው በዕንጨትና ድንጋይ ተጽፎ ሲያድነንና ጥቅም ሊሰጠን እንደማይችል ሲያስረዳን: - «እነሆ ዘመን ይመጣል ይላል እግዚአብሔር፥ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋራ አዲስ ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ ከሰውነታቸውም የደንጊያ ልብ አውጥቼ የሥጋን ልብ ሰጥቼ ሕጌን በልባቸውና በኅሊናቸው እጽፈዋለሁ::» ብሏል፤ ኤር. 31÷31-36፤ ሕዝ. 11÷16-20::

ጌታም በወንጌሉ «መንፈስ ነው ሕይወትን የሚሰጥ እንጂ ግዙፉ ሥጋ ምንም አይጠቅምም::» ብሎ እንደሚያስተምረን መታመናችን በረቂቁ መንፈስ እንዲሆን፥ ግዙፉን ፍጡር ከነፍጥረቱ እንዳንመካበትም ሲያስጠነቅቀን ነውና ሰው የእግዚአብሔር መቅደስና ታቦት መሆኑን ሁልጊዜ አንርሳ፤ ኤር. 9÷23-24፤ ዮሐ. 6÷63፤ 1ቆሮ. 3÷16፤ 6÷15-20::

ፈጣሪን ትቶ ፍጡርን ወይም ማናቸውንም የግብረ እድ ነገር ማመንና ማምለክ ግን፥ ኢየሩሳሌምን ብዙ ብዙ ጊዜ «ዘማ፥ ዘማዊት፥ ከዳተኛ፥ ዐመፀኛ፥ ሴሰኛ፥ ነውረኛ» እያሰኘ ያስነቀፋትና ያስጸየፋት፥ የቃል ኪዳን ባልዋ የሆነውን እግዚአብሔርን ትታ፥ የአረማውያን ምዉታን አማልክት ውሽሞችን ለምዳ፥ መሥዋዕት ይዛ እየሄደች ስለ ሰገደችላቸው ነው፤ ኢሳ. 57÷3-13፤ ኤር. 2÷1-37፤ 44÷1-30፤ ሕዝ. 16÷1-63፤ 23÷1-49፤ ሆሴ. 1÷1-25::

ወንድሜ ሆይ! በአገራችን ልማድ ምንም እንኳን አብያተ ክርስቲያናቱ ቤተ እግዚአብሔር መባላቸው ቀርቶ፥ የሙታን የፍጡራን ስም ተሰጥቶአቸው ቢሰየሙም ያለ ዕውቀት የተደረገ ስሕተት ስለሆነ፥ አንተ ግን የምታመልከውና የምትሰግድለት በሰማይ ሆኖ ለዘለዓለም ሲቀደስና ሲሠለስ የሚኖረው አንዱ ሕያው አምላክ ብቻ መሆኑን፥ ቤቱም አንተ መሆንህን አስተውል:: ስጊድን ለባለ ገንዘቡ ለፈጠረህ አምላክ ካልሆነ ከቶ ለሌላ እንደማይገባውና እንደማይሰጥም ሠለስቱ ደቂቅንና ዳንኤልን ጠይቃቸው፤ ዳን. 3÷1-30፤ 61-28፤ 1ቆሮ. 3÷16::

ዐመፀኛው የአዳም ልጅ ያማረውንና የመሰለውንም ሁሉ በእጁ ሠርቶ መስገዱ ግን፥ አሮን የወርቅ ጥጃ ከሠራበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የአምላክ ሕግ አፍራሽነቱና እምቢተኛነቱ ከባሕርዩ እንዳልተለየው ያስረዳናል:: ለዚህም ዐዋቂዎች አታልለው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በሲሚንቶ አሳምረው ሠርተው፥ በ1941 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ አምጥተውና «ማርያም ፋጢማ» የሚባል ስም ሰጥተው፥ የዋሁ የአገሬ ሕዝብ ዐዲሷ ማርያምን በማየት ተደንቆ

ከኪሱና ከአንገቱ፥ ከጆሮና ከጣቱ ወርቅ አውልቆ እንደጣለላትና ማተብና ማርዳም እንዳሠራላት አይተናል።

«ሥዕልና ምስል ሠርተህ ከቶ አትስገድ፤ በእጃቸው ለሠሩት በመስገዳቸው አሳዘኑኝ።» የሚል እውነተኛው አምላክ ግን በዚህ ነገር ተቈጥቶ በሃምዋ (ዲዳዋ) ሸክላ እንኳን የሚሰግዱላትን ልታድናቸው፥ ከአሥመራ አንሥተው ወደ ሕንድ አገር የዋሆችን ለማታለል በአይሮፕላን ጭነው ሲወስዷት፥ ንዋየ ዐመፃ የሚሰበስበው አገልጋይዋ (ቄሱ) ጭምር አደጋ አግኝቷቸው ሁሉም በእሳት ተቃጥለው ከሰማይ ረገፉ ሲባል ሰማን።

«እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክና የሚባላ እሳት ነኝ።» የሚል እውነተኛው ቃሉ በዚህ ጊዜ ስለ ተፈጸመ ክብርና ምስጋና ይግባው አሜን፤ ዘዳ. 4፥23-27።

ጳውሎስ የሮም ካቶሊኮችን፥ «አምላክን በረቂቅነቱ አምኖ ማምለክን ትተው፥ በሚጠፋ በሰው መልክ ምሳሌና ሥዕል ሠርተው ስለ ሰገዱ፥ ቀናተኛው አምላክ አዝኖ ሥጋቸውን በርኵሰት ሊያጐሰቍሉና ሐሰትን የሚያምኑ እስኪሆኑ ድረስ ብርቱ ለሆነ የፈቃድ ስሕተት አሳልፎ ሰጣቸው።» ይላል፤ ሮሜ 1፥19-28። አዳማውያን በዐመፀኝነታቸው ብዛትና በሥራቸውም ክፋት፥ አምላክ ሰውን በመፍጠሩ ከሐዘንና ጭንቀት ውስጥ አግብተው እንደ አስመረሩትና መሐሪነቱንም ወደ ጭከና ለውጠው፥ መዓትን ፈቅደው አምጥተው በእምቢተኛነታቸው ራሳቸውን እንዳጠፉ አንድ ሊቅ በሚከተለው ቅኔ ገልጾልናል፤ ዘፍ.6፥1-6።

<u>መወድስ</u>

ስድስተ ዕለተ እንበለ አጽርኦ
ሐሤቶ ፈጸመ አምላከ ሙሴ መስፍን
እምድኅረ ዝኒ ነበረ እንዘ የሐዝን
እምጣነ ልሕኵቶ ቀዳሜ ኵሉ
ዐለወ ሕገ እንቲአሁ በብዙኀ ተምያን
ወእንዘ የሐዝን በአዳም
ዘመነ ማየ አይኅ አልጸቀ በዓለ ብዙኀ ተስናን
አጽሐብምዊ በደብረ ሲና ሕዝበ ምናሴ ወዳን
እንዘ ለግብረ እድ ይትቀነዩ ዘተፈጥረ እምአርን
ባሕቱ ለዮድ ባሕረ ትዕግሥት ወዛኅን
አድባረ አበሳ ኢይከብዶ እንተ በመዳልው ኢይትሜጠን

ትርጓሜ፡ - «የመስፍን ሙሴ አምላክ ያለማስታጐል በስድስት ቀን ውስጥ ደስታውን ፈጸመ፤ ከዚህ በኋላ ግን እያዘነ ኖረ፤

ከሁሉ በፊት ቀዳሚ የሆነው ሸክላው (አዳም) በብዙ ተንኰል ሕጉን አፍርሷልና:: በአዳም እያዘነ ሲኖርም የብዙ ጠብ በዓል የጥፋት ውሃ ዘመን ደረሰ፤ በአሮን የተፈጠረ (የተሠራ) የሰው እጅ ሥራ ለሆነው (ጣዖት) ሲገዙ፥ በደብረ ሲና የምናሴና የዳን ወገኖች አደከሙት፤ የትዕግሥትና የጸጥታ ባሕር ለሆነው ለአምላክ ግን በሚዛን የማይለካ የበደል ተራራ አይከብደውም::»

አ.ገ.ሥ (ዓድዋ)

ወንድሜ ሆይ! እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህና ነፍስህ በፍጹምም ሐሳብህና ኀሊናህ ውደድ፤ ማቴ. 22÷35-40:: ልብህም የአምላክ መቅደስ ነውና ንጹሕ ቅዱስ አድርገህ ያዘው፤ 1ቆሮ. 3÷16፤ ሃይማኖትህንም በምግባርህ ግለጸው፤ ያዕ. 2÷14-26:: ሰውን ሁሉ አፍቅር፤ መልካም ለመሥራት ትጋ፤ አትታክት፤ ገላ. 6÷1-9:: ሰጊድን ለሌላ እንዳትሰጥ ተጠንቀቅ፤ አንዲት ሃይማኖት፥ አንዲት ጥምቀት፥ አንድ ጌታን ብቻ አጽንተህ ያዝ፤ ኤፌ. 4÷5-6:: ወዳጄ ሆይ! ጣዖትን ከማምለክ ሽሽ 1ቆሮ. 10÷14-33፤ ከጣዖታት ተጠበቅ 1ዮሐ. 6÷18-21::

መንፈስ ቅዱስ የጸጋውን ብርሃን ይግለጽልን አሜን::

ምዕራፍ 30

አድራጊ ማድረጊያ ተደራጊ

በአገራችን በስሕተትና በልማድ ፍጡር ለፈጠረው ግብረ እድ ይሰገድለታል። ይኸውም ከንዋየ ቅድሳት ሁሉ በላይ ታቦት ነው። ይህ ታቦት ማለት ግን በዐዋቂ ተመርጦ፥ ከዱር ተቆርጦ መጥቶ፥ ሕዝብ በዋጋ ተስማምቶ፥ ዐናጢ ጠርቦ አበጅቶ፥ ሰው ተሸክሞ ወደ መቅደስ የሚያገባው ዛፍ፥ ዋንዛ፥ ኵሐ፥ ኮሶ፥ ዝግባ፥ ሲሐም፥ ዶቅማ፥ ዞጲ፥ ቅላቱ ያማረና የለሰለሰ የማይንቀዝ ዕንጨት ነው። ይህ ዕንጨት ግን ሥጋሁ ወደሙ የሚቀመጥበት የጠረጴዛ መንበር ወይም ሰደቃ ነው እንጂ፥ ሌላ ነገር ያልሆነ ያው አምላክ በዝናቡ አብቅሎ ያሳደገው የዱር ዕንጨት ነው፤ ኢሳ. 44፥9-20፤ ኤር. 10፥1-20።

መሪዎቻችን ግን የእገሌ አገር ታቦት ትልቅ ሥራ ሠርቷል፥ ተአምራት አሳይቷል፥ ስጊድ ይገባዋል ይላሉ፤ በገንዘባቸው ገዝተው የዕንጨት፥ የብረት፥ የወርቅ መስቀል አሠርተውም ሕይወት የሌለውን ምዉቱን ነገር ሕያዋን ሊስሙትና ሊሰግዱለትም ይገባል ይላሉ፤ ዘፀ. 32፥1-8። ምን ይህ ብቻ ሕዝባችን ገምቦውን ግምጃ አልብሶ ለጠመቀው ጠላ ሳይቀር ይሰግዳል።

የአዳምን ሕይወት ለማዳን የቻለው በመስቀል ላይ የፈሰሰውና መለኮታዊ ሕይወት ያለው ክቡር የክርስቶስ ደም ነው እንጂ መሰቀያው ደረቁ ዕንጨት አይደለም። አድራጊ ማድረጊያ ተደራጊ የተሰቀለውንና መስቀያውን ለይቶ ማወቅ ይገባል። ለምሳሌ በየቤታችን የምንሰቅለውን ሥጋ ቋንጣውን ብቻ እንበላለን እንጂ መስቀያውን ሕይወት ስለ ሌለው አይበላም፤ በልተነውም አናውቅም።

መስቀሉ፥ ታቦቱና ንዋየ ቅድሳቱ፥ ብዙ ተአምራት አሳይተዋል ቢሉም እውነት ነው፤ እግዚአብሔር አምላካችን እስራኤልን ከግብጽ ሲያወጣቸውና ታላቁን ባሕረ ኤርትራንም ከፍሎ ሲያሻግራቸው በበትረ ሙሴ ተአምራት አድርጎ ነው፤ ዘፀ. 4፥1-17፤ 14፥1-31። እንኳን ሕያዋን በያዙት ማድረጊያ ምዉቱ የነኤልሳዕ ዐጥንትም ከመቃብር ውስጥ ሆኖ ምዉት አንሥቶ ተአምራት አሳይቷል፤ 2ነገ. 13፥20-21። ሶምሶንም በደረቀው አጥንት (በአህያ መንጋጋ) ሺህ ሰው ገድሎ ጠላቶቹን ድል ነሥቷል፤ መሳ. 15፥14-20። የነ ጳውሎስን የልብሳቸውን

ቁራጭና ጥላቸውንም በድዉያን ላይ ቢያኖሩት በሽተኞችን እያዳነ ብዙ ተአምራት አሳይቷል፤ የሐዋ. ሥራ 5÷15፤ 19÷12።

ይህን ሁሉ ታላላቅ ተአምራት÷ ከዚህም የበለጠ ቢሠራ ግን÷ ምስጋናና ሰጊድ ለማይወሰነው መለኮትና ዘለዓለማዊ ኃይል ላለው ካልሆነ ለኃላፊውና ጠፊው ለማይጠቅመውም ዕንጨትና ዐጥንት÷ ብረትና አጽርቅት (ጨርቆች) መስጠት ከቶ የማይገባና አምላካችንን የሚያስቀናውና የሚያሳዝነው ክፉ ነገር ነው፤ ዘዳ. 32÷21፤ ኤር. 44÷8፤ ሕዝ. 16÷15-26።

በሀገራችን በዓድዋ ሲልቭስትሪ የተባለ ፈረንጅ በ1897 ዓ.ም የወፍጮ መኪና ለማበጀት ብሎ÷ የወንዙ የዓሰምን ውሃ ሽቅብ ለማውጣት ግምብ ሲገነባ የአገሬ ሰዎች እነ አቶ በጎ ሥራ አይወዱ ተሰብስበው÷ «ይህ ወንዝ የአባ ገሪማ ነው ተቈጥተው ያፈርሱብሃልና ባትሠራው ይሻልሃል።» አሉት እርሱም ፍጡራን ኃይል እንደሌላቸው ሲያስረዳ፡ - «አባ ገሪማ ድሮ የሞቱትን÷ የአገሬ መነኵሴ መች ውሃ ለመፍጠር ቻሉና ግምብም ለማፍረስ በቁ? ስንት ሺህ የሚሆን ኃይልና ወታደርስ ይኖራቸዋል? አትዋሹ ሠሪና አፍራሽ በሰማይ የሚኖረው አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ እኔ ሌላ የማውቀው ነገር የለኝም።» ብሎ ተናገራቸው፤ ኤር. 14÷22፤ ኢሳ. 44÷8።

ስለዚህ ሥራው በጥንካሬ ወይም በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ ያልተመሠረተና አምላክም ያልፈቀደው ስለሆነ÷ በሠኔ 25/1898 ዓ.ም በመርቆሬዎስ ቀን ብርቱ ዝናም ከምድራዊው ከአባ ገሪማ ሳይሆን÷ እርሱ እንዳለው ከሰማይ ዘንቦ ግምቡን አፈረሰበት። ሕዝባችን ግን ውሸቱን ለማጋነን ሲል ሐምሌ 17 በሚዘከሩበት ቀን አባ ገሪማ በተአምራት አፈረሱት እያለ ያወራል። በ25 በመርቆሬዎስ ቀን እንደ ፈረሰ ግን ጌታዬ የማነ ብርሃን አበራ ኪዳኑ (ዓድዋ) በተቀኙት ቅኔ ልንረዳው እንችላለን።

<u>**መወድስ**</u>

በመጽሔተ ማይ ርእይዎ ለመርቆሬዎስ
ጠቢባነ ጽርዕ ዘገብሩ በዓለ ተሐውሶ በማይ
ወእመ ሕፍነ ማይ ከልእዎ ለኢትዮጵያ ነዳይ
ወድቀ እመንበሩ ዘተሐንጸ በእብነ ህንደኬ ሰናዖር ዐቢይ
ርደተ ማየ አይኅ ከመ ይርአይ
መንጠላዕተ ማይ ዘሰፍሐ እደ ሰብአ ግብጽ ጠዋይ
ተወለጠዊ ጊዜ ዕረፍቱ ርእየተ መልክዑ ሠናይ
ለዝንቱ እብነ ህንደኬ ወለዝ ዕንቈ ባሕርይ
አምጣነ ጠፈሩ ዝናም ወመሠረቱ ቀላይ

ለዘገብረ ተአምረ መርቆሬዎስ በሰማይ፤

ትርጓሜ፡ - «በውሃ የመናወጥ በዓልን ያደረጉ የጽርዕ ጠቢባን በውሃ መስተዋትነት መርቆሬዎስን ተመለከቱት፤ ኢትዮጵያ ድኻን እፍኝ ውሃን በከለከሉት ጊዜም በሕንድ ደንጊያ የታነጸ ታላቁ ሰናዖር፤ ከመንበሩ ወደቀ፤ የጠማማው ግብጻዊ ሰው እጅ የዘረጋውን የውሃን መጋረጃ የጥፋት ውሃን አወራረድ ይመለከት ዘንድ፥ በሞቱ ጊዜም የዚህ የሕንድ ደንጊያ የዚህም ዕንቈ ባሕርይ ያማረው ደም ግባቱ ተለወጠ፤ መርቆሬዎስ በሰማይ ያደረገው ተአምር ባጡ ዝናም መሠረቱም የጠለቀ ነውና፡፡» ብለዋል፡፡

ሆኖም ታማኞች ቅዱሳን አገልጋዮች መሆናቸውን እንዲታመኑ ብሎ በእጃቸውና በሚዘከሩበት ቀንም ብዙ ተአምራት ቢሠራ፥ ሠሪው መለኮታዊ ሥልጣን ብቻ ሊመሰገን ይገባል እንጂ፥ እነርሱንስ ማድረጊያዎች ስለሆኑና የታዘዙትንም ተልከው ስለሚሠሩ «የታዘዛችሁትን ሁሉ በአደረጋችሁ ጊዜ እኛ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፤ ልንሠራው የሚገባንን ስለ ሠራን ምስጋና አይገባንም፡፡» እንዲሉ ታዘዋልና ለአድራጊ እንጂ ለማድረጊያስ ከቶ ምስጋና አይገባውም፤ ሉቃ. 17÷7-10፤ ሮሜ 15÷15-20፡፡

ዓለምን ከፈጠሩት ጀምረው እስኪያሳልፉት ድረስ አንድ ደቂቃ እንኳ ተአምራት ከመሥራት ቦዝነው የማያውቁት ሥላሴ ግን፥ ከ365 የዓመት ቀኖች ውስጥ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ተራ ቊጥር ደርሷቸው፥ ጥር ሰባት ቀን ባቢሎንን (ጥቅመ ሰናዖር) ያፈረሱበት ቀን ነው ተብሎ ይከበራሉ፡፡ «በኔ ተጣበቅ፥ እኔን ብቻ አምልክ፥ ፍራ፥ አክብር፡፡» የሚል ቃሉ እንዳይፈርስብን ለሥራውና ለመለኮቱ ሽሪክና ረዳት እንዳንጨምርበት መጠንቀቅ ይገባናል፤ ዘዳ. 10÷20፤ 32-12፡፡

አድራጊና ማድረጊያን ለይቶ የሚያውቅና ረቂቁን አምላክ ብቻም የሚያመልክና የሚታዘዝ አእምሮ ይስጠን፤ አሜን፡፡

ምዕራፍ 31

ጠቅላላው ማስረጃ

የተወደድህ አንባቢ ሆይ! ይህን በዚህ ከንቱ የከንቱ ከንቱ የተባለውን፥ በኀላፊው ዓለም ያለውን አግራምቢጥ የሆነ የሰው ልማድና ግዝት መጠበቁ አይገባህም፤ ስለምን ብትለኝ አምላክ ያላዘዘው ስለሆነ እልሃለሁ፤ ኤር. 23፥21-32፤ መክ. 12፥8።

አሁን ግን ኢዮብ፥ «እንደርሱ የሚያስተምር የለም፤ ከቶ አይገኝም።» ይለዋልና ፍሬ የማይገኝበትን የግዝት ተማሪ ከመሆን እውነቱን ከሐሰት መርምረህ ለይተህ የጽድቅ ዋጋ ያለው (የሚገኝበትን) እውነተኛውን ትምህርተ ወንጌል ብቻ አጥብቀህ ይዘህ የጻድቁ የአምላክ ተማሪ መሆን ይገባሃል፤ ኢዮ. 36፥22፤ 1ዮሐ. 2፥27። አምላክን ብቻ አማኝና ታዛዥ መሆን ግን የዘለዓለም ሕይወትን በእደ እምነትና ተስፋ ጨብጦ ይዞ ዐርፎና ተደስቶ መኖርን የሚያስገኝ መሆኑን የተረዳህ ሁን፤ ኢዩ. 2፥26-32፤ ማቴ. 23፥8-12፤ ዮሐ. 6፥43-63፤ 14፥26።

አሁንም «ዘአውገዘ በከንቱ ውጉዝ ውእቱ።» «በከንቱ ያወገዘ ራሱ ውጉዝ ነው።» እንደተባለው፥ ዋሾው ዓለም ቢጠላህና ቢነቅፍህም፥ «ስለ ስሜ ቢጠሏችሁና ቢያሳድዷችሁ፥ ክፉ ስም ቢያወጡባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔንም እንደጠላኝ ዕወቁ፤ ስለ ክርስቶስ ስም ቢላገዱባችሁም ክብር ያለበት የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ።» ሉቃ. 6፥20-38፤ ዮሐ. 15፥18፤ 1ጴጥ. 4፥14፤ የሚሉት ቃላት ለክርስቲያን ጌጡና ሽልማቱ፥ ምልክቱና ክብረቱ መሆኑን ሁልጊዜ በትዕግሥትና በደስታ እያሰብህ በዓለም ዘንድ እየተጠላህ አምላክህ ብቻ ያወገዘውንና የከለከለውን የሥጋ ፍሬ ገላ. 5፥19-21 ኃጣውእ ከቶ እንዳትነካና የዲያብሎስ ባርያ እንዳትሆን ዘወትር ነቅተህና ከዓለምና ከክፉ ምግባርዋ ሁሉ ተለይተህ መኖር ይገባሃል፤ 2ቆሮ. 6፥14-18፤ 1ጴጥ.5፥5-11። ወንጌል እውነተኛው ሃይማኖት፥ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አምነህ ለመመስከር ድፈርበት እንጂ አትፈርበት። ዋጋ ሰጭህ ክርስቶስ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር በክብር በመጣ ጊዜ፡ - «በእኔና በቃሌ ያፈረ፥ እኔም በክብር ስመጣ አሳፍረዋለሁ።» ሉቃ. 9፥26 ብሏልና፥ ዋጋህ ኀፍረትና ኀዘን ብቻ እንዳይሆን ተጠንቀቅ፤ ማቴ. 24፥43-51።

«መብራት (ሻማ) ሳይነድ አያበራም።» እንደሚሉ መምሬ ትግሬው አለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ፥ ክርስቲያን በእቶን መከራ

እየተመከረና እየተፈተነ÷ ለወንድሞቹ እውነተኛ ብርሃን ሆኖ ሊኖር ይገባዋል እንጂ÷ ስለአምላኩ ስለክርስቶስ ስም ሳይመሰክርና ሳያገለግል መንግሥተ ሰማያትን ሊያገኛት ይቅርና ሊያያትም አይችልም፤ ዘዳ. 8÷1-5፤ ዕብ. 12÷1-12::

ባለቤት ክርስቶስ ንጉሡ ቤቱን ከዘጋ በኋላ ክፈትልኝ ብትለው÷ ጨክኖ ቊርጥ ባለ ምላሽ «የኔውን ትእዛዝ ትተህ÷ የሰው ባህልና የሐሰት አምልኮ÷ የፈጠራና የግዝት ልማድ ነው ስትጠብቅ የነበረው፤ አላውቅህም፤ ከቶም አላስገባህም እንዳይልህ ዛሬ የጸጋ መከር ሳያልፍብህ÷ በጸሎት ነቅተህ በንጽሕና ተግተህ÷ ማሰሮ (ልብህን) ዘይት (ፍቅር) ሞልተህ መብራትህን ሁልጊዜ አብርተህ÷ መክሊቱን አራብተህ÷ ዋጋውንም ተመልክተህ÷ አሁን ድምፀ ወንጌሉን ከሰማህበት ቀን ጀምሮ ሥራውን መጀመርና ማገልገል ይገባሃል፤ ዛሬ ድምፁን በሰማህበት ቀንም ልብህን አታጽና፤ ማቴ. 25÷1-30፤ ዕብ. 3÷6-19::

ወዳጄና ወንድሜ አንባቢ ሆይ! ሽማግሌው ሐዋርያው ዮሐንስ «ዓለምንና በዓለም ያለውን ኀላፊ ነገር አትውደዱ፤ ዓለምን በሚወድ ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር የለበትም::» 1ዮሐ. 2÷1-17 እያለ ይመክረናል:: ያዕቆብ ሐዋርያም የዓለም ወዳጅ ለመሆን የሚወድ ሰው÷ እርሱ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ ተገኘ::» ይላል ያዕ. 4÷4:: <u>በእውነተኛው ነገር ክርስቲያን ከሆንህ ግን ከክርስቶስ ጋር ሆነህ በዓለም ዘንድ መጠላት÷ ወይም ከዓለም ጋራ ሆነህ ሕገ ክርስቶስን መጥላት</u> ነው እንጂ÷ ሁለቱን ደስ አሰኝቼ በሁለቱ (በአምላክና ጣዖት) እኀዳለሁ በማለት ፈንታ እጠቀማለሁ ብትል ውሸት የአንጉል ውሸት ነው፤ ገላ. 1÷18፤ 1ቆሮ. 10÷1-21::

ስማኝ ልምከርህ

አንድ ባርያ ለሁለት ጌቶች ሊገዛ አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ካልወደደ አይሆንለትም፤ ሉቃ.16÷13:: ሁለት ልብ ያለው ሰው÷ በመንገዱ ሁሉ የጸና አይደለም፤ ያዕ. 1÷8:: ምዉቅ ወይም ቀዝቃዛ መሆን ነው፤ ራእ. 3÷15:: በእጅህ ውሃ ወይም እሳት መርጠህ መጨበጥ ነው፤ ሲራ. 15÷17:: ከመሞት ሕይወትን÷ ከክፉ መልካምን ከመርገም በረከትን ዛሬ መርጠህ ያዝ፤ ዘዳ. 30÷15-20::

ወንድሜ ሆይ! በሰፊዋ ወይም በጠባብዋ <u>መንገድ መጓዝ ካልሆነ ሌላ መካከለኛ ጎዳና የለም፤ ከቶ ቢፈልጉም ምንም ሊይገኝም፤</u> ማቴ. 6÷13:: ጨለማና ብርሃን÷ ቀንና ሌሊት÷ በድምበር ተወስኖ የተለያየ ስለሆነ÷ አንድ ቀን ተፈራርቆና ተደበላልቆ ውሎ ወይም አድሮ አያውቅም፤ ዘፍ. 1÷14-19:: እንደዚሁም እግዚአብሔርና ዲያብሎስ÷ ጣዖትና ክርስቶስ÷ እውነትና ሐሰት÷ ጽድቅና ኃጢአት÷ እምነትና ክሕደት አብሮና ተስማምቶ በአንድ ሊኖር የማይቻልና የማይሆን ነገር ነው፤ 1ቆሮ. 10÷18-22 2ቆሮ. 6÷14-18::

የሰው ልብ ግን የመንፈስ ቅዱስ ወይም የመንፈስ ርኩስ ከሁለቱ የአንዱ ማደሪያ ሊሆን ነው እንጂ÷ ባዶውን ሊኖር እንዳልተፈጠረ አስተውል:: ቸሩ አምላክ ግን÷ «ልጄ ሆይ ልብህን በሞላው እባክህ ለኔ ስጠኝ» እያለ ይለምንሃል፤ ምሳ. 23÷26፤ ሉቃ. 10÷25-28:: አባትህ ሲራክም «ኢትርሳዕ ፈሪሃ እግዚአብሔር÷ ወኢትፀመዶ በክልኤ ልብ::» «እግዚአብሔርን መፍራት አትዘንጋ፤ እየተጠራጠርህ እግዚአብሔርን ሁለት ልብ ሆነህ አታገልግለው::» ይልሃል፤ 1÷27-28:: ሰሎሞንም «የሰነፍ (የኃጥእ) ልብ በግራው ነው፤ የጠቢብ (የጻድቅ) ልብ ግን በቀኙ ነው::» መክ. 10÷2 ብሏልና÷ መሐሪ እግዚአብሔር ግራውን ሥጋዊውን የሰው ሥርዐትና አሮጌ ልማድን እያስተወ÷ ቀኙን የማያሳስተውን እውነተኛውን የሕይወት መንገድና የመንግሥተ ሰማያትን በር÷ የክርስቶስን ፍቅርና የሕገ ወንጌልን ትእዛዝ ለማግኘትና ለማድረግ÷ ለመፈጸሙም እርሱ በኃይሉ ይርዳህ፤ አሜን፤ ዮሐ. 10÷1-15፤ ይሁ. 20-25::

ወንድሜ ሆይ! «ማንም ከላይ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያያት የሚችል የለም::» ዮሐ. 3÷1-15:: «በክርስቶስ የሚኖር ሁሉ እርሱ ዐዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ሥራ ፈጽሞ

ሄደ፤ እነሆ ሁሉ ታደሰ።» 2ቆሮ. 5÷17 የተባለውን ቃል አትርሳ። ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር አስተውል፤ እውነተኛውን የነፍስ ምግብ ቅዱስ መጽሐፍን አዘውትረህ አንብብ፤ ማቴ. 4÷4።

ሳትሰለች ብሉይና ሐዲስን በትጋት መርምር። ደጋጎቹ ቅዱሳን ሰዎች እንዳሉት አንተም «ቃልህ ለጉሮሮዬ ምንኛ ጣፈጠው! ከማር ይልቅ ለአፌ ጣመው፤ በትእዛዝህ ብልህ ሆንሁ፤ ስለዚህ የሐሰትን መንገድ (መጻሕፍት) ሁሉ ጠላሁ፤ የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ የእግዚአብሔርም ምስክር የታመነ ነው፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የቀና ነው፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ጥሩ ነው፤ ዐይነ ልቦናም ያበራል፤ የእግዚአብሔር ፍርሃት ንጹሕ ነው፤ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ ነው፤ እጅግ ከጠራ ምዝምዝ ወርቅ ይልቅ ይወደዳል፤ ከማር ወለላ ነጠብጣብም ይጣፍጣል፤ እርሱንም በመጠበቅ እጅግ ብዙ ጥቅም ይገኝበታል።» እያልክ ድምፅህን እንደመለከት ከፍ አድርገህ ቃሉን ብቻ ሁል ጊዜ ሳታፍር መስክር፤ መዝ. 19÷6-11፤ 119፤ 103፤ 104፤ ሉቃ. 24÷46-48፤ የሐዋ. ሥራ 1÷8፤ ኢሳ. 58÷1።

ወንድሜ ሆይ! የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን በቀንና በሌሊት አንብበው፤ ኢያ. 1÷6-9። በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚለው፥ ሕጉንም ብቻ በቀንና በሌሊት የሚያስብ ሰው «ብፁዕ» የሚባል ስም እንደተሰጠው የተረዳህ ሁን፤ መዝ. 1÷1-3። በሰው (በፍጡር) የሚታመን ሰው «ርጉም» ነው ተብሏል። በእግዚአብሔር ብቻ የሚታመን ሰው ግን በውሃ አጠገብ እንደተከለለች ዛፍ ሆኖ፥ ሁል ጊዜ ለምልሞ የመንፈስ ፍሬ ከማፍራት ስለማያቋርጥ «ቡሩክ» ነው የሚባል ስም ተቀብሏልና፥ አንተም እንደዚህ አንድ ጌታህን ኢየሱስን ብቻ አምነህ ብትከተለው ብፁዕና ቡሩክ የሚባል ስም ለማግኘት የበቃህ ትሆናለህ፤ ኤር. 17÷5-8።

ልቦናዊ ዐይንህን በቃለ እግዚአብሔር ፋና አብርተህና ተኵለህ፥ ማንበብና ማስተዋል በሚባል ልዝብ መድኃኒት እየቀባህ፥ አሮጌና ሻካራ ዝገቱን አስወግደው። ኢየሱስ የጸጋ ብርሃኑን ይዞ በልብህ ደጅ ቆሞ ሁል ጊዜ ክፈትልኝ እያለ ይመታዋልና፥ ቶሎ ብለህ የእርሱ ድምፅ መሆኑን ለይተህና አስተውለህ፥ በእምነትም ከፍተህ ዛሬ አስገባው፤ ዮሐ. 10÷1-4፤ 14÷23፤ ኤፌ. 1÷15-18፤ ራእ. 3÷14-22።

ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም የሚወስድ (የሚያስገባ) እውነተኛ መንገድ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ብቻ መሆኑን በጊዜውም አለጊዜውም ለሁሉ ንገር። ክርስቶስን ማመኑ ብቻ አይበቃህም፥ ስለ

ስሙ ደግሞ መከራ መቀበል ይገባሃል፤ ፊልጵ. 1÷27-30፤ 2ጢሞ. 4÷2::

ወንድሜ ሆይ! እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ የዓለምን ነገር ይናገራሉና ዓለም ይሰማቸዋል:: እኛ ግን ከእግዚአብሔር ነን÷ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤ የእውነቱንና የሐሰቱን መንፈስ በዚህ እናውቃለን፤ 1ዮሐ. 4÷1-6::

እኛ ግን የሃይማኖት መንፈስ የሆነ አንድ መንፈስ ብቻ አለን፤ «አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ::» መዝ.116÷1 እንዳለ÷ እኛም እናምናለን፤ ስላመንንም እንናገራለን፤ 2ቆሮ. 4÷13::

<u>እኛ ግን በሚድኑቱና በሚጠፉቱ መካከል የክርስቶስ ሽቱ ነን:: የእግዚአብሔርን ቃል ከሌላ ጋር እንደሚቀላቅሉ ብዙ ሰዎች አይደለንም፤</u> 2ቆሮ. 2÷15-17::

እኛ ግን አካሄዳችን ምንም በሥጋ ቢሆንም÷ በሥጋ ስልት አንዋጋም፤ የምንዋጋበት ጋሻና ጦር ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው:: በእርሱም ጽኑ የሆነ አምባ እያፈረስን÷ በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ የሚታበየውን ሐሳብና ትምህርት÷ የዚህ ዓለም ጥበብንም ሁሉ ለክርስቶስ ወደ መታዘዝ እንማርክበታለን፤ 2ቆሮ. 10÷1-8::

እኛ ግን የእግዚአብሔር ልጅ መጥቶ ዕውቀቱን እንደ ሰጠን እናውቃለን:: በእውነተኛው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻም እንኖራለን:: እውነተኛው አምላክ÷ የዘለዓለምን ሕይወት የሚሰጥ÷ ኃጥኣንን በደሙ አንጽቶ ወደ አባቱ ቤት መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ እርሱ ብቻ ነው:: እኛ በኃጢአታችን እየተናዘዝን ብንጠብቀው (ብንቈየው) እርሱ በተገለጠ ቀን አናፍርም፤ 1ዮሐ. 1÷8-10፤ 2÷1-6፤ 5÷20-21::

<u>እኛ ግን ክርስቶስ ጌታችንን ብቻ እንጂ ራሳችንን የምንሰብክ አይደለንም፤ ወንጌላችንም ለጊዜው የተሰወረች ብትመስል÷ ለሚጠፉት ብቻ የተሰወረች ትመስላቸዋለች እንጂ አምነው ለሚድኑባትስ የተገለጸች ናት፤</u> 2ቆሮ. 4÷1-12::

እኛ ግን በእውነተኛው በክርስቶስ ፍቅር ብቻ እንኖራለን እንጂ÷ እንደ ሕፃናት የዓለም ሞገድ ወዲህና ወዲያ የሚያመላልሰውን÷ ሰዎች የፈጠሩትን የሐሰትና የተንኰል÷ የጥፋትና የማታለል ትምህርት የተዘነቀበትን አልተከተልንም፤ ኤፌ. 4÷13-24::

እኛ ግን ነፍሳቸውን ለማዳን ከሚያምኑት ነን እንጂ÷ ወደ ጥፋት ከሚሄዱት ጋር አይደለንም፤ ዕብ. 10÷35-39::

እኛ አብ ልጁን የዓለም መድኃኒት ይሆን ዘንድ እንደላከው አይተንና አምነን እንመሰክራለን፤ 1ዮሐ. 4÷14።

እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው አማላጅም (መካከለኛ) አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ጻድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ 1ጢሞ.2÷1-7።

ሥጋዊ ነገር ብቻ ማወቅ ለጥቂት ጊዜ ይጠቅማል፤ ተስፋ ያለውን የወንጌልን አምልኮ ዐወቆና መርጦ መያዝ ግን÷ በሁለቱ በዚህና በሚመጣው ዓለም ነዋሪ የሆነ ዘለዓለማዊ ደስታ ያለው ሕይወትን ያስገኛል÷ ያሰጣልም፤ 1ጢሞ. 4÷8-16።

እኛ ግን ለአይሁድ ዕንቅፋት÷ ለአሕዛብም ስንፍና የሆነውን የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ እናስተምራለን። በእምነትና በዐዲስ ልደት ለተጠሩት ሁሉም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ መሆኑን አምነን እንመሰክራለን፤ 1ቆሮ. 1÷18-31።

ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል፤ እኛም ዓለምን የምናሸንፍባት መሣሪያችን የወንጌል ሃይማኖታችን ብቻ ናት፤ 1ዮሐ. 5÷1-5።

ስለዚህ ለሰው ሁሉ÷ ይልቁንም ለሚያምኑት የሚያድነውን ሕያው እግዚአብሔርን ብቻ አምነን ስለአስተማርን እየተሰደብን እንደክማለን፤ 1ጢሞ. 4÷10።

እኛ ዐውቀን አመንን፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅሩንም የሚያስረዳን አንድ ልጁን ስለ ኃጢአታችን ማስተስረያ እንዲሆን መላኩ ነው፤ በልጁ ያመነም አይኰነንም፤ ዮሐ. 3÷16-21፤ ዮሐ. 4÷7-21።

እኛ ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን የመሠረታቸው (የጀመራቸው) ሙሴና የፈጸማቸው ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ሁለቱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው÷ «በዚህ መጽሐፍ ላይ ከቶ አንዳች አትጨምሩ÷ ወይም አታጕድሉ፤ ቀኝ ወይም ግራ አትበሉ፤» ብለው እንደ አስተማሩን ዐጠረ ብለን ልንቀጥልበት÷ ረዘመ ብለንም ልንቀንስለት ከቶ የማይገባንና ሐሳባችንም ያይደለ ነገር ነው፤ ዘዳ. 4÷1-2፤ 12÷32፤ ኢያ. 1÷1-9፤ ምሳ. 30÷5-6፤ ኢሳ. 30÷21፤ ራእ. 22÷18-21።

ወንድሜ ሆይ! የከበረውን ከተዋረደው÷ እውነቱን ከሐሰት መርምረህና ለይተህ ያዝ፤ እነርሱ ወዳንተ ይመለሱ፤ አንተ ግን ወደ እንግዳይቱና ወደ ጠማማይቱ ትምህርት (ሃይማኖት) አትመለስ፤ ኤር. 15÷19፤ ዕብ. 13÷9። መንፈስን (ትምህርተ

ሃይማኖትን) ሁሉ ሳትመረምር አትመን፤ 1ዮሐ. 4፥1-6:: ሁሉን መርምር፤ ክፉውን የማይረባውንና የማይጠቅመውን እየተውህ እግዚአብሔር የሚደሰትበትን መልካሙን ነገር ብቻ ያዝ፤ ፊልጵ. 1፥10::

ሃይማኖትህ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በተጥባበ ሰብእ (በሰው መጠበብ) የተሠራ እንዳይሆን አስተውለህ በመንፈስ መርምረው፤ 1ቆሮ. 2፥ 5::

ማንም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ካልሆነ ኢየሱስ ጌታ ነው ለማለት አይችልም፤ 1ቆሮ. 12፥3-7::

መንፈሳዊ ሰው ሁሉንም ይመረምራል እርሱ ግን በማንም አይምረመርም፤ 1ቆሮ. 2፥10-16::

ወንድሜ ሆይ! የሃይማኖት አባቶቻችን አብርሃም፥ ይሥሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ነቢያትና ሐዋርያት የሄዱበት እውነተኛው የሕይወት መንገድ የትኛው ነው ብለህ፥ ብሉይና ሐዲስን ብቻ ጠይቅ፤ አጥብቀህ መርምር፤ እነርሱም ባመለከቱህ ሂድ፤ ለነፍስህም ዕረፍትን ታገኛለህ፤ ኢሳ. 30፥21፤ ኤር. 6፥10-16፤ ማቴ. 11፥28-30፤ ራእ. 6፥9-11፤ ኤፌ. 2፥18-22::ሪ

አሁን ግን ሦስት ነገሮች አሉ፤ ሃይማኖት፥ ተስፋ፥ ፍቅር፥ ከነዚህ ሁሉ የምትበልጠው ግን ፍቅር ናት፤ 1ቆሮ. 13፥13::

መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት ምን ብሎ እንደሚናገር ጆሮ ያለው ይስማ፤ ማቴ. 13፥1-9፤ ራእ. 3፥6::

ወንድሜ ሆይ! የነገሩን ፍጻሜ ስማ፤ እግዚአብሔርን ፍራ፥ ትእዛዙንም ጠብቅ፤ መክ. 12፥13:: እርሱ ካዘዘው አትጨምር፥ ወይም አታጉድል፤ ዘዳ. 4፥2፤ ራእ. 22፥18-19:: በደስታ ጊዜ ኀዘን፥ በጥጋብ ጊዜም ረኃብ፥ በብርሃን ጊዜ ጨለማ፥ በንዑ (ወደ እኔ ኑ በሚለው) ፈንታም ሑሩ (ከእኔ ዘንድ ሂዱ የሚለው) መኖሩን ዘወትር ዐስብ:: ይህ ሁሉ ከፊትህ ይጠብቅሃል፤ ሉቃ. 6፥20-25፤ መክ. 11፥8፤ ማቴ. 25፥34-46:: ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርምና፤ ማቴ. 4፥4:: የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ መስተዋት ከዐይነ ልቦናህ ዘወትር አይለይህ፤ ተመገበውም፤ ዘዳ. 6፥1-9፤ ምሳ. 3፥1-26::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰወረውን ነገር (በጎ ወይም ክፉ)፥ በግልጥ ሊፈርድና ለሁሉም ለእያንዳንዱ ዋጋውን እንደ ሥራው መጠን ሊሰጥ እስኪመጣ ድረስ፥ አንተ ግን ያለነውርና ሐሜት እንድትገኝ ራስህን በፍቅረ እግዚአብሔርና በንጽሕና ከክፉ ሁሉ ጠብቅ፤ 1ተሰ. 5፥23፤ ይሁ. 21:: ክርኵስና

ጥቅም ከሌለው ከምናምን ነገር በሐሰትም ዕውቀት ወይም ሊቅነት (ፊሎሶፊያ) ከሚባለው መከራከር ራቅ፤ 1ጢሞ. 6÷8::

እግዚአብሔር አምላካችን የዚህን ዓለም ኃያላንና እኛ ጠቢባን ነን የሚሉትን እንዲያሳፍር ብሎ÷ ገሮችና የዋሆችን÷ ሰነፎችና ደካሞችን እንደመረጠ አስተውል፤ 1ቆሮ. 1÷18-31፤ ጥበብ ከበዛ ዘንድ ኀዘንና ድካም ይበዛልና፤ መክ. 1÷16-18፤ ነፍስና ሥጋ የሚድኑበት÷ ተጠምተው የሚረኩበት÷ ደስታና ዕረፍትን የሚሰጥ የሕይወት ምንጭ ምሳ. 14÷27፤ ለጥበብ መጀመሪያውና መጨረሻው የሆነ <u>የክርስቶስ ተማሪ ለመሆን በውድ ተጠምዶ÷ ዳግም በቃለ ወንጌሉ ተወልዶ ሕያው እግዚአብሔርን መፍራት ብቻ ትልቅ ጥበብና ማስተዋል ነው፤</u> ኢዮ. 28÷28፤ ምሳ. 2÷1-9፤ 14÷27፤ ዮሐ. 6÷45፤ መዝ. 111÷10::

የክፋት ሥር ሁሉ ገንዘብን መውደድ ስለሆነ÷ ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብን ሲወዱና ለለቅጥ እያከማቹ ልባቸውን ሲጥሉበት መዝ. 62÷10፤ በብዙ ፈተናና የሞት ወጥመድ ተይዘው ጠፉ:: ከሃይማኖትም ተለይተው ራሳቸውን ወደ ብዙ ኀዘን አስገቡ፤ 1ጢሞ. 6÷7-16:: ልጆቼ ሆይ! በሀብት (በገንዘብ) ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገቡ ዘንድ እንዴት ይጨንቃል፤ ማር. 10÷17-25::

የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! አንተ ግን ከዚህ ሁሉ ሽሽ፤ ምግበ ዕለትና ልብሰ ዓመት ካገኘህ÷ በአምልኮና በጽድቅ÷ በፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ (የባልንጀራ ፍቅር)÷ በትዕግሥትና የውሃት እየተመላለስህ ራስህን በዓለም ላይ ካለው ርኩሰትና ስስት በንጽሕና እየጠበቅህ ያዕ. 1÷27፤ ለዘለዓለም የማይጠወልገውን የድል ዘውድ እንድትቀበል እውነተኛውን የሃይማኖት ገድል ተጋደል፤ 1ጢሞ. 6÷11-12:: እንደ እውነተኛው የክርስቶስ ወታደር መከራ ተቀበል፤ በሁሉም ንቃ፤ 2ጢሞ. 2÷1-13፤ 4÷1-8::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን የአድኅኖ (የማዳን) ችሎታ ያለው ራእ. 7÷12፤ 12÷10፤ የነገሥታት ንጉሥ÷ የጌቶችም ጌታ ዘዳ. 10÷16-22፤ እርሱ ብቻ የማይሞት ራእ. 1÷13-18፤ ሰው በማይቀርበው ብርሃን የሚኖር÷ ብቻውን ክብርና ጽንዓት ያለው እርሱ እስኪመጣ ድረስ÷ የልብህን ወገብ ታጥቀህ÷ በተስፋ ነቅተህ÷ መብራትህን አብርተህ÷ ጌታ ሆይ! ኢየሱስ ና! መንግሥትህ በቶሎ ትምጣልን፤ ብለህ እየጸለይህ እርሱን ብቻ መቄየት (መጠበቅ) ይገባሃል:: ከአምላካችንስ በቀር ሌላ መጠጊያ ማነው? 2ሳሙ. 22÷32፤ መዝ. 18÷1-6፤ ሉቃ. 12÷35-48፤ 1ጢሞ. 6÷1-21፤ ጸጋው ከሁላችን ጋራ ይሁን፤ አሜን::

ምዕራፍ 32

መንፈሳዊ ምክር ለመንፈሳውያን

ሮሜ 8÷1-10፤ 1ቆሮ. 2÷4-16፤ ገላ. 5÷16-25::

1. ጉሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ
ርኅብኩ ጽድቀከ ክርስቶስ አምላኪየ
ፋት ብዬ ጭረስሁት ዳዊትን በቃልየ፤

2. አድኅነኒ እያልኩኝ እስከ ነቢያት
ብደግም ብደግም ቀንና ሌሊት
ርዳኝ የኔ ጌታ እኔ ብታክት
ኃጢአቴ ብዙ ሥራዬ ክፋት
አንተ ልትሰጠኝ የይለፍ ስርየት
ድምፅህን እንድሰማ ቃለ ብሥራት
ዋ! ብዬ ነገርኩህ አምላከ ምሕረት፤
ሉቃ. 18÷9-14::

3. ያገር ልጆች ስሙኝ ትንሽ ልምከራችሁ
ክርስቶስን እመኑ ፍጡራን ትታችሁ
ቅን መንገድ እርሱ ነው ሂዱበት ተግታችሁ
እምነትና ተስፋን ምርኩዝ አድርጋችሁ
መገሥገሥ ይበልጣል በእግረ ልቦናችሁ፤
በሃይማኖት ጉዳይ ለምን ተጣላችሁ
አንድ ፀሓይ ብቻ ተሰቅሎ በዓይናችሁ
ክበቡን ሙቀቱን ብርሃኑን አይታችሁ
ሦስት አካል አንድ አምላክ አድንቁ እባካችሁ
መጽሐፍን መርምሩ በውል ጠንቅቃችሁ
በከንቱ ክርክር ምንም አይጠቅማችሁ፤
1ቆሮ. 2÷10፤ 1ጢሞ. 6÷20::
እውነትን ለማግኘት ፈልጉ ሁላችሁ
የልባችሁን ወገብ በእምነት ታጥቃችሁ
1ተሰ. 5÷21፤ 1ጴጥ. 1÷13::
ወንጌል ተመገቡ ኃይል እንዲሆናችሁ፤
ሮሜ 1÷16::

ተነሡ ገሥግሡ በአንድነት ሆናችሁ
እንዴት ወደ ኋላ መቅረት መረጣችሁ
አጉል መቀመጡ ምንም አይረባችሁ
ተዉ አታሳዝኑ ርኅሩኅ አምላካችሁ
ክርስቶስ ሲመጣ ሑሩ (ሂዱ) እንዳይላችሁ

ትእዛዙን ፈጽሙ በመሉ ልባችሁ፤
ማቴ. 19÷16-19፤ 25÷35-46::

4. ሃይማኖትም ሲባል አንድ ነው ነገሩ
ዋሸቼም እንደሆን መጻሕፍት ይመስክሩ
አምላክና ወንድም ሁለቱን አፍቅሩ
በምድር ታዘዙት በሰማይ ልትከብሩ
መጻሕፍት አንብቡ እባካችሁ ተማሩ
ብሉይና ሐዲስ ለሃይማኖት ሥሩ፤
ማቴ.22÷35-40::

5. ተዋሕዶ ቢባል በከንቱ ውሸት
ጸጋ ቅብዓት ቢባል በከንቱ ውሸት
ከኒሣ ካቶሊክ በከንቱ ውሸት
አይሁድ እስላም ቢባል በከንቱ ውሸት
አድቬንቲስት ጅሆቫ በከንቱ ውሸት
አይፈርድም በጅምላ ለአንድ ሰው አንዲት÷
እኔስ የመረጥሁት የተረዳሁት
ስድስት ከወንጌል ዐሥር ከኦሪት
እነዚህን አጽንቶ በልብ በአንደበት
ጠንቅቆ መያዝ ነው ሳትጕድል አንዲት
አፍቅር ቢጸከ ዘውደ ሃይማኖት
እምነት አለ ምግባር ይእቲ ምዉት፤
ያዕ. 2÷10-17፤ ዮሐ. 2÷4::

6. በአፍ ብቻ አይሆንም በልብ እንመን
አበባና ቅጠል መልክ ብቻ ይዘን
ፍሬ ካላሳየን ቈርጦ እንዳይጥለን
ማዘን መሥራት ዛሬ መሳደብ ትተን
ምግባር ይገልጸዋል ሃይማኖት ካለን
እባካችሁ እንምከር በአንድነት ሆነን
መለያየት ትተን ትምህርተ ሰይጣን
ክርስቶስ ጌታችን አንድ ልብ ይስጠን፤
ሮሜ 15÷5-7፤ 1ቆሮ.14÷33፤ ዕብ. 3÷13::

7. የክርስቶስ ዐዋጅ ወንጌሉ ብቻ ነው
የሚፈርድብንም ወንጌሉን ገልጦ ነው
አዋልድ የሚሉት የሰው ፈጠራ ነው
ገድል ድርሳን መልክዕ እንግዳ ብቻ ነው
ለምስክር ካልበቃ ጥቅሙ ለምንድር ነው?
ወሬ ቢሰበሰብ ገለባ ማለት ነው
የሚበላ ፍሬ ብሉይ ከሐዲስ ነው

አይቀነስበት አይጨመርበት በቂ መድኃኒት ነው
ከጠገቡ ወዲያ ቢበሉ ርኵሰት ነው
በቃን! ብላችሁ የማትጠግቡ ምነው?
ሕዝ. 16÷28-34፤ ኢሳ. 56÷10-12::

8. ደግሞም አስከትለው ጽፈው ሐዋርያት
አትጨምሩ እያሉ በቃል በውግዘት
ነቢያት ሐዋርያት የተናገሩት
፹ወ፩ ነው የሠለስቱ ምእት
እኔን ግን ባታምኑኝ ፍትሐ ነገሥት
አማጥኛለሁኝ አሁን እንድታዩት
አንቀጽ ሁለተኛ በእንተ መጻሕፍት
ብሉይ ሐዲስ ብቻ አምላካውያት
ገድለ ጠቃሽ ተብሎ ሲሰደብ ከጥንት
አዋልድ አታስገቡ ከቤቱ ቅድስት
ገለባ ከስንዴ የለው አንድነት
ለሰው ምግብ አይሆን ብቻ ለእንስሳት
ኤር. 23÷28፤ ገላ.6÷12::

9. ወንጌል እያነበቡ መስማቱን እየጠሉ
ለምን ሰበሰቡት የማይጠቅመውን ሁሉ
እውነትና ሐሰትን እየቀላቀሉ
ገድል ድርሳን መልክዕ ተኣምርም ሲሉ
ፍሬ አይገኝበት ሲያነቡት ቢውሉ÷
በጠላ ይጸድቃል ሕግ አፍራሹ ሁሉ
እንኳን ሁለት ሦስት ሰባ ስምንት ሰው አርደውና
ቀቅለው ጠብሰውም ቢበሉ
በሕፍነ ማይ ገነት ተከፍቷል እያሉ
ጠላ ለመጠጣት ሕዝብ እያታለሉ
ሕግን እንዳይጠብቅ ሰውን ሰደዱት ወደ ገደሉ
ወሸት ሲያስተምሩ እነ ቄስ በኃይሉ
ዕውቀት ባነሰው ሕዝብ ታምነው ይኖራሉ፤
ኢሳ. 29÷9-13፤ ሕዝ. 13÷1-23፤ 34÷1-25::

10. ስሙኝ ወንድሞቼ ያገሬ ልጆች
ዛሬስ ከጨለማ ብርሃን ተለየች
በሰፌድ አእምሮ ትበጠራለች
ትምህርት መድኃኒት ዕውቀት ቀለብ ነች
በኃይለ ሥላሴ ሕዝብ ዐይን አወጣች
ብርሃን ተወልዶ ጨለማ ሞተች
ዛሬ የምሥራች ኢትዮጵያውያኖች፤

ስሙኝ አባቶቼ እናንተ ካህናት
እንዴት እንጥላለን የአበውን ተረት
መጠምጠም ኋላ ነው ትምህርት ግን በፊት
ፍሬና እብቁ ለምን በአንድነት
ተመዝኖ አያውቅም እውነት በሐሰት
መለየት ይገባል በወንጌል ወንፊት
ካህን አይደለም ወይ ለሕዝቡ መብራት
ለሥራ ታጠቁ ነውር ነው ሐኬት
ወንጌልን ስበኩ የእውነት እውነት
መቅበር አይገባም ትልቁን መክሊት
እንዳይሆን ዋጋችሁ ውርደት ከኀፍረት፤
ሚል. 2÷1-7፤ ማቴ. 25÷13-30::

11. እዚህ በአገራችን ነገር ተበላሽቶ
ግራኝ ያፈረሰው መቼ ተተክቶ
ካህንና መጽሐፍ በአንድነት አጥፍቶ
ብሉይና ሐዲስ በስተውጭ ቀርቶ
አዋልድ ፈጠራ አለቤቱ ገብቶ
ያልተማረ ሁሉ በዚያው ተመክቶ
ውሸትን በእውነት ፍሬ ብሎ አጥንቶ
መሪና ተመሪው ምኑ ተለይቶ
ድንቊርና ልማድ በጫንቃው አንግቶ
ዱር ለዱር ይጓዛል ጎዳናውን ትቶ
መድረሻው ሲኦል ነው ልቡን አመንትቶ
ወንጌል ነግሮለታል ለሁሉም ፈትቶ፤
መዝ. 82÷5፤ ማቴ. 15÷14::

12. ያለፈው አለፈ ለወደፊቱ ግን
ምክር ያስፈልጋል የሚሻለውን
ሰባራና ደኅና አንድ ላይ ሆነን
ምንም አንሠራ ካልተለያየን
ማቴ. 10÷33-38፤ 2ተሰ. 3÷6::
መንገዱን እናብጅ ለመጪው ዘመን
የእኛስ መቸም ሆኗል ለልጆቻችን
ጠንካራ መሠረት እንጣል አሁን
ዛሬ እናሳያቸው ክርስቶስ ማእዘንን
በቤታችን ያለ ጳጳስም አቡን
ለነገ ብንል ግን ቃሉ እንዳይነቅፈን
የዐላማችን ሰንደቅ በዐዲሱ ዘመን
ተርትሮ ማንበብ ነው አሁንም አሁን÷
ብዙ ጥቅም አለው የጠቅል ሚዛን

ለተቀባው ንጉሥ ዕድሜ እየለመን
ትምህርት እንመገብ ጤና እንዲሆነን
መጽሐፍን እንመርምር ለማወቅ ሐቁን
ለሥራ እንታጠቅ ጊዜ ሳይመሽብን
ዐጭር ሱሪ ጃባ ድርቡ መነን
በጣም ያስፈልጋል ላዲሱ ዘመን
ወታደር፥ ነጋዴ፥ ገበሬም ካህን
በፍቅር እንሥራ ፈጣሪን አምነን
አምላክ ይጠብቀው ኢትዮጵያዊውን
በቃለ መላእክት አሜን ወአሜን
ጸረ አምላክ ይባላል ውሸት የሚያምን
ሮሜ 1፥25፤ 1ዮሐ. 2፥18።

13. ምን ይጠቅማል ከቶ ወዳጆች ቢያበዙ
የጥፋት ጎዳና ለባዕድ (ቢያመልኩ) ቢገዙ
ነቢያት ተናግረው ሐዋርያት ወገዙ
ክርስቶስ ብቻ ነው የነፍስ አበጋዙ
ሌሎች አትጨምሩ እርሱን ብቻ ያዙ
ምንም አይጠቅማችሁ አማልክት ቢበዙ፤
ዘዳ. 32 16።
ተግሣጽና ምክርን ፈልጋችሁ ግዙ
ከእጃችሁ አትለዩት በኪሳችሁ ያዙ
<u>እንብቡ መርምሩ ዛሬስ አትፍዘዙ</u>
<u>በነፍሳችሁ ጉዳይ እንዳትገበዙ</u>
<u>ዘየአምን በወልድ ይበቃል ለብዙ</u>
<u>ከባሕር ይሰፋል ጸጋውና ወንዙ</u>
<u>ቅዱና ጠጡለት በጥም ሳትያዙ፤</u>
ኤር 2፥13፤ ዮሐ.4፥10-14።
ከቤቱ እንድትገቡ መንጋው እንድትበዙ
በምድር ላይ ፈሷል የክርስቶስ ወዙ፤
ሉቃ. 22፥39-44።
ግርማዊ ጃንሆይ መልካም ጌታ ያዙ
ምስካየ ኅዙናን የዓለም አበጋዙ
ስለጠበቁለት ሕጉን ከትእዛዙ
መልሶ አመጣቸው አገራቸውን ገዙ
የሱስን ብቻ እመኑ ወዳጆች አታብዙ
መድኃኔ ዓለም ነው ለዲያብሎስ መርዙ
ሆሴ. 13፥14፤ 1ዮሐ. 3፥8።

14. አምልኮ ወሰጊድ ለአምላክ ባሕቲቱ
ተብሎ የተጻፈውን ብትመለከቱ

ይገርማል ይደንቃል በውል ካሰቡቱ
ዕንጨትና ደንጊያን ማምለክ በምውቱ
ፈጣሪ ይቈጣል በእነዚህ ሁለቱ
እሱን ብቻ እመኑ ተዉ አታመንቱ
እጎው እጎዋሁ ኢያድጎን ሎቱ
ንጉሥ በመንግሥቱ ጉልማሳ በሚስቱ
አምላክ ቀናኢ ነው ይልቅ ከሁለቱ
ለአምላክ ልብ መቅደሱ ማጎደሩና ሚስቱ
ሌላውን ማምለክ ነው የሚሆን ዝሙቱ
ተዉ ተመለሱ በከንቱ አትሙቱ
ኢየሱስን ያዙ ጽልሁት ዘአልቦቱ
እውነተኛ አማላጅ የሰጠን አባቱ
ዮሐ. 6÷27-40፤ 17÷1-26፤ 1ዮሐ. 2÷1፤
ራእ. 1÷5-8፤ ዘዳ. 4÷24፤ ኢሳ. 58÷3-10፤
ኤር. 2÷17-25፤ ሕዝ. 16÷1-63፤ 23÷1-49፤
ሆሴ. 2÷1-15።

15. ሃይማኖት አንድ ነው ብዙ ዐይነት ያይደለ
የግል ጉዳይ ነው የተስተካከለ
ሁሉ ሰው ይወቀው ሞኖፖል ከሌለ
በክርስቶስ መንግሥት ባሪያ ጨዋ የለ
ይተርጐም ይሰማ ጳውሎስ እያለ
ነጻነት ካገኘ ይምረጥ የተሻለ
የብዙ ሰው ሐሳብ በጽሑፍ ካልበቀለ
አናገኝም ፍሬ ወርቅን የመሰለ
ነጻነት ነጻነት ዴሞክራሲ እያለ
ስሜቱን ለመግለጽ ሁሉም ተቃጠለ፤
1ቆሮ. 14÷6-12፤ 1ተሰ. 5÷21።

16. ከፍ ባለ ሥፍራ ይሰበክ ወንጌል
የዓለም ብርሃን ነው የክርስቶስ ቃል
የተራራ መንደር ሊሰወር አይችል
ተቀብሮ ቢቀመጥ ያ መክሊት ቊልቊል
ሳይረባ ቢቈየው አንድ ሳያክል
ጌትየው ሲመጣ ከመ ነበልባል
በሥራው ላይ እንዲህ ካገኘ እንዝህላል
ለሠራተኞቹ በሚያስቈጣ ቃል
ከማይጠፋ እሳት ከማይሞተው ትል
ሑሩ ካለ አይራራም ይሰዳል ሲኦል፤
ማቴ. 25÷13-30።

የነገሩን ፍጻሜ እንስማ፤ እጅግ የተወደዳችሁ የክርስቶስ ወገን የሆናችሁ÷ ለወንጌሉ ብቻ የተለያችሁ ፍጹማን ክርስቲያኖች ሆይ! በሙሉ ልባችሁ ወደ እግዚአብሔር የምትመለሱና የምትጸጸቱ ከሆናችሁ÷ እንግዶች አማልክትንና (አሥታሮትንና) የማይጠቅም አሮጌ ልማድን ከመካከላችሁ አርቃችሁ÷ ዐዲስ የሕይወት ቀምበር ቃለ ወንጌሉን ብቻ ተሸክማችሁ ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር አቅኑ፤ እርሱን ብቻም አምልኩ፤ 1ሳሙ. 7÷1-12፤ ማቴ. 11÷28-30፤ 21÷35-40::

አሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍጹምና ባልተከፋፈለም እውነተኛ ልብ አምልኩት:: አባቶቻችሁ በዱሮ ዘመን ያለዕውቀት ሲያመልኩአቸው የነበሩትን ጣዖታትን÷ ፍጡራንን (አዋልድና ዐውደ ነገሥትን የማታለያና የሐሰትን መጻሕፍት) ከመካከላችሁ አርቃችሁ እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ:: እግዚአብሔርን ማምለክ ቢከፋችሁና ደስ ባይላችሁ ግን የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፤ እኔና ቤተ ሰዎቼ ግን እግዚአብሔርን ብቻ እናመልካለን፤ ኢያ. 24÷14-25፤ ሕዝ. 20÷13::

መንፈስ ቅዱስ ለእርሱ ለብቻው የሚታዘዝና እርሱን ብቻ የሚያመልክ ብሩህ አእምሮ ይስጠን፤ አሜን::

ኢትዮጵያ አገሬ ሆይ! እንግዲህ የእግዚአብሔርን የአምላክህን ሕግ÷ ትእዛዙንና ፍርዱን ጠብቅ፤ በልብህም አጽንተህ ያዝ፤ በመንገዱም ሂድ:: አሁንም ቃሉን ብትሰማ÷ ኪዳኑንም ብትጠብቅ÷ ለእርሱ ከአሕዛብ ሁሉ በላይና የተመረጠ ርስቱ ትሆንለታለህ፤ ዘፀ. 19÷1-6፤ ዘዳ. 7÷1-15፤ 8÷1-11፤ 26÷16-19::

ለአምላክህ ባትታዘዝ÷ እምቢ ብትል÷ በቃሉ ላይ ብታምፅና ኪዳኑን ብታፈርስ ግን÷ የእግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና ሰይፍና መቅሠፍት ይበላሃል፤ ኢዮ. 36÷7-12፤ ኢሳ. 1÷18-20፤ ዘዳ. 28÷1-68::

እናንተ የሐዲስ ዘመን ልጆች ሆይ! እግዚአብሔርን ከመከተል ፈቀቅ አትበሉ፤ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ አምልኩት እንጂ ከቶ አትፍሩ:: ወደማይረባችሁና ወደማያድናችሁ ልማድ አትመለሱ፤ ከንቱ ነገር ምናምን ነውና ከአምላካችሁ ፊት አትራቁ፤ በክርስቶስ ደም ብቻ ታረቁ፤ እግዚአብሔርን ብቻ ፍሩ፤ በእውነትም ከነልባችሁ ሁሉ ተገዙለት፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትሰሙና ብትገዙለት÷ አምላካችሁን ብቻ ብትከተሉ በዘመናችሁ ሁሉ መልካም ይሆንላችኋል:: የእግዚአብሔርን ነገር ባትሰሙና በቃሉ ብታምፁ÷ ብታቃወሙትና ክፉ ብትሠሩ ግን እናንተ ከነንጉሣችሁ ትጠፋላችሁ፤ 1ሳሙ. 12÷1-25፤ 1ነገ. 9÷1-9፤ ዘዳ. 28÷1-68፤ 30÷1-20::

ሕዝቤ ሆይ

እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ጌታችን ኢየሱስን የበጎች ጠባቂዎች አለቃ ከምዉታን ያስነሣ፥ እርሱ በዘለዓለማዊ የሥርዐት ደሙ በመልካም ሥራ ያጽናችሁ፤ በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን የምታደርጉ ያድርጋችሁ፤ ከማወቅ የሚበልጥ የክርስቶስንም ፍቅር እንደታውቁና ፍጹማንም ትሆኑ ዘንድ ይስጣችሁ፤ በክርስቶስ ሃይማኖትና ፍቅር ጸንታችሁ ሥርና መሠረቱን እንድትይዙና እርሱም በልባችሁ አድሮ እውነትና ሐሰትን ሁሉ ለመለየት እንድትችሉ ጸጋውን አብዝቶ ያፍስስላችሁ፤ አእምሮንም ሁሉ የሚበልጥ የእግዚአብሔር ምሕረትና ሰላም ልባችሁንና ሐሳባችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ይጠብቅ፤ ወንድሞቼ ሆይ! ዓለምና በዓለም ያለውንም ሁሉ አትውደዱት፤ ከዚህስ ይልቅ እውነትና ቅንነትን፥ ጽድቅና ቅድስናን፥ ስምምነትና በጎነትን፥ ንጽሕናና ትዕግሥትን፥ የተወደደ መንፈሳዊ ሥራና አንድነትን አጥብቃችሁ እንድትይዙ ያብቃችሁ አሜን፤ ዕብ. 13፥20-21፤ ኤፌ. 3፥14- 21፤ 2ጴጥ. 1፥11፤ ፊልጵ .4፥4-9።

ክርስቲያን ተሰኝተህ የምትመካበት ዐላማህ መስቀሉ ብቻ የሆነና የሆንክ ሕዝብ ሆይ ዘፀ. 17፥15፤ ከሁሉ አስቀድመህ እርስ በርስ በሃይማኖት መከራከርና መለያየትን፥ መጣላትና መበታተንን ትተህ በዘመነ ኦሪት አረሚነት፥ በዘመነ ክርስቶስም እስላምነት የተባለ ኃይሉን ሰውሮ የሚኖር የሃይማኖት ተቃዋሚ (ተረፈ ግራኝ)፥ በመካከልህ እንደ አለብህ ዐውቀህ፥ ማንም ሲደፍረው የማይቻለውን <u>አንድነትና ፍቅር</u> የሚባለውን የወንጌል ጋሻ በእውነት አንግበህ፥ የአሥታሮትንና የመሕርምን ስም አምዘግዝገህ ጥለህ፥ ዛሬ ክርስቲያናዊ መብትህን ነቅተህ ካልዘረጋኸውና ካላስፋፋኸው፥ «እርስ በርሱ የሚከፋፈል ቤትና መንግሥት ይጠፋል እንጂ ከቶ አይጸናም።» ተብሏልና ወዮልህ! ወዮልህ! ወዮልህ! ማቴ. 12፥25።

እንደዚህስ ካልሆነ የዮአስና የአሞን ፥ የሴዴቅያስና የሰናክሬም ፍርድ፥ በአንተም ላይ እንደሚፈጸምብህ ነቅተህ ዐስብና ነገሩን ጠርጥረህ ወይም አጥልቀህ መርምረው። ትግሬው ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፥ «ጥበብ በጥበብ ካልሆነ በሌላ ነገር ሊታገድ አይቻልም።» ብለዋልና ችላ ሳትል መከላከያውን ዕወቅበት፤ 2ነገ. 12፥17-21፤ 19፥36-37፤ 2ዜና. 24፥1-27፤ 33፥1-25፤ ኤር. 52፥1-30።

እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ ማቴ. 24፥25።

ይህችን የሚያስተውል አስተዋይ፥ የሚያውቃትስ ማነው? የእግዚአብሔር መንገድ የቀናች ናት፤ ጻድቃን ይሄዱባታል፤ ተላላፊዎችና ሕግ አፍራሾች ግን ይወድቁባታል፤ ሆሴ. 14፥9፤ 1ጴጥ. 2፥6-8።

አነቃቅቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ አምላክ ክብርና ስብሐት፥ አምልኮና ስግደት የብቻው ገንዘቡ ነውና ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ዓለም ድረስ ለብቻው ይሁን፤ አሜን፥ አሜን፥ አሜን፤ ሮሜ 16፥27፤ ይሁ. 26።

ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ በ1941 ዓ.ም
በኢትዮጵያ ዓድዋ ከተማ ተጻፈ

የሃይማኖታችን መሠረትና ጸሎት

ሁሉን በሚችል÷ ሰማይና ምድርን÷ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ደግሞም ዓለም ሳይፈጠር እርሱ ብቻውን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ከአብ የተወለደ÷ የተፈጠረ ያይደለ÷ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን÷ ከአምላክ የተገኘ እውነተኛው አምላክ÷ በባሕርዩ ከአብ ጋር ትክክል በሆነ÷ ሁሉ በእርሱ የሆነ÷ ያለ እርሱ የሆነ የሌለ÷ እርሱም እኛን ስለማዳን ከሰማይ የወረደ÷ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከቅድስት ማርያም ድንግል ሥጋ ለብሶ ሰው በሆነ በአንድ ጌታ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። እርሱም ፍጹም ሰው ሆኖ በጲላጦስ ጴንጤናዊ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ፤ መከራ ተቀበለና ሞተ÷ ተቀበረ÷ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈም በሦስተኛው ቀን ተነሣ÷ ወደ ሰማይም ዐረገ÷ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ÷ ዳግመኛም በሕያዋንና በምዉታን ሊፈርድ በምስጋና ይመጣል÷ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

ከአብና ከወልድ ጋር እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ ከአብ በሠረጸ÷ በነቢያት በተናገረ÷ አዳኝ ጌታ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ኀጢአትን ለማስተስረያ በተደረገች በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን። ደግሞም የምዉታን ትንሣኤንና ገና የሚመጣውን ዓለም የዘለዓለም ሕይወትንም ተስፋ እናደርጋለን፤ አሜን፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 242 ተመልከት።

የተነሳሕያን ጸሎት

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ምድር ሁሉ በግርማው ሞልቷል፤ እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ዙፋኑም በሰማይ ነው፤ ትሑትና የተዋረደ መንፈስ ላላቸው ግን ቅርብ ነው:: አዝነው የሚናዘዙትን ይሰማል፤ ጸሎታቸውንም ያደምጣል፤ ስለዚህም በእምነት ወደ ጸጋው ዙፋን እንቅረብ፤ ኃጢአታችንንና ዕዳችንንም እንዲህ ብለን እናስታውቅ::

እኔ ችግረኛና ኃጢአተኛ፥ በኃጢአትም የተለወድሁ ሰው፥ ኋላም በዘመኔ ሁሉ በብዙ ዐይነት ኃጢአት አንተን የበደልሁ፥ በፍጹም ልቤ ኃጢአቴን በፊትህ እናዘዛለሁ:: አቤቱ ቅዱስ፥ ጻድቅ አምላክ፥ ፍቅር የሞላብህ አባት ሆይ! አንተን ከሁሉ አብልጬና ባልንጀራዬንም እንደ ነፍሴ እንዳልወደድሁ አስታውቅሃለሁ፤ በሐሳብ፥ በቃል፥ በግብር አንተን በደልሁ፤ ቅዱስ ትእዛዛትህን ተላለፍሁ፤ ስለዚህም እንደ ጽድቅህና እንደ ኃጢአቴ መጠን ብትፈርድብኝ የዘለዓለም ኵነኔ እንደሚገባኝ ዐውቃለሁ::

አሁን ግን ፍቅር የሞላህ ሰማያዊ አባት ሆይ! ወደአንተ ለሚመለሱ፥ ወደ ምሕረትህና ወደ መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ምግባርም በሕያው እምነት ለሚጠጉ ሁሉ፥ በኃጢአታቸው ለሚናዘዙ ኃጢአተኞች በየዋሃትና በጸጋህ ልትቀበላቸው ተስፋ ሰጥተሃል፤ የበደሉህን ሁሉ ይቅር ትላቸዋለህ እንጂ በኃጢአታቸው ከቶ አትቈጣጠራቸውም::

እኔ ችግረኛና ኃጢአተኛም ይህንኑ የማይመረመር ጸጋህንና ስጦታህን እምነቴ አድርጌ፥ ለቅዱስ ስምህ ምስጋና ክብር ብለህ በዚሁ እንድታዝንልኝና እንድትምረኝ፥ ኃጢአቴንም ሁሉ እንደምትተውልኝ በተስፋህ አምኜ እለምንሃለሁ::

ሁሉን የሚችል ዘለዓለማዊ አምላክ በማይመረመር ትልቅ ምሕረቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምግባር ብሎ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይበለን አሜን:: ኑሮዋችንንና አካሄዳችንን ሁሉ እንድናቀና ጸጋውን ይስጠን፤ አሜን:: ከዚች ከምታልፈው ሕይወት በኋላም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ብፅዕና ያካፍለን አሜን::

እርሱ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር እንደሚልልን የታመነ ነው፤ ይህም ስለ ዓለም ሁሉ ነው እንጂ በተለየ ስለ እኛ ኃጢአት ብቻ አይደለም፤ 1ዮሐ. 2፥1-2::

ጸሎት

አቤቱ ቸርና ርኅሩኅ፥ ጻድቅና ቅዱስ ሰማያዊ አባቴ ሆይ! አስቀድሜ በአንድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰጠኸኝ ጸጋና የኃጢአት ይቅርታ በጣም አመሰግንሃለሁ። ነገር ግን ይህ ብቻ ኅሊናዬን አያሳርፍልኝምና ያንተውን ስጦታ በምግባሬ እንድገልጸው ሕይወቴን በሞላ ለአንተ ቀድሳት፤ ሰማያዊ ኃይልህንም አልብሳት።

ቸር አባት ሆይ! እኔን ኃጢአተኛ ባርያህን ለኔ የማይገባው ለጋሥነትህና መሐሪነትህ ከሞት ወደ ሕይወት አሻግሮ በአንድነትህ ውስጥ አስገብቶ ስለ አስደሰተኝ እጅጉን አመሰግንሃለሁ። ይኸውም ጸጋህን በውስጤ ስለ ሞላህ ወሰን የሌለው ምስጋናና ውዳሴ ይጎርፋል። ቸር አባት ሆይ! እኔ ለዚች የገዛ ነፍሴ ጥልቅ የሆነው መሻትዋ እንዴት እንደሚገባው ከቶ አላውቀውም።

አንተ ግን ለፍጥረትህ ሁሉ ለያንዳንዱ የሚያስፈልጉትን ነገሮችና ስጦታዎች አውቀህ ትሰጠዋለህ። እኔ ለዚች ከአንተ ለተገኘ ችው ነፍሴ እንደአንተ አድርጌ አፈቅራት ዘንድ ከቶ አይቻለኝም። አንተ ወሰን የሌለው ፍቅር የሞላህ ፈጣሪዬ፥ በህላዌ ስላቆምከኝ በሙሉ ልቤና ኅሊናዬ አንተን ወድጄና ታዝዤህም ቢሆን ኑሮ ነፍሴን እወዳለሁ ማለት ይቻለኝ ነበር። ይህችም ፍቅር አንተ ነህና ነፍሴም አንተን ብቻ የምትናፍቅና ከአንተ ከፈጣሪዋ ብቻ የምትጣበቅ ልብ ስለ ሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ።

ጌታዬና አምላኬ ሆይ! አንተ ለኔ፥ ሕይወትህ በሕይወቴ፥ መንፈስህም በመንፈሴ፥ ሁለንተናዬ አንተ ብቻ ነህና፤ እኔም አንተን ወሃቤ ሕይወታትን እንጂ ምድራውያት ሀብታትን ስጠኝ ብዬ አልለምንህም። የልቤ ጥማትም አንተን ብቻ ሲያገኝ ነው የሚረካልኝና፥ ለአንተ ቤት (ማደሪያ) እንዲሆንህ ብለህ ስለ ፈጠርኸው፥ ከቆሻሻነቱ ሁሉ በመንፈስህ ጠርገህ አንተ ከምትጠላውም ሁሉ አስጥለህ አንተ ዕረፍበትና ለዘለዓለሙም ነግሥህበት ኑር፤ አሜን።

አንተ ቸር መምህሬ ሆይ

ይህ የዛሬው ከአንተ እግር በታች መቀመጥ÷ ኋላ ወደ ሰማያዊው ዙፋን ለመቀመጥ የሚያበቃ ስለሆነ ከፍ ካለ ግርማ ካለው ምድራዊ ዙፋን ይልቅ በጣም የበለጠ መሆኑን ተረድቼዋለሁ። ስለዚህም ይህችን የሰጠኸኝን ሕይወቴን በሞላዋ የተወደደች መሥዋዕት አድርጌ ይኸውና ከእግርህ ጫማ በታች አኖራታለሁ። ጌታዬ ሆይ ተቀበለኝና አንተ በፈቀድኸው አገልግሎትህ አውለኝ። ነገር ግን አንድ ቅንጣት ዐፈር እንሥተህ በምሳሌህ ሠርተኸኛልና÷ አንተ የኔ ነህ፤ እኔም የአንተ ነኝና የእጅህን ሥራ ችላ አትበለኝ፤ ከክፉ ሁሉም ጠብቀኝ÷ ወደ ፈተናም አታግባኝ፤ አቤቱ በመንግሥትህ ስትመጣ ዐስበኝ፤ አሜን።

ክብርና ግርማ ውዳሴና ምስጋና የአንተ ነውና
ለዘለዓለማተ ዘለዓለም ለአንተው ይሁን አሜን።

ዓመት አልቆየም መጽሐፉም ታትሞ ወጣ፡፡ ጠዋት ቁርስ ስንበላ የሆነ ሰው ውጭ ሲጣራ ሰማን፤ አባቴን ጣቢያ እንደሚፈለጉ ነግሮ ይዟቸው ሄደ፡፡ አባቴም ታሠሩ፡፡ በጨርቅ የተቋጠረ ምሳ ተሸክሜ እስር ቤት ሳመላልስ ትዝ ይለኛል፡፡ በዋስ ተፈትተው ቤት ቢመለሱም እንኳ፥ የታተመው «ተግሣጽና ምክር» መጽሐፍ በጠቅላላ ተይዞ የትም እንዳይሸጥ ጥብቅ ትእዛዝ ተላለፈ፡፡ በአባቴም ላይ «ቤተ ክርስቲያንን ተሳድቧል» የሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ፍርድ ቤት ቀረቡ፡፡ ጉዳዩ ይግባኝ እየተባለ ከዓድዋ ወደ መቀሌ ፥ ከዚያም አዲስ አበባ ከጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ድረስ ደረሰ፡፡

ተግሣጽና ምክር በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት መካከል ባሉት ልዩነቶች ቢያተኩርም እንኳን በጣሙን የሚዘልፈው መሠረተ ሃይማኖቱን ሳይሆን ልማድ ይዘው ፥ሃይማኖትን ተመርኩዘው በቤተ ክርስቲያኑ የነበሩትን ጉልህ ጥፋቶችን ነው፡፡ ....

አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ ከጠቅላይ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ቤት ቀርበው ምንም ጠበቃ ይሁን ነገረ ፈጅ ሳይፈልጉ በአንድ እጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው፥ በሌላው ጥቅሶችን እያወጡ በመጠቈም፥ ከመላው የቤተ ክህነት መሪዎች ጋር ፊት ለፊት፥ ዐይን ለዐይን ተፋጥጠዋል፡፡ በኋላም ከጃንሆይ ችሎት ፊት ቀርበው ንጉሡ «በሉ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሶ ይኸው ይከራከራችኋል፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሳችሁ ነው መልስ መስጠትና መርታት...» ቢሏቸው፥ አጥጋቢ ጥቅስ አቅርበው ሊከራከሩና ሊረቱአቸው አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ጃንሆይ «እንግዲያውስ በቂ መልስ ከሌላችሁ የተያዘው መጽሐፍ ነጻ እንዲለቀቅ አዝዘናል፡፡ መልስ አለን የምትሉ ከሆነ መጽሐፍ ጽፋችሁ ዓጸፋውን መልስ ስጡት፥ እስካሁን ለተጉላላው እናንተ በግዳችሁ ትከፍሉታላችሁ፡፡» ብለው ፈረዱላቸው፡፡

ልጃቸው ገ/ኢ. ጉርፋ፡፡

ወንድሞቼ አንባቢዎች ሆይ! እውነትን ግን እንኳን ከምድር በላይ አስረዋት ይቅርና ፥ከምድር በታች ቢቀብሯትም በድንጋይ መዝጊያ ተዘግቶ፥ በብርቱ ጥንካሬ ተሠርቶ በትጉሃን ዘበኞች በሚጠበቅ ጥልቅ ሕንጻ ውስጥም ቢዘግዋት፥ አእላፍ ሐሰተኞችም ቀብረው ሊይዟት ስላልቻሉ፥ በሦስተኛው ቀኗ ተነሥታ ሁሉንም ከንቱ አድርጋ እስከ ዛሬ ድረስ በእውነተኝነትዋ እየፎከረች፥ ዐዋቂዎች ነን የሚሉ ሰዎችን ስታሳፍራቸው ትኖራለች፤ ማቴ.27፥57-66፤ 1ቆሮ. 1፥18-22፡፡

ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ

«ተግሣጽና ምክር» የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ ከተጻፈ ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ ብዙዎችን አነጋግሯል፤ ከመንፈሳዊ እንቅልፍም ቀስቅሷል። በመጽሐፉ መነሻነትም ብዙዎች የወንጌልን እውነት ተረድተዋል፤ በታሪክ መልክ ብቻ ያውቁት የነበረውን የክርስቶስን አዳኝነትም በትክክል አምነውበት ድኅነተ ነፍስን በእምነት ለመቀበል ችለዋል።

መጽሐፉ በተደጋጋሚ ታትሞ የተሠራጨ መሆኑ ይታወቃል፤ የመጨረሻው እትም ታትሞ ከወጣ ግን ከሦስት ዐሠርተ ዓመታት በላይ ተቈጥሯል። በዚያን ዘመን በነበሩ ሰዎች እጅ ካልሆነ በቀር በተለይ በዚህ ዘመን ትውልድ እጅ አይገኝም፤. . . ስለዚህ ዛሬ ያለው ትውልድ ይህን ተገንዝቦ ፣ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ልማድ የያዘውን ሃይማኖት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እንዲመረምርና እውነተኛውን ነገር ከሐሰተኛው እንዲለይ መርዳት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ተግሣጽና ምክር እንደገና እንዲታተም አስፈልጓል።

ስለ ተግሣጽና ምክር ጥያቄ ወይም አስተያየት ቢኖርዎ
በፖ.ሣ.ቍ. 8109
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ብለው መላክ የሚችሉ መሆኑን በትህትና እንገልጻለን

Price 12 USD